መግቢያ

ሊለወጥ የሚይቸል እግዚአብሐር ዘመናትን፣ ትወልድን፣ ታሪክን፣ ሥርዓትን፣ ትምህርትን፣ ሰዎችን፣ ፍጥረትን ... ወደ ሚይለዋወጠው ፈቃዱ ሲለወጥ ተስተወሷል፡፡ በተለይም በዚህ ጊዜ ሁሉም ነገር ደስታው ወደ ሆነ ፈቃዱ እየተለወጠ ይገኛል፡፡ በእርግጥ ባለንበት በአሁኑ ዘመን ከእግዚአብሐር ዘንድ በሁሉ ላይ የተለቀቀው ለወጥ ግን ያለ ጌታ ልብ ሆነን ልናየወና ልንመላከተው አንችልም፡፡ በለወጠም ሚዕበል የሚይናወጠው ጸንቶ ሲኖር ሌላው ግን ሚለት የሜጠወጠው የተፈጠረ ይሆን ዘንድ ይለወጥ ዘንድ አለው፡፡ የዚህም ለወጥ አራሚጅ የሆነ ሕያው መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ወደ እግዚአብሐር ሜልከና ምሳሌ ለወጦ ሊያስማሰል በተጋበት ዘመን ሁሉ ለናመና የሚጠቀስ ሥራን መሥራቱ የታመነ ነው፡፡ አሁን ግን እርግጠኛ፣ የሜጨሻና የፍጻሜ ለወጥ መጥቷል፡፡ ለወጡ ግን ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ስምና ማንነት ጀምሮ መሆኑን ተደነቁ፡፡ አንድ ዘመን በተዘጋበትና ሌላኛው ሊከፈት በተዘጋጀበት ጫፍ ላይ ደርሰናል፡፡ ወገኖች ሆይ፣ በልባችን የበራውን ንጋት - የጌታ ቀን ሚዳ ለወጫጀ ነገር የታሰርንበትን ሁሉ እያስረጀ መሆኑን ለሚዳት መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለወን ለመሳማት መንቃት አለብን፡፡ ከሁሉም በላይ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ዘመን ሚለቁንና መምሸቱን ወደ እኩለ ሌሊቱም መድረሱን እንዲሁም የለወጡ ደወል አስቀድመው ከማነፀንዋ ለተወለዱት ልጆች የምሥራች መላገሩ የደመቀው የመንግሥቱ ሚሕ ጅሚሬ ለመሆኑ ሰሚያት ይመሳከራሉ፡፡

እስከ ዛረ ስለ ለወጥ ብዙ ተብሏል፡፡ በዓለምም ሆነ በቤተክርስቲያን ታሪክ የተለያዩ ለወጦች ተካሂደዋል፡፡ አሁን ያለንበት ዓለም ራሱ የለወጥ ወጤት ነው፡፡ ለወጥም ተራሚጅ ስለ ሆነ ይቀጥላል - ሁሉም ነገር ወደ እግዚአብሐር መላት (እግዚአብሐር ሁሉ በሁሉ ወደሚሆንበት) እስኪለወጥ፡፡ ሰው ግን ባለው ሚዳት ለወጥ የሚለው ፅንሰ ሐሳብ የብርታቱ ወጤት ይመሳለዋል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሐር በዓለምም ሆነ በቤተክርስቲያን ለወጥን ያመጣው ሁሉ ነገር፣ ያ ዘመን፣ ያ ትወልድ፣ ያ ሥርዓት ሲደክምና ሲያልቅ ሲያረጅም መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዘመኑ፣ ሥርዓቱ፣ ትወልዱ፣ እምነቱ፣ አስተሳሰቡ... ሲበላሽና ሲበሰብስ ለወጥ ሁኗል፡፡ ለዚህ ነው ማንም የለወጥ ባለቤት ሆኖ ሊመላ ያልተፈቀደለት፡፡

የትኛውም ዓይነት ለወጥ የድካም፣ ተስፋ የመቁረጥ፣ ከልብ የሆነ ጩኸት ወጤት ነው፡፡ እያንዳንዱ፡- ‹‹እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?›› ወደሜልበት ጩኸት ሲመጣ ነው ጌታ እግዚአብሐር የተነሣለት፡፡ ለወጥ፣ ሪቫይቫል ትንሣኤ... ምን ጊዜም በአቋም፣ በእምነት፣ በሕይወት፣ በአካሄድ፣ በሥርዓት፣ በትምህርት፣ በባሕል፣ በሁለንተና... የመሞት፣ የማላሽትና የማስበስ ወጤት ለመሆኑ መጽሐፉችሁን ተጠግታችሁ ተመልከቱ፡፡ ዛሬ በዚህ ጊዜ ተሰጥቶት የነበረ ዘመን፣ ትምህርት፣ ልምምድ፣ ሥርዓት፣ ስጦታ... ያላረጀበትና ለወጥን ወይም መነብናትን የሚፈልግ ከእኛ ማን ይሆን?

‹‹ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች›› ለምን? የሉምና! ስለ አንድያ ልጅ የራሔል ልጆች አለቁ - ታረዱ፡፡ ስለ ምን? በዚህ አንድያ ልጅ ሁሉም ትንሣኤ ይሆንላቸው ዘንድ፡፡ ዛሬም ከርስቶስ ጌታ በእያንዳንዱ ይሳልና ይገለጥ ዘንድ የእያንዳንዱ ሜልከ በብልሃተኛው ገፋፊ እየተገፈፈና እየተበላሸ ይገኛል፡፡ ወገኖች ሆይ፣ በሜጨሻ የበሬው ዕድል ፈንታ ምንድር ነው? መታረድ አይደለምን? በብዙ ሲሳይ በበሬ ዘንድ ነበር፡፡ ግን በሚጨሻ መሥዋዕት መሆን አለበት፡፡ መታረድ፣ መገፈፍ፣ መታጠብ፣ መቃጠል አለበት (ዘሌ.1÷3-9)፡፡ ሁሉም እንደዚህ ሜጨሰ አለበት፡፡ የሜጨሻወም መታደስ (ሥራ.3÷21)፡፡ የዚህ ወጤት ወይም ፍሬ ነው፡፡ የራሔል (የቤተ ክርስቲያን) ዘመን አልቋልና የመጀመሪያ ወበቷና ሜራኪቷ የለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የምትፈራበት ዘመን ላይ አይደለችም፡፡ እቴጌ እንጂ ንግሥት መሆኗ አልታየም፡፡ ከዝመቷ ወይንም ጠጅ የጠጡ በዝተዋል፡፡ የስርቆት ወኃዋ እንደ ምን ሁሉን አሚለ?!

በዚህ ትገኝ ዘንድ ተፈርዷል፡፡ ጊዜዋ፣ ዘመንዋ፣ አገልግሎቷ፣ ሥርዓቷ፣ ፕሮግራሚ.. ልብ የሚጣልበት የሆነበትን ምክንያት ለምን ጠልቃችሁ አላይ አላችሁ? የተፈጸመው ዘመን በእርግጥ በሜጸም ላይ መሆኑ አይደለምን?... ወገኖች ሆይ፣ ወደ ወስጣቹሁ ተመላሱ፡፡ ዛሬ የእግዚአብሐር ሥራ በዚህኛው መድረክ ነው፡፡ ወጫጀው መድረክ አልቆበታል - አርጅቷል፡፡ የሰው ተወኔት የሚታይበትም ሁኗል፡፡ ወዶች ሆይ፣ ይሄ አጭር ጽሑፍ ቤተ ክርስቲያንን በመቶቸት ላይ የተመሠረተ አይምሳላችሁ፡፡ ሊሆን ከቻለ ተግሣፅ ይሁን፡፡ በፍጹም ተራ ትችት አይደለም፤ በጌታ እለምናችኋለሁ፡፡ ጌታ ግን የልቡን ሐሳብ በዚህ ዘመን ለልጆቹ እንደ ገለጠው ማጠን ምሥክር እንከፋፈላለን፡፡ መሳማት ከቻላችሁ፡- የቤተ ክርስቲያን ዘመን አልቋል፡፡ ድካሟ በእርግጥ የዚህ ምክንያት ነው፡፡ ማንም በማንም ላይ አይፍረድ፤ ይሄ ከላይ ተወስኗል፡፡

ስለሜመጣው ቀን - ስለ መንግሥቱ መላትና መለጥ የዘሙኑ ድካም እንደ ሰሚያት ወሳኔ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ወድቀት በእርግጠኝነት ጥቂቶች ብቻ የሚገሩት እወነት ሳይሆን እያንዳንዳችሁ (ሁሉም ሚለት ይቻላል፡፡) በራሳችሁ አጥቢያና እልፍኝ የምታዩትና የምታስተወሉት ይሁን፡፡ ካልደነዘዝን በስተቀር ይሄ ሁኔታ በእያንዳንዳችን ዘንድ የፀሐይ ንዳድና ብርሃን ያህል ከማንም ዕይታ የተሰወረ አይደለም፡፡

በዚህ አጭር ጽሑፍ ጌታ የፈቀደውን ያህል ስጽፍ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለወጥን ያመጣው ከብዙ ድካምና ተስፋ መቁረጥ በኋላ መሆኑ ሚስረጃዎችን በማበዛት የዛሬው ድካም የዚያ መርሐ ግብር የሜጪሻ ገጽታ መሆኑን በመግለጽ ነው። ከዚህም በሚልፍ የቤተክርስቲያን ዘመን ሚለቅ እውነት ታሪክንና መጻሕፍትን በመጥቀስ ሚመሰን ይቻላል። ምናልባት ሁላችን በምናምንበት መንገድ ጉዳዩን ሚስረዳት ቢቻል በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ። ሥነ መለኮት የተቀበለውን የጊዜ ቀመር ተጠቅመን ለመረዳት ብንሞክር በሁላችሁ ጥያ እንቆቅልሽን ለመፍታት ተሞክሯል። የራሳችሁን መጽሐፍ ካላመናችሁ ግን የሌላውን እንዴት ታምናላችሁ?

ስፍረ - ዘመናት

እነዚህ የሚባሉ ስፍረ ዘመናት (Dispensations) እግዚአብሔር እንዴት አንዱን በአንዱ ላይ እንዳመጣ እናያለን። ተቆራርሰው በተሰጠት በእነዚህ ዘመናት እግዚአብሔር እንዴት እንደ ሠራ ሳይሆን ይሽው ተሸንሽኖ የተሰጠው ዘመን እግዚአብሔር እንዴት እንደ ለወጠው ነው የምናየው። ሚለትም የመጀመሪያው ዘመን እንደ እግዚአብሔር ቸርነት የተዘጋጀ ሁኖ በሌላኛው ሊተካው ሲነሣ የመጀመሪያወን በማበርታትና ጉልበት በመስጠት ሳይሆን በሚድከምና በማረጀት ነው። እናቱን ሳያደክም የተወለደ ልጅ የለምና የመጣው - የተገለጠው - የተወለደው አዲስ ዘመን የነበረውን ሳያደክምና ሳያስረጅ ሁኖ አያወቅም። ይህንን በመጽሐፍ ቁልጭ ያለ እውነት ሆኖ እናገኘዋለን።

ቁም ነገሩም ታሪክንና ትወልዶችን ለማጥናት ሳይሆን ለትምህርታችን በተጻፈው ዘመናችንን በተለይም የቤተክርስቲያንን ዘመን ሚለቅ እንድናይ ጥርጥር የለውም። ያለፉት ዘመናት በድካምና በሞርጀት ሚልቃቸው አይደለም ትልቁ ሚወቅ የሚባን ቁም ነገር። ነገር ግን አሁን ያለው ዘመን ሚለትም ዘመነ ቤተ ክርስቲያን ራሱ በድካም እኛም አሁን ባለንበት ዝለት እንደሚያልቅ ተረድቶ ዘሙን መዋጀት፣ ከድንጋጤ መትረፍ፣ ነገሩም ፍርድና መቅሰፍት አለመሆኑን ነገር ግን የእግዚአብሔር ቅድመ ሐሳብና እቅድ መሆኑ ተረድቶ ሚረፉ ላይ ይሆናል።

በአንድ በኩል በቤተ ክርስቲያን ባሉት ዘንድ ታላቅ የእንቅልፍ መንፈስ የተለቀቀ ሲሆን - ራእይ ሁሉ እስኪታተም፣ መጽሐፍም እስኪዘጋ... በሌላ በኩል ግን በጥቂት ቅፌታዎች በኩል እግዚአብሔር እየለቀቀው ያለው የመንፈሱ ሚዳት እጅግ አስደናቂ ነው። እስከ ዛሬ ያልተገለጠ ነገር እየተገለጠ ሲሆን በዚህም ያለፈውን ሁሉ እያስረጀና እየሻረ ይገኛል። እነዚህም ጥቂቶች ናቸው ያለቀወንና የመሸወን ይህንን የቤተ ክርስቲያን ሌሊት የሚነጉት። ወገኖች ጊዜው ለአሥሩም ቆነጃጅት ሌሊት ነው። አሥሩም እስከ እኩለ ሌሊታቸው ተኝተዋል። በሌሊት የሚዝሙት ጉበኞች ግን በጌታ ቀን ማነት ይራመዳሉና - ይመጣሉና የቤተ ክርስቲያንን ሌሊት ያነጉታል። ይህም ሚልእክት በጥቂቶች በኩል ወደ ቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ ሚለቀቁ ቤተ ክርስቲያንን ለማሰመን ሳይሆን በመካከሏ ያሉትን በአዚሟም ላይ የነቁትን ይበልጥ ይነቁ ዘንድ ለማሾል ይሁን።

ዛሬ በዚህ ወሳኝ ወቅት ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን አጠቃላይ ሚልክ ለወይይት ቢቀርብ የሚይኮንነው አእምሮ ያለ እስከሚይሰክል ተደርሷል። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ከሰጠው ልክና ካነሣው ምልክት በታች እንደ ሆነች በዚህ ጊዜ የሚከራጠር ይገኝ ይሆን?... ስብራትን በጥቂቱ የሜዠወስ ነገር ሞኖ አይካድም። ነገር ግን የተፈለገው አርነት የለም። የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠጥቶ የሰከረ ነበዝ ብቻ ጊዜው መማሸቱን አላወቀም። እርሱን በምን መቀስቀስ የቻላል? ስካሩ እስኪበርድለት ድረስ ለጊዜው ብርድ - ተወት። ወቅቱ ግን ሁሉን የሚነጋግር፣ ሁሉን ግራ የሚያጋባ፣ በሁሉ ላይ ጥያቄ የሜጥር... ወቅት ነው።

ወገኖች ሆይ፣ በዚህ ጊዜ ዘሙ እንደዚህ ስለ ሆነ ታዝኑ ይሆን? የዚህ ሚልስ ነው ዘመነ የተሰጣቸሁ ወይም ያልተሰጣቸሁ መሆኑን የሚወስነው። በዚህ ጊዜ መሆናችን፣ ዘሙ እንደዚህ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ... ዕድለኞች ነን እላለሁ። በለወጥ፣ በአዲስ ቀን፣ በጌታ ቀን ዋዜማ ሁል ጊዜ እንደዚህ ነወና ይህንን ነው ከመጽሐፍም ከታሪክም በመጥቀስ ለማሾት የምንሞክረው። ከሁሉም በላይ ‹‹የአዲስ ኪዳን›› ታሪክ ለሁላችንም ሚስረጃ ይሁን። ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተፈጸሙት፣ ያለቁት፣ ያረጁት እንደዚህ ነው ልብ በሉ። ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሰባቱ ክፍለ ዘመናት አይደሉምን? ሰባት ሲያልቅ ያለ ጥርጥር ስምንት ነው። ስምንት የአዲስ ነገር መጀመሪያ ነው። ስምንት የትንሣኤ ቁጥር ነው። የአዲስ ነገር - የአዲስ ሕይወት ሚዝሪያ ነው ስምንት። በመጽሐፍ ቅዱስ ስምንት ሰዎች ከመቃን እንደ ተነሡ ታውቃላችሁ? ክርስቶስ በስምንተኛው ቀን የተነሣ አይደለምን? ስምንት ትንሣኤ ከሆነ እንግዲያስ ሰባቱ በሞሉ መሞት አለባቸው። በአሁን ዘመን የቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ አቋም ፈጽሞ ቢደክምና ቢሞት ወደ አዲስ ዘመን - አዲስ ትወልድ - አዲስ ሥርዓት ልትገባ ነወና እሰየሁ። በዚህም - ‹‹ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ›› የሚለው ቃል ይፈጸሚል።

ሰባቱ ዋና ዋና ስፍረ ዘመናት

ከሁሉ በሚቀደም ብዙ የሥነ መለኮት ተማሪዎችና አስተማሪዎች የሚመጣቸወን ሰባት ክፍለ ዘመናት(ስፍረ - ዘመናት - Dispensations) እንጥቀስ። እነዚህም ተራ በተራ እንዴት እንዳለቁ ስንመለከት ያለንበት ዘመንም ዕድሉ ከዚያ ወጭ

አለመሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በመጨረሻም የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናትን በእነርሱ ምሳሌ የተነገረላቸውን ሰባቱ ክፍለ ዘመናት እንዴት እንደ ተፈጸሙ እናያለን፡፡ ከእነዚህ ማስረጃዎች በኋላ ነው እንግዲህ የዚህን ዘመን ቤተ ክርስቲያን፣ ሚስትሪዎችና እንቅስቃሴዎች እንዴት እንደሚያልቁ ሳይሆን በመንፈስ ዓይን እንዴት እንዳለቁ የምንመለከተው፡፡

‹‹አንደኛ - የቅን ልቦና - የንጹሕ ሕሊና ዘመን (Dispensations of Innocence)፤ ሁለተኛ - የሕሊና ወይም ሰው በሕሊናው ተጠቅሞ የኖረበት ዘመን (Dispensatons of Conscience)፣ ሦስተኛ - የሰው ግዛት (መንግሥት) ዘመን (Dispensatons of Human Goverment)፤ አራተኛ - የተስፋ ወይም ተስፋ የተሰጠበት ዘመን (Dispensations of Promise)፤ አምስተኛ - የሕግ ዘመን - ዘመነ ሕግ (Dispensations of Law)፤ ስድስተኛ - የጸጋ ዘመን (Dispensations of Grace) እና ሰባተኛ - የመለኮት ግዛት (የአንድ ሺው) ዘመን (Dispensation of Divine Government or Millennium.) ዘመናት እንደዚህ ተሸንሽነው መቀመጣቸው ‹‹እውነት ነወን?›› የሚለው ሳያስጨንቀን ዘመናቶቹ እንዴት እንዳለቁ ማወቁ ላለንበት ለዚህ ዘመን ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

1. የቅን ልቦና - የንጹሕ ሕሊና ዘመን

በዚህ ዓይነት የዘመናት ሽንሽና የሚያምኑ ወገኖች የዘሙኑ ርዝመት ከሰው ፍጥረት እስከ ወድቀቱ ያደርሱታል፡፡ በዚህ ጊዜ ወስጥ በጣም ሰፊ ነገር ማጥ ይቻላል፡፡ ሰው የተፈጠረለት ዐቢይ ዓላማ ሳይቀር ተገልጦ ተነግሯል፡፡ ከምዕራፎቹ ሽስ ምክንያት የዚህ የቅን ልቦና ዘመን በጣም አጭር ጊዜ ይምሰል እንጂ በሰው ልጅ ታሪክ ሰፊውን መሠረት የተጣለበት ተግባር ያሳየ እንደ ሆነ የተገለጠ ነው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ የተገለጠው መንፈሳዊ ሰው ወይም የእግዚአብሔር ሚልክና ምሳሌ የሆነው ሰው የተሰጠው ግዛትና የግዛቱ ወሰን ተስፋ ከማሆኑ በቀር ምን ያህል እንደ ተለማመደው በመጽሐፍ ግልጽ የሆነ ታሪክ የለወም፡፡ ሰማይን፣ ምድርንና ባሕርን ሁሉ የሚየካልለው ግዛቱ መንፈሳዊው ሰው በእርግጥ ገና የሚያገኘው ታላቅነት ነው፡፡ ዳሩ ግን ዘግይቶ የተገለጠው ፍጥረታዊው ሰው - ከሜት ሜታዊ የሆነ ወና ሕያው ነፍስ የተባለው ሰው በዘፍጥረት ምዕራፍ ሁለት ብቻ ብዙ ሊባልለት የሚያስችል ታሪክ አለው፡፡ አሁን ላነሣነው ሐሳብ ግን ብዙም ስለ ሚያስፈልገን እናልፋዋለን፡፡

ይሄ ‹‹መልካም›› የተባለው ዘመን ዕድሜውም ሆነ ታሪኩ እስከ ምዕራፍ ሦስት ይዘልቃል፡፡ አስቀድመን እንዳልነው የዘሙን ርዝመት ምን ያህል መሆኑን ለማወቅ ሳንቸገር ይሄ እንደ ስሙ ችግር የሌለበት የሚሻለው ዘመን በወድቀት ማዘጋቱ ነው የተነሣንበትን ሐሳብ የሚደግመው፡፡

‹‹እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አወሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ ነበር›› (ዘፍ.3÷1)፡፡ ይሄ የመጽሐፍ ክፍል እስከ ዛሬ የተተረጎማትን ሐሳብ መከተል ትተን መንፈስ የሚልጠውን ብንል አስገራሚ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ከምድር አደረገ (ዘፍ.2÷19)፡፡ ይህም እባብ ከምድር ከተደረጉት ጋር የተቆጠረ ነው፡፡ እርሱም ‹‹ከምድር አወሬ ሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ›› ተብሎላል፡፡ ይህም ተወዳዳሪ የሌለው ተንኮለኛ አወሬ በምዕራፍ ሦስት አልተፈጠረም ተንቀሳቀሰ - ተገለጠ እንጂ፡፡ በተንኮል ወደር ያልተገኘለት አወሬ በኋለኛው ዘመን የተገለጠው ነቢይ የሰው ልብ አድርጎ ገልጦታል፡፡ ‹‹የሰው ልብ እጅግ ክፉ ማንስ ያወቀዋል?››ብሎ፡፡ በምድር የነበረው አወሬ የኋላ ኋላ በታሪክ ወደ ባሕር ተሳበ፡፡ ይሄ ከባሕር የወጣውና ገናም የሚወጣው አወሬ ‹‹የሰወን እንጂ የእግዚአብሔርን የሚያስብ›› ጠላት ሰይጣን ነው (ማቴ.16÷23)፡፡ የጥልቁ ዘንዶ - የሰው ክፉ ሐሳብ በሁሉም (ባሕር - ጥልቅ) ወስጥ የተኛ ነው፡፡

ያ ‹‹መልካም›› የተባለው ዘመን በዚህ አወሬ መንቀሳቀስና መለጥ ተዘጋ፡፡ አወሬው በማነቱ ተገለጠ፡፡ ወድቀትም በዚያ አወሬ ምክንያት እንደ ተወሰነለት ሆነ፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ይሄ ዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ዘግናኝ ታሪክ ነው፡፡ ‹‹የንጹሕ ሕሊና ዘመን›› ወይም ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድና ሁለት በዚህ ሁኔታ ተዘጋ፡፡ ያ ዘመን ወደ ሌላኛው የተሻገረው በዚህ ዓይነት አሳዛኝ ድካም ነበር፡፡ በእግዚአብሔር እወቀትና ፈቃድ ዘሙን የተረከበው ወድቀት ‹‹መልካም›› የተባለውን ዘመን ዘግቶ ‹‹ክፉ›› የተባለውን ዘመን ከፈተው፡፡ ከዚህ ሁሉ ምስቅልቅል በሚሻል አካሄድ እግዚአብሔር ወደ ሐሳቡ ግብ እየተራመደ ነበር፡፡ በዚህም ዓይነት እርምጃ ‹‹የቅን ልቦናን ዘመን›› ዘግቶ ሌላኛውን ለመክፈት የተጠቀመው ወድቀትን ነው፡፡ ማን? እግዚአብሔር፡፡ ተደነቁ!

እንግዲህ ‹‹የቅን ልቦና - የንጹሕ ሕሊና ዘመን›› እንዴት አለቀ እንላለን?... ስለዚህ እንዲህ ቁጡ! በወድቀት - በጨለማ - በራቁትነት - በኩነኔ - በሞት - በጥላቻ፡፡ በብዙዎች ዘንድ የተኮነነው ወድቀት (በእርግጥ ማንም ያጸድቀው ዘንድ አይችልም፡፡) የአንድ ዘመን መዘጊያና የሌላኛው መክፈቻ ሁኖ እንደ መካከለኛ ሠርቷል፡፡ ወድቀትም በእግዚአብሔር ቅድመ ዝግጅት (ፕሮግራም) ወስጥ የነበረ ከሆነ ሰው ወድቀት አምጪ ሳይሆን ከእርሱ ጋር የነበረውን ገለጠ፡፡ ሰውም ወድቀትን በመገለጥ ባገኘው ፍርድ የሚርስበት ሌላ የእግዚአብሔር ቸርነት ነበረው፡፡ ደኅንነትን በወድቀት አግኝቶታልና!

ሰው ‹‹በነፃ ፈቃዱ›› በመከቀም ወይም ባለመከቀም ያስቀረው ወይም የፈጠረው አንዳችም አዲስ ነገር የለም፡፡ በጉ ከዓለም ፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ መታረዱ የዚህ እውነት አስረጂ ነው (ራእ.13÷8)፡፡ ወድቀት የአንድ አጋጣሚ ከስተት ወይም

አዳም በራሱ ‹‹ነፃ ፈቃድ - (Free will)›› ባለማጠቀም የተፈጠረ (በእግዚብሔር ዘንድ ግን ጨርሶ ያልታሰበና ያልተወሰነ) አዲስ ነገር ከቶውንም አይደለም፡፡ የክርስቶስ ሞት በቀደመችው በእግዚአብሔር እወቀት (ሥራ.2÷23) የታወቀና የተወሰነ ከሆነ ወድቀት ዱብ ዕዳ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ሌላኛው ፕሮግራም የሚያሻግር ነበር፡፡ ወድቀት ‹‹በረከት›› አይደለም፤ ግን ሰው ወደ እግዚአብሔር ማዳን - ወደ ሕያው አዳኝ - ወደ ክርስቶስ የሚመጣበት መንገድ አድርጎታል፡፡ እያንዳንዱ በጊዜው መላጡ እንጂ አስቀድሞ የታወቀና የተወሰነ ነው (1ጴጥ.1÷20)፡፡ ማንም ይህንን - ‹‹አስቀድሞ የታወቀወን) ይለውጥ ዘንድ አይችልም፡፡

እባብን - ከምድር አውሬ ሁሉ በተንኮል የላቀወን ለአንድ ዘመን ሽግግር ምክንያት ያንቀሳቀሰው ከእርሱ በላይ የሆነ ሉዓላዊ አለው፡፡ በእርግጥ ሥዓሊዎች በአንድ ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ከአንዲት ራቁቷን ከሆነች ሴት ጋር የሚጋገር ‹‹እባብ›› እንደ ነበረ የምናባቸወን ወጠጮ አቅርበዋል፡፡ ዳሩ ግን መጽሐፉ የተጻፈበት መንፈስ ማንንም እንዲህ ይረዳና ስለ እባቡ ያስብ ዘንድ አይመክርም፡፡ እነርሱ ቃል በቃል ነው የሳሉት፡፡ ከዚያ የባሰው እባብ ግን የሰው ልብና የሚያፈልቀው ሞርዝ መሆኑን ብዙዎች አልተረዱም፡፡ የሆነ ሆኖ በዚህ ማንነት አንድ ዘመን ተዘጋ፡፡ በዚህ ሁኔታ ነበር ሰው ከድጡ ወደ ማጡ የገባው፡፡ የተባረከ አባት እግዚአብሔር ሰወን በዚህ ሁሉ ይመራው ነበር - እስከ ጎልጎታ - የታሪክ እምብርት፡፡

እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ወደ ደኅንነት የወሰደበት ስለ ምን ማወቅ መቀበልም አልፈለግንም? እግዚአብሔር ወደ ደኅንነት የተራመደው በወድቀት መሆኑን ያወቅንበት ቅጽበት ወስጣችን በዕረፍት ይሞላል፡፡ ወድቀት ዘመንም ዕድልም ተሰጠወ፤ አስገራሚ ነው! እርሱም የነበረወን ጊዜ አስረጀ፡፡ ሰወም ወደ ተፈለገውና የእግዚአብሔር የዘመናት ዓላማ ወደ ሆነ ጫፍ ይሄድ ዘንድ ወድቀት ገጠመው፡፡ እግዚአብሔር ወደ ራሱ ግብ በቀየሰው አንድ ሚሞር ላይ ወድቀት አብሮ ተሰምሯል፡፡ ደኅንነት ያለ ወድቀት፤ ብርሃን ያለ ጨለማ፤ ክብር ያለ ወርደት፤ አከሊል ያለ ሚቀል፤ ትንሣኤና ሕይወት ያለ ሞት፤ ... አልሆነም፡፡ ስለተባለም‹‹የቅን ልቦና - የንጹሕ ሕሊና ዘመን›› ተዘግቶ ወደ ሁለተኛው ዘመን የገባው በወድቀት እንደ ሆነ ልብ ሚለት ያሻል፡፡ ይሄ ዘመን ወደ ሌላኛው ሲሻገር ድል፣ መከናወን፣ መታቃቃት፣ ብርታት፣ አሸናፊነት፣ ... ኖሮት ሳይሆን ወድቀት፣ ጨለማን፣ ሞርገምን፣ ኃጢአትን፣ ሞትን፣ ፈተናን... ሕይወቱ አድርጎ ነው፡፡ እግዚአብሔር ዘመናትን የለወጠበት መንገድ እንግዲህ ከዚህ ተነሥቶሁ አንድ ልትሉ ነው፡፡

2. የሕሊና ወይም ሰው በሕሊናው ተጠቅሞ የኖረበት ዘመን

ስለ ኋለኛው ፊተኛው መሻሩ ከርከር የሌለበት ነገር ነው፡፡ ከፊተኛው - ‹‹ከቅን ልቦና ዘመን›› የዚህኛው መኮላት ስለ ተሻለ አይደለም፡፡ የኋለኛው ዘመን ግን ተሻለም አልተሻለም የኋለኛው የተፈለገና የተወሰነ ስለ ሆነ የፊተኛው ወይም የቀደመው ዘመን በድካምና በስንፍና ሚለቁ በሁላችሁ ዘንድ እወነት ይሁን፡፡ የልዑል እግዚአብሔር ፕሮግራም ደግሞ ዘመናትን ወደ አንድ ግብ ይወስዳቸው ዘንድ አለወና አንዱ በአንዱ እየታረደና እየተለወጠ ወደ ጌታ ቀንና ወደ ተወደደው ወደ እርሱ ዓመት ያደርሰዋል፡፡

የዚህ የሕሊና ዘመን (Dispensations of Innocence) ጊዜ እርዝመት ከአዳም ወድቀት አንሥቶው እስከ ኖኅ ስድስት መቶኛው ዓመት ድረስ ያደርሱታል፡፡ ምናልባት ለዚህ ከፍለ ጊዜ የተሰጠው ማጠሪያ ‹‹ሰው በራሱ የሕሊና ሕግ ሊጠቀም ዕድል ተሰጥቶት ነበር›› ብለው ስለሚያምኑ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህም ምክንያት በቃልም ይሁን በጽሑፍ ሊጠቀስ የሚቻል አንዳችም የተሰጠ ሕግ አልነበረምና ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ‹‹ሰው በተሰጠው በዚህ በሁለተኛው ዘመን በሕሊናው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽሞ ተገኝቶ ነበር ወይ?››የሚለወን ለመመለስ ታሪኩን ተጠግቶ መመልከት አስፈላጊ ሊሆን ነው፡፡ በመላኮት የተወሰነው ወድቀት ከተገለጠ በኋላ - ከዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት በኋላ እስከ ኖኅ ስድስት መቶኛው ዓመት ድረስ ታሪክን ስናጠና በሰው ሕይወት ከቁጥጥር ውጭ የወጡ ብዙ የተበላሹ ነገሮች ሆነዋል፡፡ እግዚአብሔር ሰወን በወቃ ጥፋት እስኪበቀለው የሰው መንገድ፣ አካሄድና አኗኗር በእግዚአብሔር ፊት ፈጽሞ ተበላሽቶ ነበር፡፡

ቁም ነገሩ የነዚያን ዘመናት ባሕሪይ ለማጥናት አይደለም አነሣሣችን፡፡ ዋናው ነገራችን፡- ‹‹ዘመናቱ እንዴት አለቁ?›› ከሚለው ጥያቄ የሚኘው መልስ ነው፡፡ ይህም ሁኔታ አሁን እኛ ያለንበት ዘመን ሚለት ለእኛ የተሰጠው መጋቢነት (ሥፍረ - ዘመን) እንዴት ያልቅ ዘንድ አለወ? የሚለወን ልናይበት ያስችለናል፡፡ የዚህ የሁለተኛው ዘመን ጅማሬ የቃየን መወለድና የቃየናዊነት በምድር ሁሉ መከፋፋት እንደ ሆነ ይታወቃል፡፡ ይሄም ጅማሬ እስከ የት እንደ ደረሰ ምዕራፎቹን በጥልቀት ሞት የተገባ ነው፡፡ ሰው በቅናት ወንድማ ከገደለበት የታሪክ ድፍርስ አንሥቶ ያለ እግዚአብሔር በመኖር ራሱን እስከ ገደለበት ጨለማ መጥቷል፡፡ በአንድ ሰው - በአቤል የጀመረው የሞት ታሪክ ሰዎች ሁሉ (ከኖኅና ከቤተሰቦቹ በስተቀር) ከምድር እስኪጠፉ የደረሱበት አኗኗር እንደ እግዚአብሔር ቅን ፍርድ ሲታይ ፈጽሞ የተበላሸ ነበር፡፡

የቃየን መንገድ ወይም ቃየናዊ አካሄድ መጽሐፍ በትክክል እንዳስቀመጠው የቅናት አካሄድ ነበር፡፡ የእርሱ ሥራ ክፉ የወንድሙ ሥራ ግን ጽድቅ ነበርና (ዮሐ.3÷12) ወንድሙ መሥዋዕቱ ሰምሮለታልና ቀንቶ ገደለው፡፡ በቃ ይኸው ነው፡

‹‹የወንድሜ የአቤል መሥዋዕት ለምን ተቀባይነትን አገኘ?›› ብሎ ከታናሹ መምር ያልወደደ ነበር የቃየን አካሄድ፡፡ ይሄ የትዕቢት መከተዋት ነው፡ የሰው ታሪክ ጅማሬ ቅናት፣ ትዕቢት፣ ኩሩነት፣ ታናሽነትና መቃወም፣ ሁል ጊዜ በልጦ መገኘት… ናቸው፡ እነዚህ ‹‹እጅግ ከፉ›› የተባለው የሰው ልብ የሚታፍቸው ሚዞች አይደሉምን? ጻድቁን አቤልን ለመግደል አላመነቱም፡ እነዚህ ከሰው ገነት - ከልቡ ወጡ፡ በሥጋም ተገልጠው አቤልን ገደሉ፡፡ በገነት (ደግሜ ልበል) - በሰው ልብ የጀመረው ተንኮል - ወድቀት - ጨለማ - ኃጢኣት… በገሀዱ ዓለም ይፈጸምና አካል ያገኝ ጀመር፡፡ እስከ ጥፋት ውኃ የዘለቀው የሰው አካሄድና አኗኗር ፈጽሞም በእግዚአብሔር ፊት መጣላሽት የመጀመሪያው ጥንስስ መፍላቱና መጨልጡ ምልክት ነበር፡፡

በእርግጥ በዚህም ዓይነቱ ስፍረ ዘመን ወስጥ ስለ ነበሩት የእግዚአብሔር ቅሬታዎች ከብሩ ለራሱ ነው፡ ልዑሉ ሁል ጊዜ የራሱ የሆኑት አሉት፡፡ በእነዚህም ነው ነባሩን ዘመን የሚያስረጀውና የሚሽረው፡ ቅሬታው በመመረጡ፣ በማጋጀቱ፣ በሚዳኑና ሊገለጥ በመቅረቡ ብቻ የነበረው ዘመን ሲደክም፣ ሲነቅዝ፣ ሲበላሽና ሲያልቅ ተስተወሏል፡፡ እነርሱም ያለወን ገድለው ከሌላኛው ዘመን ጋር ለአዲስ ቀን ይነሣሉ፡፡ ያ ዓለም - ያ ዘመን ያልነበረ ሲሆን - ሲጠፋ በእርግጥ የኖኅ ዘመን ተገለጠ፡ አስቀድመን እንዳልነው ‹‹ለኖኅ የተሰጠው ዘመን ከመምጣቱ በፊት የነበረው አሮጌው ዘመን እንዴት ነበር?›› ብለን ስንጠይቅ እውነታው የሚዘገንን ነው፡ ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን በሚሳትና በመተው በርትቶ ነበር፡፡ የትኛውም ክፋትና ጥፋት እርሾው ይሄ አይደለምን?... ከወድቀት ጊዜ አንሥቶ እስከ ኖኅ ስድስት መቶኛ ዓመት ድረስ ያለው የጊዜ ርዝመት ቀላል አልነበረም፡ በሦስትና በአራት ምዕራፎች ብቻ እንደ ተወሰነና እኛም በአምስት ደቂቃ ወስጥ እንደምናነበው ኣጭር ጊዜ አልነበረም፡ ታድያ ይሄ ሁሉ ረዥሙ የሰው ልጅ ታሪክ ያሳየው ዕድገት ቢኖር የሰው ልጅ የልቡ ክፋት ነበር፡፡

ዘፍ.6÷5፣ 11-13፡ - ‹‹ቁ.5 እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፣ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁል ጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ ቁ.11 - ምድርም በእግዚአብሔር ፊት ተበላሽች፣ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በምድር ላይ መንገዱን አበላሽቶ ነበርና፡፡ ቁ.13-እግዚአብሔርም ኖኅን አለው፡ - የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሶአል፣ ከእነርሱ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለችና፤ እኔም እነሆ ከምድር ጋር አጠፋቸዋለሁ፡፡›››

የኖኅን አዲስ ዓለም - አዲስ ዘመን ያመጣው ያለ ጥርጥር ጥፋት ነው፡፡ ከጥፋትና ከፍርስራሽ ወስጥ አዲስ ዓለም - አዲስ ዘመን - አዲስ ትወልድ ወጣ፡፡ በጥፋት ወስጥ የቃል ኪዳን ዘመን ታየ - ሃሌሉያ! የጥፋት መሻሻው ክፉት ቢሆንም አዲሱ ዓለም እንዲህ ተገኘ፡፡ ያስገርመል! የሕሊና ዘመን እንዴት አለቀ?... የዚህ መልስ የምጽፍበት መንፈስ እንደ ሆነ በድጋሚ አሳስባለሁ፡፡ እንደ መጀመሪያው ሁሉ ሁለተኛውም ዘመን - ዓለም ወደ ሦስተኛው ሲዘወር ወይም ሲገባ የተሰጠውን ፈተና አልፎ ሳይሆን ወድቆ ነው ልብ በሉ፡፡ አስደናቂው የእግዚአብሔር አሠራር እዚህ ጋ ነው፡፡ እያንዳንዱ ስፍረ ዘመን በመወደቅ - በድካም - ተስፋ በመቁረጥ - በኃጢኣት - ከእግዚአብሔር ፈቃድ በሜግፈግ - ፈጽሞ በመሞት - ከጀመረበት ጉልበት ፈጽሞ በማል… ነው ወደ ሌላኛው ዘመን የተሻገረውና የተነሣው፡ በብርታት - በጉብዝና - በማቃቃት - እግዚአብሔርን ደስ በሚሰኝትና ፈቃዱን በሜጸም - በከብርና በድል - በብሃንና በሕይወት… የተፈጸመ ዘመን ጨርሶ አልታየም ወገኖች ሆይ፡፡

በጊዜአቸው፡ - ‹‹ወርቃማ፣ የከበረ፤ ደማቅ… ዘመናት›› የተባሉ ሁሉ ከተከናነቡት ድካም፣ ጨለማና ወድቀት የተነሣ ከፉኛ ደበሱ - ተበላሹ - በሰበሱ፡፡ የደመቀው ዘመናቸው በቀስታ እየከሰመ እየረገፈ ከሰው ሁሉ ልብ ወጥቶ ዋጋ ቢስ ሆኗል፡፡ በእነርሱም የነበረውና ተስፋ የቆረጠው ትወልድ ሌላ ዘመን ተመኘ፡፡ የሰው ወይም ለሰው የተሰጠው ዘመን የፀሐይን ጉዞ ይመስላል - በፀሐይ አካሄድ ይመሰላል፡፡ ንጋት አለው - ብሩህ ንጋት! ውብ ሚለዳ! ብርሃኑንና መቅቱን እየጨምረ ቀትሩ ላይ ይደርሳል፡፡…መልሶ መበረድ ይጀምራል - ትኩሳቱ ይደከማል፡፡ ያዘቀዝቃል፡፡ ይደበዝዛል፡፡ ይገባል፡፡ ፈጽሞ ይሰወራል - ይጨልማል፡፡ … መልሶ ይነጋ ዘንድ የሰው ቀን - የሰው ዓመት - የሰው ዘመን… እንዲህ ይሆናል፡፡

ስለዚህ ከዘፍጥረት ሦስት እስከ ኖኅ ስድስት መቶኛ ዓመት ድረስ በሁለተኝነት የሚታወቀው የሕሊና ዘመን ነጋ - ጋለ - በረደ - ደከመ - አዘቀዘቀ - ገባ - መሸ - ጨለመ - በድቅድቅ ተዋጠ፡፡ ሌላ ዘመን ነጋ፡፡ ሦስተኛው ዘመን ጀመረ፡፡

3.የሰው ግዛት (የሰው መንግሥት) ዘመን

ኖኅ በቀስተ ደመና ምልክት በብዙም የተስፋ ቃል አዲሱን ዓለም ከቃል ኪዳን ጋር ከተረከበው አንሥቶ እስካለቀበት እስከ አብርሃም ጥሪ ድረስ እጅግ ሰፊና ወሰብሰብ ነገሮች በጉልህ ታይተዋል፡፡ በምዕራፍ ዘጠኝ ሰው የሚጸደድበትን ባለፉት ዘመናት ያልነበረ ሕግን አገኘ፡፡ በእርግጥ በኖኅ ብዙ አዳዲስ ነገሮች ተጀምረዋል፡፡ ከዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ አንሥቶ እስከ ኖኅ ስድስት መቶኛ ዓመት ድረስ በምድር ላይ ዝናብ እንዳልነበረ ካያችሁ ሚልካም አይታችኋል፡፡ በዚህም አዲስ ነገር ነው የነበረው ዓለም ሰጥሞ የጠፋው፡ በእርሱም ሌላ ዓለም ተገለጠ፡ በኋለኛው ዘመን የተገለጠው የደም ሥርዓት (የመሥዋዕት ዋጋ) በኖኅ አዲስ ዘመን ሲገለጥ ሰው በተጨማሪ ሥጋን ይበላ ዘንድ ተሰጠው፡ ኖኅ የስሙ ትርጓሜ - ‹‹እግዚአብሔር በረገማት ምድር

ከተግባራችንና ከእጅ ሥራችን ይህ ያሳርፈናል›› ማለት ነው፡ ነገር ግን ለእርሱ የተሰጠው የዕረፍት ዘመን ሳትመጣ የነበረው ደከሞ መወገድ ነበረበትና ይሄ ሆነ፡፡

የአበላል ወግ፤ የአስተዳደር ሥርዓት... በአዲሱ ዘመን ተካትተዋል፡፡ ሦስቱ የኖኅ ልጆች በትንቢት መንፈስ በዚያው ምዕራፍ የወደፊት ዕድላቸው ተወሰነ፡፡ ስለ እርግማን እንኳ ቢወሳ የተረገመው በእርግጥ ከኖኅ ሦስት ልጆች አንዱ የነበረው ካም ሳይሆን የካም ልጅ ከነዓን ነበር፡፡ ካም ቢረገም እንኳ መርገምን በአካል የሚልጠው ወይም ለመርገም አካል (ሥጋ) የሚሰጠው ከነዓንን ለዚህ አስነሥቶት ነበር፡፡ የማንም ዕድል በእግዚአብሔር የታወቀና የተወሰነ ነውና፡፡ ያም ቤተሰብ እየሰፋ ሄደና ሕዝብ ሆነ፡፡ አሕዛብ በእነዚህ ተከፋፈሉ፡፡ ምድር ተከፋፈለች፡፡ ሕዝብና ሀገር ሰፋ ተከፋፈሉም፡፡

ዘፍጥረት ምዕራፍ አሥራ አንድ የሚከፋፈል መጀመሪያና መጻሻ ምዕራፍ አልነበረም መጽሐፉን ተጠግተን ካስተዋልነው፡ ይሁን እንጂ መጠተንና መላያየት የተገለጠው በዚህ ምዕራፍ እንደ ነበረ አይካድም፡ የሕዝቦችም ዕድል በኖኅ በተገለጠው የትንቢት መንፈስ (በምዕራፍ ዘጠኝ) ተወስኗል፡፡ አሥረኛውም ምዕራፍ አሕዛብ በየወገናቸው መከፋፈላቸውን ነው የሚገረን፡፡ የምዕራፍ አሥራ አንድ መከፋፈል በቋንቋ ከሆነና ቋንቋም የሐሳብ መለጫ ነውና ሰዎች በሐሳብ፣ በሚዳት፣ በወሰጥ ስሜት... የተከፋፈሉበትም ሁኔታ ነበረ፡፡ ጉዳዩ ላይ ላዩን ከምናየው የበለጠ የከፋ ነበረ፡፡ ከዚያ በኋላ ሕዝቦች ሊደባለቁ የሚችሉ ሆኑ፡፡ ከዚያ ታሪክ ወደዚህ ሰዎች በአስተሳሰብ፣ በሚዳት፣ በአመላካከት፣ በባሕል፣ በአኗኗር፣ በቋንቋ... የተለያዩና የሚነጋገኙ መሰሉ፡፡ ዓለም እስከዚህ ዘመን ድረስ ሊታረቅ - ሊዋሐድ... በማትችልበት ልዩነት ላይ የመድረስዋ ችግር የዚያ መሻሻ ውጤት ነው፡ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፡- ‹‹ብረቱ ከሸክላው ጋር ተደባልቆ እንዳየህ፣ እንዲሁ ከሰው ዘር ጋር ይደባለቃሉ፤ ነገር ግን ብረት ከሸክላ ጋር እንደማይጣበቅ፣ እንዲሁ እርስ በርሳቸው አይጣበቁም›› (ዳን.2÷43)፡፡

ከዘፍጥረት ምዕራፍ ዘጠኝ የመጀመሪያ ጥቅሶች አንሥቶ እስከ ምዕራፍ አሥራ አንድ የሚጨረሻ ጥቅሶች የዘሙ (የሰው ግዛት - የሰው መንግሥት ዘመን - (Dispensations of Human Government) እርዝመት ቢሆንም አጭር ጊዜ ይመስላል፡፡ ግን አይደለም፡ ያ ቅሬታ - ኖኅና ቤተሰቡ ሕዝቦችና ሀገሮች እስከሚሆኑ በዙ፤ ተባዙ፡፡ የተነሣንበትን ሐሳብ ሚስረጃ ስናበዛ የሚያስገርመው ነገር ያ ቅሬታ - ያ አዲስ ዘመን፣ አዲስ ሥርዓት፣ ቃል ኪዳንና አስተዳደር... የተሰጠው ወገን እንኳ አርጅቶና ደከም መገኘቱ ይሆናል፡፡ በመድከሙም መላወጥ አስፈለገው - ያስገርማል!

እግዚአብሔር ማንንም አንድን ነገር ሰጥቶ አልሞከረም፡ ከሰጠውም መከራ ተነሥቶ አላቀደም፡ አልወሰነም፡ ዓላማውን አልፈጸመም፡ ፕሮግራመንም ለሰው ከሰጠው መከራ፣ ፈቃድ... ወዘተ ተነሥቶ አልዘረጋም፡ በጭሯሽ፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ግዛትን ሰጥቶ አልሞከረውም፡ እግዚአብሔር ለዓለም እየገለጠው ያለው የመከራውን ውጤት ሳይሆን አስቀድሞ ያወቀውና የወሰነው ዘላለማዊ ሞረሐ ግብሩ ነው፡ እስከ ዛሬ እግዚአብሔር አምላክ የሚይዘከም፣ የሚልቅ፣ የሚለወጥ፣ የሚረጅና ተፈትኖ የተሰጠ ዘመን ለየትኛውም ትወልድ አልሰጠም፡ ሊደክምና ሊያረጅ ተሰጥቶ የነበረው የትኛውም ዘመን ጊዜው ሲደርስ እንደ ተወሰነለት ሆነ፡፡ አሁን በእነዚህ መከሚሮች እያየነው ያለው ዘመን በቃል ኪዳን፣ በቀስተ ደመና በማሉ ቢደረግም የሚለወጥ - የሚደክም - የሚያረጅ ዘመን ነበረ፡፡ ይሄ በኩራት ነው በዘፍጥረት ምዕራፍ አሥራ አንድ የቦካወና ቡሆ ሆኖ የተጋገረው፡ መጀመሪያ የሌለው በኋላ አዲስ ሆኖ የተከሰተ ምንም ነገር የለም፡፡

የካምና የሴም ነገዶች ከያፌቶች ይልቅ ተስፋፍተው የታዩበት ዘመን ነበረ የመጀመሪያው ዘመን፡፡ ታላቁ ናምሩድ የገነባው ‹‹ኢምፓየር›› ሃይማኖትንና ፖለቲካን ያጣመረ ሲሆን ባዕድ አምልኮዎች የመሠረት ድንጋያቸው የተተከለው በዚያን ዘመን ነበረ፡፡ ይህም ዘመን ብዙ ዓመታት እስከ ወዲህኛው ተጉዟል፡፡ በዚህ ዘመን መጨረሻ (Climax) የጣኦት አምልኮ ጣራውን የነካበት ጊዜ እንደ ነበረ ይታያል፡፡ ‹‹አባቶች›› የተባሉት ከወንዝ ሚዶ ሌሎችን አሜልክት - በባሕሪይአቸው አሜልክት ያልሆኑትን አሜልክት የሚያመልኩበት ጊዜ ነበረ ጊዜው፡ ታሪክ እንደሚገረን አብርሃም ከአባቱ ከታራ ጋር የጨፈቃ ጣኦት አምርቶ ይሸጥ እንደ ነበረ ነው፡ እርሱስ የተቅበዘበዘ ሶሪያዊ አልነበረምን? በዚህ ሁኔታ የተገኘ አባት ነው፡ የኖኅ ዘመን - የሰው ግዛት ዘመን እየተጓዘ በቀስታ እዚህኛው ጫፍ ላይ መጥቶ ነበር፡፡ ያ ‹‹ወርቃማው የሰው ግዛት ዘመን›› እንደ ጅማሬው ሳይሆን ቀርቶ በድካሙ ጣራ ላይ ደርሷልና እርሱም ይለወጥ ዘንድ ተገባው፡

ዘሙ የተጀመረው ‹‹እግዚአብሔር በረገማት ምድር ይህ ያሳርፈናል›› በተባለው፣ በባለ ራእዩና ዓለምን በእምነት በኮነነው በኖኅ እንደ ሆነ ይታወቃል፡፡ የዚህስ ጊዜ ጅማሬ ቃል ኪዳንና ተስፋ አልነበረምን?... ታድያ ምን ይሁን እንዲያም ሆኖ ማለቁ አልቀረም፡ በእርግጥ የአንድ ዘመን ጅማሬ ይሄ ቢሆን ወይም ከዚህ ይበልጥ ቢሻል ያንን ዘመን ከማርጀትና ከመድከም ያድነው ወይ ይጡበቀው ዘንድ አይችልም፡ ተፈጽሞ የተሰጠ ዘመን የለምና! ዘሙም በረዘመና ባረጀ ማጠን የሰው መንገድ - አካሄድ - ሕይወት ከእግዚአብሔርና እርሱን ከመምሰል እየራቀ ሄደ፡፡ የወሰጠፁ ባዶነት፣ ጭፍቀትና አለማረፍ በእጆቹ ስራና በተፈጠረ ሃይማኖታዊ ተግባር ሊያሳርፍ የተጋበት ዘመን ነበረ የሰው ልጅ፡ በሥራውም ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚገባውና እንደ ሌለ መከረ፡፡ ሰው የበለጠ ሰው እየሆነ በአወሬነቱ ቁንጮ ላይ ተደላድሎ የታየበት ዘመንም ነበር ዘሙ፡፡ እንደ ቀደሞት ሁለት ከፍለ ዘመናት ይህኛውም ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተወሰነለት የሚጨረሻውን ድካም ደከመ፡ የእምነት አባት የተባለው

አብርሃምም የተጠራው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን አብርሃም ለቅሬታነቱ የተለየ የሕይወት ሚስረጃ ልናጣቅስለት ባንችልም እግዚአብሔር ለሚሥራው አዲስ ነገር ግን በአብርሃም መጀመሩ የታመነ ነው፡፡

የሰው ግዛት ዘመን እንደ ጀመረ አላለቀም፤ መቼውንም፡፡ ሰው እንዳነሣሡ ጨርሶ አያወቅም፡፡ በየትኛውም ዘመን የነበረው የሰው ግዛት እንደ ጀመረ ዘግቶ አያወቅም፡፡ በዓለም ላይ ብዙ ሀገሮች ጠንካራ ግዛትና ሰፊ ኢምፓየር ነበራቸው፡፡ ፍጻሜአቸው ግን በጀመሩበት አልሆነም፡፡ በምንነጋገርበት ዘመን ወስጥ የነበረው የአሞራውያን ግዛት እንደ ምሳሌ ብንጠቅስ እንዴት ጀመረ? በብርታት - በጥንካሬ - በኃይል - በማስፋፋት - ሁሉን በማንቅለል ጀመረ፡፡ ሲጨርስ ግን ሁሉን በማጣት - በድካም - በማለቅ - በድህነት ነበረ፡፡ ዋናው ነገር ግን በርትቶ ያለቀ ዘመን አለመኖሩን ማወቁ ላይ ነው፡፡ ለሰው ወይም ለአንድ ትውልድ የተሰጠው ዘመን ልክ እንደዚያው ሰው ወይም ትውልድ ዕድሜ ዓይነት ነው፡፡ ሰው ይወለዳል፡፡ ያድጋል፡፡ ወጣት - ጎልማሳ ይሆናል፡፡ ይኖራል፡፡ ያረጃል፡፡ ሙሉ ኃይሉ ያልቃል፡፡ በሜጨረሻ ሙሉ በሙሉ ወደ አለመቻል ይመጣል፡፡ ዘመንም እንዲሁ ነው፡፡ በቀስታ ከወጣበት ከፍታ ማዘቅዘቅ ይጀምራል፡፡ ባደገበት ሳይሆን በጀመረበት እንኳ ላይገኝ ፈጽሞ ይዝለፈለፋል፡፡

አዲስ ዘመን ሲነጋ በአሮጌው ዘመን ላይ ይመሻል፡፡ ያለው ሁሉ ነገር በድካም፣ በወርደትና በማስበስ ይዘራል፤ በኃይል፣ በክብርና ባለ ማስበስ ሊነሣ፡፡ የሰው ግዛት(መንግሥት) ዘመንም እንዲሁ ሆኖበታል፡፡ የሰው ግዛት ዘመን ወደ ሌላኛው አዲስ ዘመን ሊነሣ ሞተ፡፡ ወደቀ፡፡ በሰበሰ፡፡

4.የተስፋ ወይም ተስፋ የተሰጠበት ዘመን

ይሄ በአብርሃም የጀመረ ዘመን እንደ ነበረ ይነገራል፡፡ አብርሃም በተጠራ ጊዜ ከትወልዱ መካከል የሚያስመካው ወይም በትወልዱ ጻድቅ ሆኖ የተገኘበት ነገር እንደ ነበረ አናነብም፡፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ጥሪ ላይ ያረፈ ነበር የአብርሃም ሁኔታ፡፡ መጽሐፍ ስለዚህ ሰው ሲናገር፡- ‹‹አባትህ (አብርሃም መሆኑ ነው፡፡) የተቅበዘበዘ ሶሪያዊ ነበረ›› ይልለታል፡፡ ይሄ ሰው ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ለዓላማው በተቃኘ ጊዜ አቻ ያልተገኘለት የእምነት አባት (ፓትርያክ) ሆኖ ተገኘ፡፡ በእርሱም የጀመረው ዘመን ሕግ እስከ ተሰጠ እስከ ኮሬብ ዘለቀ፡፡ አራት መቶ ሠላሳ ዓመት ያህል ሚሞላት ነው፡፡ ይሄ ዘመን እንዴት ጀምሮ እንዳለቀ ከአብርሃም ጀምሮ መቼ እስከ ተነሣበት ጊዜ ድረስ ማየት ይቻላል፡፡

እግዚአብሔር እንዴት እንደ ጀመረ እስኪ ተመልከቱ፡፡ ብዙ ጊዜ በአንድ ሰው ወይም ቤተሰብ ነው እግዚአብሔር አዲስ ነገር የሚጀምረው፡፡ በተለይ ለወጥን በብዙኃን አምጥቶ አያወቅም፡፡ እግዚአብሔር በቡድን ወይም በማነበር ምንም አልጀመረም፡፡ የጀመረበት ዘር ግን ወደ ቡድንና ማነበር ሁሉንም ወደ መመረስ ሲያድግ ተስተውሏል፡፡ ከዚህ ነው ሕዝብን - ቁጥር የሌለውን ወገን ያደረገው፡፡ ግን እግዚአብሔር እንዴት እንደ ተራመደ ታዩ ዘንድ በርቱ፡፡ አብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት ነገር እስከ እኛ የሚደርስ ከሆነ በክርስቶስ የዚህን ፍጻሜ ለማምጣት እግዚአብሔር አምላክ በተጓዘበት የጽድቅን፣ የእውነትን፣ የሞገንና የመነብነት ጎዳና ሁሉ ሰውም ተከትሎ ለመጓዝ የደረሰበት ውጣ ወረድ - ከፍተኛና ዝቅታ - ብርታትና ድካም... አስገራሚ ነው፡፡

አብርሃም ሕዝብ እስኪሆን ወይም እስራኤል ሀገር እስኪሆን የተጓዘው ጉዞ በሰሚይ ምሪት ይሁን እንጂ የምድር ድካምና ሚርጀት ሳይለየው ነበር፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ ብቻውን ይሠራ ነበር፡፡ አብርሃም - እስራኤል ሕዝብ ሆኖ ያለቀው - የተፈጸመው በብዙ ድካም እንደ ሆነ ምስክርነታችሁን አብዙ፡፡ እግዚአብሔርም ስለ አብርሃም፣ ስለ ዘሩና ስለ ርስቱ ተስፋን በሰጠ ጊዜ አብርሃም አንድ ጥያቄ ጠይቆ ነበር፡- ‹‹... እንድወርስ በምን አወቃለሁ?›› ብሎ፡፡ የዚህ መልስ በምልከቶች ደረሰለት፡፡ ‹‹ጨለማና ከባድ እንቅልፍ›› ሆነ፡፡ ይሄ ከመሥዋዕት በኋላ አይደለምን? አብርሃም እንስሳትን ሠውቷል፡፡ ሰው በዘሙ ሁሉ ከእርሱ ወጭ እንስሳትን ይሠዋ ነበር፡፡ ከርስቶስ ግን ራሱን ሠዋ፡፡ አብርሃም እንስሳትን ከሠዋበት ከዚህ ምዕራፍ ብዙ ዓመት በኋላ ራሱን በይስሐቅ በኩል ሠውቷል፡፡ የርስቱ ሚረጋገጫ ግን ‹‹ጨለማና ከባድ እንቅልፍ›› መሆኑ ምሥክር አለው፡፡ እንዴት እንደሚመረስ ሚረጋገጭው ነበርና፡፡ በሰው ዘመን ሲመሽ - በሰው ሌሊት በእርግጥ እግዚአብሔር አንድ ነገር ይሠራል፡፡ ሰው ይነሣ ዘንድ መወደቅ አለበት፡፡ ቤተ ክርስቲያን (ፍጥረት ሁሉ) በከባድ እንቅልፍ ተገኝታለች (ተገኝቷል)፡፡ የአብርሃም ከባድ እንቅልፍ የርስቱ ሚረጋገጭ መያዣ ነበር፡፡

ተስፋ የተሰጠበት ይሄ ዘመን ይበልጡኑ በአንድ ወገን ላይ ያዘነበለ ነበር በእርግጥ፡፡ ታሪክ ከዚህ ወዲህ አንድን ወገን ብቻ ተከትሎ ይዘግብ ጀመር፡፡ እግዚአብሔር አሁን በጅምላ ሳይሆን በነጠላ ሞት ጀመረ፡፡ በዚህ አንድና ታናሽ ዘር ሁሉን ያድን ዘንድ አለወና!

‹‹እግዚአብሔር ያፌትን ያስፋ፡- <u>በሴምም ድንኳን ይደር፤</u> ከነዓንም ለእርሱ ባሪያ ይሁን›› (ዘፍ.9÷29)፡፡ ምርጫም ሆነ ርስት፣ መወደድም ሆነ መላየት በመንፈሳዊ በረከት (በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ) ላይ ያረፈ እንደ ሆነ ሚስተዋል

ይቻላል፡፡ ያፌትም በሴም ድንኳን የሚኖሩ ምሥክር የሴም ድንኳን በሴም አምላክ ስለ ተባረከ አይደለምን? የተነገረውም ትንቢት ራሱ ሴም የተለየ ወገንና ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ግንኙነት እንዳለው አሚልካች ተደርጓል፡፡ ቀስ በቀስ ደግሞ ብዙ ሚላኮታዊ መለሎች በእርሱ ሚስጥር እወጓ ሆኑ፡፡ ይሁንና በሴም ሚስጥር አብርሃም... ይሁዳ... ዳዊት... ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ወልደት ከመምጣታቸው በፊት በመንፈሳዊው ዓለም ካልሆነ በቀር የሴም ነገር ለራሱም ሆነ ለትወልዱ ለሚጋገጥ ቀርቶ ለጥርጣሬም አልዳዳወም፡፡

‹‹የሴም ትወልድ ይህ ነው፡ ሴም የመቶ ዓመት ሰው ነበረ፣ አርፋክስድንም ከጥፋት ውኃ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ወለደ›› (ዘፍ.11÷10)፡፡ ይሄ ከባቤል በኋላ ነው፡፡ ሆኖም ግን እዚህ ሰፈር ስንደርስ እግዚአብሔር የታሪክን አቅጣጫ በእጅጉ ሚልክ ሊሰጠው የፈለገ ይሚከላል፡፡ ከዚህም ምዕራፍ ወድያ የነበረው ታሪክ በጥቅሉ ስለ አዳም ዘር ሞላው የዘገበ ሲሆን አሁን ግን አዲስ ነገር መጀመሩን እናሰምርበታለን፡፡ የሴም ታሪክ እየጎላና እየደመቀ መጣ፡፡

ሴም በተመረጠውና በተፈላጊው ሚስጥር መገባቱን ከሚጋገጡ በፊት የአይሁድ ወይም የአሕዛብ ተብሎ የተከፈለው ነገር የታወቀና ጉልህ አልነበረም፡፡ ይሄ እንኳ በጣም ሩቅ ነው፡፡ አብርሃም ተጠርቶ ቢወጣም ይስሐቅ እስከ ተወለደ ድረስ የተስፋ ዘር ማንነትና ግቡ ገና ግልጽ አልተደረገም፡፡ ‹‹አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው›› ተብሎ ያልተከፈለው የቀደመው የወል ታሪክ መዛከርነቱ ስለ አንድ ወገን - ስለ አዳም ነበረ፡፡ በታሪክም ጉዞ ከሰፊው ሚስጥር አንድ ቀጭኖና ጠባብ ሚስጥር ራሱን ገለጠ፡ ታሪክም ለዚህኛው ቀኙን ለገሰው፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የጀመረው ምንጭ (አዳምና ሔዋን) ባሕር (ሕዝብ) ሆነ፡፡ አስደናቂው ነገር ደግሞ እነሆ፣ ያ ባሕር ራሱ ከዚያው ከራሱ በወጣው ምንጭ መንጻቱ ወይም ሚከሱ ነበር (ዘፍ.12÷3)፡፡ ይሄ ከባሕር የወጣው ዝርት ግን ማን ነው? ሴም ነው፡ አብርሃም ነው፡ እስራኤል ነው፡

የሴም ነገር ከደኅንነት ታሪክ አኳያ ሲታይ የከበረ ነው የሚለው እውነት እጅግ የጸና ቢሆንም ቅሉ ከእርሱ ሚስጥር የሆነው አብርሃም ተጠርቶ እስከ ወጣና ተስፋ እስከ ተሰጠው ድረስ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበው ነገር ገና ድብቅና ስወር ነበር፡፡ በሴም ሐረግ አሥራ አንደኛ ትወልድ የነበረው የአብርሃም ጥሪ ነው የእግዚአብሔርን የዘላለም እቅድ በድንቅ ያፍታታው፡ ሴም ከታወቀው ባሕር የወጣ ሌላ ባሕር ሁኖ በሚዩም ይሚከላል ከራሱ ሌላ የጠራ ምንጭ የወጣው፡ በልበ ሚሉነት ለመገር ከዚያ የተገኘው ምንጭ ነው ከዚያ ወዲህ የታሪክ አንኳሩ - እስራኤል - መዳን ከአይሁድ ነውና!

በሴም በኩል እስከ አብርሃምና እስከ ዘሩ ካልዘለቅን ሴምንና ዘሩን በጅምላ የወሰድነው እንደ ሆነ አደገኛ መንፈሳዊ ቅዠት ወስጥ እንዳከራለን፡፡ ምክንያቱም ከለዳውያን በባቢሎንወያን፣ ፋርሶችና አረቦች... ሴማውያን ናቸውና፡፡ እነዚህና ሌሎች የሴም ነገዶች የደኅንነት ተካፋዮች ይሁኑ እንጂ መዳን የሚኝበት ሰባዊ ቧንቧ ሊሆኑ አልተመረጠም፡ ለዚህ የበቃው ተስፋንና የተስፋን ዘመን የተሰጠው አብርሃም - ይስሐቅ - ያዕቆብ - እስራኤል ብቻ መሆኑን በቃል ኪዳን ተረጋግጧል፡፡

ይሄ ዘመን በተለይ በምድር ላይ ላለ አንድ ወገን የተሰጠ ዘመን ነበረ፡፡ ይሄ የተስፋ (ለአብርሃም ስለ ተሰጠ ነው የተስፋ ዘመን ተብሎ የተሰየመው) ዘመን በአብርሃም፣ በይስሐቅና በያዕቆብ ዘመኑ ብርቱና ወርቃማ የነበረ ቢሆንም እስራኤል በቁጥር በበዛበት ዘመን ደከሞ ታይቷል፡፡ (ዘጸ.1ና2)፡፡ እስራኤል ወደ ግብፅ ሲገባ ምንም ሰባ ነፍስ ቢሆን ቤተሰብ ሆኖ ነው የገባው፡ ይህም እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ ወስጥ ነበረ (ሥራ.7÷6)፡፡ የዘሩና የሕዝቡ ጭቃቀት ከተስፋ ጋር ተቀላቅሏል፡፡ በእግዚአብሔር አደራረግ ይህኛው እጅግ የሚነቅ ነው፡ ቀኙን ለመለጥ ሁል ጊዜ ግራወን ያስቀድሚልና! የምንጽፍበት ዋናው ሐሳብ ይሄም አይደለምን? ዕብራውያኖች በሚጨቁበት ምድር ግን፡- ‹‹አፈሩ፣ እጅግም በዙ፣ ተባዙም፣ እጅግም ጸኑ ምድሪቱም በእነርሱ ተሞላች›› ተባለላቸው (ዘጸ.1÷7)፡፡ በመጽሐፍ፡- ‹‹እግዚአብሔርም ለአብርሃም የሚለት የተስፋው ዘመን ሲቀርብ›› ተብሎ እንደ ተጻፈ በሕዝቡ ዘንድ ሚጎት ሁኖ ነበረ፡፡ በሚበዙበት - በሚበዙበት ምድር ግን ተጨቁ፡፡ ያለ ጭቃቀትና ጨቦት ግን አልነበረም፡ የእግዚአብሔር ተስፋ በጭቃቀት፣ በመከራ፣ በኀዘን፣ በጭቆና... ተፈጸመ፡ ሕፃን በምጥ - በጭቃቅ - በጨቦት... እንደሚወለድ እንዲሁ እስራኤል በጭቃቀት፣ በጭቆናና በጨቦት ተወለደ፡፡ ሕዝብም ሆኖ ከግብፅ ወጣ፡፡

‹‹ከዚያም ከብዙ ቀን በኋላ እንዲህ ሆነ፤ የግብፅ ንጉሥ ሞተ፤ የእስራኤልም ልጆች ከባርነት የተነሣ አለቀሱ፣ ጮኹም፡ ስለባርነታቸው ጨቦታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ፡፡ እግዚአብሔርም የልቅሶአቸወን ድምፅ ሰማ፡ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገወን ቃል ኪዳን አሰበ፡፡ እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አየ፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ያለወን ነገር አወቀ›› (ዘዳ.2÷23-25)፡፡

የአራተኛው ከፍለ ዘመን - ስፍረ ዘመን ሚለቂያው ታሪክ ይሄ ነበረ፡፡ እስራኤል ስለ ዘሚና ስላሚከ እግዚአብሔርም በሚፈልገው ልክና ደረጃ ስለ ነበረ አልነበረም ሌላ ዘመን የተሰጠው ስላለቀሰና ስለ ጮኸ እንጂ፡፡ ይህም ዘመን በድካም እንዳለቀ ምስክራችሁን አብዙ፡፡ ሕዝቡ በሕይወቱ ስለ በረታ ዘመን - አዲስ ዘመን አልተሰጠወም፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር

ሁኖም አያወቅም። እግዚአብሔር ግን አዲስን ዘመን ለማጣት መንገድ ያደረገው የነበረውን ዘመን በሚጨርስና በሚደክም ነው። ዘመናት ሁሉ ከደረሱበት ጫፍ መልሰው አዘቅዝቀው ታድሰዋል። በወጣት ልክ ወድቀው ተፈጥፍጠዋል። ስለዚህም ተለወጠዋል።

እግዚአብሔር አምላክ የነበረውን ዘመን ለመቀየር ሲነሣ፦ - ‹‹... የእስራኤልን ልጆች አየ፤ እግዚአብሔርም በእነርሱ ያለውን ነገር አወቀ›› ነው መጽሐፍ የሚለን። ምንድር ነው በእነርሱ የነበረው? ድካም፣ ሞቆና፣ ጨቨት፣ ተስፋ መቁረጥ... ነበረ። በዚህ ዘመን ወስጥ ሳሉ ነው ሌላና አዲስ ዘመን ወስጥ የተሻገሩት። ተስፋ የተሰጠበት ዘመን በአብርሃም እንደ ጀመረ ያም ዘመን ሲያልቅ በልጆቹ እንደ ቀድሞው አልሆነም። ደግሜ እላለሁ በኃይል የተጠናቀቀ የትኛውም ዘመን አልነበረም የለምም። አንዱ ባለቀበት ነው ሌላው የጀመረው። የመጀመሪያው በሞተበት ሁለተኛው ተነሣ። ሁሉም ዘመን እንዲህ እያለ ነው ወደ ማጠቅለያው የገሠገሠው።

5.የሕግ ዘመን

ከኮሬብ ጀምሮ የተሰጠው የሕሊናም ይሁን የሥርዓት ሕግ ዓላማ ነበረው። ሕግ ከፍጥረቱ ወይም ከባሕርይው እንደ ተሰጠበት ዓላማ የተከነነ አልነበረም። ለሕይወት የተሰጠው ነገር ግን ለሞት ሆኖ ተገኘ (ሮሜ.7÷10)። ሕግ ምኞትን - ኃጢአትን ያነሣሣ ነው። ያለ ልክ ኃጢአተኛ ያደረገ ነው። ሕግ ኃጢአትን በሰው ወስጥ አሟሰለው - አጦዘው። አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሕግን እንዲህ ይመነለዋል፦ - ‹‹አንድ ከመኝ ጋር የተያያዘ ምኳሌና ራእይ አለ። መኙ አቧራ የሞላበትን ከፍል ያያል። በዚህ ሚዛል አንዲት ሴት መጥታ ልታጸዳው ብትሞክር አቧራው ይነሣል - ይቦንናል - ሚስነጠስም ይጀምራል። ሌላዋ መጣችና በከፍሉ ውኃ አርከፈከፈች ጠረገችውም። አቧራው አልተነሣም። በቀላሉ ከፍሉ ጸዳ። ትርጉሙ እንዲህ ነው፦ - ሕግ አቧራን - አፈርን - መሬትን - አዳምን - ኃጢአትን ያነሣዋል - ያቦንነዋል እኛን ከአሮጌው ሰው ማንነት ነፃ አያወጣንም። የመጀመሪያዋ ሴት ምሳሌ ሕግ ነው። የቀጠለችው ግን መንፈስ ቅዱስ - ጸጋው መጣ። ከቃሉ ጋር በውኃ አጽንቶ ቀደሰን።›› የጥቅሱ መጨረሻ።

ሕግ ተሰጥቶ የተሞከረበት ሕዝብ በሕግ ካልጸደቀ ሕግ ማንንም እንደሚያጸድቅ ታወቀ። ያ የተመረጠው ሕዝብ በመላእክት ሥርዓት ሕግን የተቀበለ ቢሆንም የተቀበለው ሕግ ለጽድቅ ሳይሆን ለሞት ሠራበት። ጸጋ - ደኅንነት ይመጣ ዘንድ ሰው በሕግ በኩል ሞተ። ሕጉ የተቀበለውን ሕዝብ ከሌላው በበለጠ ዓለማዊ - ኃጢአተኛ አደረገው። የበለጠ ለእግዚአብሔር መኖር የሚይችልና የሚይጠቅም አደረገው ሕጉ። መጽሐፍ፦ - ‹‹እንደ ባሪያዬ ዕወር ማን ነው?›› ብሎ እንደ ጠየቀ እስራኤል በሕጉ ምክንያት የከፋውን ሕይወት ኖረ። የእግዚአብሔር ፍርድ በተቀበልነው እውነት ልክ ነውና እስራኤል ከአሕዛብ ያለፈውን ተግሣፅ እንደ ድርሻ ወሰደ። ሕጉ እስራኤልን የበለጠ በደለኛ ከሚድረግ ሌላ ለምንም አልጠቀመውም። የሕጉን መንፈሳዊነት ለሟት (ለሚዳት) ጊዜው አልነበረምና እስራኤላውያን ለሕጉ ፍጥረታዊ ትርጉም ሰጥተው አማዘሩበት። ያለ ሕግ የነበረው አሕዛብ የተሻለ ባይሆንም የሕጉ ባለቤቶች ግን በሕጉ የተፈረደባቸው ፍርድ በለጠ። የባለ ሕጉ ሕዝብ ፈጽሞ ወደ ተበላሸበት ደረጃ ላይ የደረሰ ነበረ።

በሕጉ መጨረሻ ብዙ የተዘበራረቀ የሕይወት ተመክሮ ነበረ በእስራኤል ማነበር። ይህንን በነቢያት ምክርነትና በክርስቶስ አገልግሎት ሚረጋገጥ ይቻላል። ሕዝቡ በከንፈሩ እያመሰከ ልቡን ከእግዚአብሔር ያራቀበት ደረጃ ደርሷል። ይህ ወድ ሕዝብ ከሃይሞኖኝነትና ሥርዓትን በወጉ ከመኮግበር ውጭ የእግዚአብሔር ሕይወት ሽታ ርቆት በከንቱነት ለብዙ ዓመታት (በሕጉ ዘመን ሁሉ) ኖሯል። አንደኛው ዘመን ሌላኛውን በሚስገርም ሁኔታ ያስረጀው እንጂ ራሱ የደከመባትና ያረጀበት ሁኔታ ሲታይ እጅግ ዘግናኝ ነው። ዘመን ሕግ (Dispensations of Law)የተሰፋውን ዘመን ያስረጅ እንጂ ራሱ የደከመባትና ያረጀበት ደረጃ ሲመረመር የበለጠና የጠለቀ ነው በብልሹነት።

ሕጉ ሰውን ሁሉ ወደዚህ ጨቨት ያመጣው አልነበረምን፦ - ‹‹... እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?...›› (ሮሜ.7÷24)። ታድያ የእግዚአብሔር ሕዝብ የነበረው እስራኤል መንፈሳዊ ሕይወቱ እስከ መጨረሻ በተበላሸበት ወቅት ነበር ክርስቶስ የመጣው (የተገለጠው)። ሕግ የተሰጠው ለሕይወት ነበር። ዳሩ ግን ከክርስቶስ (ከሕይወት) ወጭ ስለ ተቀበልነው ለሞት ሠራብን። ሕግ መንፈሳዊ ሆኖ ሳለ ሥጋዊ አደረግነው - ወደ ታች አወረድነው። ሥጋዊ ትርጉምና ሥርዓት ሰጠነው... እስራኤላውያን መንፈሳዊ ሕግ ተሰጣቸው። በሥጋ ተረጎሙት። የሚጠቀስ አንቀጽ (Codified) አደረጉት። ኃይሉን ካዱት። በአሮጌው ሰው ሕግን መጨረም ወይም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ከቶ እንደሚቻል ሳያወቁ ተፍጨርጭረው ወደቁ። በሕግ ኃጢአት ኃጢአተኛ ሆነ። ከነበረበትና ካደባበት ተገለጠ። ኃጢአት በሕግ ቦነነ። ሁሉንም አስነጠሰ!

‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታወቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና›› (ዘፍ.2÷16-17)። በዚህ ክፍል ከክፉ ጋር

የአንድን ወገን መልካምነት አያለሁ (ይሄ እወቀቴ ግን ሁለትነት ነው - ከሰው ያገኘሁት፡፡) ያየሁት መልካም ነገር ግን በሌላ ጎን ያየሁትን ክፋትን እንዳስወግድ ወይም መልካምን እንድፈጽም ጉልበት አይሆነኝም፡፡ ሕግ እንዲህ ነው፡፡ እንዳላደርግ ይነግረኛል፡፡ ላለማድረግ ግን ኃይል አይሆነኝም፡፡ ወይም እንዳደርግ ይነግረኛል ለማድረግ ግን አቅም አይሆነኝም፡፡ የተሰጠኝ የሕግ ዘመን እንዲህ እንዲያልቅ ተወስኗል፡፡

ሕግና ሰው ተጋብቶ የኃጢአትን ፍሬ አፈራ (ሮሜ.7÷5)፡፡ ሕግ በደለኛ ያደርግሃል እንጂ ከበደልህ ታመልጥ ዘንድ ወይም በደልን ታሸንፍ ዘንድ ኃይል የለውም፡፡ ስለዚህ አቅም አይሆንህም፡፡ ሕግ በሰው የነበረውን የጨለማ ማንነት ሊገልጥ ከሚጨምሩ አልፎ ሰውን የበለጠ የከፋ ያደርገዋል፡፡ ሰው እስከ ሚጨረሻ እንዲከፋ ሕግ ተጨምረ፡፡ የሰው አወዳነት የተገለጠው በሕግ ነው፡፡ ኃጢአት በሕግ እንዲታወቅ የእግዚአብሔር ጽድቅም ያለ ሕግ ተገለጠ፡፡ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- ‹‹አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፣ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለ ሚጸደቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና›› (ሮሜ.3÷19-20)፡፡

የኃጢአትን ሰውነት የገለጠና ሰውም ተስፋ ወደማቈርጥበት ደረጃ የመጣው በሕግ ነው፡፡ ሕግ ኃጢአትን አጋለጠው፡፡ ከተደበቀበትና ካደባበት በሰውነት ይገለጥ ዘንድ አስነሣው፡፡ እግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ እንደሆነ እንዲሁ የዓመፅ ምሥጢር በሥጋ መገለጡ ነው፡፡ ኃጢአት ዓመፅ ነው በሥጋ ይገለጥም ዘንድ ሕግ ተሰጠ፡፡ በሕግ የሚኖር ማንኛውም ሰው ‹‹ጽድቅ ሚለት ከፉውን እየተዉ መልካምን ሚድረግ ነው፡፡›› ከሚል ትምህርትና መደምደሚያ ያለፈ አይደለም፡፡ ከዚህ ሁሉ ጋር ሰው ለሕግ የሚሞተው በዚያው በሕግ በኩል መሆኑ ያስደንቃል፡፡ ሕግ የሚኖረው ሰው እስካለ ነው፡፡ ‹‹ሕግ የለም›› የሚሉትም በእነርሱ ዘንድ ሰው እንደ ሌለ ያረጋግጡ፡፡ የትኛው ሰው? አሮጌው ሰው፡፡

የሕጉ ዘመን ያለቀው ሙሉ በሙሉ በሚቀሉ ነው፡፡ በእኛም የሕጉ ዘመን ሚለቁ እርግጠኛ የሚሆነውና አካል የሚያገኘው ዕለት ዕለት ስንሞት ይሆናል፡፡ በክርስቶስ በመፈስ የተሠራው ሁሉ በእኛ አካል ሞክኘት - ሥጋ መሆን አለበት፡፡ ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ዘልቀዋል (ሉቃ.16÷16-17)፡፡ በመፈስ አሠራር ሕጉ በሚቀሉ በተሠራው ሥራ ቢያከትምም በፍጥረታዊ ሁኔታ የተወገደው ግን በ70 ዓ.ም ነበር፡፡ አይሁዳዊ የሃይማኖት ሥርዓት (ጁዲዝም) ለሚጨሻ ጊዜ በሮማውያን ወታደሮች ተጠረገ፡፡ መቅደሱም ፈረሰ፡፡ በሚቀሉ አንድ ነገር ተወገደ - ተገደለ፡፡ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፡- ‹‹የሚቃወመንንም በትእዛዝ የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በሚቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል›› (ቆላ.2÷14)፡፡

በሕጉ ሌሊት ክርስቶስ ሞተ፡፡ አስቀድሞም የክርስቶስ መንፈስ በትንቢት መጽሐፍ ጉባኤ ሁሉ ስለሚያርደው በግ ሲናገር፡- ‹‹ሲመሸ ይረደው›› ይላልና፡፡ የጸጋው ዘመን ይነጋ ዘንድ በሕጉ ምሽት በጉ ታረደ፡፡ የክርስቶስ ሞት ያንን ዘመን ሻረው፡፡ ወደ ኋላ አስቀረው፡፡ አዲስ ጊዜ ጀመረ፡፡ ፀሐይ ወጣች፡፡ የእግዚአብሔር አዲስ ጅማሬ ቀጠለ፡፡

የሕጉ ዘመን ፈጽሞ በደከማቸትና የባለ ሕጉ ሕዝቦች ለጽድቁና እግዚአብሔርን ለመምሰል ፈጽመው አቅም ባጠፉት ጊዜ ነበር ስድስተኛውና የጸጋው ዘመን በክርስቶስ የተገለጠው፡፡ የሕጉ ባላደራዎች - በሕጉ ጉልበት ወደ ጸጋው ዘመን የተሻገሩ ሳይሆን ሕጉ (ዘሙ) አድከሟቸውና ገድሏቸው እንደ ሆነ እናውቃለን፡፡ የአንድ አዲስ ዘመን ጅማሬ የነበረው ዘመን ሚለቅ ነው፡፡ የትኛውም አዲስ ቀን የሌሊት ውጤት ነውና! መጽሐፍ፡- ‹‹...ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ›› ይል የለምን? በእርግጥም አዲስ ጅማሬ ነው፡፡ አዲሱ ትውልድ ያረጀው ትውልድ ሚለዳ ሁኖ ተተክቷል፡፡ የነበረው ሲያልቅ አዲስ ይጀምራል፡፡ የእያንዳንዱ ዘመን ወርቃማ ጊዜ በጨለማ፣ በድካም፣ ተስፋ በመቁረጥ... እየደበሰና እየጨመ ተለውጧል፡፡ ያለንበት የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከዚህ የተለየ ሌላ ዕድል ይኖረዋል ትላላችሁ? የቤተ ክርስቲያንም የሥርዓት፣ የትምህርትና የአካሄድ ጀንበር እየጠለቀ መሆኑን እባካችሁን በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ የድካምና የሚለቅ ምክክርነት እዩ፡፡ እርግጥ ነው ዘመነ ‹‹ኤክሌዝያ›› - ስድስተኛውና የጸጋው ዘመን የሕግንና የነቢያትን ዘመን አስረጅቶ ሲሸር በሙሉ ኃይሉ፣ ጉብዝናውና ወርቃማ ዘመኑ ነበር፡፡ አሁን ግን እርሱንም አገኘው፡፡ ከእንግዲህ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ተሰፍሮና ተሰጥቶ የነበረው መንፈስ፣ ጸጋና እውነት፣ ሕይወትና ክብር... መላት ሊያገኘው ተከፍተው ነበርና አሁን ሁሉም ይለወጣሉ፡፡

6.የጸጋ ዘመን

የጸጋ ዘመን ሲባል ጸጋ በግልጽ መሥራት የጀመረበትን ጊዜ ለማለየት ይመስላል፡፡ በዚህ ሕይወት ዘመኑን ‹‹የቤተ ክርስቲያን ዘመን›› ማለቱ ተስማሚ ያደርገዋል፡፡ በእርግጥ ‹‹የጸጋ ዘመን›› ቢባል እንኳ ‹‹በጸጋ ላይ ጸጋ›› መሆኑ አይቀርምና የመጀመሪያው ወደ መላት ይገባል፡፡

የዘሙን ጅማሬ እንዲህ እናየዋለን፡- ‹‹ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና፡- ዘሙ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም አምኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ›› (ማር.1÷14)፡፡ ከዮሐንስ በኋላ በመንፈስ አዲስ ጅማሬ ተጀመረ፡፡ በተፈጸመ ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ተነገረ፡፡ በዘመን ፍጻሜ የተገለጠው (ዕብ.1÷1-2) አዲስ ነገር ጀምሮ ነበር፡፡ በዚህ ‹‹የጸጋ ዘመን - Dispensations of Grace›› በተባው ክፍለ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ጉልህ ድርሻ ይኑራት እንጂ የክርስቶስ ስብከት ቤተ ክርስቲያን ላይ ሳይሆን መንግሥቱ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ዋናው ግብ አሁን በዓለም ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን መንግሥቱ ነበር፡፡ በእርሱም አካሉን የሚሥሩትን በእነትና በመንፈስ የተወለዱትን ልጆቹን ማኅበሰብ ነው፡ ይህንንም (መንግሥቱን) በሁሉም ፍጥረት ላይ ለማሳካት በጸጋው ዘመን ጠሪወና መራጩ ለስሙ የሚሆንን ወገን - በኩራቱን ወስዷል (ሥራ.15÷14)፡፡

ስድስተኛው ዘመን በእርግጥ ወደ ሰባተኛው ሻቫጋገሪያ ነበርና ፍጻሜውን ስናይ ከሌሎች ዘመናት በባሰ መድከመን እናስተውላለን፡፡ ስድስት የሰው ቁጥር ነው፡ ሰው ሚለቅ አለበት፡፡ ሰው ሲያልቅ ግን በሚሉ ሰውነቱ ተገልጦ ነው፡ ሰው(ነት) ወደ ጥፋቱ ጣራ መውጣት ተገብቶታል፡፡ በባሕር (በሰው ሁሉ) ያለው አውሬ - ከባሕር (ከሕዝብ) የሚወጣው አውሬ የአውሬነቱ መላት (Climax) መድረስ ያለበት በዚህ ስድስተኛው ዘመን መዘግያ ነው፡ የአውሬው መቀመጫ መጋለቢያ ባቢሎን ናት፡፡ ባቢሎንም ስለ እርሱ ፍጹም ባቢሎን መሆን አለባት፡፡ የዓመፅ ሰው መቅደሱን የሚሞላበት ዘመን (2ተሰ.2÷4) ይሄ የስድስተኛው ዘመን ሚለቂያ ነው፡ ብዙዎች አሟሾች፣ የቤተክርስቲን አስተማሪዎች... አውሬወን ከእነርሱ ወጭ ይጡበቁታል፡፡ ከፍጥረታዊ ባሕር ፍጥረታዊ አውሬ የሚጡበቁ መንፈሳዊ ዕወሮች አሉ፡፡ እያንዳንዱ በእርሱ ያለወን አውሬ ሊገድል ይሄ ሚልእክት መጥቶለታል፡፡ አውሬው ዕለት ዕለት በመሞት ከራሳችሁ አስወግዱት፡፡ ከአሮጌው ባሕሪያችሁ፣ ከኃጢኣት ሰውነታችሁ ሌላ አውሬ የትም የለም፡ የእናንተን አውሬ በክርስትናና በሃይማኖት ስም እየቀለባችሁና እያሰባችሁ ከመካከለኛው ምሥራቅ ሌላ አውሬ ትጡበቃላችሁ? ይሄ የአስተማሪዎቻችሁ ትፋት ነው፡ ተጸየፉት፡፡ በክርስቶስም ጥበብ ፍሪዳችሁን (Your beast) እረዱ ምላ.9÷2 K..J.V፡፡

ቤተ ክርስቲያን በትምህርት መዳራት ከክርስቶስ ትምህርት ከወደቀችበት ከጨለማው ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ብዙ እንግዳ ትምህርቶች አሏት፡፡ ከእነዚህም አንዱ የአውሬው ትምህርቷ ነው (ስለ አውሬው የበለጠ ማወቅ ከፈለጋችሁ ‹‹አውሬው ማን ነው?›› በሚል የተዘጋጁ ካሴቶች ስላሉን ጠይቁን)፡፡ ወደዚህ ሐሳብ በጥልቀት ሳንገባ ሰውነት - አውሬነት ባለንበት ዘመን እየተፈጸመ መሆኑን ማጆት ለአሁን በቂ ነው፡

ሰው በዚህ ስድስተኛው ዘመን (በጸጋው ዘመን) መመላትና ሜጸም እንዳለት ተወስኗል፡፡ ‹‹ኃጢኣተኛ ወደ ፊት ኃጢኣትን ያድርግ፤ ዓመፀኛም ወደ ፊት ያምፅ›› ተብሎላታል ስለ ሰው፡ ይሄ ሁሉ የሚያልቀውና የሚሟላው ግን በሃይማኖት፣ በቸርች ሲስተም፣ በሥርዓት፣ በአገልግሎት፣ በወግ... ተከልሎ መሆኑ ይዘገንናል፡፡ ከሕደቱ ከወጭ ሳይሆን ከወስጥ ነው፡ ከሐዲው አምኖ የነበረ ነው፡ ሳያምን (ሳያወቅ) ማን ይክዳል? የሞኘውቀውን አናወቀውም፡ ዓመፀኛው በመቅድ እንጂ ከመቅደስ ወጭ አይደለም፡ ስለዚህ ዋናው ወንጀለኛ (ዋናው ነው ያልኩት) የሚሸሽገው በሃይማኖትና በቤተ ክርስቲያን አሮጌና ደካማ አሠራር እንጂ በፖለቲካ ጉያ አለመሆኑ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ ነገሥት ከዝመቷ ወይን ጠጅ ጠጥተው ሰከሩ፡፡ ጠጁን የጣለችው ግን ባል አልባዋ ባቢሎን ናት፡፡

ሰው(ነት) በቤተክርስቲያን አሠራር መላቱን እያገኘ ነው፡ የኃጢኣት ሰውነት መንፈሳዊ በሚሳሉ አምልኮዎች፣ ፕሮግራሞችና ሥጋዊ ሥነ ሥርዓቶች ለመላለጡ ወደ ብቃቱ እየመጣ ነው፡ ሰው በሰውነት - በሥጋዊነት - በአውሬነት መላት፣ ብቃትና ፍጽምና የሚለጠው በዚህ ስድስተኛው ዘመን ማበቂያ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሰው ተጨቁናለች፡፡ ደክማለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሰው ሰፈር (Realm) እስከትሆን ወድቃለች፡፡ እግዚአብሔር ከሰጣት ልክ ወርዳለች፡፡ ሙሉ በሙሉ ከመንፈሳዊነት ወጥታ በሯን ከኋላዋ ዘግታለች፡፡ ሰው በሃይማኖት ሰብቷል፡፡ አውሬው ደንድኗል፡፡ የቤተክርስቲያን አገልግሎትና መንፈስ የጎደላቸው ሥነ ሥርዓቶች የአውሬው - የሰው በዓላት (Festivals) እየሆኑ ናቸው፡ ማንም እግዚአብሔር በተወው ሥርዓትና አገልግሎት እስከ ሜጨረሻ ቢጠፉ እንጂ ተስፋ የለወም፡ መጥፋቱም መገኘቱ ነው - ከብር ለእግዚአብሔር ይሁን! ማንም ይሁን አሁን ባለበት ሁኔታ፣ ባለው መረዳት፣ በተቀበለው ትምህርት፣ በሚጡበቀው መንገድ... አሁን ካለበት ተነሥቶ ሪቫይቫል ይሆንልኛል አይበል ራሱንም አያታልል፡፡ አሁን አለኝ የሚለው ሁሉ ለሞቱና ለቀብሩ ቢሆነው ነው - ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መላትና መለጥ ሊነሣ፡፡

ከበዓለ ኀምሳው (ሥራ.2÷1) በዓል ዕለት በመጀመር ቤተ ክርስቲያን ጉልበቷን እያሳየች በዚያ ሚለዳዋ የተጓዘችወን ተጉዛለች በእርግጥ፡፡ እነ ወንድም ጳወሎስ የመሳሰሉ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አዕምሮች እስከ ተነሠላት ቀትሯ ድረስ ለዘሙ በተሰጠው ኃይለኛ መንፈስ እንደሚባ ተራምዳለች፡፡ ዳሩ ግን አብዛኞቹ ደቀ መዛሙሮትና ሐዋርያት ሰማዕታት ሁነው ካለፉ በኋላ የቤተክርስቲያን ፀሐይ (ቀትር) ከግለቱ በመቅዝቀዝ የእርሷም ጀንበር ሊጠልቅ አዘቀዘቀ፡፡ ሽማግሌው ዮሐንስ በኋለኛው ዘመን

ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናትና ያሉበትን ሁኔታ በመንፈስ ሲያይ መጽሐፉን የጻፈው በቤተ ክርስቲያን ፀሐይ ሚለት ሳይሆን በጀንበሯ ብርሃን ነበር፡፡

እነዚያ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት እግዚአብሔር እንደ ናማ የወሰዳቸው እንጂ እነርሱ በነበሩበት ዘመን በሌላ ቦታ አብያተ ክርስቲያናት ያልነበሩና ብቸኛ የደከሙ ሁነው አይደለም፡፡ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ሰባት ክፍለ ዘመናት ናቸው፤ ወገኖች ሆይ፥ በዚህስ ልብ በሉ፡፡ በኤፌሶን የጀመረው ዘመን በሎዶቅያ አለቀ፡፡ በኤፌሶን የነጋው ዘመን በሎዶቅያ ሸኘ፡፡ የቤተ ክርስቲያንን መጀመሪያ - ኤፌሶንንና መጨረሻዋን ሎዶቅያን በሚስተዋል ትመላከቱ ዘንድ ይሁን፡፡ በኤፌሶን የደመቀው የኤፌሶን ዘመን ሰሚይ በሎዶቅያ ዘመን ጭጋግ አጠመቀው፡፡ ዛሬ የብዙዎች ሰሚይ ወኃ በሌለባቸው ደመናዎች ተሸፍኖ ሞቱ የሎዶቅያነት ምሳሌ ሚጸም ነው፡፡ ኤፌሶን ሚልካም ጅማ ነበረ፡፡ የዚህ ሚልካም ጅማሬ ሚለቂያ ሎዶቅያነት መደረጉ ያለ እግዚአብሔር ቅድመ እወቀትና ወሳኔ አለመሆኑን ማመቅ እንዴት አስደሳች ነው? የቤተ ክርስቲያን ቀን ለመንግሥቱ ቀን ይነሣ ዘንድ የግድ መሞሸት አለበት፡፡ ከኤፌሶን የተነሣችው - በኤፌሶን የጀመረችው ቤተ ክርስቲያን ዙረቷን ጨርሳ በሎዶቅያ ታጠቃልላለች፡፡ በኤፌሶን (ኤፌሶን ሚለት የተወደደ ሚለት ነው) የተነሣው ምንጭ በሎዶቅያ አሸዋ - አፈር ሰረገ፡፡ ይሄ የቤተ ክርስቲያን ጅማሬና አካሄድ ፍጻሜ ነውና ማንም አይዘን፡፡ ራሱንም አይኮንን፡፡ በኤፌሶን ንጋት ዙረቱን የጀመረው የሰዓት እጅ በሎዶቅያ ቆመ፡ የቤተ ክርስቲያ ሰዓት አቆጣጠር ሲያበቃ የመንግሥቱ ቀን ይጀምራል፡፡ ቤተ ክርስቲያን - ስድስተኛው ዘመን የሚቆም ሰዓት ነው የተሰጣት (የተሰጠው)፡፡ ብዙዎች በዚህ ዘመን ወደ ቤተ ክርስቲያ መጀመሪያ ሊመላሱ ‹‹ራእይ›› እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ ይሄ ግን ራእይ ሳይሆን ባሉበት ሌሊት ሁነው ከረሃባቸው የሚልመት የሰዋት ሕልም ነው፡፡ እነዚህ ያለፈው ዘመን ጎታቾች ምን ዓይነት ነገር ሆነላቸው?! ከእንግዲህ የኤፌሶን ሐዋርያነትና ነቢይነት... የሉም፡ አሁን ሎዶቅያነት ነው፡ ቀጥሎ መንግሥቱ ነው፡ በመንግሥቱም ልጅነትና አባትነት እንጂ ሐዋርያነት፣ ነቢይነት፣ መጋቢነት፣ ወንጌላዊነት፣ አገልጋይነት... በአንድነት የሉም፡ ስለዚህ ወደ ኋላ መሄዳችሁ ምን ልታመጡ ነው? እግዚአብሔር ወደ ኋላ አይሄድምና ተመለሱ፡፡ የእናንተ የዛሬ ሐዋርያት፣ ነቢይነት፣ መጋቢነተ... የደከመ ነው፡ ልብ የሚጣልበት፣ የሚፈራ፣ የሚከበር፣ በሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚመጣ... ሚዛለያና ማጉረፊያ ነው፡

በዚህ በስድስተኛው ዘመን ሁሉ የሰባቱም አብያተ ክርስቲያናት ባህሪይና ማንነት በሁሉም ጉልህ ተንጸባርቆ ታይቷል፡፡ ዛሬም ኤፌሶንነት፣ ሰርምኔስነት፣ ጴርጋሞንነት፣ ትያጥሮንነት፣ ሰርዴስነት፣ ፊልድልፊያነት፣ ሎዶቅያነት በከፊል ወይም በመላት የሌለበት የለም፡ ይሁን እንጂ በዚህ በስድስተኛው ዘመን መዘጊያ የማንም ሚጨሻ የመጀመሪያይቱ (ኤፌሶን) ቤተ ክርስቲየን ወይም ስድስተኛይቱ (ፊልድልፊያ) ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ሎዶቅያ ሚሆኗን ሁሉም በራሱ ሕይወት ይሚልከት፡፡ በየትኛውም አጥቢያና ዲኖሜሽን የሚኝ አው በዚህ ዘመን የሎዶቅያነት መንፈስ ተጠናወቶታል፡፡ ‹‹አንድ በአንዱ ሲስቅ...›› እየሆነ እንጂ ሁሉም በአንድ ዓይነት የሕይወት ቅኝት ላይ ተገኝቷል - ለብ ብሏል፡፡ ግን ግን በየስፍራው ስላሉ ጥቂት ድል ነሺዎችና ቅሬታዎች እግዚአብሔር አባታችን ይከበር፡፡ ከሎዶቅያ ጋር አልደከመም፡ እነዚህም ዘማ ኤፌሶንን ወይም ፊልድልፍያን ለማሞጣት ወደ ኋላቸው የሚዩ ሳይሆኑ የመንግሥቱን ቀን ከራሳቸው ወስጥ (ምክንያቱም መንግሥቱ ከወስጥ ነውና - ሉቃ.17÷20-21) በመጀመር በሁሉ ላይ ሊያዩት ይዘረጋሉ፡፡

እውነት እላችኋሉሁ፤ የአብያተ ክርስቲያናትና የሚስትሪዎች ጉዳይ በዚህ ዘመን ‹‹የዝንጀሮ ቆንጆ የለወም›› ዓይነት ነገር ሁኗል፡፡ ሁሉም መንፈሳዊ ሚልካቸው ጠፍቷል፡፡ መጽሐፍ ስለ እነርሱ ከሚለው ወድቀዋል፡፡ ብልሃተኛው እግዚአብሔር ወበታቸወን ገፈፈ፡፡ የትኛውም ከየትኛው አይሚጥም፡ ሁሉም በአንድነት ተበላሽተዋል፡፡ አንዳንዶች በራሳቸው ምክንያት አጥቢያ ሲቀይሩ ወይም ሲከፍቱ አያፍሩም፡ የተወትን ሚልክ እዚያው ያገኙታልና! ሀላችን በዚህ ወስጥ አለን - እሰየሁ! ለምን? ታገሡኝ እነግራችኋለሁ፡

በሁሉም ዘንድ መንፈሳዊው ነገር ጨልሞበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ብዙ ነገር አያሳርፍም፡ የሚደረገው ሁሉ ነገር ከተትረፈረፈው ሕይወት ሳይሆን ሃይሞታዊ ግዴታን ከመወጣት ነው፡ ... ይሄም ቢሆን ከእግዚአብሔር ነው፡ ለምን? ሊነጋ ነው፡ የጌታ ቀን - የመንግሥቱ ዛሬ ሊገለጥ ነው፡ በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ያለው ጎበዝ ግን አለመድከመን ቢከራከርና ሊያምን ባይፈልግ ግን አይባልም፡ ከሕይወቱና ከአገልግሎቱ ምስክርነት ወድያ ምን ይፈለግበታል? ጎበዙም የተቆረጠወን የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ሊቀጥል ቢሻ እና ‹‹በበረታ›› ከሥጋ ነው - ከአጋንንት፡፡ ቢሆንለት የመንግሥቱን ዘመን ሊያዘገይ ይሳካለታልን?

እያንዳንዱ በሌሊት አገልግሎቱ አለ፡፡ ስብሰባወ፣ ፕሮግራመ፣ ሪቫይቫሉ፣ ከሩሴዱ፣ ሴሚናሩ፣ ትምህርቱ፣ ዝማጅቱ፣ አምልኮው... በእኩለ ሌሊታቸው ናቸው፡ ከአሥሩ ቆነጃጅት ያልተኛ አለን?... መቸራወስ የመጣው በሁሉም እኩል ሌሊት አይደለምን? ማን ነው ታድያ ከእነዚህ ተለይቶ ቀን ያለው? ቢኖር ይህንን በራሱ ይቁጠረው፡ አብዛኛው እየባነነ ነው፡ ግማሹ እያለመ ነው፡ ገማሹ እየቃዠ ነው፡ የቀረው ከባድ እንቅልፍ ወስጥ ነው፡ አያሌው ተጫጭኖታል፡፡ የሚበዙትም ባሉበት መንፈሳዊ እንቅልፍና አልጋቸው ሁነው ሲገላበጡ እንቅስቃሴ (ሪቫይቫል) ይመስላቸዋል፡፡ በእርግጥ ዛሬ ‹‹ነፍሳት›› አይድኑም? አላልኩም፡ ፈወስ የለም? እርሱንም አላልኩም፡ ልሣንና ‹‹ስጦታዎች›› የሉም? የሚልእከቱ ጉዳይ ከእነዚህ ጋር

አይደለም፡፡ እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንጂ የአገልጋዩ - ‹‹የባለ ቅባቱ›› አይደሉም፡፡ አገልጋዩ ግን ከሚሠራው መንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት ነው? ነው ጥያቄው፡፡ ከሴት ጋር ተኝቶ ሳለ ስለ ሠራው የሶምሶን የቃል ኪዳን ጠቦር አይደለም ጉዳዩ ያንን ጠቦር ስለ ተሸከመው ሶምሶምና የሕይወቱ አካሄድ የዘሙም መኳፍንነት እንጂ፡፡ መቼ ዓለቱን ሁለት ጊዜ በበትሩ መትቶ ውኃ ማመንጨቱ ሳይሆን ችግሩ የተነገረውን አለመፈጸም ነበረ፡፡ ዓለቱን ‹‹ተናገረው›› እንጂ ‹‹ምታው›› አልተባለም፡፡ እግዚአብሔር በተወው ነገር ስለ ስሙ መሥራቱ መቼን አያጸድቀውም አሰናከለው እንጂ፡፡ ዛሬም የምትመክበት ስጦታችሁ፣ ልሣናችሁ፣ አገልግሎታችሁ... እንደ ሶምሶን እንደ መቼ በትር ቢያደርግ ራሳችሁንና ዘመናችሁን ግን እዩ፡፡

አሁን ያለችው ቤተ ክርስቲያ አልቆላታል፡፡ ዘሚኒ ተፈጸመ፡ ከእንግዲህ መኝታዋን ትግለጥ፡፡ ከማንኮራፋቷ ትውጣ፡፡ ከሌሊቱ ግርማ ታምልጥ፡፡... የንጋትም ኮከብ ብርሃኑን ይስጥ፡፡ የመነግሥቱ ሚለዳ የቀኑ ጠዋት በዚህ ዘመን ላይ ይውጣ፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በዘሚኒ ሚለቂያ የለበሰችውን የሌሊት ልብስ ታወልቅ፡፡ ለመነግሥቱ ቀን ትነሣ፡፡ የፍጥረትም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ልጆች ክብር ነፃነት ያርግ፡፡ አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያልቃል፡፡ ዘመናቸውም እንዲህ ይፈጸሚል፡፡

በኤፌሶን (በመጀመሪያ ዘመን) ላይ ሲመሻ በዚያው ዘመን የነበሩ ቅሬታዎች ወይም ድል ነሺዎች ሁለተኛውን ዘመን ያነጉት ዘንድ በርትተው ታይተዋል፡፡ ይህም ነገር በየዘመናቱ ሁኖ ተስተውሏል፡፡ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን በሆነባት እኩለ ሌሊት የሌሊቱን ርዝመት የሚገሩ ጉበኞች - ፈጽመው የማይተኙ አሉ፡፡ ሁለተኛው የመጀመሪያው ፈጽሞ ሚለቅ እንደሆነ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ ሦስተኛውም እንዲሁ የሁለተኛው እንደ ሆነ፡፡ እያለ እስከ ሰባት መድረስ ይገባዋል፡፡ የመጀመሪያው ዘመን ድል ነሺዎች የሁለተኛው ዘመን ጀማሪ ይሁኑ እንጂ እነርሱም ከሁለተኛው የተገኙ የሦስተኛው ጀማሪዎች ያደከሟቸዋል - ያስረጇቸዋል፡፡ የሁለተኛውን የአንደኛው ድል ነሺዎች ቢቀጥሉትም እነርሱም በተራቸው ሦስተኛውን በጠቀሱት አልቀዋል ተለወጠዋልም፡፡

እንዲህ እየተራመደ ነው ሁሉም ነገር ዛሬ እስካለንበት ሰባተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ላይ የደረሰው፡ ከእርስዋ መካከል የተገኙትና ሌላ ዘመን የተሰጣቸው ድል ነሺዎችም ሰባተኛይቱም (ያሉበትን) ጨርሰው ስምንተኛውን ይቀጥላሉ፡፡ ከሎዶቅያ ወይም ከአብያተ ክርስቲያናት (ከራእ.2 እና 3)በኋላ ምዕራፍ አራትን ስንመለከት በእርግጥ ስንምንተኛው ነገር ይመጣል፡፡ በስምንተኛው በእርግጥ (ምዕ.4)ዙፋንና ዙፋኖች ናቸው፡ በጉ ነው፡ መንፈሳት ነው፡ ሃያ አራት ሽማግሌዎች ናቸው፡ ሰባቱ ዓይኖችና አራቱ እንስሳት ናቸው፡ ይሄ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ሰፈር የወጣ ሌላ ሰፈር (Realm) ነው፡ ሁሉም በዚህ ይገኝ ዘንድ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ደከመ - አረጀ - ተሻረ፡፡

ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት - ሰባት ከፍለ ዘመናት

እነዚህ የተከፋፈሉ ዘመናት ‹‹በጸጋው ዘመን›› - ለቤተ ክርስቲያን በተሰጠው ዘመን ይጠቃለላሉ ይተረጎማሉም፡፡ አንዳንዶች የቤተ ክርስቲያንን ጅማሬ ሚቆስ ምዕራፍ ሦስት ቁጥር አሥራ ሦስትን ሲያደርጉ ሌሎች ግን ሥራ.21÷1ን ያጣቅሳሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ቤተ ክርስቲያን ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ውጣ ወረዶችን አልፋለች፡፡ በድካና በብርታ እስከዚህ ደርሳለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽማ ወይም ብቁ ሆነ በምድር ላይ አልተመሠረተችም፡፡ ወደ ፍጽምና ግን የምታድግ ናት፡፡ የሆነ ሆኖ እስካሁን ባሳለፈችው ጊዜ ቤተክርስቲያን ለፍጻሜ መቅረቧን ሳይሆን የምናየው ከጀመረችበት እንኳ ወድቃ ነው፡ ይሄም ዓላማ ነበረው፡ ቤተ ክርስቲያን ፍጽምና መላት ወደ ሆነው ወደ መንግሥቱ የምትገባው በርትታና የሚለማባት ነገር ሁሉ ተገኝቶበት ሳይሆን ከዚህ በፊት ካሉት ዘመናት ሁሉ ደካማ ሁና እንደሆነ የመጽሐፍም የታሪክም ሚዘገጃ አለን፤ አሁን ካለንበት የሕይወትና የአገልግሎ ድካም በተጨማሪ፡፡ እንግዲህ እንቁጠር፡ -

1.ዘመነ ኤፌሶን

ይህች ቤተ ክርስቲያን መሠረቷ በጳውሎስ ተጣለ፡፡ ከጅማሬዋም መሥራችዋ በአንድ ነገር ይበልጥ እንድትጠነቀቅ በብርቱ አስተነቀቃት፡፡ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡ - ‹‹ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የሚራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠምማ ነገርን የሚገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ›› (ሥራ.20÷29-30)፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን የኤፌሶንን መልእክት (የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች) ስናነብ እጅግ የጠለቀ መረዳትን እናገኛለን፡፡ ወንድሞቻን ጳውሎ ከጻፋቸው መልእክቶች ሁሉ የኤፌሶን መልእክት የበለጠ ጥልቀት ያለው ለመሆኑ ማስረጃው ብዙ ነው፡ አጠቃላዩና የተገለጠው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሞረሐ ግብርና ዓላማ በኤፌሶን መልእክት እናገኘዋለን፡፡ በእርግጥም የዚህች ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ የሚያስደንቅ እጅግም የሚበርከ ነበረ፡፡ መንፈስ የገለጠው ግን በኤፌሶን አካል መያዝ - ሥጋ መልበስ አልቻለም፡ ይሄ ደግሞ ሁሉም የሚፈተንበት አይደለምን? ኤፌሶን የኋላ የኋላ የመጀመሪያ ፍቅሯን ጣለች፡፡

የኤፌሶን ሚልእክት አንብበን እንደምንሚበት ግን በራእይ ምዕራፍ ሁለት የተጠቀሰችው ኤፌሶን ሚልእክቷን ሳትመጥን ቀርታ ወይም ከሚልእክቱ ልከና መመረጿን ስናነብ ላለንበት ዘመን ምን ያህል እንደተሚገንበት አላወቅም። በቃ፣ ይሄ የቤተ ክርስቲያን የእያንዳንዱም ብልት ዕድል ፈንታው ነው። በመወደቅ የሚገኘው መሳሣት - በድካም የሚገኘው ታላቅ ነውና። ይሄ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር አሠራር እንደ ተወሰነልኝም ማጠን እንጂ ‹‹ስለ ምነሳ ልወደቅ›› ብየየ ከወድቀት ጋር ‹‹ስለ ምበረታ ልድከም›› ብዬ ከድካም ጋር አልደራደርም። እስካሁን ባየነው ማንም በጀመረበት ካልፈጸመ ቤተ ክርስቲያንም በጀሚችበት ልትፈጽም ዕድሉ የላትም። እንዲህም አልተጻፈም። የተጀመረበት ብርታት፣ ኃይል፣ ሪቫይቫል፣ ጉብዝና... የማንም መጨረሻ ሁኖ አልታየም። ከዚህ መሚር ትችሉ እንደ ሆነ ዛሬ ስለ መድከማቸሁ ማንም አይፍረድባችሁ ራሳችሁንም አትኮንኑ። ቢሆንለት ማንም በድካሙ - በሌሊቱ - በእንቅልፉ - በማኮራፋቱ... የሚጣወዓ የመነግሥቱን ጠዋትና ቀን ያስተወል እንጂ በዘሙ ድካም ምክንያት ሊሆን የሚይችለወዓ ሊሆን አይመኝ። በዚህ ደግሞ የባሰ ይደከሚልና!

ኤፌሶን ከጀመረችበት አፈግፍጋለች። ወድቃለች። ኤፌሶን እግዚአብሔር ከጀመረባትና ካኖረባት ፍቅር፣ ትጋት፣ ሕይወት... ልክ ወድቃለች። ወገኖች ሆይ፣ ዛሬ ቤተክርስቲያን ‹‹እግዚአብሔር ከሰጣት ልክ በታች አይደለችም›› የምትሉበት አቅም አላችሁ? በእርግጥ ‹‹ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሚፈልገው ልክ ናት›› የምትሉ ከሆነ እኔ ሞት ባልችል ነውና እባባችሁን አሳዩኝ። ከጸሐፊው ጋር ግን ከተሰጣት ልክ መወደቋንና መድከሚን የምታምኑና የምታውቁ ከሆነ ታዲያ እግዚአብሔር የጣለወዓ ዘመነ ለማነሣት ስለ ምን በሥጋ ጉልበት ትወተረተራላችሁ? በድካማቸሁ የሚበረታወዓ አትጡበቁምን? ጌታ ሁላችንንም ይርዳን! ወዶች ሆይ፣ ከእወነቱ፣ ከምሕረቱ፣ ከክብሩ፣ ከሕይወቱ፣ ከጸጋው፣ ከባሕሪይው፣ ከሚሑ.. ልክ በታች ተገኝተናልና በዚህ ሁሉ እኔ ‹‹ወዮልን›› አልልም ‹‹እሰየሁ!›› እንጂ። ምክንያቱም በዚህ ዘመነ መምሻት የሚመጣወዓ ቀን - መነግሥቱን አይቻለሁና - ሴላህ!!

‹‹ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አወቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፣ እንዲሁም ሳይሆኑ፡- ሐዋርታት ነን የሚሉትን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አወቃለሁ›› (ኤፌ.2÷2)። ሐዋርያት ያልሆኑና እወሸተኞች በማነበሯ ተገኝተዋል። ግን አወቃቸዋለች። ስለ እነዚህ የነቃች ናት። ሽማግሌዎቿ ትጉዎችና ሠራተኞች ታጋሾችም ናቸው። ግን ከቀደመው ፍቅር እንዳትወድቅ ለዚህኛው አቅም አላገኙም። ለምን? የመጀመሪያው ዘመን እንዲህ ሚለቅ አለበትና። የተሰጠው - ያለው ዘመን እንዳይደክምና እንዳያልቅ ሊጡበቅ ወይም ሊከላከል ለማንም ዘብ እንዲቆም አልተሰጠወዓም። ዘመናቸው እንዳይደክም የሠሩና የሚሥሩ ሁሉ ስተዋል። ዛሬ ያለችወዓና የደከመችወዓ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በባሰና በከፋ እንዳትደክም፣ ከሌሊቷና ከወድቀቷ ሊጡበቋት ብዙ ዓይነት ፕሮግራም የሚያጣጥ፣ አያሌ ዓይነት ዘዴ የሚቃይሱ፣ ጥንታዊና የተሻሻለ ዕቅድ የሚያወጡ ሁሉ እኔ እላችኋለሁ በያዕቆብ ማነነት ያሉ አታላዮች ናቸው። ከእንግዲህ እግዚአብሔርንና ቅዱስ መንፈሱን ላለፉት ዓመታት ለተሰጠኽ ዓይነት ሥራ ማሳሣት በፍጹም አይቻልም። እግዚአብሔር ደግሞ በሰዎች ፕሮግራም፣ ዘዴ፣ ዕቅድ፣ አሠራር (System)... ስለ ሰዎች ተነሥቶና ሠርቶ አያወቅም።

የጊዜወዓ ሚልእክት ትተባበሩ እንደ ሆነ፣ ስሙ፣ የቤተ ክርስቲያን ሞኮር አርጅቷል። የሚከቧም እንጅን ተበላሽቷል። ስለዚህም የሚከቧ ዕድል ሚጠም ብቻ ነው። ሚከቧ እና የሚከቧ ብዙ ክፍል (Her Systems) ሲሰጥም ብቻ ነው ወደ እግዚአብሔር ቀን የምነጠቀው። ማንም ወደ እግዚአብሔር ፈቃድና አሁን ወዳለው ዓላማው ሊያድግ የሚሆንለት እስካሁን የያዘወዓ ትምህርት፣ መረዳት፣ ፕሮግራም፣ ሥርዓት፣ ስም፣ ዶክትሪን፣ መተዳደሪያ፣ ደንብ፣ ቀኖና... በአዲስ ሲያድስና እነዚህ የነጋዴ ዕቃዎችን የጫው ሚከቡን ሲያሰጥም መሆኑን ይወቅ። የባቢሎን ሚከብ ከጫው ብዙ ሸቀጥ አንድ ‹‹የሰዎች ነፍሳት›› እንደ ሆነ አላነበባችሁምን (ራእ.18÷13)? ዛሬ በነፍሳት ይበልጥ የሚገደው የት ነው? አምላኬ ሆይ፣ አባቴ ሆይ፣ እባከህን ዓይናችንን ክፈት! ዘንዶ በሚጫወትበት ባሕር የሚዱ ሚከቦች (እነዚህ የአብያተ ክርስቲያናት ምሳሌዎች ናቸው።) ሚጠምና ሚባበር ሊገባቸው ጊዜው የቀረበ አይደለምን? ነፍሳትን ከነጋዴዎችና ከሚከቦቻቸው ሚጣል የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ብዙዎች ግን ነፍሳት በሚበቂያ ሞሞቹው ላይ ወጥተው ጅራፋቸወዓ ያስጮኻሉ። ይሳካላቸዋልን? አይደለም። ሁሉን ዓይነት የጫው ሚከብ ሚባበርና ሚጠም ይዟል። እንዲህ ነው እግዚአብሔር ሁሉን የሚድነው - የተባረከ አምላክ ነው!

ኤፌሶናወያን የኒቆላወያንን ትምህርት ተቃወመዋል። የኒቆላወያን ትምህርት ካህናትን - ሰዎችን በሰዎች ላይ ካህን አድርጎ የሚኖም የምሥጢቃወያን ትምህርት ነው። ብዙ የአረማወያን ሃይማኖቶች የዚህ ባለቤት ናቸው። ብሉይም በዚህ ተገኝቷል። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከብሉይ ያመላጠችና ከምሥጢቃወያን ነወር የወጣች ናትን? እርግጥ ነው፤ ኤፌሶናወያን ይህንን ድል ነሥተዋል። ግን በሌላ ነገር ደከሙ። የቀደመወዓ ፍቅር ጣሉ። በብዙም ጉዞ ፈጽመው በመድከምና በሚለቅ ወደ ሁለተኛው ዘመን አለፉ።

2. ዘመነ ሰርምኔስ

‹‹መከራህንና ድህነትህን አወቃለሁ፣ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ፥ - አይሁድ ነን የሚሉት የሚነደቡትን ስድብ አወቃለሁ›› (ራእ.2÷9)፡፡

በአዲሱ ኪዳን ማለት በአዲሱ ሰው አይሁዳዊነት ሕግን በመቀበሉ ወይም በመረዙ መሆኑ ቀርቷል፡፡ ‹‹ዳሩ ግን በስወር (በወስጥ) አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው›› (ሮሜ.2÷29)፡፡ ዛሬም ‹‹ክርስቲያን›› የተባሉና የሚመጡ ብዙዎች ናቸው፡፡ በወስጥ ወይስ በወጭ? በእርግጥ በአብዛኛው በወጭ በሆነ መገረዝ ነው የብዙዎች ክርስትና፡፡ እግዘአብሔር አምላክ ሕዝቡን፡- ‹‹ክርስቲያን›› ብሎ ጠርቶ አያወቅም፡፡ ይሄ ለእግዚአብሔር ልጆች የተሰጠ ‹‹ቅጽል - Nikename›› የተገኘው በአንጾክያ አሕዛቦች ለደቀ መዛሙሮት የወጣላቸው ስም ነው፡፡ ራሱንና ድርጅቱን፡- ‹‹ክርስቲያን›› ካለው ብዙኃን ስንቱን እግዚአብሔር አብሮ ብሎት ይሆን? እግዚአብሔር፡- ‹‹አንተ ልጄ ነህ›› እንጂ ‹‹ክርስቲያን ነህ›› ያለበት ስፍራ የለም፡፡ ክርስቲያን መሆኔ ሳይሆን ልጅ መሆኔ ነው ዛሬ፡፡ ምክንያቱም ብዙዎች ሳይወለዱና ሳይለወጡ በሃይማኖትና ድርጅትን በመቀላቀል ብቻ፤ በወርስና በባሕል ብቻ ክርስቲያኖች ተብለዋልና፡፡ በክርስቲያንና በክርስትና ስም የሰይጣን ማኅበር - The Synagogue of Satan አባል ሊሆን ይችላልና ሁሉም ራሱን ይይ፤ መንገድንም ይፈትን፡፡

ከሰይጣ - ከዓም - ከአሮጌው ሰው - ከኃጢአት ሰወነት ጋር ባልተለወጠ ልቦና ባልታደሰ አእምሮ ያሉና የሚሰብሱ ሁሉ የሰይጣን - የጠላት - የተቃዋሚው - የፀረ ክርስቶ ማኅበርተኛ መሆኑ አይደለምን? በሰርምኔስ እነዚህ ሁሉ ተገኙ፡፡ የመጀመሪያውን ዘመን የጨፈሰው የዚህኛው ዘመን በዚህ ሊደክምና ሊያልቅ ተራ ገቢቷል - ጽዋውን አንሥቷል፡፡

ሰርምኔስ ማለት ሥርወቃሉ መራራ ማለት ነው፡፡ በዚህች ቤተ ክርስቲያን የደረሰው ታላቅ ስደትና መከራ ያሳየናል የስሟ ትርጓሜ፡ ቤተ ክርስቲያን ታላቁን የመከራ ጽዋ መጨልጥ የጀመረችው በሮማዊው ገዢ በኔሮ ነበር፡፡ እስከ ሞት የደረሰ መከራ ነበረ - የአሥር ቀን መከራ፡፡ አሥር የሰው ፍጹም ቁጥር ነው፡፡ አሥር መከራ (Test) ነው፡ ይሄ ጊዜ ከ170 ዓ.ም እስከ ቆንጠስጠሮስ 312 ዓ.ም ይዘልቃል፡፡ ሰርምኔስ የቱንም ያህል ባለ ጠጋ ብትሆን በተለቀቀባት መከራ ምክንያት ለሌላኛው ዘመን - ለሦስተኛው ክፍለ ዘመን ደከመች፡፡

3.ዘመነ ጴርጋሞን

ጴርጋሞን ሰይጣን የሚኖርባትና የሰይጣን ዙፋን ተብላለች፡፡ የዚህ ምሥጢር ሰፊ ነው፡፡ አታሉስ የተባለ ከለዳዊ ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ፋርስ ከመወረሯ በፊት ጴርጋሞን ይመጣል፡፡ ሰይጣን ያኔ ዙፋኑን ከባቢሎን ወደ ጴርጋሞን ያዞረው፡ ኋላም ከጴርጋሞን ወደ ሮም ዞሯል፡፡ በመጀመሪያም ጊዜ አታሉስ የክርስቶስ ተከታዮችን አሳደደ፡፡ አንቲጳስም ሰማዕታት ከሆኑት መካከል አንዱ ነበር በወቁቱ፡፡ ነገር ግን አታሉስ ብልሃቱን ወዲያው በመለወጥ ቤተ ክርስቲያንን ከፍ ከፍ ሚድረግ ጀመረ፡፡ በቆንጠንጠሮስም በኩል ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት አንድ የሆኑበት ታሪክ ተደገመ፡ ብዙ ዓለማዊ ሰዎች ያለ ምንም ለወጥና ‹‹ጌታን ሳያገኙ›› ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ የሚፋፉ ጥሪ ያቀርብ ነበርና ብዙዎች ተጨፈጨፉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ያልተለየችበት ሕይወት መጀመሪያ ይሄ ክፉ ዘመን ነበር፡፡ የኒቆላወያንና የበለዓም ትምህርት በዚህን ጊዜ ጠንካራ ምሽግ ያዘ በቤተ ክርስቲያን ወስጥ፡፡

ሰው በሰው ላይ በክህነት አሜካኝነት ተሾመ፡ ሰው በሰው ላይ በአገልግሎት ስም መከፈፍ የያዘው ከዚያ ወዲህ ነበር፡፡ የነፍስ አባት፣ የክትትል ትምህርት፣ አገልጋይ፣ ካህን... የሚሉ የኒቆላወያን መሻሻ ያላቸው ሐሰቶች ቤተ ክርስቲያን የገቡት በዘመነ ጴርጋሞን ነበር፡፡ የበለዓም ሥነ ሥርዓትና የትምህርቱ ድምቀት፣ ዝና፣ ዋጋቸው የተወደደ ልብስና ልብሰ ተክህኖ በዚህ ጊዜ ተጀመሩ፡፡ ስሜታዊና ውጪ የአምልኮ ሥነ ሥርዓቶችና የአረማውያን በዓላት በዚህ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጎረፉ፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ተዳራች (በተለይ በትምህርቷ)፡፡ ጴርጋሞን ማለት ጋብቻ ማለት አይደለምን? ቤተክርስቲያን ከዓለም ጋር የተጋባችበት ክፉ ዘመን ነበር ዘመነ ጴርጋሞን፡፡ እስካሁንም መጨታት ሳትችል አብራ ትኖራለች - በብዘ መልኩ፡፡ የአሕዛብ በዓላት እንደ ገና፣ ሜሪ - ኤክስማስ፣ ፋሲካ፣ የለደት አከባበር፣ የነፍሳት ቀን... የመሳሰሉት በማኅበራት ወስጥ ተገኙ፡፡ ይህም ቦኒፌስ የተባለው ጳጳስ ዓለም አቀፍ ጳጳስ ሁኖ ዘውድ በደፋበት ጊዜ ነበር፡፡ ጊዜው ከ312 ዓ.ም እስከ 606 ዓ.ም ይዘልቃል፡፡

የአብያተ ክርስቲያናቱ (የሰባቱ) መንፈስና ልሚድ እስካሁንም በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ቀጥሎና ተንሰራርቶ እንዳለ መገመቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ማንም ያለፈውን ዘመን በሕይወቱ፡- በአካሔዱ መኮነን አልቻለም፡ ሁሉም ተመሳስሎታል፡፡ የቀደሙትን ያደከመ እኛንም ያደከም ዘንድ መንፈሳቸውና ልሚዳቸው ተከትሎናል፡፡ ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ያልተለወጠና ምንም የለወጥ ሐሳብ የሌላቸው ብዙ ሰዎች አሉ፤ ቤተ ክርስቲያንንም እየመሩ ይገኛሉ፡፡ ሰዋዊ አእምሮና ትምህርት ያራምዳሉ፡፡ መጻሕፍትንም በጥሬውና በፍጥረታዊ ሁኔታ እየተረጎሙ ያጣምማሉ፡፡ እነዚህ ናቸው ቤተ ክርስቲያንን ይበልጥ እየጣሏት የሚኙት፡፡ ዛሬም አብዛኛው አገልግሎት (አምልኮ) ወጪና ስሜታዊ፣ ሥነ ሥርዓታዊና ሥጋዊ ነው፡፡ በአብዛኛው ወጪ

የሚያገለግል ነው፡፡ የነፍስ እወቀት፣ መጽሐፍትን በፍጥረታዊ መኮርነም፣ እግዚአብሔርን ማጥናት (ቲዮሎጂ ማሆኑ ነው፡፡) ዓለማዊና የመጀመሪያ ትምህርቶች … ጉልህ ስፍራ ተሰጥቷቸው የታየበት ጦምግ ትወልድ ቢኖር ይሄ ያለንበት ዘመን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በመለጥ ሳይሆን እግዚአብሔርን ወይም ስለ እግዚአብሔር በማጥናት ትመራለች፡፡ ከዚህ የበለጠ ድካም መቼም አልታየም፡፡

በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ እየነቀዘች ተስፋዋ የተሟጠጠበት ደረጃ ላይ መጥታለች፡፡ ይሄም እንደ ተወሰነላት ማጠን ነው፡፡ በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ሌላ መሆን አትችልም፡፡ ዘመኗም ሆነ ራስዋ ያለ ድካም ወደ አዲሱ ዘመን መግባት አይኖራቸውምና! ዳሩ ግን ጴርጋሞን ድል የነሡት እንደ ነበሩ ሁሉ ዛሬም ባለችው ቤተ ክርስቲያን መካከል ድል የነሡት ጥቂቶች ከመራራው በስተቀር ብዙኃኑ የዘሙና ከላይ የተወሰነለው ድካም ወደ አዲሱ ዘመን መግባት አይኖራቸውምና! ዳሩ ግን በጴርጋሞን ድል የነሡት እንደ ነበሩ ሁሉ ዛሬም ባለችው ቤተ ክርስቲያን መካከል ድል የነሡት ጥቂቶች ከመራራው በስተቀር ብዙኃኑ ዘሙና ከላይ የተወሰነው ድካም ወጥታል፡፡ አሁን ቤተ ክርስቲያን ‹‹የእግዚአብሔር ተቋም ናት›› ከምትባልበት ደረጃ የወጣች ናት፡፡ አሁን ባላት ሕይወትና አካሄድ ማንም መሸጋገር ያደረጋት ዘንድ ወደ እርሷ የሚሸሽ የለም፡፡ አሁን ስለ እርሷ፡- ‹‹የገሀነም ደጆች አይሏትም›› ነው ሊባል የሚችለው፡፡ አሁን ካለችው ድርጅታዊቷ ቤተክርስቲያን (ከሀናዊቷ ባቢሎን) ጋር እግዚአብሔር የለም፡፡ የአገልግሎቷ፣ የሥነ ሥርዓቷ፣ የአምልኮዋ፣ የትምህርቷ፣ የፕሮግራሟ… ሽታ ለእግዚአብሔር የአፍንጫ ጫኽ ሁኖበታል፡፡

በእርግጥ እነዚህ ሁሉ በዚህ ዘመን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ፊሳ ሣጥኗ ላይ የሚጨሻ ምስማር የሚመቱ ናቸው፡፡ ወገኖች ሆይ፣ ደስ ይበላችሁ፤ ቤተ ክርስቲያን እየሞተች ነው፡፡ ሃሌሉያ! ፈጽሞም ስትቀበር ጌታዋ እንደ ተነሣ ትነሣለች፡፡ ለመኖር የሚፈልጉ ራሳቸውን ያላጡ ግን ወዮላቸው፡፡ ዛሬ ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ድካም፣ ሚለቅ፣ ሚርጅት… በቅዱስ ድፍረት አንሥቼ ስጽፍ ብዙዎች የጥላቻ ሊማከላቸው ይችላል፡፡ በፍጹም አይደለም፡፡ በሚለእክቴ እግዚአብሔርን ምስክር እጠራለሁ፡፡ እግዚአብሔር ያሳየኝን ነው የምለው፡፡ ፈቃድ በዚህ ዘመን እንዲህ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን አልቃ ነው - ደክማ ነው - ተስፋ ቆርጣ ነው - ሞታ ነው… ወደ መንግሥቱ ሚለዳ የምትነሣው፡፡ በትንሣኤው ሚለዳ የጌታዋ መቃብር ባዶ እንደ ነበረ እንዲሁ የቤተ ክርስቲያ (ያስማኑ ሳይሆን በእወነት የሞቱ) መቃብራቸው ባዶ ይሆናል - ወደ እግዚአብሔር ክበብ ይነጠቃሉ - ያርጋሉ፡፡

በጴርጋሞን ድል የነሡት ያንን ዘማ ጴርጋሞንን ገድለው አራተኛውን እና ዘማ ትያጥሮንን እንዳስነሡት እንዲሁ አሁን ባለችው ቤተ ክርስቲያን ያሉ በትክክል የተወለዱና ያደጉ በመንግሥቱም ድል የነሡት ራሱን ቤተ ክርስቲያንና ሚኒስቶሪ ብሎ የሚጠራው ድርጅት ሁሉ ሰሚይ (መንፈስ) ዘግተው የእህላቸውን ኃይል በማስበርና በርሀብ በመደል ዓለም አይታው በማታወቀው ጨለማ ተገፍኝተው ወደ ቀጣዩ - ወደ ሰባተኛው ቀን - ወደ ሰንበቱ ያነሷቸዋል፡፡ ከእንግዲህ የአብያተ ክርስቲያናትና ሰሚይ የማጋት እንጂ የመክፈት ዕድል የለውም፡፡ ይህም ሰሚይ ሲጨልም የመንግሥቱ ሰሚይ የመክፈት ዕድል የለውም፡፡ ይህም ብቻ አይደለም የዓለምን ፖለቲካና በዓለም ያሉትን ሃይማኖቶችን ሁሉ ይጨልማሉ፡፡ የጌታ ቀን የጨለማና የድቅድቅ ጨለማ ቀን አይደለምን?... እስካሁን የተሄደበት መበራት - ሚዳት - ትምህርት - ሥነ ሥርዓት… ይጨልማል፡፡ የትምህርት፣ የመለጥ፣ የሙሐፍ፣ የአገልግሎትም ሆነ የትኛውም ዓይነት ብርሃን መበራቱን በማስጠት አይቀጥልም፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ድካም በዚህ ዘመን የአገልጋዮችም መንፈሳዊ ድንክነት የዚህ አስረጅነት እንደሆነ በሁላችሁ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ እግዚአብሔር ለአዲስ ነገር - ለአዲስ ዘመን - ለአዲስ ትወልድ… ተነሥቷል፡፡ በእርግጥም አገልግሎት አልቋል፡፡ አብዛኛው ነገር የአሮ ነገር ድሪቶ ነው፡፡ በሚለጡ በብርሃን ልጆች - በቀን ልጆች ፊት እስካሁን ያለው ነገር ይጨልማል፡፡ የሴቲቱ ምጥ የወንዶች ልጅ መለጥ ጊዜ ነውና ዛሬ በሁሉ ላይ ስለደረሰው የወስጥ ጨቨት እሰየሁ - የእግዚአብሔር መንግሥት ከወስጣችን አልፎ በሁሉም ላይ ሊነጋ መቅቱንም ሊሰጥ ነው!

ስድስተኛውን ዘመን - የሰዉን ዘመን - የቤተክርስቲንን ዘመን (የቤተ ክርስቲያን ዘመን ከሰው ዘመን ጋር መጀመሩ የሚርም ነው፡፡) ያጨሙት የልጁ ልጆች - በኩሩ የተሳለባቸው ልጆች በጉንና ከብሩ፣ መንግሥቱንና ብርሃኑን በሁሉም ላይ ያበሩታል፡፡ ትናንሽ ብርሃናት ከእንግዲህ አይገኙም፡፡ የበጉን መሎ ብርሃን ለማግኘት ሻማዎችን (ጥቅሶችን) መላኮስ ያበቃል፡፡ እግዚአብሔርም በዚህ ጊዜ በሁሉ ስፍራ - በሁሉ ላይ ላንዴና ለመጨሻ ይነግሣል፡፡ ወገኖች ሆይ፣ ስመኝ አስተወሉም፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ነው የምታልቀው፡፡ ከእንግዲህ እርሷን ለማኖርና በእርሷ ለመኖ አትድከሙ፡፡ እግዚአብሔር ቀኗን ጨርሷል፡፡ ወደ ዕረፍቱ ያገባናል፡፡ ፍቃዱም በእናንተ ይፈጸም ዘንድ ብቻ ንቁ - በዚህ ጊዜ፡፡

‹‹በአንድ ስንኳ አላፍርም ነገር ግን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት፣ ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው አሁን ደግሞ በሥጋዬ ይከብራል፡፡ በእኔ ሕይወት ክርስቶስ፣ ሞትም ጥቅም ነውና›› (ፊልጵ.1÷20-21)፡፡ ለዚ ዓይነት ሰው ሞትም ሕይወትም ልዩነት የለውም፡፡ በሕይወት እርምጃ ወደ ግቡ ሊመጣ ክብርም ወርደትም አይዘም፡፡ በመከናወንም አይወድቅም፡፡ ድሎትና መከራ ለዚህ ሰው እኩል ናቸውና መከራን ረግሞ ድሎትን አይመርቅም፡፡ ችግርን አወግዞ (ገሥፆ) ስኬት አይሰብክም፡፡ ሁለቱም ወደ እግዚአብሔር መልከና ምሳሌ የሚባባቸው ርካብ ናቸውና፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው በሞት የሚገኘውን ሕይወት

ስለሚያወቀው ሞትን እንደ ሕይወት ይቀበለዋል፡፡ መቼስ እንዲህ ዓይነት ሰው ለትወልዱ እንግዳ ነው፡፡ ለዘሙም እብደት፡፡... ቤተ ክርስቲያን በወርቃማ ዘመኗ የኖረችው ኑሮ አለ፡፡ አሁን ደግሞ በሌሊት ምንጣፍ ላይ ሁኖ ከሌሊት ልብሷ ጋር የምትኖረወን ኑሮ እያየን ነው፡፡ ሁለቱም አንድ ናቸው፡፡ ለመላወጧ - ለመንግሥቱ መላት ይሠራሉና፡፡

በዚህ ሁሉ የእግዚብሔር ዓላማ ሊገባን ያስፈልጋል፡፡ ለእግዚአብሔር ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድና ሦስት አንድና አንድ ናቸው፡፡ ፍጥረት በ‹‹እጅግ መልካም ነበረ›› መሚቁም ሆነ ‹‹ለከንቱነት መገዛቱ - ከሚገም በታች መሆኑ›› በአንድ ምዕራፍ የሚታዩ ለሌላ ታላቅ ነገር የተሠሩ ናቸው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፕሮግራም ሁሉንም እንደ ፈቀደወና እንደ ወሰነው የሆነ ነው፡፡ መመለዳችን ‹‹መልካም ነው›› ያልንበት መለጥ እንደ ፈቃድ ‹‹መምታችን (ግፍ) ክፉ ነው›› ሚለታችን በሰወነት ሁነን ነው፡፡ ሞት ለሌላ የሕይወት ከፍታ እንደሚፈታን አላወቅንምና፡፡ ትንሣኤም በሞት ብቻ እንደሆነ አልተሚገንም፡፡ በሥጋ ሞት ከሠራ ከርስቶስ ከብሯል፡፡ እንደ ምን? ‹‹በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው፡፡››ልዩነት የለም፡፡ ጉዳዩ፡- ‹‹ብኖር ወይም ብሞት›› ነውና ነው፡፡ ሁለቱም አንድን ነገር ያደርጋሉ፡፡ ከርስቶስን ያከብራሉ፡፡ ይህንን ታውቃላችሁ? እንግዲያወስ በመኖሩ - በሕይወት - በድል - በብርታት - በመ ቃቃት - በጸሎት መልስ... የዘመረ በሞቱ - በሞነፉ - በኀዘኑ - በድካሙ - በሌሊቱ... አያልቅስ፡፡

አሁን ባለችው ቤተ ክርስቲያን አቋምና አሁን በያዝነው ለእያንዳንዳችንም በሚሚስለን መንገድ ከርስቶስ የሚከብር ይመስለን ይሆን? በመለጥ፣ በሕይወት፣ በእግዚአብሔር ነገር ከፍ ለሚለት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መገባት አለብን? የቤተ ክርስቲያን ሹመት ያግዘን ይሆን? ቤተ ክርስቲያን ስለ ቤተ ክርስቲን እንዳንናገርና እንዳንጽፍ ስላስጠቀቀችና እኛም ስለ ፈራን እንጅ ስለ እርሷ የምንለው ብዙ ነገር አለ፡፡ ከአታላይቱ ከዳተኛይቱ ጸድቃለች፡፡ በራድ መሆን ተሸሎ ተገኝቷል ከሎዶቅያ ለብታ - አወይ!

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ዓለምን የምትመስልበት ብዙ መልክ አላት፡፡ ከዓለም ጋር ለመወዳደር ሜዳ የገባችበት መያዋ ብዙ ነው፡፡ በዓለም መንገድ፣ ሥርዓት፣ ዘይቤ፣ አሠራር... እየሄደች ዓለምን ለሚዳን ታልሚለች፡፡ አሁን ካለችው ቤተ ክርስቲያን ዓለም ምን ትፈልጋለች?... የቀልዶች ቀልድ! ዓለም የቤተ ክርስቲያንን ዝክር - ጸበል ጸዲቅ የምትበላበት ሞኝነት ላይ አይደለችም፡፡ አሁን ግብረ ገብ ለዓለም አንዳችም ፋይዳ የለወም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም የምታስፈራ አይደለችም፡፡ ሐዋርያዊም ሆነ ትንቢታዊ መልእክት የላትም፡፡ የሀገር መሪዎች የፈለጉትን ቢያደርጉ በእግዚአብሔር ፈንታ ሁና የምትገሥፅበት አቅም ላይ አይደለችም፡፡ ... ቤተ ክርስቲያን ወድቃለች፡፡

ቤተክርስቲያን የዓለም መንግሥት ዓይነት አስተዳደርና የሕዝብ አያያዝ አላት፡፡ ፖለቲካው፣ ባሕሉ፣ ማነበራዊው ኖሮ፣ ኢኮኖሚው... በቤተክርስቲያን አቋም ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አላቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ከተቀበለችው ማንነት ጋር ስትታይ በዚህ ጊዜ የእነዚህ ሁሉ ራስ ሳትሆን ጅራት ናት፡፡ ትምህርቷ የአካዳሚ ዓይነት ነው፡፡ አስተዳደሯ መያዊ ነው፡፡ መዋቅሯ ድርጀታዊ፣ በጀቷ ጥናታዊ ነው፡፡ ሥነ ሥርዓቷ ሕጋዊ ነው፡፡ አወቃቀሯ ከልላዊና ወገናዊ ነው፡፡ አመላካከቷ አጥቢያዊ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከዚህ የተለየ አልተጠበቀባትም፡፡ ልትሆንም አትችልም፡፡ እኔም ከዚህ አቋሟ ብትለወጥ ብዬ አስተዋፅዶ ይሆንልኝ ዘንድ አልጻፍኩም፡፡ የሕይወቷ ሚጨረሻ ይኸው መሆኑን ታውቅ ዘንድ እንጂ፡፡ ይሁንና የእግዚአብሔር መንግሥት ሞርሕ በምትከተለው በዚህ ዓይነት መንገድ ለዓለም ይደርሳል ብላ አታስብ፡፡ እንደዚህም አትድከም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ለሚዳን የተላከች ባትሆንም ለዓለም ምስክር ልትሆን እርሷ ራስዋ ከእነዚህ ሁሉ አስቀድማ ትዳን፡፡ እርሷ ትድን ዘንድ ደግሞ መሞት - ሚለቅ - ተስፋ መቁረጥ - ለሚጨርሻ አንገት መድፋት አለባት፡፡ የእግዚአብሔር ቀን በሁሉም ላይ መጥቷል - የደመና የጭጋግ፣ የጨለማና የድቅድቅ ጨለማ ቀን - ሃሌሉያ!

በሞት - በመሥዋዕት - በሚለቅ - በድካም ብቻ ልናልፈው የምንችል ታላቅ ግንብ በፊት ለፊታችን እየተገዳደረን ነው - የለወጥ ግንብ - ለዚህ ነው ሁሉ ነገራችን የሚተመን፡፡ ነጥሮ ወደ እኛው ይመላል፡፡ ነገሮች ከነበሩበት ወደ ዛሬ እየተገለበጡ ነው፡፡ አዲስ ነገር የለም፡፡ ያለ ሞት የቤተ ክርስቲያን ዘመን አያልቅም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ብዛት፣ የሚሽነሪዎች ፍጅት፣ የአገልግሎቶች እጅግ እየናሩ መሄድ... አሁን ያለው ዓለም የሚለወጠው ይመላችኋል?.... አብዛኛው ነገር ለዓለም መዳን የሚሥራ ሳይሆን ለብዙዎች ገቢ ማግኛ ሁኗል፡፡ በዚህስ መንፈሳዊ ነጋዴዎች ተሳክቶላቸዋል፡፡

የጴርጋሞን ድል ነሺዎች የትያጥሮንን ዘመን ያንጉት እንጂ ትያጥሮን ራስዋ ደግሞ በዘመኗ የደከመቸው ድካም ሲታይ ይዘገንናል፡፡ ኃጢኣት፣ ሰወነት፣ አሮጌ ሰው፣ የቤተ ክርስቲያን መንፈስና ልሚድ፣ የሰው ሥርዓትና ቀኖና... በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ የበለጠ እየተበላሸና እየደከመ - ተስፋ እስከሚይጣልበት እየነቀዘ ወደ ጥፋቱ ሲያንስና ሲወርድ ታይቷል፡፡

ድካምን፣ ሚርጅትን፣ የመንፈሳዊ ከንፋችን መላበርና መላቀል... ማን በጸጋ ተቀበለ? ይሁን እንጂ ዛሬ በሁላችን እየሆነ ያለው እርሱ ነው፡፡ ደረቁ ሕይወት ደረቁ አገልግሎት፣ ወዙ የተሰወረ ስብከት፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ የቤተክርስቲያን ፕሮግራም...

የክንፋችን ማሰበርና መቀል - የወበታችን መፈፍ - የመንፈሳዊ ቅርጻችን መጥፋት ካልሆነ ምንድር ነው?... የፈለጋችሁትን መንፈሳዊ ልምምድ፣ ትጋት፣ ጾም፣ ጸሎት፣ ... ብትጠቀሙ እግዚአብሔር አሁን ካደረገወና በእያንዳንዱ ሕይወት ይሆንና ይሠራ ዘንድ ከለቀቀው ድካም፣ እርጅና፣ ሞት፣ መሥዋዕትነት አታመልጠም። እያደረግናቸው ላለመቀጠል የሚበረታታ ባልሆንም እነዚህን በሚድረጋችን ሳይፈረድብን የእግዚአብሔርን ፕሮግራም ግን ሊለወጡት እንደሚችሉ በሁላችን ዘንድ የታወቀ ቢሆን መልካም ነው።

4. ዘመነ ትያጥሮን

የዚህችን ቤተ ክርስቲያን መልእክት በራእ.2÷18-29 ያገኙታል። ሐሰተኞች ነቢያትና ሐሰተኛዋ ኤልዛቤል በትምህርታቸው ሕዝብን ያሳቱበት ዘመን ነበር ይሄኛው ደግሞ። ኤልዛቤል በአታላዩ ትምህርትና ሥርዓቷ ሁሉ ባሪያዎቹን ታስትና ለጣኦት የተሠዋውን እንዲበሉ ታደርግ ነበር። ሰው በቤተ ክርስቲያን ስም በትምህርትና በሥነ ሥርዓት፣ በልሙድና በአገልግሎት የሴሰነበት ጊዜ በጣም ብዙ ነው። ይሄ ሃይማኖታዊ (በተለይም ክርስቲያናዊ) ሥርዓት ከፍታወን የያዘው ደግሞ በሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን እንደ ነበረ የብዙዎች እምነት ነው። በቅስና ሥርዓት ብዙዎች አመንዝረዋል። እውነትንም ለምድራዊ ክብር፣ ዝና፣ ታዋቂነት፣ ገንዘብ... ሸጠዋል።

በነገራችን ላይ በዚህ በራእይ ምዕራፍ ሁለት በለዓምና ኤልዛቤል ማከቀሳቸው ምሥክር ምንድር ነው? ሁለቱ ሰዎች ዮሐንስ ራእዩን ባየበት ወይም በእነዚህ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ባሉበት ዘመን ነበሩን? አይደለም። መንፈሳቸው፣ ትምህርታቸው፣ ልማዳቸው፣ ሥርዓታቸው... እስከዚህ ዘመን መጥቶ ነበር። ታድያ እንዲህ ዓይነቱ በትምህርት፣ በሥርዓት፣ በልሙድ፣ ሚሴን አሁን የለም ትላላችሁ? የበለዓም ክብር፣ የሐሰት ደመወዝ፣ ዝና፣ ታላቅነት፣ ታዋቂነት፣ የኤልዛቤል ጣኦል፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለትምህርቷ፣ ለሥርዓቷ ማንበርከክ (የሥራ፣ የትምህርት፣ የስኮላር ሺፕ በር በመክፈትና በምታቀርበው ጉርሻ) በጉልህ የሚታዩ ናቸው። በዚህም ዘመን ጴርጋሞንና ሰርምኔስን ያደከሙ እነዚህ ክፋቶች በዚህ ዘመን (መልቸወን ለወጠው) መኖራቸው ብቻ ቤተ ክርስቲያን ያለ ጥርጥር ትደክሟለች።

የዚህ (የዘመነ ትያጥሮን) ዘመን ከ606 ዓ.ም ጀምሮ የተሐድሶ ዘመን ተብሎ እስከ ተጠራው እስከ 1520 ዓ.ም ዘልቆ ተጉዟል። ቤተ ክርስቲያን በትልቁ መከራና በረዥሙ የጨለማ ዘመን (Dark Age) ተጓዘች። የቤተ ክርስቲያን ጉዞና ታሪክ እጅግ የሚገርም ነው። ተሐድሶ እስከ ተጀመረ ድረስ ከሐዋርያቶች በኋላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እጅግ ጸያፍ ነበር። ከፍ ብላ አታወቅም ተዋርዳ እንጂ እንደ እግዚአብሔር ዕይታ ስትታይ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልትፈጽም የተፈጠረች ሕያው አካል ሳትሆን የልቡ ሐዘን ልትሆን የተቋቋመች ድርጅት ሆነች። ከተሐድሶም በኋላ የቀጠለው ነገር የነበረው ዓይነት አይሁን እንጂ በእግዚአብሔር የሚኪያ ዘንግ ሲለካ ልኩን ያልደረሰ ጎዶሎ ሕይወት ነበር። ያም ጎዶሎ ነገር በተቀሩትና በኋለኞቹ ሦስት ዘመናት በመጣዝ ይበልጥ በመዶደል ዛሬ ወዳለንበት የሎዶቅያ ልከና ሚዛን ላይ ደርሷል። በዚህም ሚለት በጴርጋሞን ድል ነሺዎች መገኘታቸው አስገራሚ ነው። እነርሱም ያንን ዘመን ሽረውና አስረጅተው አምስተኛወን ዘመን አስነሡት። ንጋት ሰጠት።

5. ዘመነ ሰርዴስ

<<... ሥራህን አወቃለሁ ሕያው እንደ ሚመንህ ስም አለህ ሞተህሚል። ሥራህን በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን... ነገር ግን ልብሳቸወን ያላረኩ በሰርሴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ሁን... ነገር ግን ልብሳቸወን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ሰዎች ከአንተ ጋር አሉ...>> (ራእ.3÷1-6)። ይህች ቤተ ክርስቲያን ከተባለችው ሁሉ - <<ሞተህሚል>> የተባለው ከባድ ነው። ስም ያለው ግን የሞተ። ባለንበት ዘመን ያሉ አጥቢያዎችና ሚኒስትሪዎች ያላቸው ስምና የሌላቸው ሕይወት የምናይበት ነው ዘመነ ሰርሴስ። ሰርዴስ ሚለት ሚሞላጥ (ያመላጠ) ሚለት ቢሆንም እንደ ስሟ መሆን ግን አልቻለችም። ቤተ ክርስቲያን በአምስተኛው ዘመኗ ሞታ ተገኝታለች። አዎን፤ በታሪክ ይሄ የተሐድሶ ዘመን ነበር። እንግዲያወስ የሞተ እውነተኛ የታደሰ። እየኖሩ መታደስ የለምና! ንስር ሲያረጅ ይታደሳል። ሰው ሲሞት ይነሣል። የእጣን ቁርባን በመቃጠል ይጨሷል! ይሸታል!። በመሥዋዕት የኃጢአት ሥርየት ይገኛል። የኃጢአት መሥዋዕት የሆነው ደም በሞት ይለቀቃል። ቤተ ክርስቲያንም በትንሣኤው ኃይል ወደ መንግሥቱ መላት የምትነሣው አሁን በሆነባት ድካም ፈጽማ ሞታ ነው።

ዘመነ ሰርዴስ ሲጀምር (በ1500 ዓ.ም አካባቢ) ሃይማኖት ፈጽሞ- ከርስትና መሉ በመሉ መልኩን የለወጠበት ጊዜ እንደ ነበረ የታሪክ ሚዘገጃ አለን። <<ከርስትና>> ለመጽሐፉም ሆነ ለእግዚአብሔር እንግዳና ባዕድ የሆነበት ጊዜ ላይ ደርሶ ነበር። ይሄኔ ነበር ጥር31,1517 እ.ኤ.አ ሚርቲን ሉተር በጀርመን በሚገኘው በዊልን በርግ ከርስቲያን በር ላይ ዘጠና አምስት ቴሲሱን ጽፎ የለጠፈው። ያኔ ነበር በብዙዎች ላይ ተጽዕኖን ያሳደረ ተሐድሶ የተጀመረው። እዚህ ላይ አንድ ነገር ሚለት ያሻል፡ - የሉተር ተሐድሶ (ሥር ነቀል ተሐድሶ ግን አልነበረም።) የሉተር ተሐድሶ የቤተ ክርስቲን ድካምና ሚለቅ ወጩት እንደ ነበረ ማወቅ ያስፈልጋል። ሁል ጊዜ ይቻላል፤ ሁልጊዜ ተሐድሶ ወይም መነቃቃት የድካም - ተስፋ የመቁረጥ -

የብልሹነት - የሞት ወጠመኔ ሁኖ ታይቷል። የሆነ ሁኖ በብዙ ሀገሮች በዚህ ጊዜ ከሃይማኖት ነፃነት ይልቅ የፖለቲካን ነፃነት ለማግኘት እንቅስቃሴ የተደረገበት አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። በተለይም በጀርመን። ሮም ሃይማኖታዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ፖለቲካንም ትቆጣጠር ነበርና የሉተር እንቅስቃሴ አንዳንዶችን ረዳ። ብዙዎችችም የሮምን የሃይማኖት ቀንበር ሲጥሉ የፖለቲካውንም ቀንበር አብረው አሽቀነጠሩት።

ሉተር በጀመረውና ለወጠኔ በበቃበት ተሐድሶ ሮም ተጎዳች። በእርግጥ ሉተር አወፌወን ባይገድለወም አቁስሎታል። ስላልገደለወም ነው ለሞቱ ከሆነው ቁስል የተፈወሰው አወፌው (ራእ.13÷3)። አሁን ባለንበት ዘመን ያሉ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች አብዛኞቹ ይሄ አወፌ ከቁስሉ ከተፈወሰ በኋላ የተፈለሰፉ ናቸው። የሉተርን ትምህርት ለማክለስ ሲባል የተፈጠሩ ትምህርቶችና መጽሐፍት የቤተ ክርስቲያን የገበያ ዳር ልጆች ወጠኔ ናቸው። ‹‹አወፌው ከሰው ወጭ የሚጠበቅ ሌላ ፍጥሩ እንደሆነ፣ ባቢሎን በትምህርት መዳራት ከወደቀችው ቤተ ክርስቲያን ወጭ እንደሆነች፣›› 666 ሲስተም እንጂ ስብዕና እንዳልሆነ፣ የጌታ መምጣትና የመንግሥቱ ማንነት የሩቅ ጊዜና ስፍራ እንደ ሆኑ… ወዘተ የመሳሰሉ ትምህርቶች ከቁስሉ የተፈወሰው አወፌ ትምህርቶች ናቸው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ከእነዚህ ትምህርቶች የነጻች ናት? ማንም ራሱን ይይ።

በዚህ ታሪካዊ ተሐድሶ ግን ብዙዎች ደኅንነትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእምነት (በጸጋ) እንጂ በሥራ እንዳልሆነ እየተረዱ መጡ። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነትም ታላቅ እንቅስቃሴ በዓለም ሁሉ ተጀመረ። ያም ሥራ እስከ ብዙ ዘመን የቀጠለና እስከ ዛሬ ያለ በረከትን አስነሥቷል። ይህንን መሳመር ለምታነቡ ወገኖቼ አንድ ነገር ልብ ልትሉ እለምናለሁ። እርሱም ይሄ ዓይቱ ታላቅ ተሐድሶ የተነሣበት ዘመን አምስተኛው ዘመን - ዘመነ ሰርዴስ መሆኑን እንድታዩ ነው። ሰርሴስ ደግሞ - ‹‹ሞተህሟል›› የተባለበት ዘመን ነው። አዎን፤ በሞት ሕይወት ይገኛል። በወድቀት ደኅንነት ነው። በጨለማ ብርሃን ይበራል። ሕይወት በሞት ደጅ አልፎ ሞትንም ውጦ ይደርሰናል። ቀን ከሌሊት በኋላ ነው። አዲሱ ሰው ከአሮጌው ሰው ቀጥሎ ይገለጣል። (ስለዚህ ነገር ይበልጥ ማወቅ ከፈለጋችሁ ‹‹ሞት የሕይወት ደጅ›› የሚለውን ተከታታይና ወጥ ጽሑፎችን አንብቡ - ብትጠይቁን እንልካለን።››

የዚህ (የዘመነ ሰርሴስ) ዘመን ከ1520-1750 ዓ.ም ድረስ ይዘልቃል። አሁንም የሰርዴስ ድል ነሺዎች ዘመነ ሰርዴስን ዘግተው ዘመነ ፊልድልፊያን ቀጠሉ። በሰርዴስ ሌሊት ላይ የፊልድልፊያ ቀን ጀመረ። ዘመነ ፊልድልፊያ ዘመነ ሰርዴስን አስረጅቶ ሻረው።

6.ዘመነ ፊልድልፊያ

(ራእ.3÷6-13)። ከዚህች ቤተ ክርስቲያን ስም ትርጓሜ በመነሣት የፊልድልፊያ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ዘመን የወንድማማች ፍቅር እንደ ታየበት ሞቱም ሟሉም ይቻላል። እስካሁን ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናትና ዘመናቸው በበለጠ መቀራረብና ኅብረት መፍጠር በዚህኛው ታይቷል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ዘመን መንፈሳዊ ብርታትና ጥንካሬ የታየበት ጊዜ ነበር። አንድ ኃይሉ የታደሰ ሰው በኃይል ተነሥቶ እንደሚያደርግ እንዲሁ ፊልድልፊያ ቤተ ክርስቲያን - ዘመነ ፊልድልፊያ በሕያው መንፈስ ጥንካሬዋን የያዘችበት ወቅት ነበር። በእርግጥም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን ታላቅ ነበረች። በዚህ ጊዜ ነው እጅግ ብዙዎች በመንፈስ ቅዱስ ድንቅ እንቅስቃሴ ለደኅንነት የተሟረኩትና የታጨቁት። ታላላቅ ተአምራቶች፤ ድንቆችና ምልክቶች ሆኑ። የበዓለ ኀምሳው ልምምድ - ‹‹ጸንጠቆስጤ›› እንደ ገና ትንሣኤን አገኘ። አስደናቂ ታሪክ ያላቸው የጀማ ወንጌሎች ተካሄዱ። ‹‹ከተሞችና ሀገሮች በዚህ እንቅስቃሴ ተሟርከው ተወሰዱ።

ጆርጆ ኋይት ፊልድ በ1739 ዓ.ም ያደረገው የጀማ ወንጌል ከእርሱ በፊት በነበረው ታሪክ ተወዳዳሪ አልተገኘለትም። እርሱንም የተከተሉት እነ ጆን ዊስሌይ፣ ቻርለስ ዊስሌይ፣ ጆፌኔ እና ዲ.ኤል.ሙዲ… የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ (ከነበረው ንጻር) መሉ በመሉ ቀየሩት። ቤተ ክርስቲያንም ወዳላየችው ልምምድ ገባች። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ፣ ልሣኖች፣ ልዩ ልዩ ስጦታዎች… በየስፍራው አቆጥቁጠው የቤተ ክርስቲያንን የድካም ሕይወት ዋጡ፣ የዚህም ዘመን ጊዜ ከ1970 አንስተው እስከ 1900 ያደርሱታል።

በካሊፎርኒያ አዙሳ ከተማ የተቀጣጠለወና ከእርሱ በፊት ባለው ታሪክ አቻ ያልተገኘለት እንቅስቃሴ ‹‹የኋለኛው ዝናብ›› እስከ ጀመረበት እስከ 1948 ዓ.ም (እ.ኤ.አ)ድረስ ትልቅ ትዝታ አለው። የአዙሳ እንቅስቃሴ ለዚህ ዘመን በእርግጥ ትዝታ ብቻ ነው፤ አሁን ባለነው ዘንድ የፈጠረው ነገር ቢኖርም። በዘመነ ፊልድልፊያ የጀመረው ሪቫይቫል (አሁን ተሐድሶ - Reformation ሳይሆን ሪቫይቫል ነው።) እስከ ኋለኛው ዝናብ ቀጥሏል እየጠፉም እየበራም። ከ1948 የኋለኛው ዝናብ እንቅስቃሴ በኋላ እስከ 1970ዎቹ መጨረሻ ድረስ የተነሡት እንቅስቃሴዎች፣ መጻሕፉቶችና አገልግሎት መቼውንም ተወዳዳሪ አልተፈጠረላቸውም። የብዙዎች ሕይወት በሚያስገርም ሁኔታ ተለወጠ። ጴንጠቆስጤ እንደ ሰደድ እሳት የሁሉን ቤት አንኳኳ። በዚህ ጊዜ የተነሡት የፉል ሳልፌሽንና የደሊቨራንስ፣ የፌይዝ መቪመንትና የፉል ጎስፕል ቢዝነስሜን ጅማሬዎች… ጉልህ

ተጠቃሽነት አላቸው፡፡ አሁን ያለንበት ዘመን ከእነዚህ አገልግሎቶች ጅማሬና ጥንታዊነት ካላቸው ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የወጣ አይደለም፡፡

እነዚህ ጅማሬዎች ግን በዚህ ዘመን እንደ ጀመሩበት ጊዜ ሳይሆኑ ከስመው ታይተዋል፡፡ ለማንም ግን በወስጡ ፍም አስቀርተወለት እንደ ሆነ ራሱን ይይ፡፡

የኋለኛው ዝናብ ወጩት ታላቅ የወንጌል ስርጭትና የብዙዎች የሕይወት ለወጥ ታይቶበታል፡፡ የእያንዳንዱ ሀገር በር በወንጌል የተንኳኳው በዚህ ታላቅ እንቅስቃሴ ነበር፡፡ የሀገራችንም የጰንጠቆስጤ እንቅስቃሴ የዚያ ዋቢ ነው ምንም እንኳ ከኋለኛው ዝናብ ብዙ ዘግይቶ ቢደርስም፡፡ ገን አንድ ነገር ማጠቃ የግድ ያስፈልጋል፡፡ ትላንት ወደ ዛሬ ፈጽሞ ሚመጣት እንደሚቻል፡፡ እግዚአብሔር ፈጽሞ ወደ ኋላ ሄዶ አያወቅም፡፡ እርሱ ሁል ጊዜ ከአሁን ጋር ነው፡፡ የኋለኛው ዝናብ ዘመን ጀማሮች አሁን በዚህ ጊዜ በጀመሩበት ጉልበት አልተገኙም፡፡ ከርስትና ዱላ ቅብብሎሽ አማላቸው አልታጠም፡፡ እግዚአብሔር በአንድ ትወልድ አዲስና ትኩስ ነገር ይጀምራል እንጂ ያደረ እንጀራ አያሞቅም - አሮጌ ቅባት አይቀባም፡፡

በእርግጥ ብዙ ወንድሞች ራሳቸውን ታላቅ አድርገው የቆጠሩ ወገኖች ይሄ ያሉበት ዘመን በ1950ዎቹና ስድሳዎቹ የነበሩት ዘመናት ይመሳላቸዋል፡፡ ያንንም ዘመን ወደ አሁን ጊዜ እየሳቡት ነው ብዙ ዘመን ጎታች - ዘመን ሳቢ ወንድሞች፡፡ የከሰረ ባለ ሱቅ የሚሸጠው ሸቀጥ ሳይኖረው ሱቁን መክፈቱ መገዱ ነውን?... አንድ ነገር ልንቀበል ተገድደናል፡፡ ከዚያ ‹‹ከተወደደው›› ከስድስተኛው ዘመን ወጥተን ወደ ሰባተኛው ዘመን - ዘመነ ሎዶቅያ ገብተናል፡፡ ብዙዎቻችንም አንወቀው እንጂ ገብተንበታል፡፡ እየኖርንበትም ነው፡፡ የኋለኛው ዝናብ ዘንቦ ያባራበትና ሰሜኑ በጠራበት ጊዜ ላይ ነን፡፡ አሁን ያለው ወይም አለ የሚለው ዝናብ ካለፈው ጋር ስስተያይ የደከመ ነው፤ በአብዛኛውም ሐሰተኛውና የሰው ዝናብ (እንቅስቃሴ) ነው፡ ብዙዎች የእንቅስቃሴና የሪቫይቫል ቋንጣ ነው ያላቸው፡፡ ከአሕያይቱ ራስና ከርግቢቱ ኩስ በቀር የቀረ ነገር አልነበረም - በነቢያት ልጆች አገልግሎት ዘመን፡፡ አሁንም ሁኔታዎች ከዚህ የተለዩ አይደሉም፡፡ የሪቫይቫል አጽምና ኩስ እየተሸጠና እየተሸመተ ነው፡ እግዚአብሔር ባደከመውና በጨረሰው ሪቫይቫል ወስጥ ሁላችንም አለን፡፡

7.ዘመነ ሎዶቅያ

(ራእ.3÷13-22)፡፡ ይሄ የቤተ ክርስቲያን ‹‹ዕድገት›› እና ሜጨረሻ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ከጀመረችበት ጊዜ አንሥቶ የተጓዘችው እስከ ሎዶቅያ እንደሆነ በግልጽ እናያለን፡፡ ቤተ ክርስቲያን በሎዶቅያ ሜጨረስ ጥሪዋ ነው፡ በቃ፤ የቤተ ክርስቲያን ዕድል ፈንታ ሎዶቅያነት ነው፡ ከዚህም ወጭ ልትሆን አትችልም፡፡ ሎዶቅያ በራድም ትኩስም አይደለችም፡ በወጭ ተሸልሟለች እርግጥ ነው፡ ይሄም የነፍስ አገልግሎት ከማሆን አላለፈም፡ ወጪው ሰው - ‹‹ሁሉም ነገር አለኝ›› ብሏል፡፡ አንዳ እንደሚያስፈልጋት ቤተ ክርስቲያን ብላለች፡፡ ልመናዋ - ጥያቄዋ ሁሉ አፋዊ ነው፡ ትወልዱ ልቡን አርቆ በአፉ ያሜካል፡፡ አምልኮ ሁሉ ወጪ ነው፡ ሁሉም በወጭ እየሞቀ ነው፡ የቤተ ክርስቲያን የወጭ መቀት ከወስጧ ቅዝቃዜ ጋር ሲደመር ለብታን ፈጥሮባታል፡፡ ቤተ ክርስቲያ ከዚህ ጊዜ ከመንፈሳዊወም ከዓለማዊወም አይደለችም፡ እንግዳ ፍጥረት እየሆነች ነው፡ በወስጧ ያሉት ድል ነሺዎችም ይበልጥ እያበሰበሷት ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም ወደ አለመባስበስና አለመጥፋት - ወደ መንግሥቱ ያመጧታልና!

በዚህ ዘመን ያለችወን ቤተ ክርስቲያን ዘርፈ ብዙ ችግር በዚህ አጭር ጽሑፍ ዘርዝሮ ሜጨረስ አይሞክርም፡ በዚህ ሁሉ ግን አንድ ነገር እንድታዩ ተሞክሯል፡፡ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን - እያንዳዱ ዘመን አንዱ አንዱን እያደከመና እየጨረሰ የመጣበትን የእግዚአብሔር አሠራር ሞት ይበቃል፡፡ ሁሉም ደግሞ በሎዶቅያ ሚለቃቸው ይደንቃል፡፡ ሁኖም ሎዶቅያን በተራው የሜጨርስ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አለመሆኑ ሚወቅ ይበልጥ ጠቃሚ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ዘመን በኋላ ሌላ ዘመንም ዕድልም የላትም፡ ሎዶቅያን ወይ አሁን በዚህ ጊዜ ያለችወን ቤተ ክርስቲያንን የሚያስረጀወ፣ የሜፈጽመው፣ የሜጨርሰውና የሚሸረው ሌላ የተነ ቃቃ፣ ከቁስሉ የተፈወሰ፣ የታደሰ... ሚኒስትሪ ወይም ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን መንግሥቱ ነው፡ ለመለጠፍ ለመላቱ ሁሉን እያስረጀ ያለው እርሱ ነው በዚህ ዘመን፡፡ ለዚህ ነው መጽሀፍ፡ - ‹‹ከዚህ በኋላም (ከአብያተ ክርስቲያናት በተለይም ከሎዶቅያ በኋላም) አየሁ፣ እነሆም በሰሚይ የተከፈተ ደጅ፣ እንደ መላከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፡ - ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገወን ነገር አሳይሃለሁ አለ›› (ራእ.4÷1)የሚል፡፡

ከአብያተ ክርስቲያናት በተለይም ከሎዶቅያ በኋላ ዙፋን ነው፡ መንግሥት ነው፡ ቤተ ክርስቲያን በመንግሥቱ የምታልቅበትና የምትፈጽምበት (የምትሞላበት) ጊዜ የደረሰ መሆኑን ማንም አሁን ባለበት ወስብስብ ችግርና ድካም ያስተወለው፡ ከዚህ በኋላ የማንም ልብ፣ መንፈስና እርምጃ አሁን ካለችው ቤተ ክርስቲያን ጋር አይሆንም፡፡ ሁሉም ልቡ እየወደቀበት ነው፡ ሁሉም በአጥቢያው ላይ ተስፋ እየቆረጠ ነው፡ አገልግሎቱ አድክሞታል፡፡ አገልግሎቱ ራሱ ደክሟል፡፡ ፕሮግራሙ ሁሉ የግዴታ ነው፡ በብዙዎች ሕይወት የሚቀሉ ኃይል ዝሏል፡፡ የትንሣኤው ኃይል ታሪክ ሁኗል፡፡ ወንጌል ዛሬ ዛሬ በዓለም በየወቅቱ

ከሚከሰቱ ትኩስ ወሬዎች ያነሰ አድማጩና ኃይል ነው ያለው፡ ሁሉም የክርስትናውን መሻፈኛ (ማሐረቡን) ፊቱ ላይ ጥሎ እያንቀላፉና እያንኮራፉ ይገኛሉ፡፡

አንዳንዶች፡ - ‹‹እኛስ ሕያው ነን›› የሚሉና በዚህ ጸሐፊ ላይ የሚቆጡ መልእክቱም የተጋነነ የሚሰላቸው ቢኖሩ በሰነት ጉልበት - በ‹‹መንፈሳዊ›› ጉርምስና ኖረው ወገባቸውን በራሳቸው የሚታጠቁበት ጊዜ ሊሆንላቸው ይችላል ካልዋሹ (ዮሐ.21÷18)፡፡ ሆኖም እነርሱም ከዘመነ ሎዶቅያነት አይወጡምና ያሉበት ጉብዝና የለብታ ሌላኛው ገጽታ ነው፡ እኔ አንድ ነገር አይቻለሁ፤ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሚጀቱንና ሚለቁን፡፡ ሎዶቅያነት በሁሉም ቤት ሞኖሩን፡፡ የዚህም ጊዜ መዘጋት የመንግሥቱ ጠዋት - የግዛቱ ቀን - የልጆቹ መለጥ - የአባትነቱ መላት መሆኑን አይቻለሁ - የምሥራች!

አንድ ነገር አወቃለሁ፤ እስራኤላውያን በሃይማኖታቸው፤ በሥርዓታቸውና በወጋቸው ጉልበት ምክንያት ወደ ጠንካራ ፈሪሳውያንነትና ግብዝነት ላይ በደረሱበት በሕጉ ምሽትና እኩለ ሌሊት የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ እንደ ሞኖና የጸጋ ዘመን እንዳመጣ እንዲሁ በሰባተኛው ዘመን - በዘመነ ሎዶቅያ ሚለቅ ሰባተኛውን ቀን - ዘመነ ዕረፍትን - መንግሥቱን ያመጣል ዘንድ የእግዚአብሔር ልጆች በቤተ ክርስቲያን ምሽት - እኩለ ሌሊት ላይ ይሰቀላሉ፡፡ ትምህርታቸው፤ አገልግሎታቸው፤ ስሞቸው፤ ክብራቸው ይሰቀላል፡፡ በእነዚህ መሳቀል ግን የአብያተ ክርስቲያናት ፀሐይና ጨረቃ ይጨልሟሉ፡፡ ክርስቶስ ሲሰቀል እርሱን የሰቀሉበት የፀሐይ ብርሃን ጨለመ፡ መቃብሮች ተከፈቱ፡፡ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ለሁለት ተተረተረ፡፡ ዛሬም ብዙዎች የእግዚአብሔርን ልጆች የሚቃወሟትና የሚያወግዙበትና የሚሰቅሉበት ሌላ ትምህርት፤ ሚዳት፤ ብርሃን... ቢኖራቸውም ይጨልማል፡፡ የሁሉ ሰሚይና ምድር ይናወጣል፡፡ የአንዱ ሞት ሁሉን ገድሎ እንዳስነሣ ሞቱን ለመሻከም በኩራት የሆኑ ልጆች በቤተ ክርስቲያን ባ መንፈሳዊ ሕፃናት ሲዋረዱ - ሲሰቀሉ የሚሠበት ትንሣኤ በፍጥረት ሁሉ ላይ ያመጣል፡፡ እስከ አሁን እግዚአብሔር ዘመንን የለወጠው በተሰቀለ አንድ ሰው ወይም በአንድ ቤተሰብ ነው፡፡

በእነዚህ ጥቂቶች - የተዋሐደ አካል ምሳሌ መለጥ በቤተ ክርስቲያን ያለው ሁሉ ወደ ክብር ይነሣል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ያሉ የደረቁ አጥንት ናቸው፡ ወደ ታላቅ ሠራዊትነት የሚሠት፡፡ የደረቁ አጥንቶች በመሳሣትና ወደ ርስታቸው በመግባት ከጨረሱ በእርግጥ መድረቃቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበረ፡፡ የሕዝቅኤል ትንቢት ምዕራፍ ሰላሳ ሰባት ፍጥረታዊ ተፈጻሚቱ በፍጥረታዊ እስራኤል ላይ ቢሆንም መንፈሳዊ ተፈጻሚቱ ግን በእያንዳንዱ ብልትና በእግዚአብሔር ማነበር ሁሉ ነው፡ አጥንቶች አንድ (Corporate) ሆነው አንድ አካል (ሠራዊት) ሆነው የተነሠት ከደረቁ በኋላ እንደ ሆነ ለሁላችሁም ግልጽ ይሁን፡፡ ይህ የእግዚአብሔር አሠራር ነው፡

ታድያ ለምንድር ነው ዛሬ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደረቁ ፈጽመው እንደ ደረቁ ነቢዩም እንደ ተነገረው ሲናገር የሚቆጩት? ‹‹አልደረቅንም›› ነው? ሐሰት ነው፡ የእያንዳንዳችን ሕይወት ምስክር ይሁን፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ሎዶቅያ፡ - ‹‹ሀብታም ነኝና ባለ ጤጋ ሆኜ አለሁ አንድም ሰንኳ አያስፈልገኝም›› በምትለው ሁሉ ስለ ተገኘች ነው፡ - ‹‹አልደረቅሁ›› የምትለው? ወገኖች ሆይ፤ እግዚአብሔርን በማሳልፋ፤ በጽድቅ ኑሮ፤ በወንጌል ምሳሌነት፤ ለዓለም ብርሃንና ጨው በመሆን... በኩል አልደረቅንም ትላላችሁ? በእነዚህ ነገሮች ያልደረቀና ቀኙ ያልሰለለ ቢኖር ለምን ተነሥቶ አያሳይም? ስለ ምንስ ለሌሎች ምሳሌና ምስክር አልሆነም? አሁን ካለበት ሁኔታ በመሳት ለወጥ፤ ሪቫይቫል፤ ጉብኝት... የሚይፈልግ ካለ በእርግጥም አልደረቀም፡

ማን ነው ከራእይ ምዕራፍ አራት በኋላ ቤተ ክርስቲያንን ፈልጎ የሚገኝ? ይሁን እንጂ ከምዕራፍ አራት በፊት የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ሎዶቅያ ከሆነች ወይም ቤተ ክርስቲያን ሞላዋ ወደ ሎዶቅያነት ከወረደች ማንም ወደ መንግሥቱ ይገባ ዘንድ - ወደ እግዚአብሔር ሰማያት ያርግ ዘንድ ከሎዶቅያነት ወቺ ምን ዕድል አለው? በእግዚአብሔር ቅድመ እወቀትና ፕሮግራም ሎዶቅያነት (መንፈሳዊ ድርቀት) ወደ መንግሥቱ የሚጥቅ መንገድ ተደርጓል፡፡ ድካም ከብርታት፤ ሞት ከሕይወት፤ ጨለማ ከብርሃን፤ ነፍስ ከመንፈስ፤ አሮጌው ከአዲሱ... በፊት ተገኝቷል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሜጨረሻ ሎዶቅያ (ለብታ) መሆን ወደ መንግሥቱ እንድትገባ ነው - የምሥራች! ቤተ ክርስቲያን በሎዶቅያ መገኘቷ አያሳዝንም በእግዚአብሔር ፕሮግራም ከተገኘን፡፡

ሎዶቅያነት ከእንግዲህ በመንግሥቱ ወንጌል፤ ሕይወት፤ ክብርና ሞርሐ ብቻ የሚለወጥ ነው፡ ከእርሷ በኋላ ሌላ የቤተ ክርስቲያን ዘመን አልደረቀም፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው ዮሐንስ አብያተ ክርስቲያናትን ያየበት ከበብ ምንም በመንፈስ ሁኖ ቢሆንም በፊጠም ደሴት ሁኖ ነው፡ ምዕራፍ አራትን (Kingdom Dimension) ያየው በሌላ ከፍታ፤ ‹‹ሪሊም›› ጥሪ ሁኖ ነው፡ ለዚህ ነው፡ - ‹‹... ወደዚህ ውጣና›› የተባለውን ትእዛዝ የተቀበለው፡ ይሄ በተከፈተው ደጅ ነው!

የመንግሥቱን ሞከንና ልክ መላት፤ ሕይወትና ክብር፤ መለጥና ሥልጣን... አሁን ባላችሁበት የቤተ ክርስቲያን ስም፤ ዲኖሜሽን፤ ትምህርት፤ ብርሃን (ሚዳት)፤ ልምምድ፤ ስጦታ... ሆናችሁ ልታዩትና ልትገቡበት በጭራሽ አትችሉም፡ እነዚህ ሁሉ ከሰሚያታችሁና ከምድራችሁ ተናወጡው እንደ ቃርሚያ መገፍ አለባቸው፡ ሰሚያታችሁና ምድራችሁ በመንግሥቱ በሚመጣው መዳት

ንጹሐን መሆን ይገባቸዋል፡፡ የመጀመሪያወም (የደኅንነት ልምምድ) ሆነ ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን (የበዓለ ኀምሣ ልምምድ)ትምህርቶች መኖር አልተገባቸውም፡፡ እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ለበለጠው ከብሩና መረዳቱ ይህንን አድርጓል፡፡ ከክርስቶስ ጋር የኖሩት የነገሥት ስለ ኢየሱስ ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጠባቸው ናቸው (ራእ.20÷4)፡፡ ማንም በቤተ ክርስቲያን ዘመን ራሱን - እኔነቱን His false Identity – the mistaken Identity አላጣም፡፡ አሁን በዚህ ዘመን በሆነው እውነት ግን እየተሰየፉ ያሉ ይነግሣሉ፡፡ ራሳቸውን አጥተዋልና ሌላ ራስ ሆነላቸው፤ እርሱም የሕይወት ራስ የሆነው ክርስቶስ ነው፡፡ ሰይፍ (እውነት) አራጁን በእርግጥ ያገኘዋል፡፡ እውነት - ሕያው እውነት ልጆችን ወደሚይወዱት ነገር ግን ወደ አብ ፈቃድ ይወስዳቸዋል፡፡

እንደ እግዚአብሔር ቅድመ እወቀትና ፕላን መሠረት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ለእኛ ከወሰነው ልክ መወደቃችን ያለ ምንም ዋጋ ባይሆንም ትልቁ ችግራችን መወደቃችንን አለማወቃችን ነው፡፡ ግና መወደቅ ስንል ምን ማለታችን ይሆን? እንዲህ ነው፡- እግዚአብሔር በዘሙ ካስቀመጠውና ከሰፈረው የሕይወትና የአካሄድ ልክ መዮደል ነው መወደቅ፡፡ የእግዚአብሔርን ቅርጽና እግዚአብሔርን መምሰል መላካት አልቻልንም፡፡

ከአሥር ዓመት ወደዚህ በሀገራችን ብዙ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ተከፍተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ይበልጡኑ በገንዘብና በማቴሪያል ከወደ ምዕራቡ ዓለም ተደራጅተው የማጡት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትና ከዚያ ከምዕራቡ ዓለም በሚደረግላቸው ዕርዳታ የተከፈቱ አብያተ ክርስቲያናት ከነባሮቹ አብያተ ክርስቲያናት በዲሲፕሊን የተባረሩት፣ በተለያየ ምክንያት ያኮረፉትን፣ ከማልገላቸው በፊት የአገልግሎት ጥማት የነበራቸውን... ሰበሰቡ እንጂ አዲስ ይዘወት የማጡ የለውጥ - የተሐድሶ ቅመም ምንድር ነው? የአምልኮአቸው ዘየ (styel) ከማላወጡ በቀር አዲስ ማጨዎቹ ከነባሮቹ ጋር በአንድ ምዕራፍ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ናቸው፡፡

ብዙዎች የሚይታዘዙ፣ እሺ የሚይል ትወልድ፣ በገዛ መንገዱ የሚሄድ፣ ኩሩ ወገን... አፈሩ - አፈራን፡፡ በላያችን ላይ ሰውን ለመሾምና ሽማግሌዎችን በመንፈስ ምሪት ሳይሆን በሰው መንገድ ለመምረጥ ራሳችንን ብንሸጥም የሾምናቸውን ለማክበር ግን አልታደልንም፡፡ ብዙ ነገር በቤተ ክርስቲያን ወስጥ የተወሳሰበና ጫፉ የጠፋ ቱባ ሁኗል፡፡ በዚህ ጊዜ ሥጋ በትክክል መንገሣን በመድረክ ላይ ራሱን አሳይቷል፡፡ በፑልፒታቸው አጠገብ ብዙዎች ሽማዝ ሰብስበዋል - ሊዋጣላቸው፡፡ ወንድሞቻውን ጎትተው ከጉባኤ አወጥተዋል፡፡ ተካስሰው ፍርድ ቤት ተገኝተዋል፡፡ አንገት ለአንገት ተናንቀዋል፡፡ አሳፋሪ ሥራ ተሠርቷል በማኅበራችን፡፡ አወግዘናል፡፡ ወረቀት በትነናል በሌላው ላይ፡፡ የሚረ ጥላቻ ተጣልተናል፡፡ ለመገደል የዛተም አለ፡፡... ወድቀት ከዚህ የበለጠ ምን ሊሆን ይችላል? ቤተ ክርስቲያን ከዓለም በምን ትለያለች? ‹‹በአምልኮ ሚልክ›› ካላችሁ አሁን ያለችበትን አይታችኋል፡፡ ፍቅራችን እስካልተጣላነው - ያሳዝናል!

አሁን ያለችው ቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ አቋም እንጂ በሕይወት - በአካሄድ የተመሳከረላት የእግዚአብሔር ምሳሌ (Pattern) የላትም የእግዚአብሔር ልጅ - የባሕሪዩ ምሳሌና ነጸብራቅ በእኛ ገና ተስሎ አልታየም፡፡ ወድቀታችን በአብዛኛው ያረፈው እዚህ ላይ ነው፡፡

ዛሬ ዓለም ለለባት ቀወስ ለምሳሌ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ ወደ ቤተ ክርስቲያም መምጣትና መፍትሄ ማግኘት ትችላለችን? ቤተ ክርስቲያን ‹‹የብሔራዊ (የኤድስ) ኮሚቴ አባል›› መሆኗ ያስማሳግናታል ወይስ ያሳፍራታል? ቤተ ክርስቲያን ‹‹የብሔራዊ ኮሚቴ አባል›› መሆኗ እንደ መንግሥት ‹‹የባሕሪይ ለውጥ›› ልትሰብክ ነው ወይስ ከፈነ ብልት (ኮንዶም) ልታድል ነው? መንግሥት እነዚህን ሚድረጉ ትክክል ሁኖ ከዚህም በሚልፍ ዕድሜ ሚራዘሚየ መድኃኒቶችን ያለ ቀረጥ እያስገባ ይገኛል፡፡ ቢሆንለት በሽታውን እስከ ማጥፋት ይደክሚል፡፡ በቃ፤ ተልዕኮው ነው፡፡ በዓለም ላይ ለሚፈጠር ማንኛውም ዓይነት ቀወስ ቤተ ክርስቲያን ዓለማዊ መንግሥት በሚይድበት ፕሮግራም በመሄድ አባል ለመሆን መፍቀዷና እግዚአብሔር በተፈጠረው ቀወስ የሚልገወን ዓላማና ግብ አለማወቅ ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን በብዙ መንገድ እንደ ከሰረች በግልጽ ይታያል፡፡ የ‹‹ብሔራዊው ኮሚቴ›› በኤድስ ላይ ያለው አቋም በራሱ ልክ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህንን በዓለም እንድትኖር ከተፈጠረችበት ዓላማ ጋር እንዴት ትጋራዋለች?... በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ስለ ኤድስ ሚልስ የላትም፡፡ የራስዋም ችግር ነውና! ዝሙት የቤተ ክርስቲያን ችግር ከሆነ ወሎ አድሯል፡፡ የኅብረተሰቡ ችግር የእርሷም ችግር ነው፡፡ ... ቤተ ክርስቲያን አልወደቀችም? ‹‹ቤተ ክርስቲያን››ስ ልትባል ይገባታል? ‹‹... ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህሚል - You are supposed to be alive, but (in reality) you ar dead, Amp.የተባለው ሰርዴስነት በእኛም ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በሕይወት፣ በማንነት፣ በኑሮ፣ በአካሄድ፣ እግዚአብሔርን በማሳል... ምሳሌ በመሆን ኅብረተሰቡን ምን አስተማርነው? ሰው ስለ ዘመረ፣ ጸሎት ቤተ ስለ ሄደ፣ ሃይማኖት ስለ ቀየረ ብቻ... እንዴት ለዓለም ምስክር ሊሆን ይችላል?... መወደቃችን እርግጠኛ ነው፡፡ ሕይወትን ኖረንና ተርፎን ሞክፈል አልቻልንም፡፡ የሞትም ሆነ የሕይወት ሽታ መሆን አልቻልንም፡፡ ማንም

ለምንም እስከሚፈልገን፡፡ በመጽሐፍ ያሉትን ነቢያትንና አባቶችን ማለን በሕይወት ዓለምን የኮነነው ምን ጊዜ ነው? ሐዋርያዊ ‹‹ታፔላ›› ሳይሆን ሐዋርያዊ ሕይወታችን የት አለ? መነግሥት ከዚህች ዓይነቱ ቤተ ክርስቲያን አንዳች ይጠበቅ ዘንድ ሞኝ አይሆንም፡ አይገባውምም፡

ወገኖች ሆይ፣ በሂደት የሚፈተን ቢሆንም ዛሬ መነግሥታችን ተሐድሶን እየሰበከ አይደለምን? ኢሕአዴግ፡- ‹‹እንደ ድርጅት እየታደስኩ ነው›› እያለ መሆኑን ሰምተናል፡፡ ይሄ የመነግሥታችን ራእይ ነው፡ ማን ያውቃል፤ የእነርሱ ተሐድሶ እነርሱ ለሕዝባቸው ካላቸው ቅንነት ሊሆን ቢችል? አባባላቸውንም በትዕግሥት ሞት አለብን፡፡ የሚሳዝነው ግን ቤተ ክርስቲያን ለራስዋ እንደ ድርጅትም ሆነ ለምትመራው ምስኪን ሕዝብ የመታደስ ራእይ እንዳለት ምንም አላሳየችም - የሁለቱ የተሐድሶ ጎዳና ለየቅል ቢሆንም፡ ገና ‹‹ወድቀናል›› ሌላው ‹‹አልወደቅን›› እየተከራከሩ ነውና!

ክርስቶስ በሥጋው ወራት በዘመኑ እንደ ነበሩት መቃባውያን (የእስራኤል የአርነት ታጋዮች) የፖለቲካ ችግር አልነበረበትም፡ የእነርሱን አካሄድና ሥርዓት ሳይሆን የእስራኤልን ሃይማኖታዊ ድንቁርናን ሲፋለን እናገኘዋለን ክርስቶስን፡፡ ... የዘመናችን ችግር የፖለቲካ ችግር አይደለም ቢሆን እንኳ የቤተ ክርስቲያን ችግር ነፀብራቅ ነው፡ የቤተ ክርስቲያን - የመንፈሳዊ ሕይወት ችግር ነው የዘመናችን ችግር በአጥቢያዎቻችን ጉባኤዎች፣ በኮንፈረንስ፣ በክሩሴድ... ያፈሰናቸው ‹‹ነፍሳት›› በበር ገብተው ስለ ምን በጓሮ ይወጣሉ? ሕይወትን (ክርስቶስን) እንደ ሰበክናቸው እንዲሁ ሕይወታችንን ስሚያገኙት ነው፡ በኃጢኣት እስራት፣ በዲያቢሎስ ፈተና፣ በሥጋ መሻት ላይ ድልን የሚሰጥ ሕይወት - የሚኖሩበት እምነት አናካፍላቸውም፡ ስለዚህ እኛ ካለንበት የሃይማኖት ግብዝነት በማምለጥ ወደ ቀድሞው ሕይወታቸው ይመላሳሉ፡፡ ከእኛ ጋር የቀሩትም ቢሆኑ በግብዝነታችን ከመሳብ በቀር እያዬአቸውን ልናስቀር አልቻልንም፡ እኛ በሃይማኖት፣ በሥርዓትና በወግ እነርሱ ግን በዓለማዊነት ታስረናል፡፡ ለሁላችንም እግዚአብሔር ያስፈልገናል፡፡ እኔ እላችኋለሁ፤ እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለዓለም ያስፈልጋቸዋል - በእኩልነት፡፡

ዛሬ የአብያተ ክርስቲያናት ሚዖች ልጆቻቸው የት ነው ያሉት? ክርስትናን ሊያወርሷቸው ቢሞክሩም አልቻሉም፡ እነዚህ ልጆች በሰንበት ትምህርት ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ተነገራቸው እንጂ ከወላጆቻቸው ሕይወትን ሞት - አካሄድን መሳፈል አልቻሉም፡ ክርስትና ይወረስ ይሆናል፡፡ ሕይወት - ደኅንነት - እምነት... ግን አይወረስም፡ ክርስትና በዚህ ዘመን ድርጅት - ሃይማኖት እንጂ ሕይወት መሆኑ ቀርቷል፡፡ ብዙዎች ልጆቻቸው እንዲድኑላቸው ኳየር - አገልጋይ አድርገዋቸዋል እነርሱም ሆነ ወላቸዋል፡፡ ወላጆች ‹‹የኑሮአቸውን ፍሬ›› ከማየት ይልቅ ልጆቻቸውን ወደ አገልግሎት ጋብዘዋል (ዕብ.13÷7)፡፡ በወጩ ግን ከስረዋል፡፡ በጥንት የአርቶዶክስ ተዋሕዶን ‹‹እምነት›› ወረስን፡፡ አሁንም ኢቫንጀሊካሎችና ጰንጠቆስጠዎች ያለ እግዚአብሔር ጥሪ እምነትንና ደኅንነትን ለልጆቻቸው ሊያወርሱ ይሻሉ፡፡ ሕይወት የራቀው ወገን ልጁን በሃይማኖት - በግብረገብም ከመኮትኮት በቀር ዕድል የለውም፡ ሰው ሀሉ ከዓመጽና ከስንፍና ጋር ተፈጥሮአልና በግብረገብ ያደገው ልጅ ዓመፃውንና ስንፍናውን የሚልጥበት ደረጃ ላይ ሲደርስ የወላጅ ሃይማኖት ይፈነዳል፡፡ ግብረ ገብም ይፈሳል፡፡ ልጁም ይጠፉል፡፡

አገልግሎት ሕይወት የሚለጥበት ወይስ ሕይወት ሟቋያ? ቤተ ክርስቲያን ‹‹ያሙትን ለማጽናት›› በሚል ጥናታዊ ዘዴ ለብዙዎች አገልግሎት ትደለድላለች፡፡ አገልግሎት ከሕይወት መኮረፍረፍ መሆኑ ቀርቶ ሰው መጎጥ ተደርጓል፡፡ የቤተ ክርስቲያን በዚህ ጊዜ ዓይነተኛው ትኩረት የነጠረ - የወጣ - የተለየ... ሕይወት መሆኑ ሳይሆን የሰው ብዛትና በዚያ ሳቢያ የሚመጣው ገንዘብ ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብን የምትይዝበት መሳተንግዶ (ኢንተርቴይንመንት›› ለእግዚአብሔር ሕይወት ከምትሰጠው ስፍራ የበለጠ ነው፡ የቤተ ክርስቲያን ጥንካሬና ዕድገት በአጥቢያዎች ብዛት፣ በሕዝብ ቁጥር፣ በአገልጋዮች ብዛት ተደርጎ የተወሰደበት ቀልደኛ ዘመን ላይ ነን፡፡

የክርስቶስ ስብከትና ትምህርት ዕለት ዕለት የሚድለው ነበረ - የሚያሲዘው ነበረ፡፡ ዛሬ ግን ‹‹አገልግሎታችን›› በሰው ላይ እንድንሰፍፍ የሚያደርግ ሁኗል፡፡ የሰውን ቁስል ዳር ዳር የሚከከው ስብከታችን የነቢይንና የሐዋርያን ጽዋ እንድንጠጣ አልፈቀደልንም፡ ዛሬ አንድ ነገር ስንል - ወደ ፑልፒታችን ስንወጣ ይጨበጨበልናል፡፡ ስሜትን በሁሉም ሰው አፍ ይዘሙልል፡፡ እንደ እስጢፋኖስ በራሳችን ላይ ድንጋይ የሚያወረወር፣ የሰሙትን ጥርት የሚያስነክስ፣ የአድማጮቻችንን ጆሮ የሚሳክክና የሚያደፍን ስብከት፣ ትግሣፅ፣ እውነት ስለምንጠፉብን?... ከዚህ ሁሉ ጋር የዚያች የጋለሞታ ዋጋ - አንዲት እንጀራ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በዝቶ መታየቱ አሳፋሪ ነው፡ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ስብከት እንጂ እግዚአብሔር በጊዜው የወደደውን አልሆነም፡ መጋቢውና ምዕመኑ በሁሉ ነገር እኩል የሆነበት ዘመን ላይ ነን፡፡ እንደ ተፈቱ ‹‹እልፍ ያለና እልፍ የሌለው›› አልተገኝም፡ ሁሉም በሰንበት የሚሸሽ ሁኗል የሚያርፍ እልፍ ቀርቶ፡፡ በከረምትም ለሟሸና ለሚሞጥ የተዘጋጁ አልታጠም፡ የሕይወት ከረምት በብዙዎች ሰሚና ምድር ላይ ታይቷል፡፡ በዚህ ጊዜ አያሌዎች ይሸሹ ዘንድ እንጂ ዘራቸውን መጣል አልሆነላቸውም፡ በከረምት ይታረሳል - ዘር ይጣላል፡፡ የስንዴው ዘር የወደቀውና የሞተው በትወልዱ ከረምት አልነበረምን? በከረምት ያልዘሩ ነገር ግን የሸሹ የሳር ወራት ያልፋቸዋል፡፡

በመጽሐፍ መሉ አያሌ ተሐድሶዎችን ልንቆጥር እንችላለን፡፡ ግን ከሁሉም በላይ የመነፍንትንና የነገሥታትን ዘመን ተሐድሶዎችን ማንሣት ይቻላል፡፡ አንድ የተቀባ መነፍን ከመሣፉ በፊት ያለውን የሕዝብን ሕይወት ሥዕት ይቻላል፡፡ ፈጽሞ የተበዘበዘ፣ የተሟረከ፣ የደከመና የሜጭኸ ሕዝብ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ለዘሙሉ አንድ መነፍን (እንደ ዘመናችን ‹‹ሪቫይቫሊስት›› በመነሣት ለሃያ - ለአርባ… ዓመት ያሳርፋቸው ነበር፡፡ በነገሥታትም ዘመን እስራኤላውያንና ብዙ ርቀው ከደከመፁት፣ ከሳቱበት፣ ከወደቁበት የሚመልሳቸው ንጉሥ ይቀባ ነበር፡፡ እርሱም አምልኮአቸውን፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውንና መቅደሳቸውን… በሚደስ መንፈሳዊ ተሐድሶን ያመጣ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የትኛው መነፍን ወይም ንጉሥ የተነሣበትን ዘመን ሥዕት አልመጣም፡፡ ተሐድዎች በተደረጉበት ዘመንና ታሪክ ሁሉ ይህንን ነው የምናስተወለው፡፡ ያለ መንፈሳዊ ድካም፣ ሕይወት ሳይበሰብስ፣ ክርስትና ሳይግምሚ… ተሐድሶ የተነሣበት ዘመን የለም አልተጻፈምም፡፡

ዛሬም ለተሐድሶ ብቻ ያልሆነ ነገር ግን ለመታደስ ዘመን (ሥራ.3÷21) እንድንቃትት የሚያደርግ ፍጹም መድከም፣ ሚለቅና መበስበስ ተወስኗል፡፡ ወገኖች ሆይ፣ አትድከሙ፤ መታደስ ከተፈለገ የዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በባሰና በከፋ መድከም፣ መዛል፣ ተስፋ መቁረጥ… አለባት፡፡ ማንም የትኛው መንፈሳዊ ኅበዝ አሁን ያላትን ‹‹ጥቂት ነገር›› እንኳ ያቆይላት ዘንድ አይችልም፡፡ በመከከ የተሰሙ፣ ሥጋቸው የወፈረ፣ መልካቸው ያሚረ ሰባት ላሞች በደከመ፣ ሥጋቸው በከሳ በመልከ ክፉ ላሞች የተበሉና የተዋጡ አይደለምን? የዳበሩ እሸቶች በደረቁና በሰለቱ በምሥራቅም ነፋስ በተመቱ እሸቶች አልተዋጡምን?(ዘፍ.41ን ይመልከቱ)፡፡የዘመናችን ከፋትና ድካም፣ ድርቀትና ከፋት የነበረውን መንፈሳዊ ስባት አልዋጠም ትላላችሁ? ሃሌ ሉያ! አባት ሆይ፣ ለሚለጠው ዓላማህና መነግሥትህ እያደረግህ ያለውን ጨምረህ አድርግ - ይሁን!

ሰባቱ ስፍረ ዘመናትና ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንዳለቁ እስካሁን ያየነው ነው፡፡ የመጀመሪያወም በሚያልቅበት ዘመን እጅግ የተዋረደ - የተናቀ - የሚፈለግ - የሚታፈርበት ሆኖ እንደ ሆነ የተገለጠ ነው፡ ለምሳሌ ዘመነ መነፍንት ሶምሶን በፈረደበት ሃያ ዓመት አለቀ፡፡ ሳሙኤል ተነሥቶ እስከ ፈረደና የነገሥታት ዘመን እስከ ጀሚረ ድረስ የእስራኤላውያን ሕይወት የሚዘገን ነበር፡፡ (እባክዎት የመጽሐፈ መነፍንትን የሜጩሻ ምዕራፎች ይመልከቱ)፡፡ የነገሥታትም ዘመን በሕዝቡና በንጉሣቸው ምርኮ ሲያከትም ሕይወታቸው የሚታፈርበት ነበር፡፡… ያለ ድካም የተፈጸመ ዘመን የለምና እኛም ስላለንበት ዘመን ድካም ሳያስጨቀን እንደ ልጆች በጨዋው የሚመጣውን ብርሃን - በሌሊቱ የሚመጣውን ቀን እናስተወል፡፡ ማንም ባለበት ሁኔታ ወደ ሌላ ዘመን አይሻገርም፡፡

ሁሉም በርትቶ ባለበት ዘመን ሪቫይቫል መጥቶም አያወቅም፡፡ ሪቫይቫል የብዙዎች፡- ‹‹አስበን›› የሚሉት ጨቨት ወጩት ነው፡፡ የዛሬው የቤተክርስቲያን በሚያሳፍርና አንገት በሚያስደፋ ሁኔታ መድከም ለሌላና በታሪክ እስከ ዛሬ ላይታይና ምንም ነገር ለሚይመነለው ታላቅና ዋነኛ መታደስ (Restitution) እንደሆነ በሁላችሁ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ ይህንንም ስናስብ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ደከሟ፣ ዝላ፣ ተስፋ ቆርጣ፣ ደርቃ፣ ቀኝዋ ሰልሎ በታላቅ ሽለቆ ብትገኝ የልባችን ሳሎን በደስታ ሲሰክር በሆነለት መንፈሳዊነት ነው፡፡ የሚመጣው - የሚለጠው የጌታ ቀን የዛሬወን ክብር ያስረጀዋል፤ በልባችንም ተስፋ ያሳጣዋል፡፡ ዛሬ መንፈሳዊነት በልባችን ዋጋ ሟጡ - አቅሙ መዘለፍለፉና ልብ የሚጣልበት መሆኑ ያለ ዋጋ አይደለመና እሰየሁ!

የሌሊቱን እርዝመት እንደሚያወቅና እንደሚገር ጉበኛ በዚህ ሌሊት ላይ ቁሜ አንድ ነገር በቅዱስ ድፍረት እንደ ቃሉ እናገራለሁ፡- ጊዜው (ምንም በድካም - በድርቀት - በመበስበስ… ቢሆን) የመከር ጊዜ ነው፡፡ የመወደቃችንና መንፈሳዊ አቅም የሟጣታችን ወጩ ይሄ ነው - ተደሰቱ! አበባ ለፍሬ ይረግፋል፡፡ አበባ ባለበት ፍሬ የለም፡፡ አበባ የፍሬ አብሳሪ ነው፡፡ የበዓለ ኀምሳው - የጰንጠቆስጤ አበባ የመከር ( ) የምሥራች ነው፡፡ የጰንጠቆስጤ አበባ ለመከር በዓል (ለመነፈስ ፍሬ) ይረግፋል፡፡ በዚህ ዘመን ይህንን በሕይወታችሁና በአገልግሎታችሁ የምታዩት አይደለምን? እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን ይክፈት፡፡ ፍሬው (መከሩ) ሊታይ አበባ በጫሯሽ ይጠፉል፡፡ ይሄም ብቻ አይደለም፤ ፍሬም ሲበስል መልኩን ይለወጣል፡፡ ብዙ የጥራጥሬ እኅሎች (ተክሎች) በመከር ይጠወልጋሉ፡፡ ወገኖች ሆይ፣ አይዟችሁ አሁን ያለው መንፈሳዊ ሕይወት ማጠወለግ ለመከር - ከእግዚአብሔር ጋር ለመነብሰብ ነው - ክብር ሃሌሉያ!

በእርግጥ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከፋትን ወደ ጽድቅ፣ ድካሟን ወደ ብርታት፣ መበስበስዋን ወደ አለመበስበስ፣ ሞቷን ወደ ሕይወት፣ ወርደቷን ወደ ክብር፣ አሮጌው ዘመን ወደ አዲስ ሥርዓት… ይለወጠዋል፡፡ በዚህ ሐሳብ ብዙ መጽሐፍ ባያስፈልግም ይሄ ሰባተኛወና የመጣ ዘመን ነው፡፡ እርሱ በልባችን ነግሷል፡፡ መሉ ቀን እስኪሆን ይጨመራል፡፡ ሁሉም በዚህ ቀን ከድካሙ ለሚረፍ ወደ ዕረፍት ይገባል አሜን ይሁን!

የባቢሎን ጫጉላ (ርዕሱ ቢለወጥ)

ከወዲሁ የምንለው አንድ ነገር ግን ብዙዎች ዛሬ፡- ‹‹እኛ የጰንጠቆስጤ አማኞች ነን›› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ እነዚህ ወድ ወንድሞች በእርግጥ ቀኑን ነው የሚያምኑት ወይስ በቀኑ የተፈጸመው መንፈሳዊና ሰማያዊ መነብኘት? ‹‹አካሉ የክርስቶስ››

ከሆነ በሕጉ መንፈሳዊነት ላይ ቆመን በዚህ ቀን የምናስተወለው መንፈስ ቅዱስን ይሆናል፡፡ ጰንጠቆስጤ አይታመንበትም፡፡ ከዚህም ቀን የበለጠ ቀን አለና! በዚህኛውም ቢሆን አይታመንም፡፡ የቀኑ ሚጸጸም ግን በእርግጥ ‹‹የጌታን ቀን›› ያደርጋልና የምንታመነው ያንን ነው፡፡ እኛም በቃላችንም ይሁን አሁን እንደምናደርገው በሚልእክታችን እግዚአብሔር በሌላ በዓል ያስረጀውን ጰንጠቆስጤን በተለያየ መልክ ስንተቸው (‹‹ኮሜት›› ስናደርገው) ሰዎች ከቀኑ ጋር ያላቸውን መጣበቅ(ቁርኝት) ሚስጣል እንጂ በቀኑ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ላይ የምንተች አይደለንም፡፡ በጄሮሽ፡፡

በጰንጠቆስጤ ፍጹምነት ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ - በቤተ ክርስቲያን አሠራር ተፈጽመን ቢሆን ኖሮ ሌላ ቀን - ሌላ በዓል - ሌላ ልምምድ በሚጨረሻም የመንግሥቱ ሕይወት ስለምን ያስፈልጋል?! ቤተ ክርስቲያን እስካሁን በጰንጠቆስጤ የዞረችው ዙረት ቢዘረጋ እስከየት ይደርስ ነበር? እስከ ዛሬ ዙረቷ ግን ስለመድከሚ ሆነ፡፡ ለመዛል ሆነ፡፡ ለመሸነፏ ሆነ፡፡ ለመጨቋ ሆነ፡፡ ለምጧ ሆነ፡፡ ለምን? የታላቁ ንስር ክንፍ እንድታገኝ - ወንዱን ልጅ እንድትወልድ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ሚልቅ በእርሷ ተሰወሮ የሠራው መንግሥት መገለጥ ይሆናልና አዲስ ጅሚሬ ነው፡፡

በእጁ ባሉ ሰባት መቅረዞች ወስጥ የተገኘው ድካም፣ ኃጢኣት፣ የኒቆላወያን ትምህርት፣ የበለዓም የሐሰት ገንዘብና ክብር፣ ሐሰተኛ ብልጽግና፣ የኤልዛቤል መንፈስ… ሲታይ ባቢሎን ‹‹ከቤተክርስቲያን›› ጋር ‹‹ቤተክርስቲያንም››ም ከባቢሎን ጋር ሚመዘርዋም አይደለምን? የባቢሎን የጫጉላ ሽርሽር(Honeymoon) ያለ ጥርጥር ከህናዊቷ ቤተክርስቲያን ወስጥ መሆኑን ልብ በሉ፡፡ ለሽርሽሩ ደግሞ ድምቀት የሰጠው የተበረዘው ‹‹ጰንጠቆስጤ›› ነው ልንላችሁ አንፈራም፡፡ በጰንጠቆስጤ ስም ታላቅ ወንጀል ተካሂዷል ለሚለት ቢያሳዝንም፡፡ በጰንጠቆስጤ ነፍስ(ባቢሎን) ሰብቷል፡፡ በጰንጠቆስጤ በራሱ ‹‹የቤተክርስቲያን›› ፍጽምና እንደሆነና እንደሚመን ማከበቁ ራሱ የባቢሎን አዚመት ነው፡፡ ብዙዎች ወደ ወጠበት ሊመላሱ - ወደ ትፋተቸው ሊመላሱ መንፈሳዊ ሻንጣቸውን ቆልፈዋል፡፡ ያፈረሱትን ድንኳን እንደገና ሊሠሩ ችንካራቸውንና ካስማቸውን ከጣሉበት ፈልገው አግኝተዋል፡፡ ይህም ነገር እ.ኤ.አ ከ1948 ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለውን ግሩም የታሪክ አጋጣሚ ያለ ቦታውና ያለ ጊዜው ማጠቀምና ሚደፍረስ ነው!! ይህንን በሌላ ጊዜ እንመጣበታለን!፡፡

ብዙዎች ወደ ፊት - ወደ ግብ - ወደ መንግሥቱ - ወደ መጥራቱ ዋጋ የሚመራቸውን በትራቸውን አሽቀንጥረው ጥለዋል፡፡ በመጨረሻው ልክ(Standard) እየተመላለሱ የወሰጣቸውን ድፍረት፣ ጥንካሬ፣ ማኅወር… ጥለዋል - ያሳዝናል፡፡ መጽሐፍ፡- ‹‹በመቅደሱም ውጭ ያለው እድሞ ለአሕዛብ ተሰጥቶአልና ተወው አትለካውም›› የሚለውን ሚስማት አልቻሉምና ውጪን ለክተው ይመላለሳሉ፡፡ ያገለግላሉም(ራእ.11÷2)፡፡ ስለዚህም በሆነው ሁሉ ልባቸወ ቀልጧል፡፡

(በበዓለ ኀምሳው ቀን በዓል - በስንዴ መከር በዓል የተቀባው ሳኦል - 1ሳሙ፡12÷17-18 ሳይቀር) የሕዝቡ ሁሉ ልብ በጎልያድ ፊት የቀለጠውና የወደቀው በውጭ በለኩት ልክ ምክንያት አይደለምን? አሥሩም ሰላዮች ‹‹ያገለገሉት›› ነገር ቢኖር ፍርሃትን፣ መሞላስን፣ መሸሽን… ነው፡፡ በውጭ ልክ የሚደረገው ሁሉ የባቢሎን ዋጋ እንደሆነ ለልባችሁ ልብ ይገለጥ ዘንድ እንጸልያለን፡፡

የእነዚያን አገልግሎት ለምክርነት ከጠራን ዛሬ በጰንጠቆስጤ ስም የሚሰጠው አገልግሎት ሰይጣንን፣ አጋንንትን፣ ዓለምን፣ ሥጋን… በተመላከተ የሕዝቡን ድፍረት ነው ወይስ ፍርሃት ነው የሚገልጠው?... ሕዝቡን ካለበት እንዴት አላወጣ ወም? ጰንጠቆስጤ የአጋንንት ስቃይ ሚታገሻ ነው ወይስ አጋንንትን ሚወጫ?... ዳዊት የሳኦልን ስቃይ በዜማ ያስታግሥ ነበር፡፡ ይሄ በመጀመሪያ ሕይወቱ ነው፡፡ ነገሮች ሲጀመሩ ብዙ የሚዩባለቁ ነገሮች አሉ፡፡ እየቆዩ ግን ይጠራሉ፡፡ ዳዊት ለሳኦል በገና ይጫወት ዘንድ አልተቀባም፡፡ የዳዊት ቅባት ግን ለሳኦል ስቃይ ሚስታግሻ(ለፈወስ አይደለም) መመንዘሩ ለምን? ዘመናችን ይህ ጉዳይ አይመላከተውም ትላላችሁ?... ነፍስ እግዚአብሔር ሊያጠፉት ሲነሳ የጰንጠቆስጤ ዜማና ቅባት ወደዚያ (ወደ ሚስታግሻነት) መመንዘሩ ምንዝርና ነው፡፡

ሳኦል በሞኙ ዘመኑ - በሰፋው መንግሥቱ እያለ(ግን ያለ እግዚአብሔር ነበር) ዳዊት ተቀባ፡፡ ሳኦል ይህንን ያወቀዋልን? አያወቀውም፡፡ ሳኦል የስንዴ መከር ንጉሥ - በጰንጠቆስጤ በዓል ጊዜ የተቀባ ንጉሥ እንደ ሆነ ደግሞቹሁ ልብ በሉ፡፡ እግዚአብሔር ግን በዳዊት አስረጅቶ ሻረው፡፡ ሳኦል የሕዝብ ልብ ምኞት ነው(1ሳሙ፡9÷20)፤ ዳዊት ግን የእግዚአብሔር ሐሳብ(ልብ) አገልጋይ፡፡ ዳዊት ከሳኦል እየሸሸ ወደ ዙፋኑ ሲወጣ ሳኦል እያሳደደ ሰይፉ ላይ ወደቀ፡፡ ማንም የዛሬ ብርታት አይሁንለት፡፡ ሲደክም ያኔ ኃይለኛ የሚሆነው ግን በመንግሥቱ ተፈላጊ ነው፡፡

በሳኦል እስራኤል ድኗል፡፡ እስራኤል በሳኦል አርፏል በተወሰነችው ዘመኑ፡፡ ሳኦል ፈጽሞ ያለ ምንም ጥቅም ነበር አይባልም፡፡ ሳኦል በእግዚአብሔር የተቀባ - የተሾመ - የነገሠ መሆኑን አናጣውም፡፡ ግን የሚሸረው - የሚያስረጀው በተዘጋጀበት ጊዜ የቀባው እግዚአብሔር መልሶ ሻረው፡፡ ስለ ጰንጠቆስጤ የቀኑ ሚጸጸም ስንናገር ብዙዎቻችን ተባርከንበታል፡፡ ተፈወሰንበታል፡፡ ነፃ ወጥተንበታል፡፡ ድል አድርገንበታል፡፡ ጰንጠቆስጤ ካሪዝማቲክ ወሰናቸወን አስፍተው ሁሉን (የሃይማኖት

ቤት) አገልግለዋል፡፡ ጳንጠቆስጤ ብዙ ጉባኤዎችን፣ ትምህርቶችን፣ ልምምዶችን፣... በማረጀት የብዙዎች ዕረፍት ሁኖ ሁለት ምዕተ ዓመት አስቆጥሯል፡፡ በዘማ ጳንጠቆስጤ(እስካሁንም ድረስ) ሚልካም ያልሆነለት ቢገኝ ጥቂት ነው፡፡

ዳሩ ግን ጳንጠቆስጤ በሚሉ ዘሙና ጉልበቱ ትወልዱን የጠቀመውን ያህል ጌታ ወደ ሌላኛው ቀኑ ሊያሻግረን ፈልጓልና በዚህ ዘመን ሲበዛ ደክሞ ታይቷል፡፡ ጳንጠቆስጤ ከብዙዎች ልብ እየወደቀ - ተስፋ እያጣ ነው፡፡ ስለ እርሱ ድሮ የነበረን ናፍቆት፣ ትጋት፣ ልብ... የለንም፡፡ እግዚአብሔር አንድን ልምምድ፣ አንድን ክብር፣ አንድን እምነት፣ አንድን ጸጋ ሲያስረጅ እንዲህ ነው፡፡ በዚህም ጊዜ የሚከር ዘመን ቅሬታዎች - አዋጅ ነጋሪዎች - በእግዚአብሔር እርሻ ቀድመው የበሰሉ በተሰውሩበት በእግዚአብሔር ሁነው(ቆላ.3÷4) የመጣውንና በመላት እየመጣ ያለውን ዘመናቸውን ያወጁ፡፡ በዚህም ያለምንም ጥርጥር ጳንጠቆስጤን ያስረጁታል፡፡

‹‹ከነቢዩ ሚልክያስ እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ዘመን አራት መቶ ዓመት ነበር›› ሲባል በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሌላ ነቢይ አላስነሣም(እርግጥ ነው በግል - በስውር የሚገራቸው ምስክሮች ነበሩ)፡፡ ዳሩ ግን ያንን የዝምታ ሰሚይ ሰንጥቆ የመጣው የመንግሥት ሰሚት ሚልእክት ብዙዎችን ከተኙበት መንፈሳዊ አልጋ አወረዳቸው፡፡ ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ደርሰው በዝምታ ሲጨርሱ የተረከባቸው ድምፅ ለሚመጣው አዳኝ አዋጅ ነጋሪ ነበር፡፡እንደዚሁ ከአሥሩ ቆነጃጅት ማሕል ያልሆኑ ቆነጃጅቱን ግን ከተኙበት የሚያወኩና የሙቃሰቅሱ አስቀድመው የወጡ - የተዋጁ ደናግል(ራእ.1÷5) የጳንጠቆስጤ፣ የቤተክርስቲያንና የእስካሁኑ የትኛውም ዓይነት ልምምድ ሰሚይ በሚያንኳኩድ መበረቃቂ ሚልእክታቸው የሰወን ትምህርትና ሰው ራሱ ከተንጠለጠለበት ሲያራግፉት በእርግጥም ሁከት ይምሰል እንጂ የእግዚአብሔር ክብር መሞላስ በአሕዛብም የሚበቀው ዕቃ መምጣት መሆኑን በመንፈሳችሁ ስሞት(ሐጌ.2÷6-7)፡፡

‹‹አምላካችን እግዚአብሔር በኮሬብ እንዲህ ብሎ ተናገረን፡- በዚህ ተራራ የተቀመጣችሁበት በቃ፤ ተመልሳችሁ ተጓዙ፤ ወደ ተራራማው ወደ አሞራውያን አገር ወደ ድንበሮቹ ሁሉ፣ በዓረባም በደጋውም በቆላውም በደቡብም በባሕርም ዳር ወዳሉ ወደ ከነዓናውያን ምድር፣ ወደ ሊባኖስም እስከ ታላቁ ወንዝም እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ሄዱ፡፡ እነሆ÷ ምድሪቱን በፊታችሁ አድርጌአለሁ፤ ግቡ፤ እግዚአብሔር ለእነርሱ ከእነርሱም በኋላ ለዘራቸው ይሰጣት ዘንድ ለአባቶቻችሁ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም የማለላቸውንም ምድር ወረሱ››(ዘዳ.1÷6-8)፡፡

የዛሬውም ትወልድ የጥንቱን ሚስሎ በለመደው ነገር መመላለስ - መንሸራተት እንጂ ጉዞን - መሄድን ስለምን እምቢ አለ? እግዚአብሔር ‹‹በቃ›› የሚለው ስለምን አልበቃም? ስለምን አላለቀም? በእርግጥ የቤተክርስቲያንና የስንዴ ሚከር (የጳንጠቆስጤ) ልጆች ስለ ስንዴአቸውና አጥቢያቸው እንጂ ስለሌላኛው ሊነግሩን አይቻላቸውም፡፡ እነርሱንም ከፍ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር መላት የሚያንቀሳቅስ(የሚስጉዝ) ከመከላላቸው የሕግ ሰጪው ምሪት(The direction of the law giver… - ዘኁ.21÷18) ያለው አይገኝም፡፡ የዚህ ጸጋ በዳስ በዓል ልጆች እጅ ነውና በእርግጥ እንግዳ ነገር በምድር ላይ ይሆናል(ራእ.11÷19)፡፡

እስራኤል የተባለው የምድረ በዳው ማነበር(ቤተክርስቲያን - ሥራ.7÷38) የምድሪቱን የፍሬ ሚከር ገና በምድረበዳ እያለ ነው የቀሚው በአሥራ ሁለት ሰላዮች አማካኝነት፡፡ ... እግዚአብሔር ጊዜም ስፍራም አይወስነውም፡፡ የመንግሥቱ ፍሬ በየትኛውም ዘመን ነበር ምንም እንኳ መሉ በሚሉ ባይገለጥ፡፡ የከነዓንን ፍሬ(ወተትና ሚር) የቀሚው ያ ወገን ግን የቀሚውን በመላት ሊበላ መራመድን እምቢ አለ፡፡ እኛም በጳንጠቆስጤ የከበረ ልምምድ የመላቱን ፍሬ እንደቀሚን እናውቃለን፡፡ ግና ከጳንጠቆስጤ ወደ ካሪዝማቲክ ዞርን እንጂ(እስራኤል ከቃዴስ እንደዞረ) ተራምደን የዳስ በዓልን ዘመን ስለ እኛ ያንጠባጥብ ዘንድ አላስነሣነውም፡፡ የሚከር በኩራት(ፍሬ) የቀሚው ወገን ተራምዶ ሁሉን የራሱ ለሚድረግ አለመፈለጉ ጸጋ ነው አዚም? ሁሉም ባለበት እየተሸከረከረ ቅምሻ (ጸበል) ይቀምሳል፡፡ ሳንፈራ እንንገራችሁ፤ በጳንጠቆስጤ ማንም በመላት አልበላም አልጠግብምም፡፡ በኋለኛው ዝናብ እንኳ ይሄ አልሆነም፡፡

ግን ጳንጠቆስጤን ካሪዝማቲክ በዘማናቸው ሁሉ ጥማትንና ርሀብን ፈጥረውብን ወደ ሌላኛው ብልጫም ወዳለው ክብር እንድንሻገር አገልግለዋል፡፡ ስለዚህም ተሰጥተዋልና! ዛሬ ግን እነዚህ ሁለት ልምምዶች - ስጦታዎች እንደ ጅሚሬአቸው ለምን አቅም አጡ? ስለምን ደከሙ? በብዙ ወጪ ከሩቅ ከአውሮጳ ወይም ከምድረ አሜሪካ ለዚህ ‹‹የጸጋ ስጦታ›› ተፈጻሚት የሚመጣው ‹‹ነጭ›› አገልጋይ አገር ቤት ካለው አገልጋይ ለምን አልበለጠም?... በእርግጥ ‹‹የተቀቡ›› የምነላቸው ፈረንጂዎችም ከልባችን ወድቀዋል፡፡ ብትቀበሉት ከእንግዲህ ፈረንጂዎች ለወንጌል ገንዘብ ይሰጡ እንደሆነ እንጂ ወንጌልን - የሙ ወቀወን ልዩ መላጥ ሊሰጡ አይችሉም፤ አትሳቱ፡፡ እነርሱም አልቆባቸዋል፡፡ ግን ሳምኮን ‹‹እንደ ወትሮው ሚስሎት›› እንደ ተንቀሳቀሰ ዛሬም በወትሮ(እግዚአብሔር ግን ባስረጀው) ልምምዳቸው የሚሙተረተሩ አልጠፉም፡፡

‹‹በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ዓመፃችሁ እንጂ ወደ እርሷዋ መውጣትን እንቢ አላችሁ›› (ዘዳ.1÷26)፡፡

እንዴት ዓይነት ነገር ነው!! ሰፈሩ የሞቀውና ሊለቀው ያልፈለገ ማነበር!! ስለዚህ ቃል እኛ የት ነን? ለመሆኑ ካለንበት ለመውጣት እሺ ብለናል? የኮሬብ ልምምድ ምሳሌነቱ በትክክል የበዓል ጎምላው ቀን ልምምድ ጥላ እንደሆነ ታውቃላችሁ?... ከዚያ ሰፈር ነው ሕዝቡ አልወጣም ያለው፡ ዛሬ ከልሣን፣ ከትንቢት፣ ከስጦታዎች፣ ከቤተክርስቲያን ሥርዓት... ሌላ የሌለ መሰለን ወደ ሌላው ብልጫ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር ከፍ ያለው ሐሳብ አንወጣም ያልነው ስንቶች ነን? ማነበራት ሁሉ ናቸው፡፡

መጽሐፍ ስለ እስራኤላውያን፡- ‹‹... መውጣትን እምቢ አላችሁ›› ካለ በኋላ፡- ‹‹በድንኳናችሁም ወስጥ... አጉረመረማቸሁ...›› ይላቸዋል(ዘዳ.1÷27)፡፡ አስገራሚ ነው! ሕዝቡ አልወጣም ብሎ ወደ ድንኳኑ ሸሸ፡፡ ጸንጠፅስጤ የድንኳን ዘመን ነው፡ በጸንጠፅስጤ ያበዛነው ነገር ቢኖር ድንኳኖችን - ጉባኤዎችን ነው፡ አገልግሎታቸው ሻል ቢል ጉርምርምታ ሲከፋ ማጉረምረም፡ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት በጸንጠፅስጤ ናቸው፡ የስንዴ ማሳር ንጉሥ፤ የሳአል ሰባት ልጆች ለምን ተሰቀሉ (2ሳሙ:21÷6-9)? ወገኖች መጽሐፍትን ሚገምሩ፡፡ ሰባት ድንኳኖች ዘመናቸው አጭር ነው፡ የእግዚአብሔር መላት በጥፋት ወደ መንግሥቱ ይቀበላቸዋል - አሜን? ይሁን!

በራእይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት የተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት የብዛት - የመላት ምሳሌ እንጂ ከእነርሱ ሌላ በዚያን ዘመን አብያተ ክርስቲያናት አልነበሩም ማለት አይደለም፡ በሮሜ በቆሮንቶስ፣ በገላትያ፣በባቢሎን፣ በተሰሎንቄ፣በኢያሩሳሌም... አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ፡፡ ድንኳኖች በዝተው ነበር፡፡ በዘመናት ሁሉ - ድንኳኖች በበዙበት ዘመን ሁሉ የሚያስገርመው ቅሬታዎች ነበሩ፡፡ በሰባቱም አብያተ ክርስቲያናት፡- ‹‹ድል ለነሣው›› እና ‹‹ድል የነሣው›› የተባሉት ናቸው፡ ‹‹መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት›› የሚለውም ድምፅ (መልእክት) የመጣው ለእነርሱ እንጂ እነዚያ ሊሰሙ አልነበረም፡ በዚህ ለመውጣት እምቢ ባለው በምድረበዳው ማነበር መካከል እንኳ ቅሬታዎች ነበሩ፡፡ በእስራኤል ወገብ የነበሩ እነዚያ ታናናሾች ወርሰዋል፡፡

ረሀብ - ቸነፈር - ዋይታ = በከተማ

ቃየን ከእግዚአብሔር ፊት ከመገኘቱም ከብር ወጥቶ ለራሱ ከተማን ሠራ(ዘፍ.4÷16-17)፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ የኖረበት ዘመን ሁሉ የሰው ‹‹ከተማ›› ዘመን ነው፡፡ ሰው ያለ እግዚአብሔር በረከት፣ ርጉም ነው፡፡ የሰዎች ከተማ ሰዎች ራሳቸው ለራሳቸው የፈጠሩት የድካሞቸው ሰፈር እንደሆነ ሕይወታቸው ይገልጸዋል፡፡ እንደሚሉትም፡- ‹‹ለኑሮ መልካም በሆነች ከተሞቹው ውኃው(ሕይወት) ይጩኹ ግፋል››(1ነገ.2÷19)፡፡

በዘፍጥረት መጽሐፍ በመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ሰው ከእግዚአብሔር ተመልሶ የራሱን ሰፈር (ክበብ) ያደረገበት ጊዜ አያሌ ነው፡፡ የሰወም የታሪኩ ሜጩሻ ከዚህ ያልተለየ መሆኑን ደግመን እናስተወላለን፡፡ ከእርሱ ጋር አስነሥቶን በሰማያዊ ስፍራ የተቀመጥንበት ‹‹መሠረት ያላትና እግዚአብሔር የፈጠራት ከተማ›› ከማንነት ሌላ ካልሆነች ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ርቀውና ወጥተው የሚሠሩት እምነት፣ ትምህርት፣ ልምምድ... የሰው ከተማ ይባላል፡፡ ከዚህ ከተማ (ከባቢሎን) እንድንወጣ ነው የእግዚአብሔር ሰማያዊና ተደጋጋሚ ጥሪ፡፡

‹‹እናንተ ግን ተመልሳችሁ በኤርትራ ባሕር መንገድ ወደ ምድረበዳ ሂዱ››(ዘዳ.1÷40)፡፡ እርግጥ ነው እስራኤል ከእግዚአብሔር መንገድ ከእርምጃወም ተመልሶ ወደ ኋላ በሄደበት ዘመን ሁሉ ምልከቶች፣ ድንቆች፣ ተአምራቶች፣ የኪዳኑ ክብር፣ አደራረጉ፣ ታማኝነቱ፣ ጥበቃው፣ መናው... አልተለየውም፡፡ የየዕለቱ እንጀራ፣ የቀን የዳመና ዐምድ፣ የሌሊት የእሳት ዐምድ.. በጌታ ታማኝነት ቀጥለው አገልግለዋል፡፡ ነገር ግን መፄድንና መራመድን ባልወደዱ ጊዜ እግዚአብሔር ተዋቸው፡ እግዚአብሔር የማነበራትን ከተሞች ትቷል፡፡ ግን በተዋቸው በእነዚህ የማነበራት ከተሞች ልምምዶች፣ ስጦታዎች፣ በረከቶች፣ አገልግሎቶች... መቀጠላቸው እማን ነው - ነገሩ ግራ ቢሆንም፡ ጌታ እግዚአብሔር ከተኛንበት አልጋ ልንወርድ ይቀሰቅሰን እንደሆነ እንጂ በዚያው አልጋ ራስጌ ሁኖ የሰው መንካትና መነብኘት ያደርግልን ዘንድ አይደለም፡ በሌላ ጊዜ እንዳስጠነቀቅናችሁ ሎዶቅያ የቤተክርስቲያን ታሪክ(ዘመን)ሚለቂያ ምሳሌ ከሆነች ጌታ በደጅዋ ቆሞ ማንኳኳቱ ከመካከሏ - ከማነበሯ - ከከተማዋ መውጣት አይደለምን? ... ይህች መቅረዝ (ቤተክርስቲያን) በእጁ ነበረች፡፡ አሁን ግን እርሷኑ ያንኳኳል፡፡ በእጅ የተያዘ ነገር ፈጥኖ ለመጣልም ምቹ እኮ ነው - ያስፈራል፡፡

ወደ ታሪኩ ሚረጋገጫ እንመለስ፡፡ እስራኤል መሚሪያ ነው - የተባረከ ይሁን! እስራኤል ሰላዮችን ወደሚባበት ወተትና ሜር ወደሚያፈስሰው ምድር በላከ ጊዜ ሰላዮች ከምድሪቱ ፍሬ ጋር ነው የተመለሱት፡፡ በእርግጥ እስራኤላውያን ለምድሪቱ

ፍሬ ቀርበው ሳለ ግና ከፍሬው ጋር የተራቁበት ዘመን ነው ዘመነ ኮሬብ። የዚህም(የዘመነ ኮሬብ) ምሳሌነት በትክክል የተፈጸመው በጴንጠቆስጤ ነው ብለናችሁ ነበር። የቀረበው ግን የራቀው ያ የጥንቱ ማነበር በእግዚአብሔር የሕይወት እርምጃ አልወጣም በሚለቱ እንደሆነ ይህ ያለንበትን ዘመን ስንፈትሽ ልብ እንለዋለን። ጴንጠቆስጤ ገበሬው ፍሬ በሚያደርግበት በዚያ ሕያው ዛፍ ላይ እንደ አበባ አይደለምን? ጴንጠቆስጤ ፍሬን የቀደመ ፍሬም የቀረበው ከቡር አበባ ነው። ዛሬ ግን የአበባው ጉንጉን ለሬሳ መሰጡቱ ነው ከፋቱ። በሞተው አዳም ባሕሪይ ሬሣ(መቃብር) ላይ ማነበራት አበባን ሞኖራቸው - ጴንጠቆስጤ ማልገላቸው የከፋ አዚም እንደሆነ በኅዘን እላለሁ። የመከሩ ፍሬ ይታጨድና ይሰበሰብ ዘንድ አበባ መገፉ - ጴንጠቆስጤ መሻሩ ለቤተክርስቲያን የመዶ ያህል ቢሆንም ከተመቸወን ለተወትና በሕግ ሰጪው ምሪት በበትራቸውም ኃይል ወደ ፈቃዱ ጫፍ ለሚራመዱ ግን የምሥራች የመነፈስም ሐሴት ነው። አሁን ያለችው ማነበር - ‹‹ሁሉን ነገር አለኝ›› ባይዋ ሎዶቅያ ከከተመቸበት የበራድነት ከተማ አልወጣም በሚቷ ጴንጠቆስጤ ስለእርሷ ለምድሪቱ(ለአዲሲቱ ምድር) የቀረበ ግን የራቀ መሆኑ የታሪክ ድግግሞሽ ነው።

ይሁን እንጂ በየትኛውም ስፍራ ዘመነ ትወልዳቸወንና ዘመናቸወን የዋጁ ጥቂት ፈንጠር ያሉ ወገኖች ነበሩ። ደግሞም አሉ። አሁን ያሉበት(የለመዱት) ፈጽሞ አያረካቸወም። ያላቸወን ግን እየረሱ የሚይዙትን ፍለጋ ይዘረጋሉ። በፍጹም የባቢሎን ምሥክር በእነርሱ ላይ ይፈጸም ዘንድ አይፈቅዱም። አሁን ያላቸው የሚያዝ አይደለምና የያዛቸወን ለመያዝ ይዘረጋሉ። ስለ ክርስቶስ የሚገረው የመጀመሪያው ነገር ከክርስቶስ ቢሆንም ‹‹ክርስቶስ ሞኑ በሞኑ›› አይደለምና ትተወት ይሄዳሉ(ዕብ.6÷1)። ዘሙሉ፣ የዚያም ዘመን ክብር፣ መለጥ፣ ልምምድ፣ ስጦታ፣ በሞኑ ኃይሉ ገናም በጉብዝናው ቢሆን እንኳ ይከዱታል። በእነርሱም በሚፈረወና በሚለጠው ሕይወትና መነፈስ ቃል ዘሙን አስረጅተው ይሽሩታል(ሚር.1÷14፤ ሮሜ.13÷11 ይሚልከቱ)።

ክርስቶስ ጌታ ‹‹ዘሙሉ ተፈጸመ›› ሲል በወጪጪ ሁኔታ አሮጌው ዘመን ገና ነበር። እርሱን ግን እንደተፈጸመ ቆጥሮ በሚሞላለስበት - በሚፍርበት መነፈስ አገልግሏል። ዘሙሉ እንደሌለ አወቆ ሠርቷል። ያም መበረቃቂ ቃል(ሚር.1÷14) በትወልዱ ብርሃኑንና ድምፁን ካደረገ በኋላ የነበረወን ዘመን በድንቅ አስወገደው። ዛሬም ተጀምሮ በነበረው በመነግሥቱ የምሥራች የሕጉን ዘመነ የተካው የቤተክርስቲያን ዘመን አሁን በበራው ብርሃንና ነጎድጓዊ ድምፁ ሚጀቱንና ሊሻር መቅረቡን እንደሌለም ሚወጃችን እንደ ክርስቶስ በሚሰብ ነው።

እንደዚያች ወርንጫ በወጭ(ሚር.11÷4) - ለወጪጪ ሥርዓት - ለሥጋዊ አሠራር ለታሰሩ ከርስቲያኖች የቤተክርስቲያን ዘመን ያለ ይሚላል። ቅሬታዎች ብቻ ይህንን ይመረምሩታል። ጌታን ተጠግተው የሚራመዱት ጥቂት የመጀመሪያ ብስሎች በስወር - በወስጥ ሕይወት - በመነፈስ እንደ እግዚአብሔር ፕሮግራም ይራመዳሉ። የእነርሱም ነገር ለብዙኀኑ እንቆቅልሽ ነው።ይሁን እንጂ በዚያው የመነፈስ እርምጃ ተራምደው ፌዘኛወን ትወልድ እስከመጪፈሻ ዘባች አድገወት ኃይሉን ሲጨርስ ለሰሚየዊው ክብር፣ ኃይልና ፈቃድ ያንበረከኩታል።

ክርስቶስ ገና የተላከበትን ዓላማ መገለጥ - ሚድረግ - መፈጸም ሳይጀምር ነው እግዚአብሔር አብ ከላይ፡ - ‹‹ድምፅ ከሰሚት መጥቶ፡ - በእርሱ ደስ የሚሎኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው›› ያለው (ማቴ.3÷17)። አብ በክርስቶስ ሊሆን ያለወን እንደሆነ ቆጥሯልና! ኢያሱስ ክርስቶስም የመገለት - የተላከለት ዋነኛ ነገር ገና ሳያደርገው እንዳደረገው በመቁጠር፡ - ‹‹እኔ ላደርገው የሰጠሽኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርኩህ›› ሚለቱ አንዳች የጠለቀ መረዳትን አዝሏል(ዮሐ.17÷4)።

ክርስቶስ ሞቶ ሳይነሣም ‹‹ትንሣኤ ነኝ›› ብሏል ራሱ(ዮሐ.11÷25)። ወደ ሰሚይ ሳይሄድ ገና በሥጋው ወራት በሰሚይ እንደሚኖር ብሏል(ዮሐ.3÷13)። እነዚህ ቃላት እንዴት የከበሩ ናቸው በመነፈሳችን አዳራሽ? ጥልቀታቸወንስ ማን ያወቃል?

ባለቀ ሥራና ዘመን ነው የምንኖረው። አሁን ያለው ዓለም ሳይፈጠር ታወቀ። ሥራውም ተፈጽሚል። ልጅነት ይህንን ያወጃል። ከዚህ እወቀት ጋር ተባብሯል። ይመላለስበትሚል። ድርጊትን - መደረግን - መሆንን የሚሥራው ሕያው ቃል እንደሚፈጥረው ያወቃልና ልጅነት አሁን ያለ በሚሞላለው ሐሰተኛ ጥላ ፈጽሞ አይታመንም። እንዳለቀ - እንዳረጀ ይቆጥራል። በመነፈስ መመላለስ ከዚህ ሌላ ምንድር ነው?... መነፈስም የራሱ የሆነ ሥርዓት፣ የራሱ ዕይታ፣ የራሱ ልምምድ፣ የራሱ ሁኔታ... አለው። አሁን ያለ የሚሞላለው ሁሉ የዚያ ጥላ እንደሆነ አታወቁምን?... እስከ መቼ በጥላ እንኖራለን? ጥላው እስካለ በእርሱም እስከተመላለስን አካሉ ሊገለጥ ከቶወንም እንደሚችል እስካሁን አልተመራችሁምን?

እንደ ክርስቶስ ልብ ያለወን እንደሌለ፣ የሌለወን እንዳለ ብንቆጥር በመነፈስ ተመላልሰናል። ድል መነሣትስ ከዚህ አካሄድ - ከዚህ መገድ ወጭ ምንድር ነው? የትስ ይገኛል?

ጣፋጩ አዳኝ - ኢየሱስ፡- ‹‹እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም›› አለ(ማቴ.5÷17)፡፡ ግና እንዴት ፈጸመ? … በአይሁዶች ሥርዓት - በአይሁዶች መንገድ - በአይሁዶች ፕሮግራም?... አይደለም፡ ‹‹ሕጉ መንፈሳዊ ነውና›› በመንፈስ ነው የፈጸመው፡ በእነዚያ ሕጎች ሁሉ በመንፈስ ተራመደ፡፡ በዚያም መንፈሳዊ ርምጃ ያለጥርጥር ዘሙን ፈጸመው፡ ጨረሰው፡ አስወገደው፡ ይሄም ታላቅ ድርጊት በማንነት ነው እንጂ ቀን በመቁጠር አልነበረም፡፡

እኛም የመንግሥት ሰሚያትን ዘመን ከቤተክርስቲያን ዘመን ይልቅ አተልቀን ስንሰብከውና ስንጽፈው በማንነት የሚፈጸም እንጂ በዓመታትና በምዕተ ዓመት ለውጥ የምናመጣው አይሆንም፡፡ ሕጉ ገና በጎልማሳነቱ - ገና በሙሉ ኃይሉ እያለ በተጀመረው በመንግሥቱ የምሥራች ተሻረ፡፡ በእርግጥ እንደ ሰው አቆጣጠር እንደሰውም ዘመን ከርስቶስ ከሞተ በኋላ እንኳ እስከ ሰባ ዓመተ ምሕረት ድረስ ተራዘመ፡ የአይሁድ ሥርዓትም(ጆዲዝም - ‹‹ይሁዲነት›› - ሥራ.2÷11) በዚያው ዓመት ሙሉ በሙሉ ለዘላለም ሲፈራርስ በከርስቶስና በመንፈስ መመላለሱ የተፈጸመው ‹‹ዘመን›› አካል ማግኘቱ ነበረ፡፡ ዛሬም ይህ ሰሚያዊ ሥርዓት አልተለወጠም፡ ያለው ዘመን የሚያልቀውና የሚሸረው በዚያው ርምጃ ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም መንገድ አይደለምና፡፡

አሁን ቤተክርስቲያን ከተሰጣት ዘመን፣ ስጦታ፣ልምምድ፣ በረከት… ጋር ልትሆን ትችላለች፡፡ በለመደችው አባቶችም በሰጥዋት ሥርዓት ትራመድ ይሆናል፡፡ ግን ይህንን ሁሉ የሚያስረድ - የሚያጨልም - የሚጨርስ - ከተሟዋን የሚሽር… ትወልድ የጊዜወን ቃል ይዞ ተነሥቷል፡፡ አዎን፤ ይሄ ጥቂት ወገን አበቃቀሉ በእግዚአብሔር በማዕወር ስለሆነ (ቆላ.3÷3) በቤተክርስቲያን አልታወቀም ቦታም አላገኘም፤ ከርስቶስ በዘሙ የሃይማኖት ሰዎች ስፍራ እንዳላገኘ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥቂቶች የሃይማኖትን ሰሚይ እየዘጉት ነው ኤልያስ ያንን ፍጥረታዊ ሰሚይ በእነዚያ ትወልድ ላይ እንደዘጋ፡፡ ‹‹የተከፈተ ሰሚይ›› ተብሎ የተሰበከበት ጊዜ በእርግጥም አልፏል፡፡ የዲኖሚኔሽን(የብዙ ከተሞች)ሰሚያት በጠባቂዎች ትእዛዝ በቅዱሳንም ቃል እየተዘጋ ስለሆነ ትወልዱ የምሩን እየጮኸ - እየቃተተ መሆኑን መንፈስ ብቻ የሚያነበውና የሚያስተውለው ነው፡ የቤተክርስቲያን ወዱ ወገን ከእንግዲህ ወዲህ በየትኛውም ዓይነት የሰው ጥበብ፣ የሰው ፈጠራ፣ የሰው ሪቫይቫል፣ የሰው የስሜት መቀት፣… ላይታለል ሁሉም ነገር ከልቡ ወድቋል፡፡ ወደ አንድ ነገር ግን አዘንብሏል - በወስጡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደተፈጠረው ርሃብና ጥማት - አሜን! ይሄ ነው ቅዱስ ርሀብ! ቅዱስ ቸነፈር!! ቅዱስ ዋይታ!!!

ግን ግን አብያተ ክርስቲያናት በሎዶቅያ ማንነት እንዲፈጸሙ ከሰሚይ ሁኖባቸው ሳለ የትኛው ‹‹መንፈሳዊ ጎበዝ›› ነው በዚህ ዘመን ለሞቷ ከሆነው ቁስል ተፈወሳ ‹‹ሪቫይዝድ ቸርች›› ሊሠራ የሥጋ ጉልበት የሚሆንለት!? በተለይም በልጅነት(Sonship)መረዳት፣ በሦስተኛው(በዳስ በዓል) ዘመን እወነትና ጥራዝ ነጠቅ በሆነ - ሙሉ ባልሆነ በመንግሥቱ ‹‹እወነት›› ሰበብ ቤተክርስቲያን ሊሠራ ቢሞክር አደገኛ ብረዛ ነውና ሰዎች አይሳካላቸውም፡ የልጅነት ከብር ትምህርት የመንግሥቱም ጥልቅ እወነት ቤተክርስቲያን ባለፉት ትምህርቶችና ልምምዶች የጎደላትን ማሟያ ወይም ለእርስዋ የሆነ ጥገናዊ ለወጥ የሚመጣላት ሳይሆኑ ቤተክርስቲያን ፈጽማ እንድታረጅ - ጨርሳ እንድታልቅ ዓይነተኛ የጊዜው መለጥ ናቸው፡ ልጅነት፣ የዳስ በዓልና መንግሥቱ እንደዚህ ካልገባችሁ በእወነት እንላለን እየቀባዠራችሁና በአእምሮ ከንቱነት እየቀባጠራችሁ ነውና የዘሙ ነቢይ ያስፈልጋችኋል፡፡

ሜ - ቴቄል - ፋሬስ!!

ለሕይወቱ ሚዛን ራእይ የሌለው ንጉሥ ባለበት ሚታ፣ በሆነው ነገር ብቻ ተፍለቅልቆ ጅንን ባለ ምሽቱ በግብጥ ቢያረፍድ ይመጣ ዘንድ ያለው የሕይወት ከብር ጨልማትና እግዚአብሔር በሚዘን ሊመዘነው ደረሰበት፡፡ ለግብጥ በተዘጋጀው ወይን ጠጅ ድግስ ከወርቅና ከብር ከናስና ከብረት ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩትን አሚልክት አሚነገነ (ዳን.5÷4)፡፡ ማንም ባለበት ቢያረፍድና በከበበውም ነገር ብቻ ያለ ምንም እይታ ወደ ፊት ላለማየት ቢዝናና ትላንት የነበረው ነገር ሁሉ፣ዛሬ ነውር ከጣሪያም ተርታ ነውና የዚህ ዕድል ፈንታ እንዲገጥመው እናውቃለን፡፡

ይህ የምሽት ግብጥ ሚዛዳው እየፈጠነ ባለው የመንግሥቱ ከብር ከብሩን እንዳጣ ስንናገር እግዚአብሔር በሰጠን ድፍረት ነው፡ የዳዊት የሁል ጊዜ የሕይወት ሚዛዳ ጅሚሬው ይህንን የሚመስከር ነው፡ ‹‹… ወደ እኔ መቼ ትመጣለህ? በቤቴ መካከል በልቤ ቅንነት እሄዳለሁ፡ ›› ይህ የሕይወት ሚዛዳው ናፍቆት፣ ይህ አሁን ካለበት የሚጥለው የእርሱ መምጣት ሲቃ መቃተት ነው፡ የሚጥለው ሁሌ ተናፋቂ እጅግም በግርምት የምንጠበቀው ተደርጓል፡፡ ከዚያ በመቀጠል፡-

‹‹ዓመፃ የሚያደርጉትን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተማ አጠፉቸው ዘንድ፣ የምድርን ኃጢኣተኞች ሁሉ በሚዛዳ እገድላቸዋለሁ››(መዝ.(101)÷2፣ 8)፡፡

የሚመጣውና አሁን በጠባብ የሚታየው የንጋት ወጋገን ጅሚሬ ግን በሰው እጅግ የሚያስከፋ ከእግዚአብሔር ለሆነው ስብዕና ግን በጭካና የሚራመድበትን የፍርድ ብርታት እናያለን፡፡ ዳዊት ሚለዳን ሲያገኝ ከእግዚአብሔር ከተማ(ከሆነበትና - ከተደረገበት የሕይወት ስፍራ) የምድርን ኃጢአተኞች(ቆላ.3÷5) በማጥፋት፣ እነርሱም ላይ በፍርድ ቁርጠኝነት በማዛት ነው፡፡

በሁላችን ዘንድ እየነጋና ወጋገኑን እያየን ያለውን የመንግሥቱን ክብር ካየን ዛሬ ‹‹ቤተክርስቲያን›› በሕይወት ምሽቷ(በተደጋጋሚ የምታደርጋቸው ያረጁ መለጦች) ያደረገችውን ግብጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሆነልን የሕይወት ሚዘን ተመዝኖ ቀሏል - ተንቋል - ተሸሯል፡፡ እናንተ እርሱን የያዛችሁ ሆይ፣ ድፋት እናንተ የ‹‹ቤተክርስቲያንን›› የተሰላቸ ምግብ የያዛችሁ ከአይበታችሁ አራግፉ! እንዲያውም እርሱን የያዛችሁበት ልብስ ጣሉ፡፡ እግዚአብሔር ስለመንግሥቱ ክብር ንጋት ንቆታልና፡፡ የሜ - ቴቄል - ፋሬስ ድምፀት ይህ ነው፡፡

ጭቃ ሊሻር በገዛ ሕይወቱ ሌት ግብጥ ያዘጋጀው ብልጣሶር ለመቁና ለመሻሩ ምን ያህል እግዚአብሔር በገዛ ልቡ እንደጣረ እናያለን፡፡ ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ግዙፍ ብትሆንና አሁን ያለው አካሄዷም በሰው ፊት ደምቆ የሚነቃነቅ ቢመስልም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበልነው መልእክት ግን ስለበለጠው የሕይወት ክብር መሻሯ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈጽሞ በሥራዋ እንደሌለ ልንነግራችሁ እንወዳለን፡፡ ይኸው እግዚአብሔር ሥራዋን ሊያይ ትወልዱን በቀደመች ልጆች ወርዶ ቋንቋዋን እንዳደበላለቀበት እያየን ነው፡፡ አንድ አጥቢያ የአንዱን ያለምንም የሕይወት ብልጫ ይንቃል - አይቀበልምም፡፡ ግና ከ2000 ዓመት ጀምሮ ያለውን የሕይወት መለጥ ይዛ እርሱም ሰፊ ሜዳ ሆኗት ልትሠራ(ዘፍ.11÷2፣4-6) የጀመረችው መንፈሳዊ ቤት ትቀጥል ዘንድ አልተቻላትም፡፡ ወገኖች እኛስ ከዚህ እናመልጥ ይሆን? እግዚአብሔር ባበራልን መለጥ ተመችቶን ወደፊትም ለሌላው መዘርጋት እስኪያቅተን ተጫጩኖን የሃይማኖት ተቋም ሠርተን ልንስፋፋና ሰፊ የአሠራር ሚብ ልንዘረጋ ከደፈርን የሕዝቡ ቁንጮ ሆነን በጥቅስ ብልጫ ለኑሮአችን ከሠራን፣ እንዳንሠራ አንከለከልም፡፡ ግና አንዳችን የአንዳችንን እንዳንሰማ እግዚአብሔር በሜ ቴቄል ፋሬስ ድምጹ አይመታምን? ይሄ ነው ጥፋት!!

ለመሆኑ የማን አጥቢያ ነው ስሕተት? በቅንነት ካሰብን የሁሉም ሃይማኖት ምሥረታ እውነትን ከመፈለግ የተገኘ የሰው ልብ ወጤት ነው፡፡ ይህ ስለሆነ አይደለም - ስለ ‹‹ጥምቀቱ›› መፈካከቱ? ገና በሕይወታችን መላት ስላልተገለጠ ‹‹ስም›› መጣላታችን? እነዚህ ሁሉ የመጀመሪያ ነገር ላይ መጫጭ የሚለታችን ወጤት ነው፡፡ የአንዱ አጥቢያ ስሕተት እንዴት ጎላልን? ለዚህ የሕይወት ብርሃን የሆነው ክርስቶስ ሊያበራልን ይገባል እንጂ የ‹‹እኔ ነው ትክክል›› ያልነውን ሌላው እንዳይቀበል እግዚአብሔር ሚድረጉ፣ ጠብ በመቀባበል የጀመርነውን ትልቅ የሃይማኖት ተቋም በዓለም ላይ እንዳይቀጥልእግዚአብሔር እየተገዳደረን አይደለምን?አዎ! ምክንያቱም የዓለምን መንግሥት የሚያስተምረው ሕዝብ አያያዝ ተመክሮአችንን እንጂ ሕይወትን አይደለምና በለዓምን የተቋቋመው የእግዚአብሔር መልእክ በእያንዳንዳችን መንገድ እየገጠመን ነው፡፡ አንዋሽ! ነፍሳችን ታክቷታል! የእግዚአብሔር ሰይፍ ‹‹አህያችንን›› አስጨኳል! ለምን አንወርድም?

ዳንኤልም ከሚዳቱ ጥልቀት የእግዚአብሔር ጣት የጻፈችውን ሦስት ቃላት በብዙ ትርጓሜ እንደተናገረ መንፈስ በእኛ የሚለውን ስሙ፡ እግዚአብሔር በየትወልዱ የዘላለም ሐሳቡን እየፈጸመ ይህንንም ትወልድ ከትወልድ እየተቀበለ ወደፍጻሜውና ወደ ማጠቅለያው እንዲያመጣው እናመልከዋለን፡፡ ስለዚህም በየትወልዱ የሚሠራ የሚፈጸምም እግዚአብሔርም ራሱ የሚለጥበት ሞርሐና አሠራር እንዳለው ካለፉት ትወልዶች ልንማር የግድ ነው፡፡ የምናመልከው አምላካችን እግዚአብሔር መላወጥ በእርሱ ዘንድ ሳይሆን በየትወልዱ ግን የሠራው አንደኛው ከአንደኛው ሳይጋጭ ነገር ግን በዓይነትም ሆነ በክብር እየገነነና እየበለጠ እንዲሁም እየጨመረ እንዲይዝ እወቁ፡፡ የፍጻሜው ክብር ከጀመረበት ክብር ይልቃል፡፡ ሰው በባሕሪው የጀመረበትን ሚድነቅ ይወዳልና የሚቃጥለውን ለመቀበል በራሱ ሚዝን መዘኖ ቢቸገርም እግዚአብሔር ግን ሁለተኛውን የሚቃጥለውን እንዳስበለጠ እንነግራችኋለን፡፡

‹‹ከፊተኛው ይልቅ የዚህ የሁለተኛው ቤት ክብር ይበልጣል፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በዚህም ስፍራ ሰላምን እሰጣለሁ፣ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡››(ሐጌ.2÷9)፡፡

‹‹አዲስ በሚሉቱ ፊተኛው አስረጅቶአል አሮጌና ወራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቧል›› (ዕብ.8÷13)፡፡

የክብር ብልጫ አለ፡፡ እርግጥ ነው ፊተኛውን ወስጥ የሚዳሰሱ፣ የሚታይ ታቦት(point of contact) አለው፡ ሁለተኛው እንደ ሐጌ መጽሐፍ ከሆነ ግን ያለ ቦታው ነው፡፡ የሚታየው የለበትም ስለዚህ በፊተኛው ብዙ ዘመናት ዕድሜአቸውን የፈጁ የሁለተኛው በዓይናቸው ፊት ከብሩ ሊገንላቸው አልቻለም(ሐጌ.2÷3፣ዕዝ.3÷12)፡፡ እግዚአብሔር ያከበረውን ዘመን የፈጀው የቀደመው ሥርዓት ሲንቀው በእኛም ትወልድ እያየን ነው፡፡ ‹‹ጳንጠቆስጤ›› ስንት ዘመኑ ነው? የሚቃጥለውም ትወልድ ገና እናስተላልፍለታለን? ምን አልባት በአንድ ትወልድ ወይም ቢበዛ በሚቃጥለው ተደርጎ ከእርሱ ያለፈውንና በክብሩ የሚበልጠውን ሌላው እንዲያገኘውስ አስበን እናወቃለን? እግዚአብሔር በእርግጥ በትወልዱ ከዚያም ዘለግ ብሎ በገዛ ሕይወታችን

እንዲፈጸም ያየው ሐሳብ፣ ወይም ፍጻሜ አባትነት ምንድር ነው? የእግዚአብሔር ሞዝን ከሕይወት ዕድገት ጋር ነው፡፡ በተገኘበት፣ ባሰበበት፣ በተናገረበት ካልተገኘን ትወልዱም ካልተገኘ የእግዚአብሔር ጣት የሆኑ ቀዳሚዎች በሜ፣ ቴቄል ፋሬስ ድምፃቸው ሁሌ እንደሚያወኩን፣ ወገባችንንም እንደሚፈቱ እንነግራችኋለን፡፡

አሁን የምትለማመዱትን ልምምድ፣ ትምህርት፣ ኑሮ... በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትእንዳለው በለመዳችሁት የሃይማኖት ልብ ጥንካሬ ከሮሜ ከቆሮንጦስ... አጣቅሳችሁ በግድና በኃይል ልታረጋግጡ መጣደፋችሁን ተዉ፡፡ እግዚአብሔር ከሕይወታችሁ ጥልቀት፣ በእናንተ ከሚኖረበት ብቃት በእናንተም ከሚሠራው ችሎት ተነሥታችሁ ተናገሩ፣ አስተምሩም፡፡ የተናቀ ነገር ሳይታወቅ ብዙ ዕድሜ ሲያስቆጥር አይተናልና፡፡ ለምን ታዲያ አልተባባባንም?ለምንስ የያዝነውን ብቻ እውነት ነው አልን?የምንሠራው ‹‹መንፈሳዊ ሥራ›› የተኮረጀ ነው፡፡ ጳውሎስ እንዳለው ጴጥሮስ እንዳለው እያልን የሌላውን ደም - ሕይወት በሕዝቡ ላለው እግዚአብሔር እያቀረብን ነው - ይህ ደግሞ አሮናዊነት ነው፡፡ ለትወልዱ በዚህ ትወልድ መጭትሄ ሊኖር ይገባል፡፡ እግዚአብሔር ከሕይወታችን ጥልቀት የምንመገበውን ‹‹ምዕመን›› ካልመገበ ሞዝኑ ላይ ‹‹ኪሎአችን›› ምን ያህል እንደሆነ እያየን ነው፡፡ ይህን ‹‹ክብደታችን›› ለሞደግና የያዝነው እውነት ፈጽሞ አለሞጀቱን ላለሞሰወቅ ወንድሞች ቀድመው ያዩትን ይዘው ሲገለጡ አንራም፣ ጥፋትም አናወጅ፡፡ ለ‹‹ኪሎአችን›› ሳስተን በትወልዱ ካለው ራእይ ተቆርጠን ካለፈው ትወልድ ጋር እንዳንደመር እንፍራ፡፡ ትወልድን መቅደምም ሆነ ኋላም መሆን በዕድሜ አልተደረገም፡፡ አሁን በሐዋርያት ዘመን ባለች ቤተክርስቲያን ከበብ ካልኖርክ እያለ በስንትና ስንት ዕድሜ ልዩነት ያለውን ይህንን ትወልድ የሚያስጨንቅ ቤቱ ይቁጠረው፡፡ ሰዶም እርሷ ዘንድ ባለው እውነት ቅፍርናሆምን በኪለዋ አንገጫገጫች፡፡ ጤሮስና ሲዶናም ከኮራዚና ከቤተ ሳይዳ ጋር ሲመዛኑ ከበድ ብለው በልጠዋል፡፡ ቅለት ነው እንግዲህ መጥፎ፡፡ አያስደንቅምን? ቅፍርናሆም በሌላ ትወልድ መካከል እያለች ግን ኑሮዋ ከሰዶም ትወልድ በፊት መሆኑ? እኛስ አሁን ካለው የእግዚአብሔር ራእይ በትወልድ ጋር ተመዘንን የት ተገኘን? ‹‹ቤተክርስቲያን›› ምሽት ላይ ናት፡፡ ይኸው በግብዣዋ ላይ የእግዚአብሔር ጣት የሆኑ ልጆች የጳውሎትን ሜ - ቴቄል - ፋሬስ!! የእናቴ (የቤተክርስቲያኔ) ልጆች ሆይ የአባታችንን የልብ ሐሳብ እናዳምጥ! ዘሞኑ ከእናታችን ጓዳ ይልቅ የአባታችንን ድንኳን የምንመደብበትና ጠኑ የመጣላችንም ሽግግር ይሁንልን፡፡ (አሜን!)

ኋላውን - ጀርባውን የተከተለ ትወልድ

‹‹እንደ ተቀመጣቸሁበትም ዘመን መጠን በቃዴስ ብዙ ቀን ተቀመጣቸሁ›› (ዘዳ.1÷46)፡፡

ይኸው ሁለት ሺህ ዓመት ቤተክርስቲያን በቃዴስ! የዛሬው ሞእክታችን ከሌላው ጊዜ የበለጠ ኃይለኛ ቢሆንና ቢገስጽ አሁንም በፍቅር ሁነን ነውና ታገሡን፡ ተግሣጹም ለምታነቡትም ለምንጽፈውም ነው፡፡ እንግዲህ ስሜ እስራኤል ያን ያህል ዓመት በቃዴስ የተቀመጠው ከሰላዮች ከሰማው ቃል በማሣት ነበር፡፡ የአሥሩ ቃል የእስራኤልን - የዚያን ማነበር ዕድል ወሰነው፡ መውጣትን - መሬድን - መድረስን እምቢ አሉ፡፡ ለዚህ ነበር ዕድላቸው እዚያው ለዚያው መዞር የሆነው፡፡ እንዳልናችሁ ይህ ሕዝብ በተደጋጋሚ መሞሪያ ሁኖናል፡፡ ያም ወገን የራሱ የሚይሆነውን - የሚወርሰውን መዞር የጀመረው ከእግዚአብሔር ፍርድ በኋላ ለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሕዝቡ ግን ይዞረው የነበረውን እግዚአብሔር እንደተወው አላወቀም፡፡ ልሞድ እንዴት ከፉ ነው?!... እግዚአብሔር አምላክ በኮሬብ የጀመረውን በሲና፣ በኤሊም፣ በቃዴስ... ሁሉ ቀጥሏል፡፡ መናወ፣ ደመናወ፣ እሳቱ፣ ጥበቃው... እንደነበሩ ነበሩ፡፡ እነዚህ ግን ምን ጊዜም የእግዚአብሔር ሁል ጊዜ ከእኛ ጋር መሆን ሞረጋገጫ አይደሉም፡፡ እነዚህ ሁሉ ያ ሕዝብ አንድ አንድ እያለ እስኪረግፍ ድረስ ነበሩ፡፡ እነዚህም ሕዝቡን ያገለግሉ ነበሩ እንጂ ያዳኑ ወደ ፈቃዱም የነጠቁ አልነበሩም፡፡ ይሄ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአል፡፡

ቤተክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እነሆ፣ እስከ ዛሬ በተመሠረተችበት ልምምድ ትመላለሳለች፡፡ አዲስ ነገር ሳይኖር ያንኑ አድሳ - ‹‹ሞዲፋይ.. አድርጋ የራሷን ‹‹ቃዴስ›› እየኖረች ለመሆኑ የማንም ሕይወት ምስክር ነው፡፡ ከቃዴስ ወደ ቃዴስ ምንም አዲስ ነገር ሳይኖር፡፡ በቤተ ክርስቲያን ጳንጠቆስጠም ሆነ ካሪዝማቲክ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው፡ ካሪዝማቲክ የጳንጠቆስጤ ግልባጭ ነው፡ አላዋቂነት ብቻ እነዚህን ሁለት ያደርጋል፡፡ በእግዚአብሔር የዘላለም ዓላማ ግን የእነዚህ ሞርጀት የቃዴስ ፈጽሞ መረሳት ይሆናል፡፡

በዚያ ትወልድ መካከል ‹‹እግዚአብሔርን ፈጽሞ የተከተለ›› አንድና ሁለት ሰው ብቻ መገኘቱ ትንግርት ነው(ዘዳ.1÷36)፡፡ እውነት ነው፤ በትወልድ ሁሉ ቅሬታዎች ነበሩ፡፡ ካሌብና ኢያሱ ከእነዚያ ይራመዳሉ፡፡ ትወልዳቸውን ኮነኑት፡፡ አስረጅት፡፡ ዋጅት - አበሩት፡፡ ካሌብ በልቡ የነበረውን ቃል ሲሞልስ በዚያ ወድ ልብ ወስጥ የእግዚአብሔር ቃል ነበር(ኢሳ.14÷7-9)፡፡ ዘሞኑ ግን የሕጉ ዘመን ነበር፡፡ ሕጉም በሞጽሐፍና በድንጋይ ተጽፎአል፡፡ ካሌብ ግን አንብቦ አልተናገረም፡ ዳሩ ግን በልቡ የተጻፈውን ተናገረ፡፡ ካሌብን ስናስብ የዕብራውያንን ሞልእክት ምዕራፍ ስምንት ቁጥር አሥርን እናስተወላለን፡፡ እግዚአብሔር በተናገረለት አዲስ ኪዳን ሕዝብ ሕጉን በልቡ እንደሞጽፍ ብሏልና፡፡ በዚያ ዘመን በካሌብ ልብ

ሕጉ ተገኘ፡፡ ለእርሱ አዲስ ኪዳን ሆነ፡፡ በዚያም የእነዚያን ዘመን አስረጀ፡፡ ዛሬአቸውንም ትላንት አደረገው - የተባረከ ይሁን!

ድርጅታዊቷ ቤተክርስቲያን እንደምታረጅ - እንደምትደክም - የተሰጣትም ዘመን እንደሚዘጋ... ያልገባው ወገን ልጅነትም በአባትነት ያረጃል- ያልቃል ቢሉት ፈዝ ሊመስለው ይችላል፡፡ ከቤተክርስቲያን ማንነት ወጪ ሌላ የሚይታየው የቤተ ክርስቲያን ሰው እንዲህ ዓይነቱም ሞኣእክት ዕብደት ሊመስለው ይችል ይሆናል፡፡ ነቢይ ግን በትውልዱ ‹‹እንደ ዕብድ›› ካልተቆጠረ እውነት እንላችኋለን፣ ነቢይም አይደለም፡፡ ትውልድን ሞኙ(ሳይሞጥ) የሚያሳፍር ሞኪብ ለቤተክርስቲያን ነው፡፡ ነቢይ ግን ሞኪቡን በሚመጠም በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ስለሚጅድ ከእርሱ ጋር ያለእግዚአብሔር አጃቢ የለውም፡፡ ነቢይ ሟች ሰፊው ወገን የተቀበለውን እየጣለ - እየረሳ - እየተወ... ወደ ጠባቡ መንገድ ፈቀቅ የሚል ነው፡፡ በእርግጥ ወዳችን በተኛንበት መጮቶ - እጁን በቀዳዳ አሾልኮ ይነካናል፡፡ ከምኞታችን - ከሞቀን ስፍራ ይረብሸናል(ሃሌሉያ!) - ይቀሰቅሰናል፡፡ ተነሥተን ስንከፍትለት ግን የለም፡፡ ፈቀቅ ብሎ ሄዷል፡፡ በተኛንበት - በማንነታችን አልጋ - አሁን ባለንበት ያገኘን ዘንድ ቢሆን እኛን መነካቱ ወይም ባለንበት ከእኛ ጋር ሊሆን ፈቀቅ ባላለም ነበር፡፡ እንግዲያወስ ፈቀቅ ሟለት አለብን ፈቀቅ ሟለትን ከእርሱ ተምረናልና፡፡ በመንዳችንም ከተሟይቱን፤ ኢየሩሳሌምን የሚጠበቁ ቢያገኙን ጥለናቸው መሄድ ይኖርብናል፡፡ እነርሱ ሊነግሩን አይችሉም፡፡ ኢየሩሳሌምን የሚጠበቁት ከመጋቢዎች ሌላ ናቸውን? እነዚህ ከተሞቹወን (ዲኖሜሽናቸውን) የሚጠበቁ ወዳችንን ሊያሳዩን አይችሉም፡፡ እርሱ ፈቀቅ በሟለት ብቻ ይገኛል፡፡ ዛሬ ካለንበት ሰፈር በራሱ ማንነት ወደ ራሱ የጊዜው ቃል በመላት ካልወጣን በለመድነው ብቻ መኖራችን መሆኑን ልብ አድርጉ፡፡

በጉባኤዎች(ጳንጠቆስጤ ጉባኤዎች የበዙበት ልምምድ ነው፡፡) መካከል እንደካሌብ የወስጠን (የልቡን) መዘገብ ከእግዚአብሔር ብቃት ከፍቶ ቃሉን የሚያወጣ ወገን አለ፡፡ በእነዚህም የቤተክርስቲያን ዘመን ሳያወላዳ ያረጃል፡፡ ያረጀወም ነገር መላወጡ አይቀርም፡፡ ሰዎች እስከዛሬ የያዙት - የለመዱት - እስከ ዛሬ ያገለገሉበት - የቃዴስ ዙረታቸው ይፈጽመታል - ያስረጁታል፡፡ ዛሬ - አሁን ካሪዝማትከም ጳንጠቆስጤም አይደለም፤ እንደ እግዚአብሔር ጊዜ - በተለይ እንደ እግዚአብሔር ልጅነት ራእይ ካየን፡፡ የመነሣቱ ሟለዳ(ንጋት) በርቷል፡፡ የብዙዎች ‹‹ዛሬ›› በጥቂቶች ብርሃን (ንጋት) ትላንት ሁኗል እነርሱ ባያወቁትም፡፡ የድንኳኖችና የጉባኤዎች መነፈስ የሌለባቸው ጥቂት ወገኖች ድንኳኖችንና ጉባኤዎችን አስረጅተዋል፡፡ ያለ የሚሞላው ነገር እግዚአብሔር ትቶታል፡፡ እግዚአብሔር ሟኬን ዓለቱን ተናገረው ብሎት ሳለ እንደለመደው መትቶ ውኃ ቢያወጣ ድንቅ አይደለም፡፡ አሮጌው እንደትላንት ቢሠራ አዲስ ነገር መፍጠር አይደለምና እንደ መነፈስ እናስብ፡፡ ደግመን እንላለን፡- ያለ የሚሞላው ነገር እግዚአብሔር ትቶታል፡፡

ይህንን እውነት ከሕይወታችሁ፣ ከአገልግሎታችሁ ወይም ከምታገለግሉት ሕዝብ ሟት አትችሉምን?... ማንም ከአሥር ዓመት በፊት በነበረው መንፈሳዊ አቋሙ ላይ አይደለም፡፡ ለሕዝቡ የምንሰጠው ቃል ጠፍቶብናል፡፡ የእረኝነታችን ብቃት ትልቅ ፈተና ወስጥ ወድቋል፡፡ ልምምዶቻችን አብዛኛዎቹ ወሸት እየመሰሉብን ነው፡፡ እረኝነታችን አታክቶናል፡፡ ከግዴታ፣ ከኃላፊት፣ ከምንቀበለው ደመወዝ... እንጂ ከተትረፈረፈ ሕይወትና ማንነት ማገልገል የሰማይ ያህል ርቆብናል፡፡ ሁሉ ነገር ከልባችን እየወደቀ ነው፡፡... እግዚአብሔር ወደ ሌላው ሐሳቡ ተሻግሯል፡፡ የሰወረወን እየተረተረ ይገኛል፡፡ ወገኖች ሆይ፣ ከሚራመደው እግዚአብሔር ጋር እንራመድ፡፡ እስራኤል የአርባ ቀን መንገድ ለአርባ ዓመት ተመላለዘበት፡፡ የሄደወን መንገድ ሄደ፡፡ ያለፈወን ሰፈር አለፈ፡፡ የኖረወን ደጋግሞ ኖረ፡፡ ያወቀወን እስኪያታክተው አወቀ፡፡ ያየወን እስኪጠላው አየ፡፡ በጀርባው ምሪት የኋልዮሽ ሄደ፡፡ ስመ፤ አስተወሉ፡፡ ለቤተክርስቲያን የሆነው ይኸው ነው፤ ለቀባሪ ሟርዳት ባይሆንብን፡፡ ወዶች ሆይ፣ ራሳችንን አናታልል፡፡ ታሪክ ተደግሞበናል፡፡ እስራኤል በምድረበዳ አርባ ዓመት ያንኑ መንደር - ሰፈር መመላለሱ ምን ይደንቃል የራሳችንን ጉድ ሟት ከቻልን፡፡

ቤተ ክርስቲያን አርባ ኢዩቤልዩዎችን ማክበሯ የባሰ አይደለምን? ጳንጠቆስጤ አርባ ኢዩቤልዩን አሳልፏል፡፡ አርባ በኅምሳም ሁለት ሺህ ዓመት ይሆናል፡፡ አወይ፣ ሟቅ! ሁለት ሺህ ዓመት እነሆ፣ በጳንጠቆስጤ!! ያታክታል፡፡ በእርግጥ ይሄም ቢሆን የእግዚአብሔር ፕሮግራም ነው፡፡ አሁን ግን እግዚአብሔር አልፎ ሄዷል፡፡ አሁን በአዲሱ የመለጡ ስፋት ሌላወን ወገን እየሠራ ይገኛል፡፡ በምድረ በዳ የተወለደው ወገን ይወርስ ዘንድ ከግብፅ የወጣው በምድረበዳ እንደቀረ ዛሬም ታናናሾች ይወርሱ ዘንድ በቀደመው መንገድ ለመሄድ ከቀደመው ልምምድ ጋር የተጣበቁት ብዙዎች ‹‹በታዴሳቸው››(በራሳቸው ምድረበዳ) እየሰሙ ናቸው፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ያንን በታናናሾች የተገነባወን ወገን ወደሌላ ወገን ያፈለሰው ካሌብንና ኢያሱን እንደ ዘር ተጠቀመባቸው፡፡ ዛሬም እግዚአብሔር በጥቂቶች የመረተውና እየገለጠው ያለው መነግሥቱ የብዙዎችን ግዛት እያስረጀው አይደለምን? አባታችን ዛሬ በጳንጠቆስጤ ወይም በካሪዝማቲክ ወይም በፈይዝ መቸመንትስ... ሐሳቡን ሁሉ ይጨርሳል - ይፈጽማል - ይሞላል... ብሎ ማንም አያስብ፡፡ በዚህ ነገር ማንም አይታለል፡፡ እነዚህ ሁሉ የስድስት ቀን አገልግሎቶች ናቸው፡፡ እግዚአብሔርም በስድስት ቀን ሥራወን ሠራ እንጂ አልፈጸመም፡፡ እግዚአብሔር ሥራወን የጨረሰው የፈጸመው) በሰባተኛው ቀን ነው(ዘፍ.2÷1-2)፡፡ ጳንጠቆስጤ የሰባተኛው ቀን (ወር) በዓል አይደለምና እግዚአብሔር በእነርሱ አይጨስም፡፡ በሰባተኛው

ወር የሚሆነው በዓል የመከተቻ - የዳስ በዓል ነው፡፡ ሰባተኛው ቀን የመግሥቱ መላት ጀምሮ ለሚጸጸም የሚለጥበት ነውና ከእንግዲህ የምናገጠው በእርሱ ብቻ ይሆናል፡፡

በፍጻሜ - በመላት - በመንግሥቱ ግዛት መለጥ ጨፈቃም ፀሐይም አለመኖራቸው አንዳች ምሥክር አለው፡፡ ቤተክርስቲያን ለዘመናት በእነዚህ እንዳገጠች የታመነ ነው(ራእ.12÷1)፡፡ ለዮሴፍ የሰገዱት ፀሐይና ጨፈቃ አባቱና እናቱ ከሆኑ ዛሬ የቤተክርስቲያን አባቶችና እናቶች በቤተክርስቲያን ናቸው፡፡ በመንግሥቱ በእነዚህ የሚገኙ የለም፡፡ መልከ ጼዴቅ አባትና እናት የለወምና በእርሱ ጥሪ - ቅባት - ምርጫ የሆኑት ፀሐይንና ጨፈቃን ያስረጃሉ፡፡ ዳግመኛ በእነርሱ አያገጠም አይገለገሉምም፡፡ ምንም እንኳ ነገር ሁሉ ከእርሱ ቢሆኑም ስለመንግሥቱ ሁሉም የሌሉ ይሆናሉ፡፡ ሁሉን የበለጠው ክብርም ወደ መንግሥቱ ይቀበላቸዋል፡፡ ስለዚህ ዛሬ ሁላንተናችንን አሁን በመፈስ ላለው ወደፊት ግን በግልጽ ለሚለጠው ዋና ነገር እንመዝረው፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ዛሬ ያልተሸጠ ነገር በመንግሥቱ ሊገኝና ሊኖር አይችልምና እንደ ልጁ እናስብ፡፡ ሁሉን ነገር ወደ ራሱ ይስብ ዘንድ ሁሉን መኮው አንዳች ምላሌነት አለወና ቸል አንበል፡፡ ዛሬ በምድራችን በተገኘው ነፃነት እየበዙ ያሉት መንፈሳዊ የነፍሳት ድርጅቶች የምንለወን፣ የእግዚአብሔርን ዋነኛ ሐሳብ ሊሥሩ አይችሉም፡፡ ምንም ቢያሳምም ስማ፤ የፓስተሮችና የሐዋርያት ብዛት እግዚአብሔር ዛሬ ባለው ፕሮግራም መሠረት አንዳች የሚያጣት ለወጥ የለም፤ በተለይ በለመዱት መንገድ የኋልዮሽ እንሂድ ካሉ፡፡ የእግዚአብሔር አሠራር ተለወጧል፡፡ ያለፈወን ታሪክ የሚትቱ መንፈሳዊ ጎልማሶች እነርሱ ወደወደዱት እንጂ እግዚአብሔር ዛሬ ወደ ተነሣለት ድንቅ ፈቃዱ ሊራመዱ አይችሉምና በመንግሥቱ የምሥራች እነዚህ እንደ እድፍ ናቸው፡

‹‹ይህች ትወልድ እርሱን የምትፈልግ ናት፣ የያዕቆብን አምላክ ፊት የምትፈልግ›› (መዝ.24÷6)፡፡ በየዘመኑ አንድ ትወልድ በአንድ ማንነት የሚኖር አንድ ወገን አለ፡፡ እርሱ የተለየ ነው፡ ያለበትንም ትወልድ በእግዚአብሔር የዘላለም ሰንሰለ (ሐሳብ) ትወልዱን ያለፈ ነው፡ እርሱም ትወልዱን ኮንኖ ያድነዋል፡፡ ኖኅ በትወልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ፡፡ ታዲያ በትወልዱ ነው፡ ከትወልዱም ወጭ የሚበበው በዚያ ትወልድ የሆነወን ነው፡ ያንን ትወልድ ግን ኮንኖ አጸደቀው (ዕብ.11÷7)፡፡ ያንን ዓለም አጥፍቶ አገኘው፡ ትወልዳቸሁን በምን ኮነናቸሁት?... ኖኅ በትወልዱ ነውና አዲስን ነገር ያደረገው በዚያው በእግዚአብሔር መንፈስ በትወልዳችሁ ላይ ምን አደረጋችሁ? ኖኅ አሮጌወን ዓለም በጽድቅ ካስረጀና ከኮነነው በኋላ ወደ አዲሱ ዓለም - ወደ ቃል ኪዳን በቀስተ ደመና ምልክት ተቀበለው፡ ኖኅም ካዳነው ቤተሰብና ፍጥረት ጋር አብሮ እንደ በኩሪት - እንደ ቅሬታ - እንደ ዘር ወደ አዲሱ ዓለም ገባ፡፡

ይህንን ትወልድ ከስብከት ወይም ከትምህርት ባለፈ በምን ኮነንነው?... ሕይወታችን ከትወልዱ ጋር ሲስተያይ የት ነን? ከትወልዳችን እንወጣ፡ ሕዝቅኤል የትወልዱ ነቢይ ነበር፡፡ ግን በዚያው በእነርሱ መካከል ተቀምጧል- ከምርኮኞች ጋር፡፡ ግን ለነበረበትና ለሚቆጥሉት ትወልዶች ራእይ ለሞት በተጠራ ጊዜ ከምርኮኞች መካከል ተለይቶ ወጣ፡ ከትወልዱም ወጥቶ የትወልዱን ነወር አየ፡፡ ከዚያ በፊት ግን የእግዚአብሔርን ራእይ ነው ያየው(ሕዝ.1÷28)፡፡ ያኔም መቆም አልቻለም፡ ሕዝብን ከሞቱ በፊት እግዚአብሔርን አየ፡፡ ይሄ ነው በትወልዳችን ጻድቅና ፍጹም የሚያደገን፡፡

በዚህ በጳንጠቆስጤ - በቤተክርስቲያን ዘመን ፍጻሜ - መላት ከሌለ ‹‹መሉ ወንጌል›› አለን ሚለታችን ምን ሚለት ነው? የርስትን መያዣ(ቀብድ) መቀበል ምኑነው መሉ የሚያደገው? እግዚአብሔር በጳንጠቆስጤ የመንፈስን (የርስትን) መያዣ ነው የሰጠው፡ አይደለም እንዴ? ነው እንጂ፡፡ መላት ገና ነው፡ ያለን - አሁን የያዝነው የመንፈስ በኩራት ነው(ሮሜ.8÷23)፡፡ ብዙ ወንድሞችና እኅቶች ራሳቸወን ሲያታልሉ ራሳቸወን ‹‹መሉ ወንጌል አሟሾች›› ብለው ይጠራሉ፡፡ በእርግጥ ድርጅታቸው እንጂ እነርሱ ‹‹ዶሮ ሲያታልሏት…››እንደተባለም ሌሎችን ጨምረው ያታልላሉ ራሳቸወን ባታለሉበት መንፈስ፡፡ አንድ ሰው እንዳለው ጳንጠቆስጤ ከኅምሳ እስከ ስድሳ በመቶ ነው፡ ይሄ መሉ ወንጌል አይደለም፡ እግዚአብሔር ብቻ መላት አለወና መላት በሚያደርግበት በዚህ ዘመን ለሚያመጣው የመንግሥቱ መላት መሣሣት አለብን፡፡ ይህም የሚሆነው ‹‹ቃይሰችንን›› ከተወነው ብቻ ነው፡ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ልሣን መናገር እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያደገው አስደናቂ በረከት ቢሆንም በዚህ ብቻ ራስን ማገኘት ወደ መሉ ወንጌል መድረስ አይደለም፡ ጳንጠቆስጤ እኮ ሁለተኛ ሰሚይ ነው፡ ሁለተኛወስ ሰሚይ እንዴት መሉ ተብሎ ይጠራል?

ለአባቶች እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚቻል አምላክ ተገለጠ(ዘጸ.6÷2-3)፡፡ ለወንድማቸን መቼ ስመ እግዚአብሔር (ያህዌህ) ተገለጠለት፡፡ እርሱም ለአባቶች የተገለጠበት መገለጥ ለመቼ በተገለጠበት መገለጥ አስረጀው፡ እግዚአብሔር በሚበልጥ መገለጥ መጥቷልና - ወርዷልና! ስለ ትወልዱ የተገለጠበትን የራሱን መገለጥ ነው በበለጠወና በሰፋው በራሱ መገለጥ አስረጅቶ ነባሩን የሚሽረው፡ ያለፈወን አድከም ይጨሳል፡፡ በሕጉም መመረድ አዲስ ነገር ተሰጠ፡ የሕጉም ዘመን የነቢያት ጊዜ ታክለላት ብዙ ዘመን ፈጀ፡፡ ይሁን እንጂ እርሱም እስከ ዮሐንስ ደርሶ ተገታ፡፡ በዮሐንስና በክርስቶስ የመንግሥቱ የምሥራችም በሕግ ላይ ሞሸ፡፡ ደቀመዛሙርትም በጀመሩት የቤተክርስቲያን ዘመን አዲስ ጊዜ ጀመረ፡፡ ከሕጉም በኋላ ቀሪወን ሁለት ሺህ ዘመን ያካለለው የቤተክርስቲያን ዘመን ነው፡ በእነዚህም ብዙ ጉባኤዎች፣ ከተሞች፣ ሥርዓቶች፣

ትምህርቶች... ተፈጥረው እስከ ዛሬ ዘለቁ፡፡ በእነ ጳውሎስ የሆነው ጸጋ የሕዑ ጊዜ ተሸሮ አዲስ ስፍረ ዘመን - የቤተክርስቲያን ዘመን እንደ ጀመረ የቤተክርስቲያን በመንግሥት ልጆች ሲያልቅ እንደገና አዲስና ልዩ ስፍረ ዘመን ይጀምራል - የመንግሥቱ ዘመን! ይሄ ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ድንቅ ነው፡ ያለውን ትተን በፊት ለፊታችን ያለውን የመጮራቱን ከፍ ከፍ ያለውን ዋጋ ለመያዝ እንዘርጋ፡፡ ‹‹አሁን ያለውን እየረሳሁ›› ካለም አሁን ያለውን በምንይዘው እናስረጀዋለን፡፡ በቤተክርስቲያን አሁን ያለው ማንኛውም ስጦታ፣ አገልግሎት፣ ልምምድ፣ ትምህርት፣ ሥርዓት... ያረጃል - ያልቃል - ይደክሟል፡፡ ከዚህም በኋላ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት፣ ሞገስ፣ ክብር፣ ብርሃን... በሁላችን መኖት ይጀምራል፡፡ ይሄ የምናወራለት ነገር ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ ጅማሮ ላይ ነውና በመንፈስ የምታዩበትን የልዑሉን ብርታት ያዙ ብለን እንመክራለን፡፡

ከእግዚአብሔር ሐሳብ ወድቀን አስከመቼ ነው የድንኳኖችና የጉባኤ መሪዎች የምንሆነው?... ከ1948 እስከ 1953 ዓ.ም እ.ኤ.አ የኋለኛው ዝናብ እንደተሰጠና በዓለም ታላቅ ሥራ እንደተካሄደ ታሪክ ይነግረናል፡፡ በዚህም ሰማያዊ መነቢኘት ሞላት የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ አያሌዎች ድንኳናቸውን አፍርሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነፈሱ ለጥቂትም ጊዜ ቢሆን፡፡ ዘግይተው ግን ሁሉም በየግላቸው ድንኳን ሰፍተው በሌሎች ላይ መከፈፍ ጀመሩ፡፡ አገልግሎቶች(ሚኒስትሪዎች) እንደ አሸን የፈሉት ከዚያ ታሪካዊ እንቅስቃሴ በኋላ ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃ አለ፡፡ ለምሳሌ፡- ፉልነስፐል ቢዝነስሜን፣ ዴሊቨራንስ ሚኒስትሪስ፣ ሂሊንግ ፋውንዴሽንስ፣ ፉል ሳልቬሽን ፋውንዴሽንስ፣ ፌይዝ መቭመንትስ፣... ወዘተርፈ በዓለም ጉልህ ስፍራ የያዙት ከዚያ ወዲህ ነው፡፡ ዳሩ ግን ከእነዚህ አያሌዎች ከድንኳን ወጥተው ‹‹የተሻሻለ - የሠለጠነ›› ድንኳን ሰፉ፡፡ ታሪክን ደገመና እኛ ከደረስንበት መለጥ ወድያ ያለው ሐሰት አሉት፡፡ የሌሎችን ነውር በመድገም ‹‹በነቢያት ዘመን በኖርን ኖሮ ይህንን አናደርግም ነበር›› እያሉ የራሳቸውን ጽድቅ አቆሙ፡ የኮነኑትን ሆኑት፡፡ የተቃወመት አገኛቸው፡ የጠሉት ወረሳቸው፡

የሚራመደውን የእግዚአብሔርን ሥራ ብዙዎች ሳያወቁ መቀልበስ ያዙ፡፡ እስከዛሬም በብዙዎች የነበረው ወኔ - የሥጋ ጉልበት የአንደኛውን ከፍለ ዘመን የሐዋርያትን አገልግሎት፣ ስጦታ፣ ዘመን... መልሶ የሞሞጣት አባዜ ነበር፡፡ እንድያውም አሁን - አሁን፡- ‹‹አፖስትሊክ ኤንዴፐሮፌቲክ›› የተሰኘ ዘመኛ ሚኒስትሪ በልዩ ‹‹ጉልበት›› ተጀምሮ ሲካሄድ እያየን ነው፡፡ በዚህም ጅምር እግዚአብሔርን በራሳቸው ልጓም ሁሉት ሺህ ዓመት ወደኋላ ሊስቡት ምኞት አላቸው፡ በዚህ ላይ ይህንን ለማለት አንፈራም፡ ዳግመኛ መሠረት አይመሠረትም፡ መሠረታችን የሐዋርያትና የነቢያት ከሆነ መሠረት በቃን፡፡ ወደፍጻሜው መሄድ አለብን ይሄ ነው የእግዚአብሔር ሐሳብ፡፡ ወንጌላዊነት፣ መጋቢነት፣ አስተማሪነት ብቻ ሳይሆኑ ሐዋሪያነት ነቢይነትም አርጅተዋል፡፡ እግዚአብሔር ዳግመኛ በእነርሱ የሚሠራበት ዘመን እየመጣ ነው፡ እግዚአብሔር(በእነዚህ) በእርግጥ በእጁ መንፈስ ለዘመናት ሠርቷል፡፡ የእጁ መንፈስ ሚሊታችንም አምስቱ የጸጋ ስጦታዎች ናቸው በኤፌሶን መልእክት ምዕራፍ አራት ቁጥር አሥራ አንድ የተመለከተው፡ ከእንግዲህ እግዚአብሔር እነዚህን የሚይሠሩ(inactive) በሚድረግ የመንግሥቱን ዘመን ይገልጣል፡፡ እግዚአብሔር ከእጁ መንፈስ ወደ አፉ መንፈስ (2ተሰ.1÷8) ሊዞር ልጆቹን እያዘጋጀ ለመሆኑ በመንፈሳችሁ ተረዱ፡፡ በአፉ መንፈስ ነውና አወሬውን (ዓመቿኛውን) የሚያርደው የእጁን መንፈስ በአፉ መንፈስ ያስረጃል፡፡ በእጁ መንፈስ(ኤፌ.4÷11) ዘመነ አወሬው ተጨቁኖ እንደሆነ እንጂ አልታረደም፡ ስለዚህ የሚበልጥ ዘመን መጥቷል፡፡ ከድንኳናችን - ከነበርንበት የእምነት አቋም የምንወጣውም ስለዚህ ስለበለጠው ሐሳቡ ነው፡፡

ቤተክርስቲያንን ለማነልገል፣ ለማጽ፣ ፍጹም ለማድረግ የተሰጠኑ የቤተክርስቲያን ስጦታዎች ሁሉ በጊዜአቸው የነበረውን አስረጅተውና ሸረው እስከዚህ ዘመን ዘልቀዋል፡፡ አሁን ግን እነርሱ ራሳቸው የሚይሠሩ፣ የደከሙ ያለቁ... ለመሆናቸው አስረጂዎቹ የሚገለግሉበት ራሳቸው ናቸው፡ በዚህ ጊዜ ግን እግዚአብሔር በስውር የመንግሥቱን ንጋት የሚያጣኑን በራሱ ማንነት እየሠራ ለመሆኑ የምታዩት ዋነኛ ነገር እንዲሆን ይህን ጽፈናል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር በየዘመናቱ ጠቅላላ (ጄኔራል) እና ልዩ ምሥክር! ሥራውን ይሠራል፡፡ ጠቅለል ያለው ሥራው ከቤተክርስቲያን ጋር ሲሆን ዛሬም ስውርና ምሥክራዊ ድንቅ ሥራው ግን ከጥቂቶች ጋር ነው›› ይለናል አንድ የእግዚአብሔር ሰው፡ በእነዚያ ጥቂቶች ነው በየጊዜው ዘመንን አስረጅቶ የለወጠው፡ ዛሬም በእነዚህ ምሥክኛ ጥቂቶቹ የቤተክርስቲያንን ዘመን አስረጅቶ የመንግቱን ዘመን መላት ይገልጣል፡፡ ይህንን ታውቁና ታምኑ ዘንድ ነው ደፍረን ያላችሁበትን ኮንነን ጫፋችን፡፡ እኛም ከእናንተ ጋር በአንድ ስፍረ ዘመን ነንና ለእናንተ የምንለው ለእኛም ነው፡ ከዚህ ዘመናችን - ከደረስንበት ፈረሳችን በመወረድ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ቀን ላይ ለመውጣት እንነሣ ነው ምክራችን

ከአዳም ዘመን ጀምራችሁ እያንዳንዱን ስፍረ ዘመን ተመልከቱ፡፡ የኖኅን፣ የአብርሃምን፣ የሙሴን... ወዘተ፡፡ እግዚአብሔር በአንድ ሰው ሲጀምር እናያለን፡፡ ዛሬ ያለው ዘመን አርጅቶ እየተሻረ ነውና ለአዲስ ዘመን የተፈለገው ስንቱ ይሆን? በእርግጥ ‹‹ከተማይቱ ሰው አልቦ እስከትሆን ድረስ›› እግዚአብሔር ተነሥቶባታል፡፡ የትኛዋ ከተማ? የሰው ከተማ - ዲኖሜሽን ሁሉ! አብያተ ክርስቲያናት በሞርጀት - በመድከም - በመሞት - በጥፋት(ሚር.8÷35)... ወደ ተዘጋጀላቸው ክብር መሞጣታቸው ከከተሞቹው ሁሉ ሰው - አሮጌው የኃጢአት ሰው ካለቀ በኋላ አይደለምን? እንዲህ ስንጽፍ ወይም ስንሰብክ ተግሣጽ ያበዛን፤ ልክን ያለፍን አድርጎ ማንም አያስብ፡፡ ጊዜው የተግሣጽ የዘለፋም ነው፡ በዚህም ወደ እግዚአብሔር ከፍታ

የሚያመልጡ አሉና! ጽሐፋችንን ስሕተት ለማውጣት ሳይሆን መንፈሱን - ጸጋወን ተጠግታችሁ አጤኑት፡፡ በአንድ ልብስ ላይ ጎብረቀለማት ይብዙ እንጂ ልብሱ አንድ እንደሆነ የዚህ ጽሐፍዓይነት ቢበዙም ሚእክቶቻችን አንድ ነው - የእግዚአብሐር መንግሥት! አዎን፤ ሰባቱ ቀለማት አንድ ቀስተደመና እንደሚሥሩ ሚእክቶቻችንም እንዲሁ ናቸው፡፡ እግዚአብሐር በዚህ ዘመን መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት ለሚለው ነገር ቆመናል - አሮጌው ዘመን፤ አሮጌው ሰው፤ አሮጌው ሥርዓት፤ አሮጌው አደራረግ ሚለፉንና የመንግሥቱን መማጣት ማበሰር! በዚህም ማንም ጀርባወን ተከትሎ እንዳይጓዝ የሚመራወን በትር እናስጥላለን - ይሁን አሜን!!

ዘመን ሲመሸ - ቀን ሲነጋ

‹‹ቁ.1 ሳሚኤልም እስራኤልን ሁሉ አለ፡- ነገራችሁኝን ሁሉ ሰምቼ አንግሼላችኋለሁ፡፡ ቁ.አሁንም የሚጣቸሁትንንና የፈለጋችሁትን ንጉሥ እዩ፤ እነሆም፣ እግዚአብሐር ንጉሥ አደረገላችሁ፡፡ ቁ.17-18- የስንዴ መከር ዛሬ አይደለምን? ወደ እግዚአብሐር እጮኻለሁ፣ እርሱም ነጎድጓድና ዝናብ ይልካል፤ እናንተም ንጉሥ በመለመናችሁ እግዚአብሐር ፊት ያደረጋችሁት ክፋ ታላቅ እንደሆነ ታውቃላችሁ ታያላችሁም፡፡ ሳሚኤልም ወደ እግዚአብሐር ጮኸ፣ እግዚአብሐርም በዚያን ቀን ነጎድጓድና ዝናብ ላከ፣ ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሐርንና ሳሚኤልን እጅግ ፈሩዋቸው›› (1ሳሙ፡12)፡፡

ዛሬም ያለንበት ዘመን ዘመነ ሳኦልን ይመስላል፡፡ ሳኦል የስንዴ መከር ንጉሥ እንደ ነበረ ተገልጧል፡፡ የስንዴም መከር የሚሆንበት በበዓለ ኀምሳ እንደሆነ አታውቁምን? ገብስ በፋሲካው በዓል ሲታጨድ ስንዴ ግን በሁለተኛው በዓል - በጰንጠቆስጤ በዓል ይከሚሾል፡፡ ሳኦል በበዓለ ኀምሣ በዓል ተመረጠ፡፡ በዚህ ላይ ልንለው የፈለግነው ሳኦል በዘሙ ብርታትና ጉልበት ሳለ ዳዊት መቀባቱን ተጠግታቸሁ ትመላከቱ ዘንድ ነው፡፡ ሳኦል ገና ሳለ ዳዊት ተቀባ፡፡ በቀስታም ሳኦል በዳዊት አረጀ፡፡ በእርግጥ ሳኦል መንግሥቱ ተቀደዶ ለጎረቤቱ ለዳዊት ቢሰጥም - እግዚአብሐር ቢተወወም ሳኦል ገና በዙፋኑ ነበር፡፡ የዳዊት ዘመን ሲመላ ግን የሳኦል ዘመን ተደፋ፡፡ ዛሬም እንዲሁ ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ዘመን በልጆቹ(በመንግሥቱ) ዘመን ከመሻሩ በፊት እነዚሁ ልጆች በእግዚአብሐር በመንፈሱም አዳራሽ እንደ ፈቃዱና እንደ ሐሳቡ ይዘጋጃሉ፡፡ ሲፈጸምም ዘመነ ጰንጠቆስጤ (የቤተክርስቲያን ዘመን) የዘመነ ሳኦል ዕጣ ፈንታ ያገኘዋል፡፡ ከሳኦል በኋላ ሰባቱ የሳኦል ልጆች አልተሰቀሉምን (2ሳሙ፡ 21÷1-9)?... በሜጪሻ የሰባቱ አብያተክርስቲያናት(የጰንጠቆስጤ ወጡቆች) ዕድል ፈንታ ምን ይሆን? አብያተክርስቲያት በሎዶቅያ አልቀዋል፡፡ እንደዚያም እየተፈጸሙ ነው፡፡ አሁን ያለወን ከሎዶቅያነት ያልተለየወን ሁኔታችንን በመንፈስ እናይ ዘንድ እግዚአብሐር ይርዳን፡፡

መጽሐፍ የተጻፈበትን መንፈስ ተከትለን የቃሉን መንፈስ የሚመርን እንደሁ አንድ ከፍለ ጊዜ አልቆ ወደ አዲሱ ዘመን ለመሻጋገር የጌታ ቀን የመጀመሪያወን እርምጃ አንሥቶ ሊጥል ሌላኛወም ተነሥቶ ሊከተል ባለበት ወቅት መሆናችንን እንረዳለን፡፡ እግዚአብሐር ለዚህች ጊዜ - ላለንበት ትወልድ የሚገረወን ሰምቶ ማስተዋል እንዴት ያለ ዕረፍት ነው? የስድስት ሚለቅ የሰባት ጅማሬ ነውና በእርግጥ በመንፈሳችን አዳራሽ በተዋጀወም ነፍሳችን ሳሎን ሰንበት እየሆነ ለመሆኑ መንፈስ ለመንፈስ ማከሸርል፡፡ የሕግንና የነቢያትን ሰፊወን ዘመን የተረከበው የቤተክርስቲያን ዘመን በተወሰነለት መጋቢነት(ስፍረ - ዘመን) የመንፈስ በኩራት ለእግዚአብሐር መንግሥት እንዲወለዱ ያገለገለበት ነበረ፡፡ በእርግጥም ከአሕዛብ የተወሰደው ለስመም የሚሆን ወገን በዘመነ ኤከሌሽያ ለመንግሥቱ ተወለዱ እንጂ መንግሥት ገና በዚህ ወገን አላደገም አልተገለጠምም፡፡ ዘመነ ቤተክርስቲያን መንግሥት መሉ በመሉ ይመጣበት ይገለጥበትም ዘንድ አልነበረም በመሠረቱ፡፡ እንዲያውም ለሚለት ቢያስፈልግ ቤተክርስቲያን መንግሥትን ደብቃ - ሰወራ ነው ማልገሏ፡፡ አሁን ከቁመታችን በላይ ፊት ለፊት የተደቀነ ጥያቄ አለ፡- ‹‹ለብዙ ዘመን፡- ‹መንግሥትህ ትምጣ› ተብሎ የተጸለየለት የአባታችን መንግሥት በቤተክርስቲያን ሚጀት ነው ወይስ መታደስ ነው የምትገለጠው?›› የሚለው ይሆናል፡፡ ምናልባት ግን ያለንበት ይሄ ትወልድ እንኳ ለዚህ ጥያቄ ሚልስ ሊሰጥ ጥያቄወን ራሱን አንሥቶ እንደሆነ ጥያቄ አለን፡፡

ሁልጊዜ አዲስ ዘመን በአሮጌ ዘመን ማለቅ - መድከም - ሚጀት ብቻ የሚኮካ ከሆነ የቤተክርስቲያን ዘመን ለመንግሥቱ ዘመን ዘሙን እንዴት የሚስረክበው ይመስላችኋል?... ሕግና ነቢያት በተካቸው በቤተክርስቲያን ዘመን ካረጁ - ከተሻሩ - ከደከመ ጉዞአቸው ከቆመ የቤተክርስቲያን ዘመን ከራሱ ዘመን ወጭ በመንግሥቱም ዘመን ሊጓዝ ጉልበቱ ከየት ነው?... ሕግና ነቢያት በክርስቶስ ተፈጽመው በመደረግ ሲጸኑ ዘመናቸው በከብር፣ በተሻለ ተስፋና ኪዳን አለቀ - ተዘጋ - ተጨረሰ፡፡ ይህም ሲሆን ሳለ በሕግና በነቢያት የነበሩት ሥርዓት፣ ወግ፣ አካሄድ፣ ስጦታዎች፣ አደራረጎች፣ ትምህርቶች አገልግሎቶች... አብረው በመቆም ተዘጉ ወይንስ ከቤተክርስቲያን ዘመን ጋር ቀጠሉ? አይደለም፡፡ ይነዳቸው - አሳፍሯቸው የነበረው ዘመን ሲደክም አብረው ደከሙ፡ ዘሙ ሲፈጸም አብረው ተፈጸሙ፡ ይሄ ሁሉ እስካሁን በተሰጠትና ባለፉት ስፍረ ዘመናት የሆነና የሚሆን የሰማይ ሥርዓት እንደሆነ ልብ በሉ፡፡ ታድያን ለቤተክርስቲያ ዘመን ሲፈጸም ለቤተክርስቲያን የተሰጠት ስጦታዎች፣ ትምህርቶች፣ ሥርዓቶች፣ አገልግሎቶች... ብቻቸወን ወደ አዲሱ የመንግሥቱ መላት ተሻግረው እንዴት ሊቀጥሉ ይችላሉ?

ይሄ የሰው ሐሳብ ነው፡፡ አዲሱ ዘመን - አዲሱ ትወልድ የራሱ የሆነ አገልግሎት፣ የራሱ ትምህርት፣ የራሱ ሥርዓት... አለወና በአሮጌው አይገለገልም፡፡

ቤተክርስቲያን እስካሁን ያገለገለችበትና የኖረችበት ጸጋዋ ለእስከ አሁኑ ነውና ቤተክርስቲያን ለበለጠው ጸጋ ትነሣ ዘንድ የቀደመው ጸጋ በጸጋ ይሆንና የተከፈለው አገልግሎቷ መታሰቢያወን ያጣል፡፡ ካለፈውና አሁን ያለ ከሚመጣለው ጋር ካልተሰፋንና ካልተበየድን በቀር የሚመጣውን ዘመን የዘመኑም ክብርና መላት የበለጠ ነውና ስለአሮጌውና ወራጅ ስለሆነ ውም እንዳያምመው እንመክራለን፡፡ ልትቀበሉት ከቻላችሁ አንድ ነገር እንበል፡- ወንድሞቹን ጳውሎስ በተሰጠው መሥሪችነቱ ለቤተክርስቲያን ያበራው ብርሃን፤ ለዘመኑ የሚጠቅት አዳዲስ መላጦችና ምሥጢራት ዛሬ በእኛ ዘመን ምሥጢር እንዳይደሉ ለማገር አንፈራም፡፡ ጳውሎስ በዘመኑ ምሥጢር ያላቸው ዘንድሮ ምሥጢር አይደሉም፡፡ ምሥጢር ሁሉም አይጋራውም፡፡ የጳውሎስ የዘመኑ ምሥጢራት ግን አሁን አሁን የዓለም አብያተክርስቲያናት ሁሉ ወገኖች ተጋርተውታል፡፡ የወል ሁነዋል፡፡ ስለዚህ ምሥጢር መሆናቸው ቀርቷል፡፡ አሁን ግን ጥቂቶች ብቻ በእግዚአብሔር ደረት ሁነው የሚሰሙት ምሥጢር እንዳለ ስንነግራችሁ በዚሁ ምሥጢር የነበረወን ለማሸረጀት ነውና ጌታ ቢረዳችሁ ንቁ፡፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር በጳውሎስ ብቻ የተገለጠ አይደለም፡፡ ከእርሱ በኋላ በዮሐንስ የተገለጠው በዚያ ሁሉ ይበልጣል፡፡ ጳውሎስ የዮሐንስን ራእይ በዘመኑ አላነበበውም አላወቀወምም፡፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር በእርግጥ እስካሁን ከተጻፈው ሁሉ በላይ ነው፡፡

ጳውሎስ ግን በእነዚያ ምሥጢራት መሠረትን መሠረተ፡፡ ማንም ግን ሌላ መሠረት መጣል ሳያስፈልገው ለሕንፃው እንዲጠነቀቅ ምክርም ሸጠንቀቂያም አለው፡፡ መሠረትን ጣራ ወይም መጀምደሚያ ብናደርገው ሕንፃን መገልበጥ ነውና ሌላ መሠረት ከመጣል የባሰ የከፋ ነው፡፡ ይሄም የእግዚአብሔር ፕሮግራም አይደለም፡፡ ዛሬ የሐዋርያትንና የነቢያትን ጅማሬ መጀምደሚያ ሊያደርጉ የሚሥሩ እንዳሉ አታዩምን? የተገለበጠ ሕንፃ ሊሠሩልን፡፡ የሐዋርያትና የነቢያት መሠረት ሕንፃ ሁኖ በእግዚአብሔር ልጆች ሚለቁ የምትቀበሉት የልጅነት ክብር ከሐዋርያነትና ከነቢይነት ክብር በልጦ መሰጡን ያወቃችሁትና የተባበራችሁት እንደሁ ብቻ ነው፡፡ ከፍ ብለን እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሥራወን ቢሠራም ሥራወን የፈጸመው ግን በሰባተኛው ቀን መሆኑን ነግረናችሁ ነበር (ዘፍ.2÷1-2)፡፡ የሥራው መሠራት መጀመሪያ ይሁን እንጂ ፍጻሜው ነው ግቡ፡፡

በእርግጥ በቤተክርስቲያን ዘመን በአምስቱ የጸጋ ስጦታዎች በድካምም በብርታትም የእግዚአብሔር ሥራ - አካሉ ተሠርታለች፡፡ ግን አልተፈጸመችም፡፡ ግብ አልሆነም፡፡ ከፍ ያለው የመጥራቱ ዋጋ አልተያዘም፡፡ ቤተክርስቲያን ገና በስድስተኛው ቀን፣ በሁለተኛው ሰሚይ፤ በከፊል አገልግሎቶችና ስጦታዎች... ናትና ገና በጉድለት ናት፡፡ ግን ተልዕኮዋን ተወጥታለች እየተወጣችም ነው፡፡ ዳሩ ግን በእርሷና በስጦታዋ በአገልግሎቷም ፍጻሜ - ግብ ይመጣል ወይም ይሆናል ብሎ ማንም ተስፋ አያድርግ፡፡ ይልቅስ በድካሟ፤ በዘሟ ሚለቅ፣ በአገልግሎቷ ዝለት፣ በሁሉ ዘንድ በሆነው ምስቅልቅልና ተስፋ መቁረጥ... የተባለው የልጆቹ መለጥ ይሆናል፡፡ ያንን የመንግሥቱን ዘመን የሚያመጡትና የሚልጠትን ያለምንም ጥርጥር ልጆቹ ናቸው፡፡ ታውቃላችሁ ስለእነዚህ ልጆች ፍጥረት ብቻ ሳይሆን የመንፈስ በኩራት ያላቸው እንኳ ለመለጣቸው ሲቃትቱ(ሮሜ 8÷23)? ወገኖች የመንፈስ በኩራትስ የጳንጠቆስጠኛ የካሪዝማቲክ፣ የፕሮቴስታንትና የፌይዝ መቸመንት ወዘተ ጎበዛዝትንና ቆነጃጅትን የሚከቀልል አይደለምን? ለዚህ ጊዜ ሚለት ለሚለጠው ክብር ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላዊ፣ መጋቢ፣ አስተማሪ፣ ዲያቆን፣ የተወለደ ግን ያላደገ፣ ምዕመናን ሁሉ - አዎን ሁሉም ይቃትታሉ፡፡ የዚያም የሰወነት ቤዛ የሆነው ልጅነት በተገለጠ ጊዜ አሁን የሚቃትቱት የእነዚህ ክብር፣ ጸጋ፣ አገልግሎት፣ ዘመን፣ ዝና... የሚፈልገው የለም፤ እሙን፡፡ አሁን ባለህበትና በተሰጠህ ለወዲያኛው እየቃተትህ የምትቃትትለት ነገር ሲገለጥ አሁን ያለህበትን ደግመህ ትሻዋለህ? በምን አቅምህ?

እነሆ፣ ዘመን መጥቷል፡፡ አሁን ያለንን ሁሉ የሚያስረሳና የሚያስተወን ዘመን - ሁሉም ነገር እስከዚህ ድረስ ተጉዟል፡፡ ዛሬ በቤተክርስቲያን ያለው ሁሉም ነገር - ፍጥረታዊም ይሁን መንፈሳዊ አፈር ሲቀምስ የእግዚአብሔር መንግሥት በሁሉም ወስጥና ወጭ ትንሣኤ ያገኛል፡፡ መቃኖች ይመጣሉ፡፡ ጌታ መሉ በመሉ ይወርዳል፡፡ ይገለጣል፡፡ ፍጥረትም ከመበስበስ ባርነት ነፃ ይወጣል፡፡ ከዚሁ ጋር በመንፈሳችሁ ብርሃን አንድ ነገር ታዩ ዘንድ ወደ ራሳችሁ መጽሐፍ እንሜልሳችኋለን፡- ‹‹ከዚያ በኋላም አየሁ፣ እነሆም፣ በሰሚይ የተከፈተ ደጅ፣ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፡- ወደዚህ ወጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሀለሁ አለ›› (ራእ.4÷1)፡፡ ምን ሊያይ ነው የተወሰደው ዮሐንስ? ‹‹ከዚያ በኋላ›› በሰሚያት የተከፈተ ደጅ ሆነ፡፡ ዮሀንስ ወደዚያ ወጣ የምድርን ሳይሆን የሰሚይን ሐሳብ ፍጻሜ ሊያይ፡፡ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ የሰሙ ትዕይንት ተከፈተ፡፡ ከዚያ በኋላ እስከ ምዕራፍ ሃያ ሁለት እያንዳንዱ ምዕራፍ የተያያዘ ይሆናል “And” በሚል ቃል (እንደ እንግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ)፡፡ ‹‹ከዚያ በኋላ›› የሰሚያት አደራረግ በየምዕራፉ ተከፍቶ እየተዘጋ ወደ ተወሰነለት ድምጻሜ ይደርሳል፡፡ ግና ይሄ ሁሉ የሆነው ከአብያተ ክርስቲያናት ሕይወትና ካሉበት ሁኔታ መለጥ በኋላ መሆኑን አስተዋላችሁት? ለዚህ ነው ምዕራፉ፡- ‹‹ከዚህ በኋላ...›› ብሎ የጀመረው፡ ከምን በኋላ? ከአብያተ ክርስቲያናት በተለይም ከሎዶቅያ በኋላ፡፡

የአብያተ ክርስቲያናትን - የሁለተኛዉን ስፍራ ልምምድ - የሁለተኛዉን ሰማይ ሕይወት በዚህ ሁኔታ ማለቁን ካላየን ለእግዚአብሐር አሠራር እንግዶች እንሆናለን፡፡ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የሰባት ክፍለ ዘመናት ምሳሌዎች ናቸው እኮ፡፡ ጅማሬአቸው ኤፌሶን ነዉ፡፡ ፍጻሜአቸው ግን ሎዶቅያ፡፡ ኤፌሶን ማለት ተወዳጅ - የተወደደ ማለት ነዉ፡፡ እግዚአብሐር በተወደደ ነገር ጀምሮ በሎዶቅያ ጨረሰ፡፡ ይሄ የቤተ ክርስቲያን ዘመንና ዕድል ፈንታ ነዉ፡፡ እግዚአብሐር ግን ተሸንፎ ነው አብያተ ክርስቲያናት እንደዚህ መጨረሳቸው? እንደዚህ እንኳ ማንም አያስብ፡፡ በአብያተ ክርስቲያናት ክብር ምትክ ሌላ የበለጠ ክብር ስላዘጋጀ ያለዉን በሚመጣው ማእረጀት - ሚድከም የእግዚአብሐር እና/ወይም የሰማያት ሥርዓትና ባሕሪይ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ በኤፌሶንና በኤፌሶንነት የጀመረው የቤተክርስቲያን የታሪክ ጉዞ በሎዶቅያና በሎዶቅያነት ካለቀ በኋላ ነው ሰማያት የተከፈቱት፡፡ ይሄ በእርግጥም የታሪክ ጉዞ ነዉ፤ ልብ ካላችሁት፡፡ ፀሐይ ከምሥራቅ ወጥቶ ምዕራብ ይገባል፡፡ በሌላ አባባል ነግቶ ይመሻል፡፡ ለምን? እንደገና ሊወጣ - ደግሞ ሊነጋ፡፡ በቤተክርስቲያንም ተመሳሳይ ነገር መሆኑን ማለት ነግቶ መምሸቱ - ፀሐይ(የጽድቅ ፀሐይ) ወጥቶ መግባቱ ለሌላ ቀን - ለጌታ ቀን - ለዘላለም ንጋት ነውና ይህንን ታላቅ መገለጥ - የዘመኑን ምሥጢር በመንፈሳችሁ - በልባችሁ ልብ ታስተዉሉት ዘንድ በፍጹም ፍቅር እንለምናለን፡፡

በኤፌሶን የወጣው ፀሐይ በሎዶቅያ ገባ፡፡ ፀሐዩን በተመሳከተ የትም አልሄደም፡፡ ብርሃን ከሚሰጥበት ማንነቱም አልተለወጠም፡፡ ሁኖም በሎዶቅያ መሸቷል፡፡ ያም ምሽት እስከ እኩለ ሌሊት ተጉዞ ቆነጃጅትን ሁሉ አስተኛ፡፡ ወገኖች ይገባችኋል? ለሚተዋሉ ብርሃን መገለጥ እግዚአብሐር ይርዳን፡፡ የምንጽፍበትን መንፈስ የወረሳችሁት ከሆነ መልእክታችን ይህ ነው፡፡ አብያተ ክርስቲያናት፣ አገልግሎታቸው፣ ስጦታቸው፣ ትምህርታቸው፣ ትጋታቸው፣ ጥሮግራማቸው፣ ሥርዓታቸው፣ የቤተክርስቲያን ሁለንተና… ወደ ምሽታቸው - ወደ ሌሊታቸው መጥቶአል፡፡ እነዚህ ሁሉ ከባድ እንቅልፍ ወስጥ ናቸው - በግማሽ ሞተዋል፡፡ አያወቁም፡፡ ይሄ አባባል ተጋግኗል? አይደለም፡፡ ራሳችሁን፣ የምታገለግሉትንና አጥቢያችሁን፣ አገልግሎቶችንና አገልጋዮችን ሁሉ መንፈስ ተመልከቱ፡፡ እኛ ስለጻፍነው እንጂ የመልእክታችን እወነት እያንዳንዳችሁ ቤት ለመሆኑ ሕሊናችሁን ምክር እንጠራባችኋለን፡፡

የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አራት ቁጥር አንድን እንደገና እናንብበው፡፡ በተለይም፡- ‹‹ከዚህ በኋላ…›› በሚለው ቃል ልናሰምርበት ይገባል፡፡በዚህ ብቻ የራእይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት የታሪክ ሂደት የተዘጋ አይመስላችሁም?... በእርግጥ ያ ራእይ(መገለጥ) ነው፡፡ ተፈጻሚ ቱና የራእዩ አካል ማግኘት ግን በየዘመናቱ የሆነ ነው፡፡ እነዚያ ምዕራፎች በዚህ ምዕራፍ ተዘጉ፡፡ እነዚያ ዘመናት በዚህኛው ዘመን አለቁ፡፡ እነዚያ ሁኔታዎች በአዲስ ጅምር ደከመው ተሻሩ፡፡ ማን ነው ከዚያ(ከምዕ.4) በኋላ ቤተክርስቲያንን ያየ፡፡ ዳግመኛስ ወደ መድረኩ ወጥታ ትታይ ዘንድ የሚጠበቅ የትኛው አማኝ ነው?... ከዚህ በኋላ ዙፋን ነው፡፡ ግዛት ነው፡፡ ሞገስ ነው፡፡ መንግሥት ነው፡፡ ያ ሁሉ ፍርድ - መቅሰፍት - ጥፋት - ተአምራት - ክብር - ርስት - ከተማ - ሠርግ… ወዘተርፈ የሆኑት አስቀድመው በምዕራፍ አራትና አምስት ላይ በተገለጡት ሰማያዊ ክስተቶች ነው፡፡ ያስደንቃል! ያለንበትን ዘመን - የቤተክርስቲያንን ዘመን ፍጻሜ በጠቀስነው ምዕራፍ ሞት ካልቻልን የእግዚአብሐርን ንድፈ ሐሳብ አልገባንም፡፡ ጳወሎስ እኮ መጋቢነት - ስፍረ ዘመን - የቤተክርስቲያን ዘመን ተሰጥቶት ለቤተክርስቲያን አካሄድ የሚሆኑ ታላላቅ ነገሮች ደንግጎ አልፏል፡፡ ቤተክርስቲያንም እስከ ዛሬ በእነዚያ የተወሰነላትን የሕይወት እርምጃ ተራምዳለች፡፡ ግን አሁን እየጠቀስነው ያለዉን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማለት ራእይን አስቀድመን እንዳልናችሁ ጳወሎስ እኮ ጨርሶ አያወቀውም አሁን ባለበት በመንፈስ ከበብ ሁኖ ካልሆነ በቀር፡፡ በምድር እያለ አያወቀውም፡፡ ዮሐንስም በአብዛኛው የሚሆነውን አየ እንጂ በዘሙ የሆነውን አይደለም፡፡ ይሄ ታድያ ከሐዋርያትና ከነቢያት መሠረት ያለፈ ሕይወትና ልምምድ እንደሆነ ማሞት አትችሉምን? ሐዋርያትና ነቢያትም የነበሩበትን ዘመን ሳይሆን የሚመጣውንና የበለጠውን ክብር አይተው ነው ያገለገሉት፡፡ በተሰፈረላቸው ዘመን ረክተው አልተቀመጡም፡፡ ስለሚመጣው ተዘረጉ፡፡ የሚመጣው ብልጫ እንዳለው አይተዋልና በደረሱበት ሳይከራከሩ ያንን ለጊዜው እያገለገሉ የሚበልጠውን ፈልገው አለፉ፡፡

በእነርሱ የነበረው መንፈስ ዛሬም በእኛም ካለ አሁን ያለው የነገሮች ሚዛቅ፣ ሚርጅት፣ መድከም፣ ተስፋ መቁረጥ… ሳያደክመን ወደ በለጠው እንሂድ፡፡ አሁን ያለዉን የቤተክርስቲያንን ሁኔታ መለወጥ የምንችለው ለቤተክርስቲያን ተሰጥቶ በነበረው(በጳንጠቆስጤ) መንፈስ መጠን - ልክ ሳይሆን በመንግሥቱ በሚፈስሰው የመንፈስ መላት ነው፡፡ አሁን ማን ነው መላት የተሰጠው?... አሁን ያለው ከፊል ከሆነ ግን በዚህ ስጦታው ዘሙን ሊለወጥ ማንም አያገልግል፡፡ ይልቅስ ያለው ከፊሉ አልቆበት በመላት ሊሞላ ዕቃዉን ያዘጋጅ፡፡ ከቆነጃጅት የሚጉርፍ የለም፡፡ የሞላም ያልሞላም ይተኛል - ያንቀላፋል፡፡ ዘሙ(የቤተክርስቲያን ዘመን) እንደዚህ ሁኖ እንዲያልቅ የእግዚአብሐር ፈቃድ የዘመናትም ሐሳቡ ነው፡፡

ወገኖች ሆይ፣ ዛሬ ክርስቶስ እኮ በእኛ የክብር ተስፋ ነው(ቆላ.1÷27)፡፡ በሌላ አባባል ክብርን የምንይዝበት - የምንወርስበት ተስፋ ነው ክርስቶስ አሁን፡፡ ያ የዘላለም ክብር - አብ ራሱ በእኛ ሲገለጥ(ሮሜ.8÷18K.J.V.) ክርስቶስ የክብር ተስፋ መሆኑ ይቀራል፡፡ ወዶች ይሄም አለ ካልከበዳችሁ፡፡ እንኳን ሐዋርያነትና ነቢይነት ክርስቶስ እንኳ የክብር ተስፋ - የክብር መያዣ መሆኑ ያልቃል - ያረጃል፡፡ እርሱ ራሱ ክብርና የክብር ጌታ ይሆናልና ራሱን በዚህ ልክ የሰፈረበትን

ጊዜ ይሸራል፡፡ ኦ! አባታችን እየተጓዘ ነው፡፡ የራሱን የአንድ ዘመን መለጥ እንኳ እያስረጀና እያደከመ ለበለጠው ክብር፣ ግርማና መንግሥት ተራምዷል - ሃሌሉያ! መጽሐፍ፡- ‹‹እናንተ የምትንቁ፣ እዩ ተደነቁም ጥፉም አንድ ስንኳ ቢተረክላችሁ የሚታምኑትን ሥራ በዘመናችሁ እኔ እሠራለሁና›› የሚለው እንዳይደርስብን የሚመክረንን ምክር እናድምጥ(ሥራ.13÷40-41)፡፡ ዛሬ እግዚአብሔር ብዙ ሃይማኖት ቤት የማያምኑትን ነገር እየተናገረ ይገኛል፡፡ ‹‹በዘመናችሁም›› ብሏልና በእኛ ዘመንም ይሄ እየሆነ ነው፡ ምንድር ነው የሚያታመን ሥራ? እስካሁን የተሠራው ዓይነት ይመስላችኋል? እግዚአብሔር ልዩ ነገር እየተናገረ ነው፡፡ እነዚህ ልጆች የተጻፈውን መጽሐፍ በልዩ ሁኔታ የሚዱበት መንፈስ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የልባቸውን መዘገብ ከፍተው ማንበብ ጀምረዋል፡፡ የተከፈተው መጽሐፍ በወሰጣቸው ነው፡፡ ይህም በውጭ ካለው የጠለቀ ነው፡፡የሰፋ ነው፡፡ የከበረ ነው፡፡ ከተነገረው ሁሉ በላይ የሚገር የእግዚአብሔር ጥበብ ነው፡፡

ኤፌ.4÷11-13፡- ‹‹ቁ.11- እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎችም ነቢያት፣ ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ቁ.12 - 13 - ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚኝ አንድነት፣ ሙሉ ሰውም ወደመሆን የክርስቶስም መላት ወደሚሆን ወደ መላት ልክ እስክንደርስ ድረስ፣ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ፡፡ ››

በቁጥር አሥራ አንድ የተዘረዘሩት ሰዎች ናቸው፡፡ ጌታም ሰዎችን ነው ለቤተክርስቲያን እንደ ስጦታ የሰጠው፡፡ በዚህ ላይ የትንቢትን ሳይሆን ነቢይን፤ ምግብን ሳይሆን መጋቢን፤ ወንጌልን ሳይሆን ወንጌላዊን… ነው እንደ ስጦታ የሰጠው፡፡ እነዚህም የጸጋ ስጦታዎች መሥራታቸውና መለጣቸው ለቤተክርስቲያን በተሰጡ ሰዎች ነው፡፡ እነዚህም በሰው ቀኝ እጅ ባሉ ጣቶች እንደ ምሳሌ ተጠቅሰዋል፡፡ ስለዚህም ከዚህ በማሣት እነዚህ ስጦታዎች የእጁ መንፈስ በሚሉት ይጠራሉ፡፡ በእነርሱም የእግዚአብሔር ሞዳን፣ የእግዚአብሔር ኃይል፣ ተአምራት፣ አሠራር… ስለተገለጠ የእጅ መንፈስ የሚል መላያ አግኝተዋል፡፡ ግን በእነዚህ የእግዚአብሔርን ሥራ የጅማሬ እርምጃ(ሥራ.1÷1-2) ከሞት ሌላ ፍጽምናን እስከ ዛሬ አድርገው አላየንም፡፡ በተጠቀሰውም ከፍል አንድ ቁልፍ ቃል እናገኛለን፡፡ ከዚያም ተነሥቶን ነው እነዚህ ስጦታዎች አድራሽ እንጂ በራሳቸው ግብ ወይም ፍጻሜ አይደሉም የምንለው፡ ‹‹… እስክንደርስ ድረስ፡፡›› እነዚህ እስከ አንድ ነገር ድረስ በማለት ሠርተዋል፡፡ አገልግለዋል፡፡ ወደተባለው - በመንፈስ ወደታየው በአካል ከደረስን ግን በቃቸው ሚለትም አይደለምን?... እዚያ ደረጃ እስክንደርስ ግን የእነዚህ አስፈላጊነት ጥያቄ ላይ የሚወድቅ አይደለም፡፡ ግን ዛሬ በእግዚአብሔር ልጅነት መንፈስ ከሰፈራችን ወጥተን በዚህ ጊዜ ያለውን ድንቅ ሐሳቡን ከተረዳን ልባችን በእነዚህ ላይ ያረፈ አይሆንም፡፡ እነዚህ ጥሜታችንና ርሃባችን አይደሉም፡፡ ማንም ግን እነዚህን በብርቱ ቢፈልግና ቢራብ ከዚህም ሚልእክት አባባል ጋር ባይስማማ አንባቢውና ጸሐፊዎቹ በመለጥ - በሚዳትና እግዚአብሔር ለአሁን ዘመን ያለውን ሐሳብ አለመገናኘት ብቻ ነው፡፡

ጌታ፡- ‹‹አባቴ እስካሁን ይሠራል›› እንዳለው በእርግጥም እስከዛሬ በእነዚህ ስጦታዎች የሚዳኑን ሥራ ሠርተዋል፡፡ ግን እነዚህ ሁሉ በቀድሞ ጊዜ እንደምናውቃቸው በጠራ ሁኔታ ሲሠሩ አናይም፡፡ በዚህም ምክንያት የብዙዎቻችን ልብ ከእነዚህ እየወደቀ ነው፡፡ በእርግጥ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለበለጠው አሠራሩና መለጠ፤ ከብሩና መምጣቱ ሲል እያስረጀ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ‹‹እስክንደርስ ድረስ›› ብቻ ይሠራል፡፡ ከዚያ ወድያ ግን መሻገር የለም፡፡ ጊዜውን በመንፈስ ስንሚምር የእጁ መንፈስ ለአፉ መንፈስ ሲባል ያረጀል፡፡ ይሄ የአፉ መንፈስ የቃሉ ሥልጣን - ስለታም ሰይፍ ነው፡፡ እስካሁን በቤተክርስቲያን ዘመን ሁሉ(የጸጋ ሥጦታዎች እያሉና እየሠሩ እንኳ) አወፌው ነበር፡፡ አሁን በሚለጠውና በሚበልጠው ሥልጣንና መንፈስ ግን አወፌውን በሚድ ይሸረዋል፡፡ በእርግጥ በቃሉ አገልግሎት - መንገሥንና ሕይወትን በሚልጥ ቃል ልጆቹ ጌታ ራሱን ወደ ሁሉም ያወርዱታል፡፡

ቤተ ክርስቲያ በቀን ናት በሌሊት?

‹‹መሸራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ፡፡ እኩለ ሌሊትም ሲሆን፡- እነሆ፣ መሸራው ይመጣል፣ ትቀበሉት ዘንድ ወጡ የሚል ወካታ ሆነ ››(ማቴ.25÷5-6)፡፡

የዚህ ጊዜ ሌሊት ነው - ወድቅት፡፡ መሸራው በዚህ ጊዜ ይመጣል፡፡ መሸራው ይመጣ ዘንድ የግድ መምሸት አለበት፡፡ ሁሉም ሞኖት አለበት፡፡ እያንዳንዱ መድከም አለበት፡፡ ማንም ጌታን በጉብዝናው አያገኘውም፡፡ ያለንበት ዘመን ይለወጥ ዘንድ ስለዚህ ከፍለ ጊዜ ሁሉም ተስፋ መቁረጥ አለበት፡፡ በሌሊት የሚዝዙ - መሸራው መጥቷል የሚሉ ግን ሌሊቱን ያነጉታል፡፡ በሌሊት ይጓዙ ዘንድ ሁኖላቸዋልና ሌላ ብርሃን አላቸው፡ ካልመሸ አይነጋም፡፡ አስቀድሞ ሌሊት ነው፡ ኋላ ግን ጠዋት(ዘፍ.1÷5)፡፡ በልባችን የወጣው የንጋት ኮከብ ምድር እስክትጠባ(እስኪነጋ) በመንፈስ ይሙናል፡፡ በሌሊት ሁነን የሚጋወን ቀን እንጠበቃለን፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ለሚመጣው ቀን ምስክር ትሆን ዘንድ በሌሊት እንድትጓዝ ተመሥርታለች፡፡ ግን በወሰጓ የነጋው የጌታ ቀን በወጪ ባለው ሌሊት መደሙ - መጨፍገጉ - መጨልሙ እርሷ ራሷ በሌለት - ባልተፈጠረ ሌሊት ወስጥ አለች፡፡ ያሳዝናል፡፡

በሌሊት - በጨለማ ሞት የሚቹሉት እንስሳት በቀን - በብርሃን ከሚዩት ይልቅ ብርሃን የተቀበሉ ለመሆናቸው የሚከራከር አይደለም። የሰዉነት መበራት ዓይን ነዉና በዓይናቸው ያለው ብርሃን በጨለማ ለሞት መቻሉ ተፈጥሮአቸው መሆኑ ነው። በሌሊት - በጨለማ ያለዉን ሊያይ የሚቹል ከዚያ የተለየ ዓይን (ብርሃን) የተቀበለ መሆን እንዳለበት አሁንም ከርከር የለበትም። ለቤተክርስቲያን ሌሊት ይሁን ቀን በየትኛው ከፍለ ጊዜ ሚሉት ስፍረ ዘመን እንዳለች ሊያዩላት የሚቹሉት በመካከሏ ያሉ የተለየ የእግዚአብሔር ብርሃን የሆነላቸው ናቸው። ‹‹ቤተክርስቲያን በሌሊት ናት›› ሚለት አያሳዝንም፤ ወይም ‹‹ቤተክርስቲያን በሌሊት ናት››ሚለት አያስፈነጥዝም። ይልቅስ ጊዜዋን ትዋጅ ዘንድ ትከክለኛ ያለችበትን ሚሳየት ነው የክብሯ ምክንያት። ለዕወር ግን ቀንም ሌሊትም አንድ ነዉና ልዩነቶቹን ቢነግሩት አይገባውም። መንፈሳዊም ዕወርነት ከፍጥረታዊው እጅግ የከፋ ነው። ኢየሱስ በሥጋ በምድር በነበረበት ዘመን የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች ዘሙኑና የዘሙን ምልከት ሚሳየት ስላልቻሉ አልነበረምን ‹‹እናንተ ዕወሮች መሪዎች›› ያላቸው? ብርሃንና ጨለማ ለእነዚህ አንድና ተመሳሳይ ነው። ግን ብርሃን ስለሌለ ነዉን? አይደለም። ሞት ስላልቻሉ ነው እንጂ። ለብዙዎች የሆነው ሌሊት ለጥቂቶች ቀን ነው በእርግጥ። የሌሊቱን ርዝመት ሊጠየቁ የሚቹሉና በሌሊት የሚዱ - ጉዞአቸው የሚገታ - እስከ እግዚአብሔር ፍጹም መላት ድረስ የሚራመዱ(ለእነርሱ የተባለው ሌሊት ሌሊት አይደለም) ።ጉበኞች አሉ።

እነዚህ በቤተክርስቲያን ፀሐይና ከዋክብት ጨረቃም የሚዙ ሳይሆኑ በሰሚይ ንጋት ኮከብ የሚመላለሱ ናቸው። አንዱ እግዚአብሔር ሌሊትና ቀን ሁኖ በግብፃውያንና በእስራኤላውያን መካከል መግባቱ አስገራሚ ነው(ዘጸ.14÷20)። የዚያኛው ወገን ሌሊት ነው። ለዚህኛው ሁልጊዜ ቀን ነው። ለዚህኛው ሁል ጊዜ ቀን ለዚህኛው ግን ሁል ጊዜ ሌሊት ሁኗል። ዛሬ ቤተክርስቲያን ያለችበትን - እግዚአብሔር የወሰነላትን ስፍረ ዘመን የሚወቁ መሪዎቿ በሌሊት - በጨለማ ናቸው። በራሳቸውም አልጋ በታላቅ እንቅልፍ ወስጥ ይገኛሉ። መጽሐፍ እንደሚል ዕወሮች ናቸው። ቀንና ሌሊቱን መላየት አይችሉም። ለእነርሱ እንደሚመላቸው ያሉበት ይህ ጊዜ ቀን ነው። ያሉበት ጊዜም ቀን ከተባለ የሰው ቀን - ስድስተኛው ቀን ነው። ይህንን ቀን ከሚገቱን አድነን - አባት ሆይ።

በቃላቸው - በድምጣቸው - በመልእክታቸው ጌታን ወደ ፍጥረት ሁሉ በማወረድ - በማመጣት የፍጥረትን ሌሊት የቤተ ክርስቲያንንም ድንግዝግዝ የሚፍፉ ቀን የሆኑ የቀን ልጆች አሁን ያለዉና ከላይ የተፈቀደለትን ሌሊት እንደ ጠላት የሚዩት ሳይሆን የብርሃን ትንሣኤ - የቀን መኮካት ይሆን ዘንድ የተሰጠ መሆኑን በመቀበል ቤተክርስቲያን በሌሊት መሆኗ እንደ ብስራት እንደ መርዶም አያዩትም። ስለዚያ ቀን እነዚህ ሁሉ ትተዋል።

‹‹ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መላከት ከሰሚይ ይወርዳልና፣ በክርስቶም የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ››(1ተሰ.4÷16)። ሦስቱም በአፍ - በትንፋሽ - በንግግር እንደ ሆኑ ታያላችሁ? እነዚህ የእጁ መንፈስ አይደሉም፣ የአፉ መንፈስ ናቸው። ‹‹በትእዛዝ›› ሚለቱም ወታደራዊ ቃል ነው። በትእዛዝ ነው - ሥልጣን ነው። እንደ ባለሥልጣን በመገር - ከማንነት በመገር - ከተከፈተ መቅደስና መጽሐፍ በመገር ይሆናል። ጌታ ራሱ ይህንን የሥልጣን ቃላቸውን ወደ ሰመት ሁሉ ያወርዱታል። እነዚህ የቀጠነ - የተበረዘ - የተቀላቀለ... ቃል የላቸውም። ከጌታ ‹‹እንደ ወረደ›› ይናገሩታልና ጌታን ለፍጥረት ሁሉ መዳን ያወርዱታል ሚለት ይገልጠታል። ይሄ በፍጻሜ - በዚያ ቀን - በልጆቹ መገለጥ የሚደረግ ብቻ ለመሆኑ እስከ ዛሬም እንደዚህ አለመሆኑ ሚረጃ ነው። ስለዚህ ቀን ነው አሁን ያለው እየረሳንና ወደ ኋላችን እያደረግን ልንራመድ መንፈስ የሚለዉን መስማት አለብን የምንላችሁ - እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን።

‹‹በመላእክት አለቃ ድምፅ›› ሚለቱስ? ድንቅ ነው! የአለቃ ድምፅ አለቃወን ያመጣዋል። እስካሁን ለተላኩት መላእክት ሁሉ አለቃ ሁኖ የሚለጠው አለቃ በድምፁ ጌታ ራሱን ያመጣዋል። የአለቃው ድምፅ ከራሱ ከአለቃው በቀር በማን ይነገራል? አለቃው ለአለቃው - እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር - መንፈስ ለመንፈስ ይናገራል። ድምፁ(ቃሉ) ሁሉን ፈጠረ። ሁሉን ሊያድስ - ሁሉን ሊጠቀልል... ወደ ሁሉ ይወርዳል። ሁሉን አናወጠ ያጸናል። ይህ አለቃ ጌታ ነው። እርሱ በልጆቹ በመመላትና በመከፈር (በመገለጥ) በብዙ ልጆቹ ድምፁን ሲሰጥ የብዙ ውኖች ድምፅ በምድር ሁሉ ይሰሚል። ብዙ ውኖችም ድምፃቸውን ሲሰጡ(የመላእክት አለቃ ድምፅ የእነዚህ በአንድነት ነው) የእያንዳንዱ ሰሚይና ምድር ይጸና ወይም ይለወጥ ዘንድ ይናወጣል።

በሥስተኝነት የተነገረው - ‹‹... በእግዚአብሔር መላከት›› የሚለው ነው። ማንም ስለዚህ ነገር ሲያስብ ፍጥረታዊ የዕድሩን ዓይነት ጥሩንባ አያስብ። ማንም፣ ከፍጥረታዊ ሰሚይ ፍጥረታዊ መላከት የጠቅንበት ትምህርትም ሆነ ‹‹እምነት›› የከሰረ ትምህርትና እምነት ነው። መንፈሳዊው መላከት ግን ሕዝቡን ወደ ራሱ ከሚፈልስበት ከፈቃዱ እወቀት - ከሕያው ቃሉ ሌላ አይደለም። እነዚህ የታመኑት መላከታቸውን በነፉት ጊዜ በሚታየውና በሚይታየው ከበብ - እስከምድር ዳርቻ ቃላቸው ወጥቶ ይሰሚል። የዚህም መንግሥት ወንጌል ስብከት ፍጻሜን ያመጣል። ፍጻሜን የሚያመጣ ወንጌል እስካሁን አልተሰበከም። ፍጻሜ ግን በመንግሥቱ ወንጌል ይሆናል (ማቴ.24÷14)። የእግዚአብሔር አንድ መላከት በሁሉም ስለሚፋ ጌታ ወደ ሁሉ ይገለጣልና

ዓይን ሁሉ ያየዋል፡፡ መንግሥቱን የሚያጣጡ - የሚልጡ - የሚያወርዱ በእነዚህ ሦስቱ የሚለገሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የአፉ መንፈስ አደራረግ ሲባል ነው የእስከዛሬው የቤተክርስቲያን ዘመን፣ መንገድ፣ ሥርዓት፣ ትምህርት፣ ደንብ፣ ስጦታ፣ አገልግሎት… የሚደክመው የሚያልቀውና የሚሸረው፡፡ በእነዚህ ሦስቱ ደኅንነት ሳይሆን አዳኙን፤ ፈወስ ሳይሆን ፈዋሹን፣ ስጦታ ሳይሆን ሰጪውን፣ በረከት ሳይሆን ባራኪውን፣ አገልግሎት ሳይሆን አገልጋዩን… ያወርዱታል፡፡

ይሄን ሚለት ግን የደኅንነት፣ የፈወስ፣ የስጦታዎች፣ የበረከት፣ የአገልግሎት… መቃወም ነወን? አይደለም፡፡ እነዚህን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ናቸው ሚለታችን ነው፡፡ በእነዚህ ሚጀት የሚበልጠው ይመጣል ሚለታችን ነው፡፡ እኛ የሚበልጠውን ነገርናችሁ፡፡ መጽሐፍም፡- ‹‹… የሚሸለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ(ትይዙ) ዘንድ›› ብሏችኋል(ፊልጵ.1÷11)፡፡ የእጁ መንፈስ በሌሊቱ ዘመን ደኅንነትን፣ ፈወስን፣ ስጦታን፣ በረከትን፣ አገልግሎትን፣… አድርጓል፡፡ የአፉ መንፈስ ግን ጌታ ራሱን ያወርደዋል፡፡ ይሄ ነው የቀንና የሌሊት ልዩነት፡፡

የነበረውና እስካሁን ያለው ከጌታ ዘንድ ከላይ የሆነ ቢሆን እንኳ የቱንም ያህል ከቡር ይሁን የሚለወጠው - የሚቃይረው - የሚሸረው… አለው፡፡ የዚህም አስረጂ መጀመሪያ የነበሩት ሁሉ ከሕዝብ ልብ መወደቃቸው እንደ ምልከት ይጠቀሳሉ፡፡ አገልግሎቶች፣ የቤተክርስቲያን ስጦታዎች፣ ሥርዓቶች፣ አሮናዊ አስተዳደር፣ አምስቱ ‹‹ቢሮዎች››፣… የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያጣጡ ሳይሆኑ በተቃራኒው የእነርሱ ሚጀትና ሚለቅ - ተገብሮ(inactive) መሆን የእግዚአብሔር መንግሥት መማጣት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ሚለት አካሉ የምትነጠቀው የቤተክርስቲያን ነገሮች በሚጀታቸውና በሚለቃቸው እንጂ ወደ ጅምራቸውና ወደ ጉብዝናቸው በማምጣት እንዳልሆነ ታዩ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ይርዳችሁ፡ አብርሃምና ሣራ ሲሞቱ - ሲደክሙ - ሲያረጁ - ሲያልቁ እንደወለዱ ለምንለው እውነት እንደሚረጃ እንደ ምስክርም እንጠቅሳለን፡፡ ለዚህ የእግዚአብሔር ሐሳብ ሙጸም ነው የአብያተ ክርስቲያናት ፍጻሜ - ሎዶቅያ መሆኑ፡፡

በሎዶቅያና በሎዶቅያነት ጅምር አገልግሎቶች፡- ሐዋርያነት፣ ነቢይነት፣ ስጦታዎች፣ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች፣ ዲያቁንነት፣ ኳየር፣ ሽምግልና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ፈወስ፣ እንቅስቃሴዎች… የሉም እኛ አላልንም፡፡ ግን አርጅተዋል፡፡ የሚፈለጉ ሁነዋል፡፡ የሚሠሩ ናቸው፡፡ ስም አላቸው ኃይሉ ተወስዶባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ይህን የሚለ ያፈጠጠ ምስክርነት እያለው የእናቱን ዘመን፡- ቀን ቢለው ሌሊትንና ቀንን አለመለየቱ ነውና ዕወርነቱን ይቀበል፡፡ ይህንም ሚነፍ አትበሉት፡፡ ዋጋችሁ ታላቅ ይሆናልና!

ሚነፍን ነው ሰው በታሪኩ የሚይፈልገውና የሚይቀበለው አንድ ነገር፡፡ ዛሬ በሰው የተሞላችው ቤተ ክርስቲያን ሚነፋን ለማመን ተቸግራለች፡፡ እግዚአብሔር ያላሸነፈው - ያልጨሰው - ያላደከመው የእግዚአብሔር ሰው ማን ነበር? ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እንዳልደከመች - ንቅዘቱ እንዳልበዛባት - እንዳልተበላሸች - በድካም እንዳልዛለች - እንደ ቀደመውና እንደመጀመሪያው እንዳልሆነች መቀበል ያቃታት ስለምንድር ነው?...ከዚህም የተነሣ ወቅት በማጠቅ በየጊዜው የሚፈጠሩ ‹‹መንፈሳዊ ኃያላኖቿ(Gaints)›› ከላይ ባልሆነ ነገር ግን ከነፍስ - ከስጫ በሆነ መለጥ፣ ሪቫይቫል፣ ኮንፈረንስ፣… ተስፋ ይዘው በመሣት የሕዝቡን ቅዝቃዜ ያተኮሱት በሚመስል በሕዝቡ ምኞታቸውን ነግደው በማትረፍ እንደተወሰነላቸው ጊዜ ይከስሟል፡፡

የቤተ ክርስቲያን የግዛት ዘመን ለስሙ የሚሆንን ወገን የሚብሰቡን ያህል(ሥራ.15÷14) መላትን ሊያመጣ አለመቻሉ ከእግዚአብሔር ስለሆነ ስለዚህ ድካምና ሚነፍ በጸጋ መቀበል ያሻል፡፡ በመንግሥቱም ግዛት ብቻ የሚፈለገው ነፃነት፣ ክብር፣ ድል፣ ብልጽግና፣ ሕይወት… ይሆናል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ ንቅዘት አለ፡፡ የበዓለ ኀምሳው ዳቦ በእርሾ መጋገሩ የዚህ ሁሉ ምላሌና አስረጂ ነበረ(ዘሌ.23÷17)፡፡ በቤተክርስቲያን ዘመን ነው እርሾ፡፡ እርሾ ገና አለ - ነፍስ አለ፡፡ ቤተክርስቲያን በሁለተኛው ስፍራ(ሰሚይ) ናት፡፡ በዚህ ስፍራ እያለን ነፍሳችን ካልተገዛ ራሱ የሚዛበት ዕድል አለው፡፡ ስለዚህ ስፍራው - ዘሙ - ከበቡ የምስቅልቅ - የሚነካክል ዘመንና ስፍራ ነው፡፡ በሌሊት ካልሆነ ሚነካክል በቀን የለም፡፡ ዛሬ በስፍራ ሁሉ - አገልግሎቶች ሁሉ ሚነካክል የለም? እንግዲያውስ ቤተ ክርስቲያን በሌሊት እንደሆነች ሚረጃ ይብዛላችሁ፡፡

እስከ ዛሬ ብዙ ‹‹ነፍሳት›› እንጂ ‹‹ቅዱሳን መንፈሶች›› አልሰበሰብንም፤ ከእነርሱም ጋር አልተሰበሰብንም፡፡ የእነዚህ ነፍሳት ዘመን ነው የጨለማ - የሌሊት ዘመን ሚሆኑ፡፡ ነፍስንም በአሮናዊ አስተዳደር - ሥርዓት - ሥነ ምግባር መግራት አልተቻለም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከአሮናዊ አስተዳደር ፈጽሞ የነፃች አይደለችም፡፡ ቤተክርስቲያን በፓስቶርያልም ሆነ በኤጲስ ቆጶሳት (በሽማግሌዎች) ትተዳደር ግን ከአሮናዊነት የጸዳች አይደለችም፡፡ በሁለቱም ዓይነት አስተዳደር አወሬነት(እኔነት) አለ፡፡ ስለ መንግሥቱ የተበረዘ - የተቀላቀለ - የቀጠነ ሚዳት ያላቸው አንዳንድ ወንድሞች የዚህን የቤተክርስቲያንን ችግር ለሚቃለል በሽብ የመንግሥቱን - የሚልከጼደቅን አስተዳደር ወደ ቤተክርስቲያን ሊያጣጡ ነፍሳቸው ሲባንን ይታያሉ፡፡ የእነዚህ ብረዛ ደግሞ የባሰ አደገኛ ነው፡፡ መንግሥቱ በሕይወት፣ በመንፈስ፣ በጽድቅ… የሚዛበት ጊዜ

ከመሆኑ በፊት የቤተክርስቲያን ዘመን፣ ግዛት፣ ስጦታ፣ አስተዳደር፣ አሠራር፣... ሚለቅ አለበት፡፡ ማላሸት አለበት፡፡ መቀየር አለበት ብትቀበሉት፡፡

‹‹እንግዲህ ሕዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብሏልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን፣ እንደ አሮን ሹመት የሚቆጠር፣ እንደመልከጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሣ ወደፊት ስለምን ያስፈልጋል? ክህነቱ ሲለወጥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና›› (ዕብ.7÷11-12)፡፡

አንድ ጊዜ የመንግሥቱን የምሥራች መናገር ከጀመርን ምንም ዓይነት ሁኔታ ይግጠመን ከዚህ የእውነት ከፍታ ልንወርድ አይገባንም፡፡ ቤተክርስቲያን ያለችበትን - ሕዝቡ የተጠናወተውን የአካሄድ ብልሹነት ተመልከተን የመንግሥቱን እውነት ማወረድ በውኃችንም ሞቅጠን የለብንም እላለሁ፡፡ እውነቱን በማውረድ - ዝቅ በሚድረግ ሕዝቡን አያወጣውም፡፡ እውነት ተናጋሪው ግን በመንፈስ ወደእነዚያ ሕዝብ ወርዶ ያነሣቸዋል እንጂ፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ነበር (ማር.1÷14)፡፡ ሜጪረሻውም እንደዚያው እንደ ነበር መጽሐፍ ይነግረናል(ሥራ.1÷3)፡፡ ለፈሪሳውያንም እንዲህ አላቸው፡- ‹‹... እነሆ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና›› (ሉቃ.17÷20-21 ይመልከቱ)፡፡ በሌላ ስፍራ፡- ‹‹እናንተ ዕወሮችና ደንቆሮች›› ያላቸው ናቸው ‹‹የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ (with in you)ናትና›› ያላቸው፡፡ እርሱ ከዚያ ወጭ አያያቸውም ምንም ቢደክሙ - ምንም ቢበላሹ - ምንም ቢዘሉ፡፡

ዛሬም ቤተ ክርስቲያን በተሰጣት ነገር እንደ እነዚያ ብትሆን በመዳንዋ፤ በመወረሷ፣ ወደ መንግሥቱ በመግባቷ የሚከራጠር የለም፡፡ በእርግጥ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መልእክት በቤተክርስቲያን ሕይወት አይደለምን? እስቲ የጳውሎስን መልእክቶች ለአንድ አፍታ እንቃኛቸው፡፡ የመጀመሪያው ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች፣ የገላትያና የቆላስይስ መልእክቶችን መጥቀሱ ይበቃናል፡፡ የተፈጠሩትን ሁኔታዎች በመተራስ መፍትሄአቸውን ጻፈ፡፡ ይሄ በቤተክርስቲያን ነው ፡፡ ታድያ ይሄ አይገባም አላልንም፡፡ ግን የቅርቡን፣ የወጨቱ፣ የከበበውን፣... እያየ የሚገረው አገልጋዩ በቤተክርስቲያን ከበብ ስላለ እንደ ሆነ ልብ በሉ፡፡ በመንግሥቱ ያለ ግን(በሌሊት ብዙ ብርሃን - ዓይን የሆነለት) ያለውን እንደሌለ የሌለውን እንዳለ እየጠራ መንግሥቱን በእርሱም የሚነውን ሕይወት ያወጃል፡፡

ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷን እንደብልሃተኛ አናጢ የመሠረተው ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን የሚነው ብዙ ድንጋጌዎችን በመንፈስ ሲሰጥ በጊዜና በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አገልግሎት ነበር፡፡ እርሱ ከዚህ የተለየ ሌላ ነገር ሊያደርግም ሊሆንም አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተሰጠው ስፍረ - ዘመን እንደዚያ ናትና፡፡ ከእርሱ ብዙ ነገር ተማርን፡፡ በመሠረቱም ላይ ብዙ አነጽን፡፡ ዳሩ ግን ወደ ወንድሞቹን ዮሐንስ ጽሑፎች(መልእክቶች) ስንዳዝ(ምንም እንኳ በአንድ ስፍረ - ዘመን ቢሆኑም) የመልእክታቸው ይዘት ወጥና አንድ ዓይነት አልነበረም፡፡ ዮሐንስ አብያተ ክርስቲያናት ያሉበትን መሠረት አድርጎ አልጻፈም፡፡ በራእይ ምዕራፍ ሁለትና ሦስት ስለ አብያተክርስቲያናት ቢጽፍ እንኳ የጻፈበት መንፈስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስና ገላትያ ከጻፈበት መንፈስ የጠለቀና ብዙ እንድንመረምር የሚያደርግ ነው፡፡

ዮሐንስ በእግዚአብሔር መንግሥት አምዶች ሊሆኑ የሚቸሉ ነገሮችን፡- ሕይወትን፣ ፍቅርን፣ ቅድስናን... አጽንቶ ጽፏል፡፡ ጳውሎስ ስለ እነዚህ አልጻፈም ማለታችን ሳይሆን አብያተ ክርስቲያናትን በተመለከተ የተቀባው ብዕራቸው ልዩ ልዩ ነበር ለማለት ነው፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ዛሬ እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ሊያደርጉ የሚይችሉበት ድካም - ወድቀት ወስጥ ቢገኙ አይፈረድባቸውምና፡፡ አልተሰጣቸውምና! ወደ ሕይወት - ወደ ፍቅር - ወደ ጽድቅና እግዚአብሔርን ማምለል መላት አለማደጓን ሳያስፈርድበት ስለ እነዚህ ፈጽማ ተስፋ በመቁረጥ - በመድከም በመሞትም እያለች የሚበላትና የሚለውጣት መንግሥቱ በመደረግ ያጸናዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ አንዱ በአንዱ ተንጠልጥሎ ያድጋል፡ ብልቶች ይደጋገፋሉ፡፡ አንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከማል፡፡ አንድ አንድን ያገለግለዋል፡፡ ይሄም ትክክለኛ አካሄድ ነው (1ቆሮ.12 በሙሉ ይመልከቱ)፡፡ ስለዚህም እስከዛሬ ማንም ለብቻው ሙሉ አይደለም፡፡ ይሄ ግን እስከመቼ የሚቆጥል ይመስላችኋል?... እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ዘመን እንዲህ እንዲሆን ፈቅዷል፡፡ ተሰፍሮም የተሰጠው መንፈስ ስለዚህ ሠርቷል(2ቆሮ.5÷5)፡፡ አሁን ግን እየተነጋገርን ያለነው ስለዚህ ደካማ ዘመን ማለቅ ነው፡፡ እያንዳንዱ ብልት በእግዚአብሔር ሙሉ ሁኖ - ራሱን ችሎ - ከመጋቢዎቹ ደረት ወርዶ - የእናቱን ጡት ጥሎ - እግዚአብሔርን በማወቅና በመተባበር ወደሚኝ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደመሆን የሚደርስበት ወንጌል - ዘመን የመንግሥቱ ወንጌል እንደሆነ ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንጮሃለን፡፡

የቤተክርስቲያን ዘመን ወንጌል(በተሰጠው ክፍለ ጊዜ ትክክል ነበር) ከመንግሥቱ ወንጌል ዋነኛ ልዩነቱ አሟሟቹን ራሳቸውን አስችሎ በእግራቸው አለማቆሙ ነው፡፡ ለመጋቢው - ለአገልጋዩ - ለሽማግሌው - ለቡድን መሪው - ለኳየር መሪው - ለሰብሳቢው… ... ጥገኛ ያልሆነ፣ በራሱ ብቃትና መላት የሚይሰማው፣ የእነዚያን አገልግሎት ካላገኘ በቅሬታ(በወስጥ ጉድለት) መንፈሱ የሚሳፈፍ ስንት አለ?!... እንግዲህ ቤተክርስቲያን ይህንን ዘመን - ሁኔታ - ድካም - አገልግሎትን ነው አትንኩብኝ የምትለው፡፡

በመንግሥቱ ነፍሳት ከሃይማኖት እስር ቤት ያመልጣሉ

ቤተ ክርስቲያንንና መንግሥቱን አወዳድረን ስንጽፍ የሁለቱ ልዩነት እንዳለ ሁኖ የቤተ ክርስቲያን መጨረሻ የመንግሥቱ ተገልጦ መሉ በመሉ መሥራት ነው ሚለታችን እንደሆነ ይታወቅ፡፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ተሰወሮ ያደርግ የነበረው መንግሥቱ ሲገለጥ የተሰወረበት ቤተ ክርስቲያን በተራዋ(እዚህ ጋ አካሉ ናት) በእርሱ ትሰወራለች - መንግሥቱን ብቻ ልትገልጥ፡፡ በመንግሥቱ እያንዳንዱ መሉ ይሆናል፡፡ ራሳችንን በእግዚአብሔር ሕይወትና መላት ወደምናቆምበት ማንነት እንምጣ፡፡ ከቤተ ክርስቲያን የታጣው ይኸው ታላቁ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው፡፡ በአገልግሎቶች ሁሉ ይሄ አልተቻለም፡፡ እንድያውም ይሄ ነገር ሲታሰብ ፍጹም ተስፋ ወደ መቁረጥ ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡ ይሄም በሚከት እቅድ ሁኗል፡፡

‹‹እኛ ሁላችን ከመላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል›› የሚለው የጌታ ሐሳብ አካል የሚገኘው በእስከ አሁን አገልግሎት ሳይሆን በመንግሥቱ እንደሆኑ አወቀን እንዘርጋ፡፡ እያንዳንዱ በመላቱ ይሞላል፡፡ ጌታም እያንዳንዱን ነው በስሙ የጠራው፡፡ እግዚአብሔር የልጅ ልጅ የለውም፡፡ እግዚአብሔር ለማንም አባት እንጂ አያት አይደለም፡፡ ስለዚህ እስካሁን በእግዚአብሔርና በእያንዳንዱ ሚከል የገባ አገልጋይ፣ አገልግሎት፣ ከህነት፣ መጋቢነት፣ ቄስ፣ ወንጌላዊ፣ …የወሰነለት በድካም - በዝለት አልቆ ስፍራውን ሁሉን ለሚዛው ያስረከባል፡፡ ይሄ መንግሥቱ ነው፡፡ ሁሉ ያወቀውና ይተባበረው ዘንድ እግዚአብሔር በሁሉ ሊኖር ነው የዘላለም ሐሳቡ፡፡ ምንም እንኳ በተባበሩ - አንድ በሆኑ ብልቶች(Corprate Body of Christ) የእግዚአብሔር መላት ቢታይም እያንዳንዱ ብልት በእግዚአብሔር ሚዛን ዋጋ ተሰጥቶታል - መሉ ዋጋ፡፡ ስለዚህ በመንግሥቱ ወንጌል ሁሉም እግዚአብሔርን ሰፍሮ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ ይሄ ታላቅ ምሥጢር ነው፡፡

እስካሁን የሆኑ አገልግሎቶችና ስጦታዎች፣ ልምምዶችና አሠራሮች እርሱን ብቻ እንድናወቅ ያደረጉ ከሆነ ሚልካም አገልግለዋል፡፡ ‹‹… ክርስቶስን እናየዋለን››(ዕብ.2÷9) ሚለቱም ማንም ከእርሱ ሌላ እንዳያይና እንዳያገለግል ሁኗል፡፡ ከመጀመሪያው ባል ሞት የተፈታነው እርሱ ብቻ ሊያገባን እንደሆነ ግልጽ ይሁን፡፡ አንድ ባል አለን፡፡ አገልግሎቶች፣ ስጦታዎች፣ ቢሮዎች፣ ቅባቶች፣ ራእዮች፣ … ወደዚህ ባል ሊያጫጉ - እኛን ለእርሱ ሊያጩ ተልከዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ ወይም በጎደለ ቢያደርጉ በሰበሰቡት ሊሰፍፉ ነው፡፡ ግን እነዚህ ሁሉ የሚሰጡቸው ግብ ይሄ መሆኑን አብያተ ክርስቲያናት አወቀዋልን?... አሳዛኙ ግን ብዙ አገልጋዮችና አገልግሎቶች በክርስቶስ ሚስት የራሳቸውን ‹‹ዘር›› ለሞር ተመኝተው በሚድረግ ለብዙ ጊዜ ማመንዘራቸው ነው፡፡ ገና ለመንግሥቱ ሰሚያት አልተሰለቡምና ለአብ ፈቃድ ጃንደረባ አይደሉም፡፡

ብዙዎች የራሳቸው ፈቃድ፣ የራሳቸውን ራእይ፣ የራሳቸውን መለጥ… በክርስቶስ ወድ ሕዝብ ላይ በሞር የተላኩበትን ዓላማ ስተው ተገኝተዋል፡፡ በቤተክርስቲያን ዘመን የጃንደረባ አገልግሎት በጉልህ አልታየም መሉ በመሉ የለም ባይባልም፡፡ በእርግጥ በመንግሥቱ ነው የጃንደረባ አገልግሎት፡፡

‹‹…ሚልከ መልካም የሆኑ ደናግል ለንጉሡ ይፈልጉለት፤ ሴቶችን ከሚጡበቅ ከንጉሡ ጃንደረባ ከሄግ እጅ በታች እንዲያደርጓቸው …የሴቶች ጠባቂው የንጉሥ ጃንደረባ ሄግ… ›› (አስ.2÷2-3፣15 ያንብቡ)፡፡

በዚህ ክፍል አንድ ነገር እኛ እንዳሰመርንበት ሳይሆን እናንተ በመንፈሳችሁ አስምሩበት፡፡ ጃንደረባ የሴቶች ጠባቂ መሆኑ! መጽሐፍም - ‹‹ጃንደረባው እኔ ደረቅ ዛፍ ነኝ አይበል›› ሚለቱ በእርግጥ ጃንደረባ ከራሱ የሚያወጣው የራሱ የሆነ ምንም የለውም፡፡ ለራሱ - ለእኔነቱ መታል፡፡ ደረቅ ዛፍ ሕይወት የለውም፡፡ ልምላሜ የለውም፡፡ስሜት የለውም፡፡ ፈቃድ የለውም፡፡ ራእይ የለውም፡፡ በቃ፤ ከዚህ ዓለም ሚልከ፣ ፋሽን፣ ባሕሪይ፣ ማንነት፣ አስተሳሰብ… ወጥቷል፡፡ ይሄ ጃንደረባ ነው - የተባረከ ይሁን! እንግዲያውስ እንዲህ ዓይነቱ ጃንደረባ ነው የንጉሥ ሚስትና የንጉሥ ሴቶች የሚጡበቅ፡፡ ንጉሥ ለእርሱ በእጁ አሳልፎ ይሰጠዋል፡፡ ይታመንዋል፡፡ ጃንደረባ ‹‹ዘር›› አልባ ደረቅ ዛፍ ነውና የንጉሥ ሚስት ወይም ሴቶች ልጆች በእጁ ይጠበቃሉ ለንጉሥም ያሰናዳሉ፡፡ ጃንደረባው ለንጉሡ ቢያጭ ወይም ቢያዘጋጅ እንደ ንጉሥ ነገር - እንደ ንጉሥ ፈቃድ - እንደ ንጉሥ የመንፈሱ ስሜት እንጂ ጨርሶ እንደ እርሱ አይደለም፡፡ በንጉሥ ነገር ብቻ ያጫል ያሰናዳልም፡፡ ጃንደረባው ከዚህ የሚልፍ ማንነት የለውም ወገኖች ሆይ፣ የምንለው ይገባችኋል? እግዚአብሔር የመንፈሱን ሚስተዋል ለእናንተ ያድርግ፡፡ … ቤተክርስቲያን ከእነዚህ ዓይነቶች በብዙ ተራርቃለች፡፡ እነዚህ ደግሞ የትም አይገኙም፡፡ በዚህ ዘመን የትም የሞሉት የራሳቸውን ነገር በንጉሥ ሚስት ላይ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ለዚህም ተመድበዋል፡፡ ይህንንም ስንል በጎዘን ነው፡፡

‹‹በእናታቸው ማኅፀን ጀንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፣ ሰውም የሰለባቸው ጀንደረቦች አሉ፣ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጀንደረቦች አሉ፡፡ ሊቀበለው የሚቻል ይቀበለው አላቸው›› (ማቴ.19÷12)፡፡

ንጉሥ አርጠክስስ የሴቶችን - የሚስቶችን ጉዳይ በጀንደረቦች እጅ ፈጽሞ መተው ትክክለኛ ወሳኔና አካሄድ ነበር፡፡ ጀንደረቦች የራሳቸውን ‹‹ነገር›› በንጉሥ ‹‹ሴቶች ልጆች›› ላይ ለሞር ዕድሉ ብቻ ሳይሆን ችሎታውም የላቸውም፡፡ ያ ችሎታ ነው እግዚአብሔር የሰለበውና የቆረጠው፡፡ ይሄ በእግዚአብሔር ብቻ ይሆናል፡፡ በቤተክርስቲያን ዘመን ግን ይሄ ነገር አልታየም፡፡ የሚበዛው ከሽለፈቱ ጋር ነው፡፡ ይሄ አባባል መንፈሳዊ ነው ወገኖች ሆይ፡፡ ብዙዎች አልተቆረጠም፡፡ አልተገፈፉም፡፡ ስለዚህ ሁሉም፡- ‹‹የእኔ ወንጌል - የእኔ ራእይ - የእኔ መለጥ - የእኔ ትምህርት (ዶክትሪን) - የእኔ ደንብ - የእኔ ልምምድ - የእኔ ስጦታ - የእኔ ፕሮግራም…›› የሚለው ለራሱ በራሱ እወቅና - ክብር - ጌትነት - ባለቤትነት… የሰጠው ነገር አለው፡፡

እንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ(በዚህ ማንነቱ) በቤተክርስቲያን ዘመን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ጋር አመንዝሯል፡፡ በምንዝርና ተይዘው በእግዚአብሔር ፊት ሟልስ ሊሰጡ የሚገቡ ብዙዎች አሉ፡፡ እግዚአብሔር በአንድ ዘመን የተጠቀማት የከበረ ስጦታውን፣ አሠራሩን… ትቶት ካለፈ የቤተክርስቲያን ጎበዛዝት በማኅሌት ቢጠቀማት - ቢያገለግሉበት ያ ነው የከፋ ማመንዘር፡፡ ታዲያ ዛሬ ቤተክርስቲያን ወስጥ ያሉ ስመጥር አገልጋዮች በዚህ የሚሰሰሉ አይደሉምን?

ደግመን እናሳስባችኋለን፤ ስለመንግሥተ ሰማያት የተሰለቡ(ፈቃዳቸው የጠፉ) ጀንደረቦች የራሳቸውን ነገር በንጉሥ መቐራ ላይ ሞኖር አይሆንላቸውም፡፡ በእነርሱ ግን የንጉሥ ዘር - የእግዚአብሔር ሕያው ቃል - ክርስቶስ አለ፡፡ ከሚራመደው ንጉሣቸው ጋር በመራመድ ሲያደርግ ያዩትን ብቻ ያደርጋሉ፡፡ ከእርሱም የሰሙትን ብቻ ይናገራሉ፡፡ ከንጉሥ ፈቃድ ወጭ ፈቃድ የላቸውም፡፡ በንጉሥ ልጅም ላይ የሚያደርጉት ይሄ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ታላቅ አገልግሎት እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

‹‹ስለዚህ ኢየሱስ ሟልስ እንዲህም አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፣ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና፡፡ … እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፣ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና››(ዮሐ.5÷19፣ 30)፡፡

ክርስቶስ ሁሉ ነው፡፡ በማን? በሁሉ፡፡ እግዚአብሔር ሁሉ ነው፡፡ በማን? በሁሉ (1ቆሮ.15÷28)፡፡ ይሄም የዘላለም ሐሳቡ ፍጻሜ ነው፡፡የዚህ መላት በእርግጥም የመጽሐፍ ብቻ ሳይሆን የመለጥም ሜጨረሻ ተደርጓል፡፡ ዳሩ ግን ይሄ ታላቁ የጌታ ቀን ይመጣ ዘንድ - ይሞላ ዘንድ አሁን ያለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን - የተከፈለ አገልግሎት ሚርጀት - ሚለቅ - መድከም አለበት፡፡ ይሄ ደግሞ በትክክል እየሆነ ነው ያለው፡፡ ራሳችንን ካላታለልን በስተቀር የዚህ ዘመን ድካም - ነቀፌታ… በአገልግሎታችንና በምናገለግለው ሁሉ እንደበዛ ምስክሩ አያሌ ነው፡፡

እስካሁን ያበረቱን - ያተጉን - ያቆሙን - ያነቃቁን እጅግ ብዙ መንፈሳዊ ተግባራት ከፍታቸውን ነክተው ወርደዋል፡፡ የብዙዎቻችን መንፈሳዊ ጅማት የተፈታ መስሎበናል፡፡ በእርግጥም መንፈሳዊ አቅማቸን ጥያቄ ወስጥ ወድቋል፡፡ ለሠራው ዶክትሪኑ የተዋጋ - የተጋደለ - የተጋ - የተዋደቀ… ሁሉ ዛሬ መዘለፍለፉ ምስክሩ ብዙ ነው፡፡ መፄጃ ስላጣ ብቻ ይሆናል፡፡ ለዚህም እግዚአብሔር ስለ ተነሣብን አይደለምን? ለምን? እንደ በለዓም በጠባብ መንገድ አግኝቶ ሊያጣብቅና ሜጫችንን ሊሰብር - አሜን ይሁን!

አሁን አሁን የሚፎረጉ ጉባኤዎች - መጋቤያዎች ተስፋ አስቆራጩና አድካሚ ዳግመኛም ባይመለሱ የሚያስኙ ሁነ ውብናል፡፡ ወገኖች ይሄ ተጋኖአልን?... እንግዲያስ መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችሁ ምስክር ይሁን፡፡ በዚህ ሁሉ(ሃሌሉያ!) የሚመጣውን ጊዜ ተስፋ እንድናደርግ ሁነናል፡፡ ተስፋ ባልሆነን ጊዜ(አሁን ያለው ሁኔታ) ተስፋ ይዘን አምነናል(ሮሜ.4÷18)፡፡ የሚመጣው ቀን እስካሁን የነበረውንና ያለውን ሁሉ ያስረሳል፡፡ ስለዚያ ቀን አሁን ያሉት ተቃጥለው ይቀልጣሉ፡፡ ያልቃሉም፡፡ በሚመጣው ቀን እስካሁን ያልሆነ ታላቅ ነገር ስለሚሆን በአሁኑ መረዳታችን የሚሆነውን መገለጥ ያስቸግራል፡፡ ብቻ እንደ ጳውሎስ እንዲህ ማለት ይቻላል፡-

‹‹ነገር ግን፡- ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ እንዲህ እንናገራለን››(1ቆሮ.2÷9)፡፡

የአብርሃም ሎሌ(ዘፍ.24- መንፈስ ቅዱስን ይመስላል በዚህ ምዕራፍ) ርብቃን ለይስሐቅ ለማመጣት እርሷን የገመጣት ጥበቡ አብርሃም ካለው ነገር ከፍሎ በመሄድና በመስጠት እንደ ነበረ ስናስተውል ለመንፈሳችን የሚቻርልን መረዳት አለ፡፡ ርብቃ ከሎሌው ጋር ወደ መቐራው ጉዞ የጀመረችው በተቀበለችው ስጦታ ነበር፡፡ ጉዞዋን የጨረሰችው ግን ይስሐቅን(ሰጪውን) መሉ በመሉ

በማግኘት - በማወቅ - በመተባበር - በመግባት ነው፡፡ ይሄም መለጥ የምንጽፍበት ዋነኛ ሐሳብ እንደሆነ ልብ በሉ፡፡ ወዶቸ፤ የምንላችሁ ዋና ነገር እኮ ይኸው ነው፡፡ በስጦታዎች የጀመረው ጉዞአችን በሰጪው ሚለቅ - መመላት - መጸጸም አለበት፡፡

አሁን በእርግጥ ለርብቃ የእጅ አምባሩ - የእግር አልቦው - የአንገት ሰንሰለቱ - የጣት ቀለበቱ - መላወጫ ልብሱ - መጓጓገ ግመሉ... ምን ይረባታል እነዚህን የፈጠረወን - የሠራወን - ያወጣወን - ያስገኘወን - የሰጠወን ካገኘች? ቤተ ክርስቲያን ባልዋን - እስካሁን የባረካትን - ያዳናትን - የፈወሳትን - የሰጣትን የምታገባው በመንግሥቱ መምጣት - መለጥ - መመላት... ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ትዳን እንጂ አዳሷን፤ ትፈወስ እንጂ ፈዋሿን፤ ትባርክ እንጂ ባራኪዋን፤ ስጦታ ትቀበል እንጂ ሰጪዋን አላገኘችም፤ መሉ በመሉ አልወረሰችወም፡፡ ሠሪው ከሥራው ይበልጣል ምንም እንኳ ሥራው የባሕሪው መለጥ ቢሆንም፡፡ ሥራወን በሌለ ሥራው ሲሸር ሠሪው ከሥራው ይበልጣል፤ ምንም እንኳ ሥራው የባሕሪው መለጥ ቢሆንም፡፡ ሥራወን በሌላ ሥራው ሲሸር ሠሪው በምንም ዓይነት ለወጥ የለወም፡፡ ስለዚህ ለቤተ ክርስቲያን ከሆነው ሥራው ይልቅ ሠሪው ከቡር ነው፡፡ ዛሬ መሉ በመሉ አዳኙን አገኘሁት የሚል ይኖር ይሆን? ለዚህ ዓይነት ሰው ልዩ ሁኔታ ሁኖለት ይሆናል፡፡ በሁላችን የሚበቀው ያ የመለጥ ቀን ግን ለማንም አልሆነም፡፡ በእርግጥ የዚያን ቀን ክብር የቀመሱ ቅሬታዎች የሉም እኛ አላልንም፡፡ ጨምረንም በዚህ በቤተክርስቲያን ሌሊት ብዙ ብርሃን ተቀብለው የጌታን ቀን የተለማመዱ የሉም አንልም፡፡ ግን የእግዚአብሔርን ልጆች የሚልጠው የልጅነት ቤዛ አልተገለጠም ባዮች ነን (ሮሜ.8÷23)፡፡ እንደዚያም እናምናለን፡፡

ዳሩ ግን በሚሻሸት ዘመናት ሊያሳየን የወሰነው የጸጋው ባለጠግነት (ኤፌ.2÷6-7) አሁን ባለው ብርሃን መሉ በመሉ ሊያየው የሚቻል የለም፡፡ የክብር አምላክና አባት ይህንን ታላቅ የመንግሥቱ ክብርና ግርማ፤ ኃይልና ሥልጣን... የሚያሳይበት ጊዜ መጽሐፍ፡- ‹‹በሚሻሹ ዘመናት...›› ብሎ ከተናገረለት በፍጹም እስከ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ታድያ ስለዚህ ታላቅ ጊዜ - ታላቅ ቀን... አሁን ያለው ደካማው፣ ድንግዝግዙ፣ የተከፈለው... ይበልጥ መድከም፣ ማርጀት፣ ሚለቅና በሚጨሻም መወገድ አለበት ስንል ማንን ይሆን የሚያመው - በዚህ ቀን ዕድል - ግዛት - ክፍል - ርስት - ሕይወት... የሌለው አሮጌው ሰው ካልሆነ?

ወደሚበልጠውና ወደሚመጣው ክብር ለመግባት የዛሬው የትኛወም ነገራችን አላስፈለገም፡፡ እንዳናድግ ግን ሰዎች ያኖሩብን የሥርዓትን ድንበር መጣስ አለመቻላችን የሚለወን ቀን በጭላንጭል እንኳ ልናየው አልቻልንም፡፡ ስለዚህም በሰዎች የሃይማኖት ፍሬምና ቅኝት ብቻ የታገትን ምርኮኞች ነን፡፡ ነፍስ (መንፈስ) ወደሚወደው መንፈስ አልቻልንም፡፡ ሚሪዎች ሲነ ቃቁ ብቻ እንድንነቃቃ፣ እነርሱ ሲያድጉ ብቻ እንድናድግ፣ ሲያወቁ ብቻ እንድናወቅ... የተፈረደብን ይመስላል፡፡ ከዚህ የከፋ ባርነት ኖሮ እንደሆነ አናወቅም፡፡ የነገሩም መክፋት ይሄ ሁሉ በቤተክርስቲያን ወስጥ መሆኑ ነው፡፡

ዛሬ እየኖርንበት ያለው የሕዝብ - የጉባኤ - የማኅበር... አያያዛችን ከየት የተማርነው ይመስላችኋል? ዛሬ ቤተ ክርስቲያን እየሄደችበት ያለው ድርጅታዊ፣ መንግሥታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አገራዊ አካሄድ (system) ... መለስ ብለን ልንፈትሸውና ካልቻልን ይዘን የሚደው ትልቅ ወደ ሆነ አዘቅት መሆኑ በሁላችሁ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ ሕዝቡ - ወዱ የእግዚአብሔር ወገን በሕይወት፣ በሕይወት ቃል፣ በጸጋ፣ በፍቅር፣ ሁሉን በሚዛው መንፈሱ... ‹‹እየተጓዘ - እየኖረ ነው›› ብትሉ ሳታውቁ ነው አልያም ዋሽታችኋል፡፡ ምንም ሳይጋነን ሕዝቡን የያዘው የዘረጋንለት መዋቅር (system) ነው፡፡ እኛም የዚህ ሚልእክት ጸሐፊዎች በጭፍን የሥርዓት - የመዋቅር ተቃዋሚዎች አይደለንም፡፡ ድርጅት- ግሩፕ እስካለ ይሄ መኖሩ ይታወቃል፤ ሁሉ ለዚያ ይታሰራል ባንልም፡፡ ግን ይህንን የሰው መዋቅር ‹‹የእግዚአብሔር ሕይወት - የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን - የአብ አሠራር... ነው›› እንዳትሉት የሚዳደራችሁ የጌታ መንፈስ እንዲሆንላችሁ ይህ ተጽፎአል፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ነገር ወስጥ የለም፡፡ ያለመፍራት እንንገራችሁ፤ አሁን ባለችው ቤተ ክርስቲያን አሠራር እግዚአብሔር የለም፡፡ ሳኦል እግዚአብሔር ትቶት ሳለ ለሠላሳ ስምንት ዓመት በግዛቱ እንደ ነበረ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ያለ እግዚአብሔር በሥጋ ጉልበት እየተውተረተረች ትገኛለች፡፡ በእርግጥ ድናለች፣ ምሕረቱ፣ ጥበቃው፣ ስለስሙ የሚያደርገው መነብኘት የለም ሚለታችን ሳይሆን ሕዝብ የተያዘበት አሠራር፣ የወንጌል ስርጭት ዘይቤው፣ የትምህርት ሥርዓቱ... ወስጥ የእግዚአብሔር ጣት የለችም፡፡

ዮሐ.6÷68፡- ‹‹ቁ.63- ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወት ነው፡፡ ቁ.68 - ጌታ ሆይ፣ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የሕይወት ቃል አለህ...›››፡፡ ከርስቶስ (ሕዝቡን ሳይሆን) ደቀመዛሙርቱን በምን እንደያዘ ልብ በሉ፡፡ ዛሬ በምንድር ነው የተያያዝነው? በልካችን በተቀባበልነው ‹‹ቃላችን - ትምህርታችን››ና ሥርዓታችን አይደለምን? ማን ነው ሕይወት የሚኝበት ቃል ያለው? ማን ነው የሚፈርድ - የሚርድ - የሚመዘዝ ቃል ያለው? የብዙዎቻችን ቃል የቀጠነ፣ የተበረዘ፣ የለሰለሰ፣ ደካማ፣ ሰወን ደስ የሚያሰኝ... አይደለምን? ከርስቶስ ግን ደቀ መዛሙርቱን እስከ ሞጨሻ የራሱ ያደረጋቸው፡- አንደኛ - በተገለጠ ሕይወት፤ ሁለተኛ - በሕይወት ቃል ነበር፡፡ እነዚህም ሁለቱ በተገለጠና በተፈጸመ በእግዚአብሔር ፈቃድ ይገኛሉ፡፡ እስከ ዛሬ በእነዚህ ልናገለግል ተችሎናል? አንዋሽ፤ ምዕመናችንን የያዘው ከጸጋ ቃል ይልቅ የፍርድ (የሚፈራሪያ) ቃላችን ነው፡፡

ብዙኃኑ ወገን ድሮም ሆነ አሁን እግዚአብሔር ባደረጋቸው ተኣምራቶች፣ ድንቆችና ምልክቶች በጸሎትም መልስ ተይዟል፡፡ ይህም መልካም ነው ለጊዜው - እንደ መቼ መነዳን እስከናወቅ - ከብሩን እስከናይ፡፡ ከመቃን ትንሣኤው በኋላ ግን ከርስቶስ ከተኣምራት ይልቅ ከአምኒት መዞ ለሚበዙ ወንድሞች ራሱን አሳያቸው(ሥራ.1÷3)፡፡ሕይወታችን በምናየው (በተረዳነው) የተወሰነ ነው፡፡ በራሱ ይራመዱ፣ ያደርጉና ይኖሩ ዘንድ ራሱን አሳያቸው፡፡ ይሄ ነው አገልግሎት በመንግሥቱ መርሕና መንፈስ ብቻ የምናገኘው፡፡ ጌታ ሆይ፣ ይህንን በእኛ ታደርግ ዘንድ ንቃ፡፡ ይሁን - አሜን፡፡

እውነተኛ ለውጥ በቤተ ክርስቲያንና በሚኒስትሪዎችሚሽነፍ ወይስ ሞሽነፍ?

ከምድር ወይም ከሰውነት ከተዋጀው ከእግዚአብሔር ልጅነት በቀር ማንም በባሕል፣ በልማድ፣ በአካባቢው ሁኔታ፣ ባደገበት ሥርዓት፣ በተማረው ትምህርት ሊታገስና ሊወሰን ተጽዕኖ ይደረግበታል፡፡ በአንድም በሌላም መንገድ ሁሉም የዚህ ሰዉ ነው፡፡ ጽንስ በማኅፀን ወስጥ ሊሆን የሚችለውን ከማኅፀን ውጭ ሊሆን ከቶውንም አይችልም፡፡ ያ ጠባብ ስፍራ ትንሹ ጽንስ - ይመቸውም አይመቸውም የተወሰነለት - የተሠራለት ልክ ነውና በዚያ ይኖራል፡፡ አስገራሚው ነገር ግን ጽንሱ በዚያ በተወሰነለትና በተሰፈረለት ልክሁኖ ለመለጥ ሚደጉና ለመውጣት መግፋቱ ይሆናል፡፡

ጽንሱ በተወለደ ጊዜ ግን፣ ቀድሞ ከነበረበት ክልል የሆነበት ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡ ሕይወቱ በሌላ ላይ መደገፉ ማበቃት ይጀምራል፡፡ ሕዋሳቶቹ ሚደግ ብቻ ሳይሆን ትከክለኛ ሥራቸውን ማከናወን ይጀምራሉ፡፡ ወደ ሌላ ክበብ - ወደ ሌላ ሁኔታ ተለውጧልና! በእርግጥ ጽንሱ መላወጥ - ሚደግ - መጠርታት ... መጀመሩ እንጂ ሌላ ነገር አልሆነ ም፡፡

ይሄ ምሳሌ ለቤተ ክርስቲያንና ለመንግሥቱ እንደሚሆን ወስደን ብንተረጉመው ተስማሚ ይመስለናል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት መላት የሚሆነው የቤተ ክርስቲያን ዕድል ቢገለጥ ዛሬ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ያለችበት ሁኔታ በጽንስ - በሌላ ዓለም - በሌላ ክበብ ናት፡፡ እርሷም ወደ ሌላ ዓለም - ወደ መገለጥ - ወደ መታየት - ወደ ምታድግበት - የተፈጠረላት(ኦርጋን)ሁሉ በትክክል ወደ ምትሠራበት ክበብ የምትገባው በመንግሥቱ ነው፡፡ አሁን መንግሥቱን እንደ ወረሰች ኋላ በመንግሥቱ ተሰወራ መንግሥቱን መገለጥ - መንግሥቱን መኖር - መንግሥቱን መሆን ትጀምራለች፡፡

ጽንሱ የእናቱ ጥገኛ ነበረ፡፡ በመወለድ - በመገለጥ ከብዙ ነገር ነፃነቱን ያወጃል፡፡ ራሱን ከሚይዘረጋበት ከዚያች ጠባብ ዓለም ብቻ ሳይሆን ራሱን ከብዙ ሁኔታ ነፃ ማውጣት ይጀምራል፡፡ በማኅፀን ሳለ ለመኮንፈስ፣ ለመበላት፣ ለመኖር፣ ለሚደግ... በእናቱ ሕልውና ላይ የተመሠረተ ነው፡፡... ወንድሞች በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ በሽል ወስጥ ያሉ ጽንስ ናቸው - የእናታቸው ጥገኛ! በእናታቸው ሕይወት መኅበን ብቻ የሚኖሩ፡፡ በእናት መታመም የሚታመሙ፡ በእናት ድካም የሚደክሙ ብዙ ናቸው፡፡ እናት ብትታመም ስለ ጽንስ መድኃኒት የማትወስድበትና ራስዋን የማታከምባት ዓለም አንድያው የሚሰጋበት ዓለም!

የሚሞላውና የሚለጠው የመንግሥቱ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ጽንሶች - ወንድሞችና እኅቶች ከጽንስ የሚወጡበት - የሚለጠበት ዘመን ይሆናል፡፡ ማንም ግን ዛሬ፡- ‹‹እኔስ›› በግሩፕ ደግሞ፡- ‹‹እኛስ ወጥተናል›› የሚሉ ወገኖችና ‹‹ሚኒስትሪዎች›› ቢገኙ በእርግጥ የእናት እንጂ የማነት ለወጥ አላደረጉም፡፡ ከ‹‹እናት ቤተክርስቲያን››(ዲኖሚሽን) መውጣት ብቻ መንፈስ እግዚአብሔር ለእኛ ወደ ወሰነው ከፍታ መውጣት ነው ብሎ ማንም በራሱ ላይ አያፊዝ፡፡ ዛሬ ከአበሾች ማኅፀን ወጥተው ወደ ምዕራባውያንና ወደ ነፍሎ ማኅፀን የዞሩ አሉና፡፡ ብዙዎች የፈረንጅ ጡት እየጠቡ ናቸው፡፡ ከ‹‹ፈረንጅ›› ወንድሙ ያልተቀበለ የትኛው ‹‹ኢትዮጵያዊ›› ወንድም ነው የትወልዱን ምልክት - የጊዜውን ቃል አግኝቶ ‹‹ሚስትሪ የከፈቱ?››... ከወጭ ወንድሞች እንማር፤ ግድ የለም፡፡ ዳሩ ግን ‹‹ከጽንሳችን›› ወጣን አንበል የሚከመንን ቀየርን እንጂ፡፡

ከእንግዲህ የማኅፀን - የእናት - የጡት ለወጥ ሚድረግ አይደለም፡፡ ይሄም መጋቢነትን - ስፍረ -ዘመንን በአደራ መቀበል አይሆንም፡፡ እርግጠኛ እንነጋገር፤ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ‹‹ጉልቻ›› ብቻ ነው የተለዋወጡት፡፡ ሁሉም ነገር ያው ነው፡፡ በእርግጠኝነት ለመሞላት፡- ማን ነው ከእኛ ዘመን - ትወልድ የተሰጠው? ዘመንን - ጊዜን ከሰው ውጭ ሳይሆን በሰው ወስጥ የለወጠ ከእኛ ማን ነው? የሰው ልብ ሳይሆን የሰው ልብስና የሰው ኪስ ዳግመኛ እንዲወለድና እንዲለወጥ ማልገል ነው ‹‹ዘመን ተሰጠኝ›› የሚያስኘው?... ከእናቴ ማኅፀን ወጣሁ የሚለው ወገን እኮ ከቀደመው ቲዮሎጂ ምንም የተለየ ነገር የለውም፡፡ ያለ ጊዜም ከማኅፀን መውጣት ወርጃ እንጂ መወለድ አይደለምና እርሱም ያስፈራል፡፡ ‹‹ወጣሁ›› ባዩ ወገን ሳያወቀው እዚያው እናቱ ሽል ወስጥ እንዳለ ዛሬ በሚሚረው፣ በሚያስተምረውና በሚመሠርተው ድርጊቱ ይቁጠረው፡፡ እኛ ግን ሁሉም ገና ያልጠነከሩ - በራሳቸው መቆም የሚችሉ - የሚይዝ ደጋፊ ከሌላቸው የሚቃጩ መንፈሳዊ እንቦቃቅላ(spiritual infants) ናቸው ለሚለት አንፈራም፡፡

የአገልግሎትና የልምምድ ኩረጃ የትም ነው፡፡ አንድ ጊዜ በካናዳ - ቶሮንቶ ከተማ ‹‹የሳቅ ሪቫይቫል›› ተነሣና ካሪዝማቲኮች ባሉበት ዓለም ሁሉ መሳቅ ያዙ፡፡ በአንድ ሀገር ‹‹በመሳካት መወደቅ›› ሲጀምር ያንን ያየ ወይም የሰማ በዚያው ዓይነት ሁኔታ ይወድቃል፡፡ የዚህ ዐምድ አዘጋጅ አንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ጠየቀ፡- ሁሉም የሚወድቁት በጀርባቸው ነው እንዴ?! ለምን በሆዳቸው ወይም በጎናቸው አይወድቁም?... በቃ፤ ይሄው ነው ያዩት፡፡ ከዚህም የተነሣ ጸሐፊው እንዲህ አስቦ፡- ‹‹ሲነካ የሚኮለው›› አገልጋይ ቢነካኝ ፊት ለፊት በሚነካኝ ላይ ነበር የምወድቀው፡ ‹‹አስተናጋጁ›› ማንን ‹‹ይደግፍ›› ኖሯል? ሁሉም አወቆ ስለሚወድቅ ሆዱ ላይ ወድቄ ችግር ቢፈጠርስ?!!... እንደ እነዚያ ወገኖች ቀልደናል - ያሳዝናል፡፡

ይሄ መወደቅ ነው፡፡ በሌላ ሀገር ደግሞ መገፍገፍ ሲጀመር ሁሉም ያንኑ ተከትሎ ይለዋል፡፡ አሁን ደግሞ የት እንደ ተነሣ ባናወቅም ‹‹ሆሊዳንስ›› ተብሎ ተጀምሯልና ሁሉም ይደንሳል፡፡ የብሔር ብሔረሰቦችም ወዛዋዜ ‹‹ኢየሱስን በሚወድሱ›› ጥቂት ስንኞች እየተበረከተልን ይገኛል፡፡ ይሄም እስኪቀር እንለዋለን፡፡ የሚሠት ፈሊጦች ሁሉ ለጊዜው የሰዉን መንፈሳዊ ጥማትና ርሀብ ያስታገሡ በመምሰል የአንድ ወቅት እሸት ያህል ዕድሜ ሳያገኙ ጠወልገው ይወገዳሉ፡፡ እነዚህንም ሰው ሠራሽ ‹‹መንፈሳዊ ሜክሪኾችን›› ያማከሉ ወገኖች ሕዝቡን ወደ ሌላ የሃይማኖትና የሥርዓት አሽኮለሌ ሊከቱት በፈጠራቸው ይቀጥላሉ፡፡

እባካችሁን እንማማር፡፡ እንተማመን፡፡ ይሄ ተራ ትችት አይምሰላችሁ፡፡ ሁላችንንም ሊያርም የመጣ የጊዜ ቃል እንደሆነ ልብ በሉ፡፡ ትችትም እኮ በጽድቅ ይጠቅማል፡፡ እኛም በሚነቸው ነገር ወስጥ በአንድም በሌላም መንገድ አለን፡፡ ይመላከተናል፡፡ ግን ተያይዘን ካለንበት ለመውጣት ጊዜ ይሁንልን፡፡ አሁን ያሉ የሚሳሉ ያለፉና እግዚአብሔር ያደከማቸው ብዙ ነገሮች በእርግጠኝነት እያለቀላቸውና እያለቀባቸው ስለሆነ ከእነዚህ ልናመልጥ መቸኮል አለብን፡፡ መንፈሱ በዚህ ጊዜ በእኛ የሚያደርገው ታላቅ ሚዳን ይሄ ይሆናል፡፡ መጀመሮትና መቀባበል ከሆነልንም ስለ ለወጥ እንነጋገር፡፡ ለወጡም የአካሄድ እንጂ(ከእኛ ውጭ) የሥርዓት ለወጥ አይሁን፡፡ የለወጥ ሐሳብ - የለወጥ ‹‹ቲየሪ››ም በቃን፡፡ ለወጥን እንደ መንፈስ አሠራር ወደራሳችን እናቅርበው - እናምጣው፡ እስከ ዛሬ በሆነው አገልግሎትና ልምምድ የተለወጠው የትኛው የሕይወታችን ክፍል እንደሆነ ም በሚተዋል እንጥምር፡፡

እውነቱን ከተነጋገርን ለወጥ የተደረገው በምላሳችን - በስብከታችን አካባቢ እንጂ በልባችንና በአካሄዳችን አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር አሠራር ‹‹ጥገናዊ ለወጥ›› ብሎ ነገር የለም፡፡ ይሄም በእግዚአብሔር መንግሥት አይታሰብም፡፡ በየትወልዱም ሚስተኛ ለወጦች ተካሂደዋል፡፡ በታሪክም የሆኑት የቤተ ክርስቲያን የትምህርትም ሆኑ የልምምድ ለወጦች በተወሰነላቸው ልክ ብቻ ነው፡፡የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመጣውን ሁሉ አቀፍ ለወጥ አንሥተን ከተነጋገርን ግን የእስከ ዛሬ ለወጦች ምንም ሚለት አይደሉም፡፡

‹‹ለወጥ አምጥተናል - የለወጥ ንጋት በሕይወታችን ጀምሯል - አዲስ ስፍረ ዘመን ተሰጥቶናል - የትወልዱ ምልክት አለን...›› የምንል ከሆነ ለአፍታ እንኳ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ የተሟርናቸው የመጀመሪያና ‹‹መሠረታዊ›› የሚሉ ትምህርቶች ያደረግንባቸው የሚዳት ለወጥ ካለ እስቲ እንመርምር፡፡... ዳግመኛ መወለድ፣ ንስሐ፣ ስለጥምቀቶች፣ እምነት፣ ቅዱስ ቁርባን... ከሚሉት የመጀመሪያ ትምህርቶች ጀምሮ ‹‹ከፍተኛና የሚጨሻ ነው›› ከሚለው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያሉት አስተምህሮዎች ለወጥ ካልተደረገባቸው ለዚህ ትወልድ ምንም ለወጥ አላመጣንም፡፡በነበረው ዘመን የምንሄድ እንጂ አዲስ ዘመን የተሰጠንም አይደለንም፡፡ እኛም የእግዚአብሔር መንግሥት የምስራች አብሳሪዎች የእስከ ዛሬው የ‹‹ቤተክርስቲያን›› እና የሃይማኖት የሚዳት ሰሚይ ሚርጀት - ሚለፍ - ሚላወጥ አለበት እንላለን፡፡ በእርግጥ አዲስ ሰሚይና አዲስ ምድር ከተፈለገ የእስከ ዛሬው የቤተክርስቲያን አሮጌ ሰሚይና አሮጌ ምድር ሚላወጥ - ማዋወጥ - ተጠቅልሎ ሚለፍ አለበት፡፡ እኛም ከዚህ ሌላ የሚያልፍም - የሚቃጠልም - ሰሚይም ሆነ ምድር እንዳለ አናምንም አናወቅምም፡፡ ይህም የሆነልን ከላይ ነው፤ ከራሳችን አንደ ሆነ የምንመካበት የለንም፡፡ ሞት ከተቻላችሁ ለወጥ ከዚህ ይጀምራል፡፡ የመንግሥቱም መገለጥ ይህንን ሁሉ ያደርጋል፡፡ የሚከበቀው የሚጨሻው ‹‹ዲስፐንሴሽን›› - ስፍረ - ዘመን - ዘመናት የመንግሥቱ ‹‹ዘመን›› ይሄ ነው፡፡

እንደ ተሰፈረለተ ጊዜ ማከን ከኖረ በኋላ ጽንስ ለመውጣት - ለመገለጥ - ለመወለድ ከወስጥ ወደ ውጭ ይገፋል፡፡ ይሄም ግፊት ለእናቱ ረብሻ - መዋወጥ - መድከም - ሕመም ነው፡፡ ይሄ ነገር በመንፈሳዊነቱ በቤተክርስቲያን አልሆነም ትላላችሁ? ምጥ - ጭንቀት - ጩኸት... በቤተ ክርስቲያን ለምን(ራእ.12÷2)? ለምን? ወንዱ ልጅ(ድል ነሺዎች) ከተሰወረበት ሊወጣ ደርሷል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሚያገባትን እስከትወልድ(‹‹ልጆችሽ ያገቡሻል›› ተብሎ ተጽፎአልና!) በጭንቅ - በድካም - በሚለቅ - በጩኸት... ወስጥ ናት፡፡ የብዙዎችም ‹‹አገልግሎት›› ዛሬ እግዚአብሔር ካመጣው ከዚህ ሁኔታ ‹‹ራስን›› ነፃ ለማውጣት የሚደረግ ትግል ብቻ ነው፡ ማንም የደረሰበት ነገር ከእናቱ ማነፀንና ጠት የሚጥለው ወደ አባቱም ድንኳን ይዛወር ዘንድ ከሆነ እንኪያስ በዚያ ድንኳን ያለውን ብቻ ይመልከት፡፡በዚያ ድንኳን ያለው አንድ ብቸኛ ደግሞ ክርስቶስ ጌታ ነው(ገላ.4÷19)፡፡ ለዚህ ነው ጌታ ለደቀ መዛሙቱ በምድር ብዙ ሥራ ካሳያቸው በኋላ አስበልጦ ራሱን ያሳያቸው(ሥራ.1÷3)፡፡ ሥራ ብቻ ያየ - ተአምራት ብቻ የሆነለት አልቆመምና የሚቆመውን ራሱን ማየት ነበረበት፡፡

ስለዚህም አደረገው፡ በሕይወታቸው እርሱ መሳል አለበት፡፡ ከዚያ ጀምሮ (ምንም ለብዙዎች የተሰወረ የእግዚአብሔር ሐሳብ ቢሆን) አንድ ነገር ብቻ ነው፡ - ክርስቶስን ብቻ አይተን እንድንራመድ (ዕብ.2÷9)፡፡

‹‹በሚያልፍ ሕይወት ኃይል እንጂ በሥጋ ትእዛዝ ሕግ ሳይሆን ሌላ ካህን በመልከ ጼዴቅ ምሳሌ ቢነሣ፣ ይህ እጅግ አብልጦ የሚለጥ ነው›› (ዕብ.7÷15-16)፡፡

ቤተክርስቲያን በሚለዋወጥ ሕይወት መሆኗ እንደ ተወሰነላት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጸጸት የለበትም፡፡ ከዚህ ወጭ ልትሆን አትችልምና! የሚለዋወጥ - የሞላ - የተፈጸመ ሕይወት በመንግሥቱ ብቻ ተወስኗል፡፡ በየወቅቱ በንስሐና በሌላ መለጥ ልምምድም ራስን ሚዳስ በቤተ ክርስቲያን እንጂ በመንግሥቱ አይደለም፡፡ ከህነቱ በሚያልፍ ሕይወት ኃይል በተመሠረተ ማኅበን እኛን የሚሥራበትና የሚያንጽበት ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ዕድሉ ዕድላችን - ሕይወቱ ሕይወታችን - ማንነቱ ማንነታችን ይሆናል - ግን በመንግሥቱ!

መልከ ጼዴቅ ከሌዊ ክህነት በፊት ነው፡፡ ከሌዊም በኋላ በዚህ ምሳሌ የተነሣው እርሱ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ከሌዊ ክህነት የነፃች ብትሆን በኒቆላውያን ትምህርት ባልተከሰሰችም ነበር (ራእ.2÷15)፡፡ በሌዊ ክህነትም ዘመን ቢሆን መልከ ጼዴቅ ከመጋረጃው ጀርባ ነበር፡፡ መንግሥቱ በቤተክርስቲያን ዘመን ከመጋረጃው ጀርባ ተሰውሮ እንደ ተጓዘ፡፡ ሌዊ እንጀራንና የወይን ጠጅን ሊያስወጣ እንጂ እንደ መልከጼዴቅ ሊያወጣ አይችልም፡፡ የሌዊ ክህነት - የ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› አገልግሎት ከራሱ የሆነ አንዳች ነገር የለውም፡፡ ሁል ጊዜ የሌላውን ደም አቅርቧል፡፡ አቅራቢው ያልተሠዋበት ዘመን ነበረ፡፡ ሕይወቱን - ራሱን የሚመገብ የተመሳከረለት መልከ ጼዴቅ ብቻ ነው፡፡ ይሄም በቤተ ክርስቲን ዘመን አይደለም በመንግሥቱ - በልጆቹ ዘመን እንጂ፡፡ ሕይወትና አለመጥራት - የሕይወት መላት መልከ ጼዴቅ ባለበትና በሞላበት እንደ ሆነ ስናወቅ አሁን ያለው የቤተክርስቲያንንና የሚስትሪን ዘመን በእግዚአብሔር ኃይል በመንግሥቱም ጉልበት ለሚሰለፍ ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር እንድንስማማ በሙሉ ኃይላችን እንነሣ፡፡

በሁለት ዓይን ያየንበት - በሁለት ጆሮ የሰማንበት - በሁለት ልብ ያሰብንበት… የሁለትነት ዘመን ሊያበቃ ደርሷል፡፡ አንድ ዓይን - አንድ ጆሮ - አንድ ልብ ጠፍሟት ነው (ሉቃ.11÷34)፡፡ “…thy eyes be single” - ይሄ መለጥ አንድ ነገር ብቻ እንድናይ የሚያሳስበን ይሁን! በእርግጥ ዛሬ በአንድ ዓይን - በአንድ ልብ አንድን ጌታ የምናይ ነን?... የዚህን መልስ እኛም ሆንን ማንም ሊመልስ አይሞክር፡፡ እያንዳንዱ የዚህን መልስ የሚገኘው ብቻ አይደለምን? ሳወል በደማስቆ መንገድ እንደ መሳለው በአንድ ዓይን እንዳለ አይመሳላችሁም? ግን አልነበረምና ጌታ በገሠመውና በጣለው ጊዜ ዓይኑን አሳወረበት፡፡ በሌላም ዓይን ተነሣ፡፡ ያንን የቀደመውን (የሕጉን) ዓለም ያየበት ዓይን አጥቶ ሌላ ዓለም - የክርስቶስን ዓለም ሊያይ (እንደ ስፍረ - ዘመኑ) በሌላ ዓይን ተነሣ፡፡ ጳውሎስ ወድቆ ከማኅዙ በፊት በሌላ ሃይማኖት፣ እምነት፣ ዶክትሪን፣ ሥርዓት፣ ፕሮግራም፣ ደንብ፣ ልምምድ… ነበር እኮ፡፡ ለወጥ ግን ከራሱ ከወሰጡ ጀመረና እርሱ ራሱ ወደ ሌላ እምነት፣ ሥርዓት፣ ልምምድ፣ ፕሮግራም፣ ትምህርት…አስወጣ (አሁንም እንላለን አደራ እንደ ተሰጠው መጋቢነት - ስፍረ ዘመኑ)፡፡

በዚህ ዘመን እግዚአብሔር እውነተኛ ሥር ነቀል ለወጥ ያደርጋል ካልን የያዝነው፣ የለመድነው፣ የምናወቀው፣ የተማርነው፣ የገነባነው ሁሉ አጥተን መሆን አለበት፡፡ ያለ ምንም ርኅራኄ፡፡ ሁኔታዎች እንዳሉ በቀጠሉበት የሚበቀው ለወጥ የሚሆን ነው፡፡ ባለንበት ሁነን ለወጥ የምንፈልግ (ነባሩ ነገራችን ሳይሸር) ከሆነ እግዚአብሔር ከኢትዮጵያ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት አልተሻለም ለሚለት ድፍረት አለን፡፡ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር የሚያደርገው ነገር ቤቶቹ እስካልፈረሱ ቀለም ብቻ ይቀባና፡ - ‹‹አድሻለሁ›› ይላል፡፡ እንግዳም ለሆነ ሰው የተቀቡ ሕንፃዎችን ሲያይ አዲስ ይመሳሉታል፡፡ ግን ከሚያቸው ሰው ሁሉ በፊት በዕድሜ ብልጫ እንዳላቸው የሚያውቀው የተረከባቸው ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ቀለም ሊቀባ አይመጣም፡፡ ያለውን ሁሉ በሞፍረስ ፍርስራሹን በመረግ (አዎን፤ በቤተ ክርስቲያን) አዲስ ሞርሐ - አዲስ ሥርዓተ - አዲስ ነገር - አዲስ ሕዝብ - አዲስ ዘመን - አዲስ ትምህርት… ያደርጋል፡፡

ይህንን አባባል የሚቃወም ይኖር ይሆን? … እንግዲያውስ ሊሆን ያለውን አዲስ ነገር የተነበዩት ነቢያትንና ጌታን ይቃወም እኛን ሳይሆን፡፡ የቤተ ክርስቲያን ለወጥ የሽምግሌ፣ የመቅር፣ የአስተዳደር፣ የሕንፃ፣ የበጀት፣ የፕሮግራም፣ የሥነ ሥርዓተ፣ የደንብ፣ የአገልጋዮች… ለወጥ አይደለም፡፡ የቤተክርስቲያን ለወጥ የእነዚህ ሁሉ በሌላ ተተክቶ መለወጥ ሳይሆን በእነዚህ በሚሉ ነገሮች ሁሉ አለመኖር ነው፡፡ የዚህም ዓይነት ለወጥ በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን እንድትቀጥል ሳይሆን እርሷ በሌለችበት መንግሥቱ እንዲቀጥል ነው፡፡

እኛ የምንጽፍበት ‹‹መጋቢነት›› ይሄ ነው፡ በዚህ ዘመን ‹‹ክርስትና›› እንደ እግዚአብሔር ቃልና ሕይወት ትርጉም የለሽና ከዓለም ሃይማኖቶች ያልተለየ የሰዎች ፍልስፍና ሁኗል የሚለኮት ሕይወት መሆኑ ቀርቶ፡፡ ሁሉም በራሱ ምንኞት(ዲኖሜሽን) ራሱን ሊመግብና ሊበላ እያበሰለና እያሸለ ከሚኖረው ሕይወት በቀር አልታየ ወም፡፡

ለወጥ ግን ከምን ይጀምራል?

ለወጥ በሰው ዘመን ወይስ በመንግሥቱ?

የዚህን ጥያቄ መልስ ፈጥነን ሳንመልስ ሌላ ተጨማሪ ነገር መጻፍ ተገብቶናል፡፡ ሳንዘገይም የምንመልሰው ጥያቄ በሁላችን ዘንድ ማጠየቁ ግድ እየሆነ ነው፡፡ ራሔል በአባቷ ተራፊም ላይ መቀመጧን ምን እንበለው? ራሔል የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አይደለችምን? የአባቷን ተራፊም ግን የማንቷ ሠረገላ ሚድረጓ የሚርም ነው፡፡ እግዚአብሔር የተወወጓ የመጀመሪያ ነገር አንሥቶን ብናስተምር ወይም ብንለማመድ ሕዝቡ ተከትሎ የሚመዘገበት ኤፉድ - ተራፊም እንዳይሆን የሚፈራና ራሱንም ሆነ ሌላወን የሚያስጠነቅቅ ቢገኝ ምስጉን ነው፡፡

‹‹መቄም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ በበትሩ መታው፤ ብዙም ውኃ ወጣ፣ ማኅበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ›› (ዘኁ.20÷11)፡፡

‹‹... የእስራኤልም ልጆች እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና መቄ የሠራወን የናሱን እባብ ሰባበረ፤ ስመኝም ነሐሽታን ብሎ ጠራው›› (2ነገ.18÷4)፡፡

‹‹ጌዴዎንም(የለመላወን ወርቅ) ኤፉድ አድርጎ ሠራው፣ በከተማወም በአፍራ አኖረወ፤ እስራኤልም ሁሉ ተከትሎ አመሳዘረበት፤ ለጌዴዎንና ለቤቱም ወጥመድ ሆነ ››(መላ.8÷27)፡፡

‹‹አዲስ በሚሉቱ ፊተኛወን አስረጅቶአል፤ አሮጌና ወራጅ የሆነወስ ሊጠፉ ቀርቦአል›› (ዕብ.8÷13)፡፡

በእነዚህ ጥቅሶች ሐሳብ ዙሪያ ለመጻፍ ከመቸኮላችን በፊት ከፍ ብለን ስለ ጠቀስነው ሐሳብ ጥቂት እንበል፡፡ በእግዚአብሔር እርምጃ ወደ ተወሰነልን የሕይወት ግብ ከመራመድና ከመዘርጋት ይበልጥ በአሮጌና በነበሩ ልምምዶች ከማኮራችንም በላይ ጠፍጣ ባልሆነና ስሜት በነገሠበት አካሄድ እንዳለን በጉልህ ይታያል፡፡ ዛሬ በአብያተ ክርስቲያናትና በሚሲትሪዎች ወስጥ ያሉት አብዛኞዎቹ ልምምዶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ሳይኖራቸው ቀርተው አይደለም፡፡ ዛሬ ልሳን ያለቦታወና ያለ ጊዜው ይደረግ እንጂ በልሳን መቃጠል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሻሻ አለው፡፡ ሰዎች ይወደቁ፣ ይንዘፍዘፉ፣ ይንዘራቸው ወይም ሌላ ነገር ይሁኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅስለት ልምምድ አይሆንም፡፡ የሚታየው የትኛወም ዓይነት ግርግር - እንቅስቃሴ - የሜዳስ - የሚሰማ ... ነገር ይሁን ከመጻሕፍት ዋቢ አለው፡፡ ነገር ግን በአሁን ጊዜ መሠረትን ለቅቆ ፍጹም ስሜታዊ - የሰው ነገር ሁኖና መስሎ መታየቱ ነው የሚያስተቸው፡፡ ስሜት ነግሷል፡፡ የሰው ሁሉ ሕይወት በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት(‹‹በመንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸወና...››) መሆኑ ቀርቶ በእንቅስቃሴና በድርጊት ታስሯል፡፡

ሁሉም ለዚህ ዓይነቱ ነገር ብቻ ትጉህ ነው፡፡ የብሉይ ማኅበር በሲናይ ተራራ የሆነለት ዓይነት የሚታይ፣ የሚዳሰስ፣ የሚሰማ፣ የሚሸተት... ነገር በዚህኛወም ማኅበር መከበቁ ያለመኖት ሐሳብ ሁኖ ሳይሆን እግዚአብሔር እንደ ተወው ሳያወቁ አሮጌን ነገር ሜለጉ ነው ያስፈረደብን፡፡ የአብዛኛዎቻችን ጉዞ የድንግዝግዝ - የሌላው ግልባጭ(ፎቶ ኮፒ) ዓይነት ጉዞ ነው፡፡ ብርሃን የተሰወረበት አካሄድና አገልግሎት ነው፡፡ ሕዝብ በስሜቱ ገመድ የኋሊት ተጠፍሮ ወደሚያወቀው በመሪዎቹ አመካኝነት እየተነዳ ይገኛል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ያዘሉና የተሸከሙ የሚሳላቸው ፈዘኞች በዝተዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ‹‹ይመራሉ››፡፡ ይነዳሉ፡፡ እወነት ለመገር ዛሬ ‹‹የክርስቶስ አካል በምድር አለች›› ብንል የሚመራት ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ወይስ ኮሜቴ? እርግጥ ነው ‹‹ማኅበራት›› እስካሉ ከዚህ አያመልጠም እኛም ይህንን አንክድም፡፡ ዳሩ ግን በዚህ አካሄድና ሥርዓት የእግዚአብሔር መላት - የመንግሥቱ ፍጽምና ይመጣል ብሎ ለማሰብ ማንም ይቀልድ ዘንድ አይፈቀድለትም፡፡ የቤተ ክርስቲያን አሠራር ለሚመጣው ዘመን ሲባል ሚጀትና ሚለቅ አለበት፡፡ ይህም ወራጅ ሊጠፉ በቀረበ መጠን የመንግሥቱ ንጋት እየደመቀ የከበረወን የሕይወት ወገግታ ያመጣዋል፡፡

እንኳን እኛ መቄ ራሱ ስለ በትሩ ዳግመኛ ማንሣት ማወራትም የለበትም፡፡ መቄ ያገለገለበት - ተላምር የሠራበት በትር ሚጀቱ - መሻሩን ሳያወቅ ሠራበትና ተሰናከለበት፡፡ ያገለገለበት ያ በትር ሳተበት፡፡ ወገኖች ሆይ፣ ተጠንቀቁ፣ የአንድ ዘመን ስጦታ በሌላኛው ዘመን ሰዎች ስተወበታል፡፡ ያንንም ተከትለው አመንዝረዋል፡፡ የቡና ቤት፣ የጎዳናና ሌሎችም ሴቶች እጎቶቻችን ከወንዶች ጋር ማመንዘራቸወን በፈረድንበት መድረክ እኛ ደግሞ በመንፈስ እግዚአብሔር በተወው ልምምድ፣ ስጦታ፣ አገልግሎት፣... አመንዝራን እንደሆነ ማን ይነግረናል? እግዚአብሔር የልቦናችንን ዓይኖች ይክፈት፡፡

የስሜት ልዕልናና የሰው ሐሳብ ከፍታ ‹‹እርግጠኝነት›› በያዘበት በአብያተ ክርስቲያናትና በሚስትሪዎች መድረክ እግዚአብሔር ከዚያ ጋር ተቀላቅሎ - ተዳብሎ ይሠራል ማለት ትልቅ ግልመትና ነው፡ ስድብም ነው፡ እግዚአብሔር በአብያተ ክርስቲያናትና በሚስትሪዎች አይደለም፡ እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነቱ ሥራ ጋር ይተባበር እንደሆነ ወይም ይህንን የምናየውን የምናስተወለውን ይሠራ እንደሆነ በእርግጥ በእግዚአብሔር ባሕሪይ ላይ ለመጥ ሁኗል፡፡ እግዚአብሔር ይከልከል፡፡ እግዚአብሔር አልተለወጠም፡ አጋንንት ቢጮኹና ቢወጣ፣ ፈወስ ቢደረግ፣ ተኣምራቶች ቢሆኑ... ይሄ አያስደንቅም፡ እነዚህ በየትም ሊሆኑ ይችላሉና፡፡ በእወነትና በጽድቅ መሆናቸው ነው የሚያስጣት፡፡ ግን አይደለም፡ ብዙ ዓይነት የተጫበረበረ ነገር አለ፡፡ አብዛኛው ነገር ግልጽና የሚሳርፍ አይደለም፡ ወሸት ተቀላቅሎ ይበልጥ ራሱን ገልጧል፡፡ ታድያ ‹‹እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ሁኔታ ወስጥ አለ፤ ይህንንም ዓይነት ነገር ይተባበራል›› ወይም ‹‹ከዚህ ጋር ተቀላቅሎና ተዋሕዶ ይሠራል›› ትላላችሁ?... እግዚአብሔር ይቅር ይበል፡፡

እግዚአብሔር አይዘበትበትም፡ ይልቅስ የሸሻችሁን - የተደበቃችሁን እግዚአብሔርን ፈልጉ፡፡ ሥርዓቶቻችሁ፣ ፕሮግራሞቻችሁ፣ የፕሮግራሞቻችሁ ቅደም ተከተል በእርግጥ እንዳለ አለ፡፡ አልተዛባም፡ ግን ይሄ ሁሉ የእግዚአብሔር መገኘት መለጥም ምልክት አይደለም፡ ሜረጃ፡- ሰባኪዎቻችሁና አስተማሪዎቻችሁ ቃል ጠፍቶባቸው ተረትና የሕይወት ገጠመኝ ብቻ ማወራት - አዲስ ነገር አለመገር ... ከምን ይመነጫችኋል? ... እግዚአብሔር በእነዚያ የጊዜውን ቃል አላኖረምና የለም፡፡ የጊዜው ቃል የትወልዱም ምልክት አልተሰጣቸውም፡ በትላንትናው ዛሬን ይኖራሉ፡፡ ከዚህም የተነሣ(ለእነርሱ) አሁን - ዛሬ ሳይሆን ነገ ሁሉም ነገራቸው ነው፡ እኛ ያየነውን እንጽፋለን፡፡ እናንተንም እናስጠነቅቃለን፡፡ ይህንን ማየት ካልቻላችሁ ምን እናድርግ? በኩበቱ(በነዉሩ) ላይ ለተቀመጠ ሕዝብ ሳንነግረው ቀርተን ብናጨጭበለት እግዚአብሔር እንዴት ይለቅቀናል? አንግዲህ የፈራነውን ፈርተን ነው የምንጽፈው፡

በሕጉ ኤፉድ ምሪት መጠየቂያ ኡሪምና ቱሚም ማኖሪያም አይደለምን? በጌዴዎን ዘመን ግን ሕዝብ ተከትሎ አመዘረበት፡፡ ለጌዴዎንና ለቤቱም ወጥመድ ሆነ፡፡ ዛሬ ያሉን ነገሮች ዘመናቸው ሁለት ሺህ ዓመት ሁኗል፡፡ እነዚህም በዚሁ ይቀጥሉ እንደሆነ ማን ነው ዋስትና የሚሰጠው? እግዚአብሔር ግን አስረጅቷቸው እንደሆነ የሚያወቅ ምን ነው ጠፉ? ወደ ሦስተኛው ሰማይ የምንገባው አሁንም የሁለተኛውን ስፍራ ልምምድ የመጥኝ ብለን ነውን? ወገኖች እንዲህ አይሁን፡፡ ሁለተኛው ሲያልቅ ሦስተኛው ይተካል፡፡ የሁለተኛው ስፍራ ልምምድ መጽሐፍ ቅዱሳዊና በአንድ ዘመን የተሰጠ የሚኮት ጉብኝት ነበረ፡፡ ነገር ግን ወደ ሦስተኛው ስፍራ ሕይወት ይዘነው እንግባ ብለን የምናማዝር እንሆናለን፡፡ አዎን፤ የተከፈሉት(የጳንጠቆስጤ) ሥጦታዎች ፍጹም በሆነው - በሰጪው መኖር - መረሳት አለባቸው፡

ወገኖች ሆይ፣ መጽሐፍ፡- ‹‹ጩኽ ነው›› ያለው፡ የታዘዘውም ካዘዘው ዘንድ ‹‹ምን ብዬ ልጩኽ?›› ብሎ ምሪትን ሽቷል፡፡ እኛም ጩኹ ተብለናል፡፡ ምን ብለን እንደምንጮኽም ተነግሮናል፡፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነው የምንጮኸው፡ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ስንጮኽ የቤተክርስቲያን ዘመን - የጳንጠቆስጤ አሠራር ሊኖር እንደሚችል ነው ጨምረን የምንጮኸው፡ መንግሥቱ በመላት እስኪመጣ ጳንጠቆስጤ መሥራቱ እንደ ቀጠለ ሁኖ መሉ ኃይላችን ግን የመጥራቱን ዋጋ ወይም ግብ ለመያዝ መዘርጋት ይሁን፡፡

አንድ ነገር ግን ተመልከቱ፡፡ ዛሬ በጳንጠቆስጤ አማኞችና በካሪዝማትኮች ዘንድ ልምምዱ ምን ይመስላል?... በእኛው ሀገር በኢትዮጵያ የስድሳዎቹ መጀመሪያ ጳንጠቆስጠ የአሁን ዘመኑ ፈጽሞ የተለየ ነው፡ ለነባሮቹ አርጅቶብናል፡፡ለዛ አጥቶብናል፡፡ የእግዚአብሔር ‹ሰብስታንስ›› ከ ‹‹ጳንጠቆስጤ›› የወጣ ይመስላል፡፡ ጳንጠቆስጤ አይሆንም፡ በሰው ስሜት የታጀበ አስመሳይ ጳንጠቆስጤ ብቻ ነው የሚሆነው፡ ደግሞስ ጳንጠቆስጤ - አሁን ያለው የቤተክርስቲያን ልምምድ በሚሞክሑ ዘመናት ይታደሳል ትላላችሁ? ... ትልቁ ‹‹የሕይወት›› እንቅልፍ እዚህ ጋ ነው፡ በእግዚአብሔር ፕሮግራም እግዚአብሔር ራሱ ወደ ዳስ በዓል(Engethering) እየወሰደን እንጂ ጳንጠቆስጤን አድሶ አይመልስም፡ የእነ ሐዋርያት ዘመን ዳግመኛ አይደገምም፡፡እግዚአብሔር ወደ ኋላ አይሄድምና፡፡ ሎዶቅያ ወደ መጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኤፌሶን አትሻገርም፡ እግዚአብሔር ድርጊቱንና ጥላውን አይዞርም፡ ይሄ የሰው ሕይወት ነው፡ እግዚአብሔር የሚራመድ ተራማጅ አምላክ ከሆነ ከፊት ለፊት ያለው ደግሞ ጳንጠቆስጤ አይደለም፡ ዛሬ ይህንን ሳያወቁ በጥንት መረዳታቸውና ልምመዳቸው ስጦታቸውም ካሉት ካረጀው ነገር ጋር እንዳመዘሩ መንፈስ ይመስከርባቸዋል፡፡

ማንም ግን ስለምንለው ነገር ተቃርኖ በአጥቢያውና በሚስትሪዎች ዘንድ እየተደረገ ያለውን ልዩ ልዩ ልምምዶች ለማስረጃ ቢጠቅስልን እንደ ሌሉ ለማስመን አንደክምም፡ ስለ ስሙ እግዚአብሔር ምን ጊዜም ለሕዝቡ መሥራቱን እናምናለንና፡፡ ግን ‹‹ይሄ ሁሉ የእግዚአብሔር የጊዜው ሐሳብ ነው›› ብለን ለመቀበል ልብ የለንም፡ የጳበል ውኃ ጠጥቶ ወይም ከሊኪከ ሄዶ ‹‹ተፈወሻለሁ›› ብሎ ‹‹የሚመስከረውን›› ሰው ‹‹አልተፈወስከም›› ብሎ መከራከር ዋጋ የለውም፡ ሰወየው የሄደበት መንገድ ግን ትክክለኛ የእግዚአብሔር መንገድ ነው ብሎ ማንም አያስተምረን አይከራከረንም፡ ልብ ከኢያሱስ በራቀበት ከንፈሮች ግን

ኢየሱስ ጠርተው የሚሆን ነገር አይጠፉምን ማንም አያስተን፡፡ የተመረጡትን እንኳ ሊያስት የሚቻል ታላላቅ ነገር በሰይጣን - በሥጋ ይደረጋልና ይህንን ልብ በሉ፡፡

ወደ ጥያቄአችን እንመለስ፡፡ ለወጥ ግን ከምን ይጀምራል? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ለወጥ ከመረዳት - ከትምህርት - ከራእይ መለወጥ ይጀምራል፡፡ ከመንግሥቱ በፊት ጥቂቶች በመረዳት - በትምህርት - በራእይ - በመለጥ - በጽድቅ - በመንግሥቱ መርሕ... እስከ ዛሬ ከተቀበሉት መለወጥ አለባቸው፡፡ የተለየ መከማች መከማች አለባቸው፡፡ እንዳልናችሁ ከንስሐ፣ ከዳግመኛ ልደት፣ ከደኅንነት... ጀምሮ ያላቸው ትምህርት አሁን በተገለጠው በእግዚአብሔር ሐሳብ መፈተሽና መለወጥ አለባቸው፡፡ በጥንቱና አሁን ባለን መረዳታችንና አምነታችን ለወጥ ሊመጣ እንደሚችል በእርግጠኝነት እንነግራችኋለን፡፡ ልንጽፍላችሁና ልንነግራችሁ እንደ ተነገረንም አሁን ባለው ‹‹መንፈሳዊ›› አካሄድ ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› የበለጠ አለመቻል፣ ድካምና ሞለቅ ወስጥ ትዘቅጥ እንደሆነ እንጂ ወደ እግዚአብሔር ከፍታ መወጣት አትችልም፡፡

ከእንግዲህ የመንግሥቱን ሕይወትና ሰላም መጻሕፍትን ተርጉሞ በማባዛት፣ በብዙ ኮንፈረንሶችና ከሩሴዶች... ሊተላለፍ ጊዜው አይደለም፡፡ ጳንጠቆስጤ በዓለም እያደጉ ካሉ ሃይማኖቶች እኩል የሚያስፈራ ቢሆንም እንደ መበዛቱ እግዚአብሔር የፈለገውን ዓላማ አለመፈጸሙ ሲታይ ግን ጳንጠቆስጤ ራሱ ከሃይማኖት ጋር ሊደመር እንደሚቻል ስጋቱ አለ፡፡ ማንም በጳንጠቆስጤ ስም እንደ ሌሎች ሃይማኖቶች ለመበዛት ትግል ካለው ዕድሉ ከዚያ ሌላ አይሆንም፡፡ እግዚአብሔር ብዙኃንን - ግሩፕን በማጥቀም ለወጥ ያመጣበት - ዘመን የለወጠበት ታሪክ አልነበረውም የለውምም፡፡ ዓለም ጳንጠቆስጤ ይሆናል ብሎ ማንም አይድከም፡፡ ጳንጠቆስጤ ግን ለስሙ የሚሆንን ወገን የሚዘጋጅ ለአንድ ስፍረ ዘመን የተሰጠ አገልግሎት ነው፡፡ ‹‹የአሕዛብ መላት››(ሮሜ.11÷25) በጳንጠቆስጤ - በኢቫንጀሊካሎች - በባፕቲስቶች - በሜቶዲይቶች - በፕሪስፕቴርያኖች - በአንጅሊካኖች - በሐዋርያትና በነቢያት ጉባኤ - በፈይዝ መቫመንቶች ወይም በሌሎች ሳይሆን በእነዚህ አለመኖር በሚኩው በልጆቹ መንግሥት ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ድርጅቶች - በጊዜው የሠሩ ልምምዶች ... መታሰቢያ የሚገኙበት ጊዜ እየመጣ ነው፡፡... በእርግጥ እነዚህ አጥንቶች ፈጽመው መድረቅና ተስፋ መቁረጥ አለባቸው፡፡ ያኔ ነው በእርግጥ አንድና ታላቅ ሠራዊት ሁነው የሚቆሙት፡፡ ከእንግዲህ እነዚህ በተሰነጣጠቀ ጥቅስ - በተደበላለቀ ሥነ - መለኮት - በተቦጫጨቀ የድርጅታቸው ስም አይመኩም አያሟርቱምም፡፡

ይህም አንዱ ሠራዊት (The corporate Body of Christ) በሆነለት አንድ ዓይን የሚያየው አንድ ነገር ነው - ቅዱስ ነገር! ‹‹ዓይንም ሁሉ››(ዓይኖች አይደሉም) አንድን ንጉሥ በወበቱ ያዩታል፡፡ ለሁሉም አንድ ዓይን ይሆንለታል፡፡ ይሄ ነገር በወስጣቸሁ፣ በትምህርታችሁ፣ በመረዳታችሁ፣ በተሰጣቸሁ መጋቢነት - ስፍረ ዘመን ከጀመረ (የአንድ ዓይን መለጥ ከሆነ) ያለ ጥርጥር እንንገራችሁ በወስጣቸሁ የለወጥ ንጋት በርቷል ለወጥም ጀምሯል፡፡ እንደ ቃሉ አንድ (Single) ዓይን ጠፍሟት ከሆነ (ሉቃ.11÷34) ሁለት ዓይን - የተከፈለ ዓይን ሕመም - መንፈሳዊ ሕመማነት ነው፡፡

‹‹እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ፣ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም››(ቆላ.3÷1-2)፡፡

በዚህ አንድ ልብ - አንድ ዓይን - አንድ መረዳት - አንድ ራእይ አንድን ነገር እንፈልጋለን፡፡ በላይ(በሰማይ) ያለውን፡፡ እርሱ ማነ ነው? መንግሥቱ ነው፡፡ የከበረው ፈቃዱ ነው፡፡ ‹‹... ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን... መንግሥትህ ትምጣ፡፡›› ይሄ ነው ጥማታችን፡፡ ይሄ ነው ርሀባችን፡፡ ይሄ ነው ልባችን ዕረፍት የሚጣለትና የሚፍቀው፡፡ የለወጥ ጅማሬ እዚህ ጋ ነው፡፡ ዛሬ ‹‹በቤተ ክርስቲያን›› ለወጥ ከማጠበቃችሁና ከመፈጋችሁ በፊት ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› ሁሉን በማስተው ወደዚህ በአንድ ዓይን አንዱን ክርስቶስ - አህዳዊወን መንግሥት ወደ ምታይበት አምጧት፡፡ በእርግጥ ከቻላችሁ ነው፡፡ ዛሬ ዓለም የብዙኃን ፓርቲዎች ባለቤት ሆና በሞታችን ይሆናል እኛም በሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አህዳዊ ያልሆነ አሠራር ፈጥረን ልንራመድ የፈለግነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የባሰ መከፋፈል - መንቀዝ - መድከም... እንጂ ለወጥ አይኖርም፡፡

‹‹... አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን <u>ቅንነትና</u> ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ››(2ቆሮ.11÷3)፡፡ የተሰመረበት ቃል ኪንግ ጀምስ የተባለው መጽሐፍ ቅዱስ፡- “…Simplicity in Christ” ይለዋል ይህም ለብዙዎች ስብከትን አቅልሎ ማስበክ ወይም ሚስእክቶችን አወርዶ ማፍ ብቻ ይመስላቸዋል፡፡ ከዚህም በመነሣት እኛን፡- ‹‹ጹሑፎቻችሁ ከባዶች ናቸው›› ይሉናል፡፡ ነገር ግን (በvine dictionary መሠረት፡- “Simplicity = haplous (Gr.) ሲሆን ትርጉሙ single or singleess ይሆናል፡፡ የዚህም ተቃራኒ ‘dipous’ ነው፡ ‘double’ ማለት ነው›› የጥቅሱ ሜጨሻ፡፡

በአንድ ነገር ላይ ብቻ መጫን - ሚረፍ - ራስን ማሳረፍ - ሌላ ላለማት መመሰንን - ያንን አንድ ነገር ብቻ ማት - መረዳት - መማር - ማልገል… ‹‹ሲንግልነስ›› ሲሆን ከዚያ ከምናየው አንድ ነገር ጋር አንድ ሁነናል፡፡ ይሄ ‹‹ዋነስ›› ነው፡ በሕይወታችን - በመስጣችን - በመረዳታችን - በትምህርታችን - በአገልግሎታችን ይሄ ነገር(singlness – ones – simplicity in Christ) ከጀመርን ያለ ጥርጥር ለወጥ ጀምረናል፡፡ ስለተባለም ሐሳባችን፣ መላጣችን፣ መረዳታችን፣ ጥበባችን… በክርስቶስ ላይ ብቻ ባደረግን ማጠን ስለ ዓለም፣ ስለ ሰይጣን፣ ስለ ሥጋ… የምንሰብከውና የምንጽፈው ጥቂትና እንደ አስፈላጊነቱ ብቻ ነው፡፡

ብዙ አብያተ ክርስቲያናትና ሚኒስትሪዎች በደረሱበት አንድ ነገር ይበልጥ አነቁን፡፡ ብዙዎቻችን ‹‹ከራየስት ኮንሽስ›› ከማሆን በበለጠ ‹‹ዴቨል አር አዳም ኮንሸስ›› የሆነው በልጧል፡፡ ብዙዎች ከክርስቶስ ይልቅ ለሰይጣንና ለአሠራሩ ንቁ ናቸው፡፡ ሰይጣንን ይቃወመቃል እንጂ ብዙወዓ ጊዜ ‹‹ሳታን ኮንሸስ›› ናቸው፡፡ ‹‹ሳታን ኮንሸስ›› ስለሆኑም ሰይጣንን ያለቦታው ይሸነቁሩታል፡፡ ሁሉም ነገር(በተለይ ክፉ የተባለው) ከእርሱ ጋር ያቆራኙታል፡፡ ለእያንዳንዱ አምልኮአቸውና ላዘጋጁት ፕሮግራም ሁሉ የተመደበ የሰይጣን ሚልከተኛ እንዳለ ሁልጊዜ እስከማያምኑ አእምሮአቸው የተበላሸ ነው፡፡ ማን ነው መዳቢው? እግዚአብሔር ሳይፈቅድ? በእርሱ ከተፈቀደስ ወግያወና ወጡቱ እስከምን ድረስ ነው?... በዚህ ዓይነት ሰዎች ትምህርትና መረዳት ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› ዕድሏ ለወጥ ሳይሆን ይበልጥ መዘቀጥ ነው፡፡

በዚህ ዓይነት አገልግሎት ለወጥ አይታሰብም፡ በመንፈስ - በአካሄድ - በሕይወት… ስላልተዋጋናቸው ‹‹መትተንና ቆራርጠን የጣልናቸው መናፍስቶች›› በሐሳባችን - በመረዳታችን - በትምህርታችን ተመልሰው ሲበዙ እንጂ ሲያንሱም አላየንም፡ ይህንን ለማለት የፈለግነው ሕዝቡ ከሲንግልነስ ወጥቷል ለማለትና በዚህም ሁኔታ ለወጥ እንደ ሚይታሰብ ለማሳየት እንደሆነ ልብ በሉልን፡፡

‹‹እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አወቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስን ልብ አለን›› (2ቆሮ.2÷16)፡፡ ማንም በዚህ ይገኝ ዘንድ ይሁንለት፡፡ የክርስቶስ ልብ ቢሆንልን ምን የምናስብ ምንስ የምናገለግል እንሆናለን? ማንም ለዚህ መልስ ፍለጋ ወደ ሌላ አይሄድም፡ በወስጡ ያለ ልብ ራሱ ያመጨዋል፡፡ በዚህም ልብ አዲሱን ሰው እናገለግላለን፡፡ ይሄ ልብ ነው ከወረሰውና ከሆነለት ከዚያ ሰው ጀምሮ የለወጥ ምክንያት(መሻ) የሚሆነው፡ ክርስቶስ ጌታ በዚህ ልብ - በእግዚአብሔር ልብ ስለ ነበረ ክርስቶስ መሉ ትኩረት ያደረገው በአንድዋ በተፈጸመች በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ነው፡ በዚህ ልብ ነው በፊት ለፊታችን ያለወዓ ፈጽመን የምንከተለው፡

‹‹ፈጽሞ መከተል››(ዘዳ.1÷36) ይሄ ልብ ባለበት ብቻ ነው፡ ካሌብ እንደ ጊዜውና ዘመኑ ፈጽሞ እንደ ተከተለ ተመሳክረለት፡፡ ዛሬም ፈጽመን የምንከተለው እንደዚህ ጊዜ - ዘመን - ራእይና መረዳት ሲሆን ነው - ልብን አንድ ነገር ላይ አኑረን መጓዝ! በዚህም ልብ ከገዛወና ከተገኘው ከአንዱ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በቀር ፈጽሞ ወጪዓ፣ ሁኔታዎችን፣ የዓለምን ጨለማም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ሌሊት አይታየንም፡ በላይ ያለወዓ የሚሹ ልባቸው - ዕይታቸው ወደ ላይ ነው፡ ወደ ምድር አይመለከቱም፡ መመልከት በመጽሐፍ መረዳት - ትምህርት… ነውና ለወጣችን ከዚህ ጀምሮ ነው፡፡

‹‹ወደ ምድርም ይመለከታሉ፣ እነሆም፣ መከራና ጨለማ የሚያስጨንቅም ጭጋግ አለ፤ ወደ ድቅድቅም ጨለማ ይሰደዳሉ››(ኢሳ.8÷22)፡፡

ሰዎች በሚያዩበት - በሚዳበት… ምድር መከራ፣ ጨለማ የሚያስጨንቅም ጭጋግ አለ፡፡ ቀጥለው ወደ ድቅድቅ ጨለማ ይሰደዳሉ፡፡ ስለዚህ መላወጣችንም ሆነ አለመላወጣችን የሚርፈው በማት ታችን - በመረዳታችን… የተቀበልነው በወስጥ መበራት - ብርሃን ማጠን ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ዘመን በመንግሥቱ ይለወጥ ዘንድ በቤተክርስቲያን ዘመን የተሰጡ የትምህርት ዓይነቶች እንደ መንግሥቱ መረዳት እየተለወጡ - ይበልጥ እየበሩ ናቸው፡ ሁሉም የቤተክርስቲያን ትምህርቶች በዘመናቸው እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት እወነት ነበሩ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በሚያመጣው መንግሥቱና በሚልጣቸው ልጆቹ ማጠን ትምህርቷ ከድካም - ከአለማወቅ ጋር ተቆጥሯል፡፡

በአብያተ ክርስቲያናት አንዱ ለአንዱ ለመቅበልም ሆነ ላለመቀበል ያደረጉት ራሳቸውዓም እወነተኛ አድርገው የማኑበት የእስከ ዛሬ ትምህርቷ - መረዳቷ - ራእይዋ - ልምምዷ - ሥርዓቷ… በጊዜው እወነት ቢሆንም ስለበለጠው የጌታ መረዳትና መምጣት - ስለ ልጆችም መላጥ የነበረው ያረጀል - ይቀራል ከሕዝቡም ልብ ይወድቃል፡፡ ባለፉት ትወልዶች የእግዚአብሔር የራሱ መላጥ በሞቱት ትወልዶች በሚረጀትና በመሻር በሚወጥም በአዲስ ተገልጧል፡፡ ስለዚህ አይደል እግዚአብሔር የተገለጠባቸው ስሞችና አሠራሮች ከቁጥር በላይ የሆኑት፡፡

ከመጀመሪያ ትምህርቶች ጋር ምንም ያህል ብንሰፋና ብንበየድም ከዚህ የሚፈታንና የሚያላቅቀን ብርቱ ትምህርት ከልጆቹ ሰሚይ ይወርዳልና የቀደሞት ከዋከብት ከሰሚያቸው በሚረግፉበት ዘመን ብርሃናቸው ሲጨልም እግዚአብሔር ብቻ የሁሉ ብርሃን ይሆናል፡፡

‹‹የፊተኛወን ነገር አታስተወሉ፣ የጥንቱንም ነገር አታስቡ፡፡ እነሆ፣ አዲስ ነገርን አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፤ እናንተም አታውቁምን? በምድረ በዳም መንገድ በበረሀም ወንዞችን አደርጋለሁ›› (ኢሳ.43÷18-19)፡፡

ለዚህ የተስፋ ቃል የምንሰጠው ትርጉም እንዳለንበትና እንደ ደረስንበት የሕይወት ደረጃ ይለያይ ይሆናል፡፡ የምትጠበቀት አዲስ ነገር ምን ይሆን? ሁላችንም ያለንበትንና ያየነወን ያህል መገር እንችላለን፡፡ ካየንበት እርሱም ከታየን ሁነን እንድንሻከር ነው የተጠራነው (ሥራ.26÷16)፡፡ የምንናገረው ባየነው ሳጠን ነው፡፡ ስለዚህ የምንለው አዲስ ነገር እርሱን ያየንበትና እርሱ ደግሞ ለእኛ የታየበት ልክ ይወስነዋል፡፡ እግዚአብሔርም የሚያደርገው አዲስ ነገር በመንቀሳቀስ ላይ አይደለምን?

ስለዚህ ከምናወቀወና ከምናደርገው ነገር ጋር ብቻ ሌላ እንደሌለ ሆነን ሳትፋት የለብንም፡፡ ጊዜው ወሳኝ ወቀት ነው፡፡ ወደ ተጠራንበት እንዘርጋ፡፡ ዋጋ ቢያስከፍልም የለወጡ ተባባሪ እንድንሆን እግዚአብሔር ዓይኖቻችንን ይክፈተው፡ ዳሩ ግን እስካሁን ከተገለጠው ከክርስቶስ መገለጥ የበለጠው ሲመጣ ብዙዎች እሺ አይሉም፡፡ ‹‹የሳቱ›› ስለሚሳላቸው ይፈራሉ፡፡ የራሳቸው ጠባቂ፡ የራሳቸው ቅጥር ራሳቸው ናቸው፡፡ በዚህም ሁኔታዎች ያላቸው እንዳይወሰድባቸው ሳጠንቀቃቸው ሊሳላቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ያላቸወን አጥብቀው ይዘው ስለሌላው ራሳቸወን ቆልፈው ይይዛሉ፡፡ አስቀድመው ከተሞሉት የተሰፋ ናቸውና የተገለጠወን አለመቀበል ብቻ ሳይሆን የጊዜወን ቃል ያሳሹንም ያሳድዳሉ፡፡ እንደሚሳላቸው እስካሁን የተሞሉት የሜጨሻ እወነት ያደርጉታል፡፡ ግን አይደለም፤ ምንም እንኳ በጊዜው መሉ እወነት ቢሆን፡፡ የነበረወም ይሁን አሁን ያለው በሌላ አዲስ ይሳላል እንጂ የመጀመሪያው ያለ ምንም ጉድለት አይደለም፡፡ አሁን ካለው ጋር መላቀቅ አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን ነገሮችን ሁሉ ካለፉት ጋር ማቆራኘቱ ሕይወት አድርገነዋል፡፡ እርሱ ግን ራሱን በእኛ በማሉለቅ አሁን አዲስ ነገር ያደርጋል፡፡ ዛሬ(አሁን) ልንገባበት ያለው ሕይወት - ማንነት በፍጹም ልዩና አዲስ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ሕይወት በእኛ መፈጸሙ ወይም አካል መልበሱ - እግዚአብሔርን የመሰል ልምምድ እንደ አንድ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ የሕይወት መጽሐፍ ይሁን! የዚህን መጽሐፍ ድርሰት ለመፃር ነው የተጠራነው ፡፡ መጽሐፉ በእግዚአብሔር ማንነት(In His essence) ተደረሰ፡፡ እርሱም ተከፍቷል፡፡ መጽሐፉም(ስለ እኛ) መጀመሪያና መጨረሻ አለው፡ በውኑ መጽሐፉን ማንበብ መጽሐፉንስ ሆነን መላበብ ጀምረን ይሆን?... ይሄ የመጽሐፉ ግብ ነው፡ መጽሐፉ በምዕራፎች ተከፋፍሏል፡፡ መግቢያም መቅድምም አለው መጽሐፉ፡፡ የመጽሐፉ(የሕይወት) ጅማሬ ንስሐ ይሁን - ደኅንነት -የኃጢኣት ይቅርታ - ዳግመኛ መወለድ፡፡ ብዙዎች በዚህ ምዕራፍ ላይ ናቸው፡፡ ከዚህም ከመጽሐፉ የመጀመሪያ ምዕራፍ አለማለፋቸው አይደንቅም፡፡ ማን ነው በመጽሐፉ ምዕራፎች እንደማባ የሄደ? የመጽሐፉ ስም ሕይወት እንደመሆኑ፣ በመጽሐፉ ምዕራፎች በሄድን ሳጠን በጥልቀት የምናየወና የምንለማመደው የእግዚአብሔር ሕይወት እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ሕይወትን የምንገልጥበትና የምስነብብበት የትኛው ምዕራፍ ላይ እንሆን ያለነው? በእግዚአብሔር ጸጋ በመፈስም ምሪት በመጽሐፉ ምዕራፍ ሁሉ መሄድ አለብን፡፡ ያለፈወንና ያለወን ትተን ወደ ሌላ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ የምንሻገረው አሮጌወን (የምናወቀወንና የተለማመድነወን) ዘግተን ወደ አዲሱ ስንገባ ነው፡፡ ብዙዎቻችን ግን ‹‹ለምን የመጀመሪያወን ምዕራፍ መዘጋት አልቻልንም?›› የሚለው ጥያቄ አድክሞናል፡፡ የመጀመሪያወን ምዕራፍ በሕይወት - በምልልስ ካልዘጋነው ሌላኛወን ለመክፈት ብንሞክር ሥርዓት ነወን? ሁለተኛው ምዕራፍ የአንደኛው መላት ነው - አካል ነው፡፡ መበዘትና መሳፋት ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ ዘመን አለው - ጊዜ አለው፡፡ ሁለተኛው ግን ይዘጋዋል - ይፈጽመዋል፡፡ ሁለተኛው በአንደኛው ላይ ይገዝፋል፡፡ ስለዚህም አይታሰብም፡ ሦስተኛወም ምዕራፍ በሁለተኛው ላይ እንዲሁ እንደሆነ የታወቀ ይሁን!

ይሄ የሕይወት መጽሐፍ ወደ መጨረሻው - ወደ መጥራቱ ግብ ሊደርስ ሦስት ዐቢይ ክፍሎች (Volumes ቅጾች) አሉት፡፡ እነዚህ ሁሉ አንዱ የእግዚአብሔር ሕይወት እንደሚባን ተለክቶ ተጽፎአል፡፡ በየክፍሎቹም የእግዚአብሔርን ሕይወት ሞት በቻልን ሳጠን አይተናል፡፡ እነዚህ የመጽሐፉ ክፍሎች መፈጸም አለባቸው - መመላት አለባቸው - ወደ መንግሥቱ መላት ለመድረስ፡፡ እንደ እግዚአብሔር ዝግጅት - እንደ እግዚአብሔር ፕሮግራም የት ነው ያለነው፡ ወገኖች ሆይ?! መጽሐፉ ምን ያህል ገብቶናል? ምን ያህልስ ተለማመደነወል? ይህንን መጽሐፍ (የሕይወት መዘገብ) ብዙዎች በእግዚአብሔር ጥሪ በጸጋወም በሆነ መላብ ቢገዙትም የመጽሐፉን የመጀመሪያ ክፍል እንጂ ሌላወን ክፍተው ማንበብም መረዳትም አልቻሉም፡፡ እንዲያወም መጽሐፉ አሁን ከከፈቱትና ከደረሱበት ሌላ ጥልቀት ያለው - ሌላ ምዕራፍ እንደያዘ አላስተዋሉም፡፡

ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱም ምዕመን በአብዛኛው በጀመረበት ምዕራፍ የሚሸከረከረው ነው። ብዙኃኑ ሌላ ምዕራፍ ለመክፈት አልታደለም። መረዳቱ ጠባብ ነው። ሁሉም በአንድ የመጀመሪያ ምዕራፍ መረዳት - ሕይወት - ልምምድ - መለጥ... ብቻ ተሰላችቶ ይገኛል። በዚህም ምዕራፍ ብዙ ስለኖሩ የመጽሐፉ የመጀመሪያ ሕይወት ወደ ልማት - ወደ ወግ - ወደ ሥርዓት - ወደ ቀኖና - ወደ ደረቅ ዶክትሪን - ተለወጠባቸዋል። ‹‹የዘሙ ክርስትና ከዚህ ድካም ያመለጠ ነው›› ብሎ የሚሟከር ማን ይኖራል? አወይ!

የመጽሐፉን - የሕይወትን ገጽ በከፈትን መጠን የእግዚአብሔር የመረዳቱ መጠን ብርሃን ይበዛል። ማነተሞችም በሕይወት ይከፈታሉ። የአንዱ ገጽ(ማነተም) መክፈት የሌላኛው (የሁለተኛው) መቀጠል ነው። እያንዳንዱ መልአክ(ለሚከፍተው ማነተም - ዘመን የተሰጠው ባላደራ መልክተኛ) ማነተሙን በከፈተ መጠን ሌላው ተተክቶ ማነተሞቹ ሁሉ ተፈትተው የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸሟል። ዛሬ ያሉን ‹‹ታላላቅ›› አገልጋዮች መልእክተኛ(መላእክት) የሚሉ ናቸውን? በማን ሕይወት የትኛውን ወይስ ስንተኛውን ማነተም ፈቱ? አጠያያቂ ነው። የምናወቀውን በሌላ ዜማ ያዜሟልና። ወድ ወንድሞቹን ቦንኬ የሚብከበት ‹‹ሰፊ ሜዳ›› አጥቶ መቅረቱ - በወጣለት ፕሮግራም - በተያዘለት አጀንዳ.. ስላልመጣ ብዙዎቻችን አወዛግቧል። የአብያተ ክርስቲያናትም ቅሬታ ወድ መጽናናት ጋዜጣ ዘግቦ አስነብቦናል። ... በእርግጥ ወንድም ቦንኬ መጥቶ በሕይወታችን የሚፈታው ማነተም ከነበረና ከቀረብን ወዮልን!... ግን መልአክ የሚያስቀረው ምድራዊ ኃይልና ችግር አለን? የምናወቀውን የትምህርት፣ የልምምድና የአካሄድ ዜማ ይዞ ይመጣ ዘንድ ከነበረ በመቅረቱ የማንም ልብ አይወደቅ። በእርግጥ ለሀገራችንም ሆነ ለዓለም አብያተክርስቲያናት የሚያስፈልጉን እንዲህ ዓይነቶቹ ‹‹ዝነኛ ሰዎች›› ሳይሆኑ በሕይወታችን ማነተም ፈቺ መልእክተኞች - መላእክት ናቸው። እነዚህ የዘላለም ወንጌል አላቸው - በሁሉም ሰሚይ ላይ ይበርራሉ። ለእነዚህም የሀገር ሜዳ - ምቹ የመሰብሰቢያ ስፍራ ሳይሆን የሚያስፈልጋቸው የእግዚአብሔር ጊዜ፣ በእርሱ የተከፈተው በር፣ የተዘጋጀው መሠወያ - የበሰለ ወቅት... ይመላከታሉ። እነዚህ ለአንድም ሰው ይሁን እግዚአብሔር በሚሠራበት ቀን ማነተም ሊፈቱ ይመጣሉ - ይሄዳሉ - ይላካሉ። ወገኖች ሆይ፣ ደግመን እናሳስባችሁ አሁን የሚያስፈልገን ማነተሞችን በመፍታት ወደ ሌላኛው የእግዚአብሔር ሕይወት ምዕራፍ የሚወስዱን የጊዜው መልእክተኞች ብቻ ናቸው።

ወዶች ሆይ፣ ዛሬ ካለንበት የሃይማኖት እንቅልፍ - የሕይወት ሌሊት ልናመልጥ እግዚአብሔር በራሳችን ማስጠንቀቂያወን እያበዛ ይገኛል። ጎማችን አልዞር ብሎን ተቸግረን ባለንበት በስብሰናል። ድንዛዜአችን - ድካማችን - የወሰጣችን ርህብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ማስጠንቀቂያ ሁነው ካለንበት ተነሥተን ለመጓዝ ካልሆኑ ምንድር ናቸው? ቤተክርስቲያን ገና ስትመሠረት ጀምሮ በከፊል ሕይወት(1ቆሮ.13) የቆመች አልነበረችምን? ዛሬ ይሄ ከፊል ሕይወቷ የትና ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ያስፈራል። ከፊሉ የባሰ እየተከፈለ በባሰ ቁርስራሽ (Fragmentation) ወስጥ ዘቅጦ እናየዋለን። ይሄም ቢሆን መልእክት አለው። ማንም ከእግዚአብሔር የሆነለት ከዚህ ይሸሽ - ተስፋወን ለመያዝ!

የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ልምምዱ በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አሥራ ሦስት ላይ የተንጠለጠለ ነው። ይህም እንደ ተወሰነለት ነው። በዚህ ኩነኔ የለባትም። ግን የተዘጋጀላትን መጽሐፍ - የተከፈተወን መጽሐፍ ገጽ በገጽ ለማበብ መንፈስ ቅዱስ በእርሷ የሚታገወን ትጋት ሞት አለባት። ይሄ ከፊል ልምምድ የመጽሐፉ ከፍል ነው በእርግጥ። የመጽፉንም ገጽ በገለጥን መጠን የሕይወት መጠን ይጨምራል። መጽሐፉን ለመክፈት ማንም አልተገኘም ከክርስቶስ በስተቀር። ዛሬም በእያንዳንዳችን የመጽሐፉን ሕይወትና ትርጉም የሚከፍት እርሱ ነው። የተዘጋወን፣ ያልተረዳነወንና ያላስተዋልነወን የፈታልን ከእርሱ ሌላ ማንም አይደለም። ከዚህ በኋላ መላእክት የተከፈተወን ገጽ በገጽ ይከፍታሉ። የተፈታወን ማነተም ደረጃ በደረጃ ይከፍታሉ። ወደዚህም የደረስን እንደሁ የሚመጣወን ፍጹም በሕይወታችን ወገግታወን እንዳበራ ሞት እንችላለን። ወገኖች በሌሎች እትሞች አስቀድመን እንዳልናችሁ አንድ ዘመን አለፈ። በአንድ ዘመን ላይ ሞቸ። አዲስ ዘመን ጀምሯል - በልባችን!

የዚህ ቀን - የጌታ ቀን ወጋገን በብዙዎች ላይ አብርቷል። በማነተሞች መፈታት አያሌዎች እየተገረሙ ናቸው። እነርሱም ከእነርሱ ባለፈ ሕይወት በሌሎች ላይ እየፈቱ ምድርን በብርሃናቸው እያበሩ ይገኛሉ። ሰሚያታቸው ከብዷል። እግዚአብሔርን ሊያወርዱት ነው። ደመናት ሆነው የያዙትን - ያዘሉትን ፈሳሽ(የእግዚአብሔርን ሕይወት - እግዚአብሔር ራሱን) ያወርዳሉ። በብዙ ይዘንባሉ - በፍጥረት ሁሉ ላይ። ወገኖች ሆይ፣ ስለዚህ ነገር ነቅታችሁ ይሆን? በእናንተ ከተከፈተው ሰሚያታችሁ ክርስቶስ ስለዚህ ነገር ካልቆመ ዘግይታችኋልና ፍጠኑ። መልእኩ በመበረር ላይ ነው - በሰሚይ። የሚረወስ ማንን ይጠብቃል?... አትዘግዩ! እግዚአብሔር በሚመላበት ዘመን(1ቆሮ.15÷28) ማንም ባያመልጥም ይህንን ታላቅ ጊዜ - የመታደስ ዘመን ለማጠን የተጠራችሁ የፍጥረት በኩራቱ ሆይ፣ ጆሮዎቻችሁን ወደሚገረው መንፈስ አዘንብሉ - እግዚአብሔር አብ አባት ሁላችንንም ይርዳን!

እርግጥ ነው በመንግሥቱ ሕይወት ከብር መላት ማንም በማንም ይሞላ ዘንድ አይጎድልም። ሁሉን መሉ ይደረጋል። የሚሟላው ራሱ እግዚአብሔር ነወና! የጀመራችሁትን መጽሐፍ አትጨርሱትምን? መጽሐፉ አልፋና አሜጋ ነው። ከላይ እንደ ተባለው የመጽሐፉ ጅማሬና ፍጻሜ (ስለ እኛ) እኩል አይደሉም በእርሱ ዘንድ መላወጥ ባይኖርም። ግና እስካሁን በሰው የምንደገፍ

ነንን? ጉድለታችን ያለ ሰዎች አገልግሎት አይሞላ ይሆን? ‹‹ሰው ለሰው›› እስከ መቼ? ለዚህ ነው ሰዎች ሰዎችን የሚያዩት፡፡ የወንድሞች ጎብረትና አገልግሎት ተቃዋሚ ነንን? አይደለም፡፡ ነገር ግን ከተወሰነልን በላይ በማንም አንገለገልም አንደገፍምም፡፡

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በሰው ተሞልተዋል፡፡ ብዙዎችም ወደዚያ ይጨምራሉ፡፡ በዓለም ላይ በጣም ግዙፍ አብያተ ክርስቲያናት አሉ፡፡ ግን በሰው ነው የገዘፉት፡፡ የሕዝብ(የምዕመን) ብዛት ‹‹የቤተክርስቲያንን ትልቅነት›› አስመሰከረ፡፡ ይሄ ግን በእግዚአብሔር ፊት የትወልዱ ፈዝ ነው፡፡ እኛም ስለ ባሕላዊ ክርስትና የምናወራበት ጊዜም ቦታ የለንም፡፡ በፕሮቴስታንት - በጰንጠቆስጤ.. አእምሮ ሆነን ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ወይም ስለ ካቶሊክ የምናወራበት ጊዜ አይደለም፡፡ የራሳችን ነወር ይበቃናል፡፡ ስለ ችግር፣ ስለ ወግ፣ ስለ ልሙድ፣ ስለ ወድቀት፣ ስለ ድካም፣ ስለ መንፈሳዊ ንቅዘት... መጻፍ ካስፈለገን የራሳችን ከበቂ በላይ ነው፡፡ ዓይን የራሱን ቆሻሻ መች ያያል? ሆነና ነው እንጂ፡፡ በሰው ያለውን ጉድፍ ለማውጣት ግን ይተጋል፡፡ በእርሱ ዘንድ ግን ምሰሶ አለ፡፡ እናንተ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት፣ እናንተ ጰንጠቆስጠሎችና ካሪዝማቲኮች፣ እናንተ ሚሲስትሪዎች ባሕላዊ ክርስትና መነቀፍ ትታችሁ ወደ ባሕላዊ ክርስትና ደረጃ እየወረዳችሁ ያላችሁትን ራሳችሁን ታድኑ እንደ ሆነ ጊዜ ይሁንላችሁ፡፡ እነዚህ ባሕላዊ ክርስትናዎች በጊዜአቸው ትክክለኛና የወቅቱን መንፈሳዊ ድካም በመቃወም ራሳቸውን ያደራጁ ናቸው እኮ፡፡ ማንም በተከፈተለት መጽሐፍ እንደሚባ ካልተራመደ - ምዕራፍ በምዕራፍ ካልሄደ በሕይወቱና በድርጅቱ ይሄ ይቀራልን? ከቶወንም፡፡ የዛሬዎቹ የምዕራባውያን ሜቶዲስቶች፣ ባፕቲስቶች፣ ሜቆናይቶች፣ ካልቪኒስቶች፣ ሉተራውያን፣ አንግሊካኖች፣ ኢቫንጀሊካሎች ከምሥራቁ ኦርቶዶክስና ከዚያው ከምዕራቡ ካቶሊክ በምን ይለያሉ?... ወገኖች ትሙ እንደሆነ ንቁ፡፡ ይሄ ሁኔታ ወደ እኛ - ወደ አፍሪቃ እንዳይመጣ ምን ይከለከለዋል?... ከተስማማን ሁላችን እንዲህ እናድርግ፡- የኋላችንን - የጎናችንን ሞት ትተን በመጽሐፉ ጥልቀት እንዋኝ፡፡ እግዚአብሔርም ወደ ወሰነው ወደ መጦራቱ ግብ እንሂድ፡፡

የደናግል ቅኔ

በቸርነቱ ቸርነት ሕይወት ለሆናችሁና የእግዚአብሔርን ዛሬ ለምትኖሩ ሁሉ፡- ሰላም ይሁን፡፡ ነገሬ ግልጥና ግልጥ ናት፡፡ የሰሚይን ሥርዓት ታውቃላችሁና የሞቃጥለውን ጥያቄ መመለስ አይከብዳችሁም፡፡ ይህንንስ(የሰሚይን ሥርዓት) ወደ ምድር(አካል ትሰጠታላችሁ ወይ?) ታመጣጠላችሁን? የአሉታችሁን ሽኩቻታ አልወድም! አዎንታችሁን እንጂ፡፡ ጉልበቱና የሕይወት ሥርዓቱን በእናንተ ማጠቅጠቁ ታዲያ ለምንድር ነው? እስቲ ዝለሉና የምንባባለውን በጥሩ ወግ እንጫወት!!

በፍጥረት ሕግ ዜማ ከረምት ካለፈ በኋላ ነው ይላሉ፡፡ ደግሞ ነውም፡፡ ከዚህ በላተኛ ‹‹አሉ››ነት መበልን ልታወጡ ትጉ፡፡ አዎ! ልጅነት አርዶ መበላትን ያውቃል፡፡ የምናየው፣ የምንሰማው፣ የሚቀሳቀሰው ሁሉ ለእግዚአብሔር ቢላዋ መቅረቡ የግድ ነው፡፡ መበል ፈላጊ ልጆች አርደው ማግኘት እንዳለባቸው የተቆጠረ ነው፡፡ ፍጥረት እየተንቀሳቀሰ(በአሮጌውና ቀድሞ በነበረው ችሎታ - በርታት -አቅም...) ከእርሱ መበልን መበላትም ሆነ መሞርን ከዚያም አልፎ ተርፎ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መንቃትን ማጠበቅ ከኩርንችት በለስን የማጠቅ ያህል ሜቄካከር ይሆናል፡፡ ጴጥሮስ እነ ቆርኖሊዮስን የሕይወቱ ተካፋይ ሊያደርጋቸው በያዘው መንፈሳዊ ቢላዋ ሚረድ አለበት፡፡ ይህን በአንድ ጽሑፍ ያልነው ነበረ፡፡

ዜማ ግን በጭቃ የለም፡፡ ዜማ በሕይወት ከረምት የለም፡፡ በተራራ ላይ የተገለጠ ሕይወትም በዚህ ጊዜ የለም፡፡ ግን ከረምት ሲያልፍ ሌላ ዘመን ነውና አበቦች ተይዘው ከነበሩበት የወስጥ ሕግ ይለቀቃሉ፡፡ የመታየት ሕግ ይገጥሟቸዋልና ይታያሉ፡፡ አ! ዘር ሰጪዎች ይታያሉ፡፡ ዘር ተቀባዮች ያለ ምንም ከልካይ ሕግ ለዘር ይከፈታሉ፡፡ የደረሰን አበባ ከማፈት ሊሞላሰው የሚቻል ተጻራሪ ሕግ የለምና መከፈት ዕድላቸው - ዕጣ ክፍላቸው ነው፡፡ ዘር ተቀባዮች ያፈራሉ፣ ዘር ሰጪዎችም ለዚህ ተሠርተዋልና ሰጥተው ፍሬያቸውን በሌላው ላይ ሊያዩ ወደ አለመታየት ክብር ይገባሉ፡፡ የገዛ ዘማቸውን አጨልመው በሌሎች ዘመን ሁሉ ደምቀው ሊታዩ ሠርተዋልና፡፡ አ! የዘላለም አምላክ እንዴት የተባረከ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የከረምት ወጤት ነውና፡፡

በዚህ ሥርዓት የፍጥረት ፊት ይታደሳል፡፡ ሌላ ዘመን መጥባቱን የሚግሩን አዕዋፋት ቅኔ ማነሊታቸውን ይዘርፋሉ፡፡ እስካሁን ያልነበረን ነገር እየነገሩን ከረምቱን - የተሰጣቸውን ዘመን ወደ መጣበት ያመጡታል፡፡ ሌላ ዘመን እንደጠበ የሚግሩን አበቦች በሀገራችን አሉ፡፡ የሐምሌንና የነሐሴን ኃይለኛ ከረምት በእነርሱነታቸው ወስጥ ተደብቀው መከረም ሲጠበ የሚለጠፉ አበቦች ‹‹አደይ አበባ›› እንላቸዋለን፡፡ ሰውም ይህን ተከትሎ ‹‹ዕንቁጣጣሽ›› ብሎአዲስ ዓመትን ያወጃል፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ፍጥረት እንኳን አሮጌው ዓመት በከረምት እንዴት እንደሚጨርሰው ያሳያል፡፡ እስካሁን ያሉት ዘመናት እንዴት እንደ ተፈጸሙ እየተረከን ነውና ለምን ዘመን እግዚአብሔር እንዳነቃን የሚያሳየን መንፈስ ሕያው ነው፡፡

አሮጌወን በከባድ ዝናብና ጭቃ ያበላሸዋል፡፡ ያስንቀዋል፡፡ ያሳድፈዋል፡፡ ሁሉም አዲስን እንዲናፍቅ፡፡ ካለንበት ሁኔታ - ኑሮ በምን ሰዓት እንደምንወጣና እንደምንገለጥ የሰወን ቀሞር ላስተምራችሁ አይደለም፡፡ ሰወና ሰው ቀሙ ብዙ ነው፡፡ መንፈሳዊ ነገር ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ዘጠና ስምንት ቁጥር ሰጥተወት መጽሐፍትም ስብከትም የሞቹሉ ሰዎች በጣም ይገርመኛል፡፡ መንፈሳዊ ነገር መለጥ እንጂ መባነብ አይደለምና፡፡

ወዶች ሆይ፣ እስቲ ማለስ በሉ ወደራሳችሁ፡፡ እየዘነበ ነው ወይስ አባርቷል? ያው(የነበረው) መንፈሳዊ ዘመናችሁ ጨቅየ? አደፈ? ወይስ ሌላ ዘመን አሸንቁራችሁ እያያችሁ ነው? ደናግሎች በሃይማኖትና እርሱም ንብረቴ ባለው ቀኖና ልብሳቸወን ያላሳደፉቱ ከረምታቸወን የት የሚያሳልፉ ማሳላችሁ? ዛሬ ራሳችንን የምናስጠጋበት - የምንሸሸግበት ብዙ ነው፡፡ ትምህርት፣ ኑሮ፣ አገልግሎት፣ ...ወዘተረፈ፡፡ ቀራኒዮ ግን ብቸኛና አማራጭ የሌለው ከረምት ማለፊያ የሆነላቸው ለጥቂቶች ነው፡፡ ለታናሽ መንጋ፡፡ ለደናግሎች፡፡ አዎ! ጽዮን ተራራ - የመለጥ ተራራ መነዱ ወይንም አዲሲቱን ቀራኒዮ ላይ ስንገኝ ብቻ ነው የምናወቀው፡፡

በእግዚአብሔር በኩራት ማነበር ታላቅና ሁሉ በእርሱ ከሆነው ከበጉ(the Lamb) ጋር ደናግሎች በጽዮን ተራራ ከመለጣቸው በፊት ቀራኒዮ የግድ አቋራጭ የሌለው መንገድ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ (የእግዚአብሔር በግ) ጽዮን በክብርና ግርማው ታይቶ ከማበራቱ በፊት ሙታረድ ገጥሞት አሸንፎ ወጥቷልና፡፡ ስለዚህ ስለ ሁሉ እርሱ ይገባዋል፡፡ ‹‹ይገባዋል›› ይገባችኋልን? ጽዮን ተራራ እኮ የብቃት - የማነት ጉዳይ እንጂ በእግዚአብሔር ስጦታዎች ተሸፋፍነን እንደ ነበር ነው እንደ በዓለ ኀምሳ(ሲና ተራራ) ሰፈር አይደለም፡፡ ‹‹ይገባሃል›› የሚልላቸው የበጉ ወንድሞችና በመታረድ የሞኖሩቱ ብቻ የሚመጡት ነው፡፡

የደናግሎቹ አሮጌ ዓመት - ዘመን - ቀን - ትምህርት - አካሄድ... ወዘተ ቀራንዮ ላይ እግዚአብሔር ዘመንን በሚሸርበት በሚቃጥል መንፈሱና የፍርድ ጉልበቱ ሲዘንብ የሚያልፍ ማንነታቸው እስኪታይ ይኖራሉ፡፡ በዚያን ዘመን የሰው የልብ እልከኝነት- ከብሩ - ስሙ - ዝናው - ገዝነቱ - ሜፈራቱ... በእግዚአብሔር የፍርድ ዝናብ ይታጠባል፡፡ እግዚአብሔር ራሱ ይዘንባልና ማን ጎበዝ ወጪወን ሊያይ አንገቱን ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ ያስግግ? በተገኘ ሁኔታ ሁሉ መሠልጠንን ያኔ እንተዋለን፡፡ የተገለጠ ፈቃድ በግልጥ ይገባናልና፡፡

እከሌን ታዩ እንደ ሆነ ግድ የለም ጠበቁ፡፡ እኔ ዛቻ ሚድረጌ አይደለም፡፡ ሕይወቴን እየጫርኩ ነው እንጂ፡፡ ማንንም ማጽትና ማንንም ለሕይወታቸው ምክንያት እስከሚታደርጉ እግዚአብሔር በኃይል ይዘንባል፡፡ ዝናብ መቼም ብዙ ያሳስብ የለምን? ልጆች ሆይ፣ ወደ ወስጥ ግቡ! ግቡ! የተዘጋባችሁን በርም ሆነ ማኸኮት ለመጪንቀል ባገኛችሁት ሁኔታ ሁሉ አትቆርቁሩ፡፡ ኖህ እኮ እስኪያባራ ጠበቀ፡፡ እግዚአብሔር ዘግቶበታልና፣ እከሌን ያይና ያስብ ዘንድ እንዴት ይቻላል? በወጭ የእግዚአብሔር ፍርድ እየዘነበ ነው፡፡ ወጪው ከረምት ነውና እስኪያባራ በሕይወታችሁ ታገሡ፡፡ አዲስ ዓለም ደግሞ የእናንተ ናትና፡፡ ይሁን! ሴላህ!!!

በኩራቶች ሆይ፡ - እኔ መቼም ይገርመኛል! ነገርን ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አሳብቦ(አላኮ) ወደ ራሱ ኑሮ የሚመስ ትወልድ እየበዛ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ምኩክ ነው ወይስ ዓይነት(Model)? በርባን ኢየሱስን እንደምትክ ወሰደ፡፡ እርሱ በእግሩ ሲተካ ፈለጉን ሊከተል አልወደደም፣ ይልቁኑ ወደ እናቱ ቤት ፈረጠጠ፡፡ ከቀድሞው ኑሮ ወደ ቀድሞው ኑሮ ተሸጋገረ፡፡ አይገርምም? ‹‹ለእኔ ተሠቃይቶልኛል››... የሚሉት አሳዛኝ ስታንዛዎች እኛን ሳይገድሉ ካኖሩን፣ ሳያሳጡ ካበለጸጉን፣ መከራን አስጠልተው ከብርን ካጎናጸፉን ወዮ! ይሽኔ ነው ሞሽሽ!! ጎበዝ ምን ታያለህ? ብዙ ሰው ዛሬ በክርስትና መለጥ ስም ከቀድሞው ኑሮው ወደበለጠወና ከፉ የቀድሞ ሰው ኑሮው እየገባ ነውና፡፡

የቀራኒዮው በግ እርሱም የታረደው በግ ነው በጽዮን የታየው፡፡ የቀራኒዮው በግ ነው በእግዚአብሔር የሚያልፍ ሕይወት ኃይል ለጽዮን ተራራ የበቃው፡፡ ልጆች ደግሞ ይህ አካሄድ የእናንተ ነውና መጫጭ አድርጋችሁ ያዙት!

መቶ አርባ አራት ሺዎቹ ስንት ከረምት አለፉ?አ!ሃሌሉያ!! ልቤ በደስታው ቀልጣለች፡፡ ጽዮን ተራራ ላይ ዝናብ የለምና - ከረምት የለምና፡፡ እግዚአብሔር በዘላለም እርሱነቱ ሲነድ በእኛ የሚቃጠል - አመድ የሚሆን - የሚበሉ ማንነት የለምና፡፡ ከረምት ሊፈጥር የሞቹል ጭቃ ከወዴት ይገኛል? ከረምትን ከረምት ያሰኘው ለዝናቡ ምድር የሰጠችው ምላሽ አይደለምን? ከረምት የለምና በዚህ ተራራ ዘመን አያረጅም፡፡ የእግዚአብሔር ብርቱ ሞልክ ከቀደመው በደመቀ ክብር እንደ ሰፊ ለምለም ማኸከና የዘላለም ብሩህ ብርሃን ሆኖ ይታያል፡፡ ይህን የሚያጨልም ሕይወት - ከረምት ከወዴት ይገኛል? ስለዚህም ይህ ዘመን - ሕይወት - ኑሮ - ምልልስ... አያረጅም፡፡ መንግሥቱ የዘላለም አይደለችምን? ልጆች ሆይ፡ - በሕይወት ‹‹አዎ!›› ብላችሁ ተባበሩ፡፡

የቤተ ክርስቲያን ዘመን - የራሔል ዘመን ከረምት ገጥሞታል፡፡ ማንም በዚህ ወጥቶ እንዲህ ነው ብሎ ቅኔን ሊዘርፍልን አልቻለም፡ እንደወም ቅኔ ጠፍቷል ታሪክ እንጂ፡፡ በማሕል ሲመላለስ የጀመረው ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ክረምት ከወጭ በር ሲያንኳኳ ታየ፡፡ ክረምት ጨለማ - ምሽት ነወና - እራት እንብላ አለ፡፡

ከዚህም በበለጠ የማነተም መፈታትም ዘመን ክረምት አለው፡፡ እግዚአብሔር ሲዘንብ ከሰው የሚወጣ ጉድፍ - ጭቃ - ሞት - ረሀብ -ሰቆቃ -አለመበቃት ይታያልና፡፡ ማንም ከመሠዊያ በላይ አልታየም፤ ስለዚህም ምክንያት የሁሉ ጭቃ በእግዚአብሔር ዝናብ ተጠርጎ እስኪወገድ ሁሉም ይሸሸግ ዘንድ ይገባዋል፡፡

የመላኮቱም ዘመን በሰው ኃይለኛ ክረምት ፈጥሯል፡፡ እግዚአብሔር በቁጣ ሲዘንብ፣ በሞት ሲዘንብ የሰው ምላሽ ከፉ ነበረና ጭቃወን ያወጣል(ራእ.9÷20-21)፡፡ በእነዚህ ሁሉ ያልረከሱ፣ እነዚህ ሁሉ ደግሞ ወርደወባቸው በሕይወታቸው ክረምትን ራሳቸወን ለመሥዋዕት በማቅረብ(ቀራኒዮ በመሆን) ያሳለፉ - የሚያሳልፉ - እያሳለፉ ያሉት ብዙ ናቸው፡ እነዚህ ዘመንን ያወም አዲሱን ከእጁ ይቀበሉ ዘንድ የተገባቸው ናቸው፡ ጽዮን በሕይወት መበቃት እንደሆነ ነግሬያችሁ የለምን? ለመነግሥቱ መንፈስ (እጥፍ መንፈስ) ተጋልጠዋልና ምንም አለመበቃት ወስጣቸው የለም፡ የቤተ ክርስቲያን መንፈስ (ተከፍሎ የተሰጠ) ያገኛቸው በእነዚያ ብቃት የለም፡ የእግዚአብሔር ችሎታ እንጂ፡፡ ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳም በለበሰው መንፈስና ኃይል ሃናኒያንና ሰጲራን ሲገድል ለገደለበት መንፈስ ግን ራሱ ብቁ አልነበረም፡ እርሱ ራሱ ግብዝ እንደ ሆነ ወንድሙ የሆነና የሆነን ጳወሎስ ተናግሯልና፡፡

ብቃት በሰማያዊ ስፍራ በእግዚአብሔር ቀኝ ነን ካልንበት በእግዚአብሔር አሠራር ወርደን ማነተማቸንን ስናስፈታ የሚሠራ ብቻ ነው፡ በቀኝ እጁ ያለው መጽሐፍ በቀኙ ከከርስቶስ ጋር የከበረው ሕዝብ(የዳነው ሕዝብ) እንጂ እንደዚህች እንደ እኔ ዓይነት ጽሐፍ ወይም መዘገብ አለመሆኑ ይጠኑ፡፡ በቀኝ እጁ ያለው ሕዝብ ወደ መታዘዝ በእግዚአብሔር ጸጋ የፈለሰው(ቀኝ - መታዘዝ ነወና) ሕዝብ ነወና ቀድሞ ዓይነት በሆነን በኩር ወንድማቸን መነገድ ወደ ብቃት እንመጣ ዘንድና የእግዚአብሔር ሚእከት ሆነን ለፍጥረት ሁሉ እንዳንነበብ የሆነበት ማንነት እስኪጠፉ ማነተማቸን ይፈታል፡፡

ወዶች፡ - ይዘንባልን?

ወዶች ሆይ፡ - እግዚአብሔር ከረምትን የመጣበትን ሕይወት ከራሳችሁ ሞርምራችሁ አገኛችሁን? በቃ! አላስወጣ፣ አላስገባ ያላችሁ ሕይወት፣ እንደ ቀድሞው በሕይወታችሁ መቀጠል ያልቻለ ሕይወት አይታያችሁምን? የእግዚአብሔር ሁሉን ምድረ በዳ ሚድረጋ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ፣ የእግዚአብሔር ዘመንን የሞኖር ጉልበቱ የተገዳደረው ሕይወት በዚህ ትወልድ በጉልህ እየታየ ነው፡ መቼም ቢሆን በራሱ ያልታገሠ ትወልድ ይህንን ያያል ለሚለት በጣም ይከብደኛል፡፡

ወገኖች በአንድ ምላሌ ወደ ነገሬ ልጥለቅ፡፡ ሁላችሁም ሰዓት አስራችኋል እንበል፡፡ ሁላችሁንም (በተለይ አንባቢ ሆይ) በአንድ ጊዜ ሰዓት የሚበይቅ ነገር ይከሰትና ‹‹ሰዓት ስንት ነው?›› ብትባሉ የብዙዎቻችሁ ዝብርቅር ሊሆን አይችልምን? መላኪያና አስታራቂ ሰዓት መቼም ሞኖር አለበት፡፡ እርሱም የአገሪቱ “Standard time” መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም ራዲዮናችሁ ሁለት ሰዓት እያለ የእናንተ አንድ ከሩብ ቢል ምን ያህል ቀርታችኋል? ወይንም ቀድሞ ሁለት ከሩብ ቢልስ? የእናንተ ብቻ ሁለት ከሩብ ስላለ ሁለት ሰዓት ከመሆኑ ያስፈረጥዋልን? የእናንተ ብቻ አንድ ከሩብ ስላለስ ሁለት ሰዓት የሚለወን ያንቀራፍፈዋልን? በዚህስ ተመርኩዛችሁ ከማን ጋር ትናበባላችሁ?

ይህች በጣም አነስተኛና ሐሳቤን በመሉ መግለጥ የማትችል ምላሌ ናት፡፡ ዘመኑ በእግዚአብሔር አቆጣጠር የደረሰበት ቦታና ጊዜ አለው፡ የእናንተ የእጃችሁ ሰዓት ሳይሆን የሕይወት ልምምዳችሁ ቀመር ከዚህ ጋር ካልተስማማ ምንኛ ከፋት አለው? እግዚአብሔር ‹‹ሦስት›› ሲል እናንተ ‹‹ሁለት ከግማሽ›› ብትሉስ? ወይም ሕዝቡ ገና ይህንን እወነት መከማት አይችልምና ዘመኑን ይዘገይ ልትሉ ትችላላችሁን? ይህ የእናንተ ጥበብ ነው፡ የእግዚአብሔር ጊዜ ካለፈው ከነበርንበት መንፈሳዊ ልምምድ ይዟል - ተሻግሯል - ወደ አሜንነቱ ገሥግሷል፡፡

በወጭ ሀገር የክረምት ወራት በረዶ በኃይል ሲወርድ ዛፎችና እርሱን ተጠልለው የነበሩት እንሰሶች ሁሉ ለወጥ ይከተልባቸዋል፡፡ ዛፎች መላ ቅጠላቸወን ይጥላሉ፡፡ በወስጥ በሆነላቸው (በቀረላቸው) ምግብ ብቻ ከረምቱን ይታገሣሉ፡ ሣርና ቁጥቋጦ ሁሉ በበረዶ ይሻራሉ፡፡ ዘራቸው ግን አይጠፉም፡ የነበራቸው ገፅታ ፍጹም ይወገዳል፡፡ ምድር በክረምት ፊት ታድሳ ስትወጣ - ስትገለጥ እንደ ገና ዘራቸው ከምድር ይወጣል፡፡ ይህ ሁሉ የሰው ልጅ ተምሳሊት ነው፡ የቤተክርስቲያን ዘመን ዛሬ ለመነግሥት ልጆች በእግዚአብር የክረምት ዝናብ - የበረዶ ጉልበት እየታጠበ ነው፡ ቤተ ክርስቲያንን ሲያስቡ ክረምትን ያስባሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት - የቤተ ክርሥቲያን ሥርዓት - የቤተክርስቲያን መለጥና ቃል ሕይወታቸው ላይ ሊሠራ ጉልበት ያጣል፡፡ እዚህ ላይ የቃሉ ሐሰተኛነት - የመለጡ ወሸታምነት አይደለም የሚታየው፡ ዘመናችን አለመሆኑ ነው፡ ሕጉ

በተሰጠበት ዘመን ምንኛ አንቀጥቅጧል፤ ዘመኑ ነውና ሁሉም ተርበድብደው ምላሽ ይሰጡት ነበር፡፡ ይህ ግን በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሳለ ደግሞ ምንም አልሆነም፡ በቤተ ክርስቲያን ስለ ኃጢኣቱ በግ ይዞ ወደካህን የሚቀርብን ሰው ብናይ እንስቃለን፡፡ ግን እኮ በሕጉ ይህ እውነት ነበር፡፡ ዘመኑ ነበራ፡፡

ዛሬ ብዙ ወንድሞች ቤተ ክርስቲያን በምትሰብከው ቃል ፈራጅ ብቻ ሆነዋል፡፡ ቃሉ እናንተን ካላገኛችሁ የዘመን ሽግግር መሆኑን አረጋግጠ፡ የዘመን ለውጥ ሳይኖር ግን ‹‹ተራ ተቺ›› ከሆንን የሚያስፈራ ነው፡ ብዙዎች ያለ ዘመን በአዲስ ቃል - የቃላት ትርጓሜ አገልግሎት ተጠምደው ሁሉንም በማንቋሸሽ ላይ ይገኛሉ፡፡ ያለ ዘመን የቃል ትርጓሜ እኔና እናንተን እንዴት ሊያስተሳስረን ይችላል? የምንለውን ጩሎ ሌላም የራሳቸውን የአዕምሮ ፈጠራ አድርገው የሚያገለግሉ በሀገራችን ሞልተዋል፤ ግን የዘመን አንድነት አለን ወይ ብለን ልንጠይቅ ዛሬ ዛሬ እንገደዳለን፡፡ ዘመን የጋራ ሰሚያችን ነው፡ ዘመን የተሰጠንን የሥራ ድርሻ የምንተረጉምበት ‹‹ፍሬም›› ነው፡ ዘመን ብቻ ካለን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ፉክክር እንገጥማለ፡፡ ዘመናችንም የተለየ ስለሆነ ምን ክርክር ያስገጥመናል? ዘመን - ያውም የወንዱ ልጅ ዘመን - ያውም የተወለደበትን (የተገኘበትን ማነፅን) ጨርሶ የተገለጠ ልጅ ዘመን - የቢኒያም ዘመን - እስራኤል ከዮሴፍ ጋር (ንጉሥ ጋር) ታርቆ አንድ ላይ የሚኖርበት ዘመን - የእግዚአብሔር ሕዝብ ራእይ ፍለጋ፣ ቃል ፍለጋ፣ መለጥ ፍለጋ፣ ከሚከራተትበት ረሃብና ጠኔ የሚያርፍበትና እነዚህ ሁሉ ላሉበት የሚኖር ዘመን… ይኸው ከፊታችን ተዘግቷል፡፡ ምን እያያችሁ ነው?

ከረምት ያለፈለት ትወልድ ባለ ዜማ ነው፡ በአዲስ ፀሐይ - ብርሃን የሚመላለስ ነው፡ አዲስ በማለቱ የፊተኛውን ፀሐይ - ብርሃን ይሸረዋል፡፡ የፊተኛው ፀሐይ - ጨረቃ - ከዋክብት (ራእ.12) በአዲሱ ዘመን የሚታሰቡም አይደሉም፡ አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ይጎድላችኋል ይሉናል፡፡ ያለፈው ዘመን ሊያማክረን ይተጋሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ አሁን ባለችው ቤተ ክርስቲያን የሚሠራው ሥራ ምንድር ነው? ልሣን ማነር? ሐሰት!ማንቀጥቀጥ?ሐሰት!አጋንንት ማውጣት? ሐሰት!... እኛ እንንገራችሁ? የቤተ ክርስቲያንን ፀሐይና ጨረቃ - እንዲሁም አክሊል የሆናትን ከዋክብት ወደ ጨለማ እየከተተው ነው፡ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሁሉ ይዛ ነው በእርሷ መንፈሳዊ ልምምድ - ሰማይ ቀይ ዘንዶ፣ የቀደመው እባብ የተገኘው፡ ይህ ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ለሌላ ክብርና ዘመን ይመሸ ዘንድ ነው፡ ሕያው አካል ሊነሣ ይሞታልና፡፡

ብዙ የተማርነው ዜማ አለ፡፡ ብዙ የተማርነው መንፈሳዊ ትምህርት አለ፡፡ ይህን ዜማ - ይህን ትምህርት (የቤተ ክርስቲያን ዘመን) ዓለም ሁሉ የሚያወቀው ነው፡ የካሴት ዜማዎች ጭር ጭር ጥሩ ‹‹መድ›› መፍጠሪያ የተደረገው በየቡና ቤቱ - ካፊቴሪያ እየተከፈቱ ነው፡ የሚያወቁት ነዋ፡፡ ትንሽም ቢሆን የሳያልን እርኩስ መንፈስ ያርቁታል፡፡ ግን ሳያል እንደ ሆነ እንጂ የተሻረ ንጉሥ ነው፡ ለምን ያርቁታል? ጫማቀቱ እስኪገድለው ለምን ዝም አይሉም? እኛም ያልገባን የዚህ ጥያቄ መልስ ነው፡ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ዓለም ሁሉ የሚያወቀው ነው፡ ሰው ወደ ‹‹ቸርች›› ይሄዳል፡፡ ይሰብካል፡፡ እጁን ያነሣና ጌታን ይቀበላል፡፡ የክትትል ትምህርት ይማራል፡፡ ይጠመቃል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በአንድ አገልጋይ እጅ መጫኛ አማካኝነት እንደ ምንም ይሞላል፡፡ ልሣን ይናገራል… ከዚያስ? ሁሉም ይህንን ያወቀዋል፡፡ ሁሉም ይህንን ይዞ ነው ክርስቶስን በወጭ አድርጎ የቆለፈው፡ የሚልጠውን ነገር ከማሐከላቸው ማንም አያወቅም፡ ምክንያቱም የሚቀጥለው ነገር ከዚያ ዝግ ቤት ወጭ የሚሆን ነውና፡፡ የሚቀጥለው ካለንበት ነቃይ ነው፡፡የሚቀጥለው አስቀድሞ ያንን ሁሉ የሚ ድል ነው፡ ለሌላ ክብርና ሕይወት ያነሣን ዘንድ፡፡

አ! የሚቀጥለው ‹‹ትቀበሉት ዘንድ ወጡ!››ነው፡ ወጡ! ከየት? እስካሁን ካለንበት!! ከረኽምና ከተንዛዛው የቤተ ክርስቲያን ዘመን! በጽዮን ተራራ የታዩት ደናግሎች ማንም ይሚረው ዘንድ የሚይቸለወን ቅኔ - እርሱም የበጉ ቅኔና የእግዚአብሔር ባሪያ የሚኬ ቅኔን ይዘው ተገኝተዋል፡፡ ቅኔው አዲስ ነው፡ አሮጌም ቅኔ አለ፡፡ ቅኔው የተለወጠው አዲስ በመሆኑ ነው፡ ብዙዎች የዚህ ምሥጢር አልገባቸውም፡ በመንግሥቱ ዘመን የሚማሩት አዳዲስ ነገሮች ፍልስፍናና ከመገዛት የሚያስከዱን አይደሉም፡ ሰሚይና ምድር ሁሉቱም ዘመን ላይ አሉ፡፡ የፊተኛውን አሮጌ ይለዋል፤ የኋለኛውን አዲስ ይለዋል፡፡ እንግዲህ ሁሉም ልምምዳችን ላይ የአካል ወይም የጊዜ ወይም የስፍራ ለውጥ ሳይሆን የመታደስ ለውጥ ነው የተፈለገው፡ ጸሎት አሮጌና አዲስ አለ፡፡ አምልኮም እንዲሁ፡፡ መስጠትም እንዲሁ፡፡ ትጋትም እንዲሁ፡፡… ወዘተ፡፡ ግን አሮጌው በዘመኑ አዲስ ነበር፡፡ አዲስ ዘመን ሲመጣበት ለመጣበት ዘመን አሠራር የሚመች ሆኖ ይለወጣል፡፡ ሞቶ ይነሣል፤ ደከሞ ይበረታል፡፡ በጉ እኮ ያለውን ይዘት ለመጣው ዘመን የሚመች አድርጎ ለውጦት ተጠቅሟል፡፡ እርሱ ሁሉም የሚዘረወን መዘመሮ ዘምሯል (ማቴ.26÷30)፡፡ ግን ዘምሮ እንደ ነበረው ዘመን ወደ ገዛ ኑሮው አልሄደም፤ ዘምሮ መንግሥቱ ወደሚጸናለት አካሄድ ፈጠነ፡፡ ወደ ሞት፡፡ ጸልዮ አልተከላከለም፤ ጸልዮ ሞትን ጠራ፡፡ መንግሥት በዚህ ይጸናልና - ሃሌሉያ! እግዚአብሔር ይባረክ!!

ቤተ ክርስቲያን ወደ ፍጻሜ ዘመኗ ነገሮችን መከላከል ነው የሚጠቅው፡ይህ ግዴታ ዘመኗ ነውና፡፡ አንድ አዳራሽ መሉ ምእመን አንድን ርኩስ መንፈስ ሊያስወጣ ሲጮህ ስናይ ምን ያህል አሮጌነት እንደተጋገረባቸው እናያለን፡፡ አንድ አዳራሽ መሉ ምዕመን ሞትንና አለመነሳትን ሲረግም ስናይ በእውነት የእግዚአብሔር ቸርነት በተለይ ሜዳ ላይ ሁሉ በድህነት ጠንቅ ለፈሰሱት

እንድናይ ያስገድደናል፡፡ ወጭ ያለወስ ሰው፣ ሜዳ የወጣው ሰው ኢየሱስን ስላላወቀ ነው የደኸየው? ወጭ ያለወስ የበለጸገው ‹‹ጴንጤ›› ስለሆነ ነወን? የሀገራችንን ባለጠጋ ምን እንላቸዋለን? ይህ በእርግጥ የዘመን ምሽት ነው - እኩለ ለሊት፡፡

‹‹... ወዳጄ ሆይ፣ ተነሺ ወበቴ ሆይ፣ ነዪ፡፡ እነሆ ክረምት አለፈ፣ ዝናብም አልፎ ሄደ፤ አበቦች በምድር ላይ ተገለጡ የዜማም ጊዜ ደረሰ የቁርዬውም ቃል በምድራችን ተሰማ›› (መኃ.2÷10-12)፡፡

የምዕራፍ አንድ ሕይወት እስከ ምዕራፍ ሁለት ቁጥር ስድስት ብቻ ዘለቀ፡፡ ከዚያስ? ከዚያማ ክረምት ገጠመው፡፡ ለምን? ለበለጠ ክብርና ሕይወት፡፡ ደናግሎች በጽዮን ተራራ ግን የሚጨረሻው የሕይወት ክብር ያገኙ ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሕይወተቸው ላይ ክረምት መጥቶባቸዋል፡፡ ሁሉም ነገር እንደ ገና ለአዲስ ክብር፣ ለአዲስ ዘመን፣ ለአዲስ ምልልስ የሚሞቹ ሆኖ ይበቅላል፡፡ የእርግቦችን ድምፅ ብቻ እንሰማለን፡፡ እስከ ዛሬ እንደ እባብ ብልህ እንደ እርግብ የዋህ ሁኑ የሚለውን ሰምተን ይሆናል፡፡ ግን ይህም ክረምት ይገጥመዋል፡፡ የእባብ ብልህነት በክረምቱ ይታጠባል፡፡ የመንፈስ ድህነት ይወርሰናል፡፡ የእርግብ ድምፅ ብቻ በምድራችን - በአዕምሮአችን ይሰሟል፡፡ ሁሉም ከወስጥ ይወጣል፡፡ በለሱ ይጎመራል፡፡ መንምራት ከወስጥ መጨለቀቅ ነው፡፡ እንደ ገና ሟበብ ነው፡፡ እንደ ገና መዓዛ ይወጣል፡፡ እንደ ገና እውነተኛ ሚልክ የሚታይበት ዘመን ነው፡፡ የልጁ ሚልክ ከክረምት በኋላ እንጂ በክረምት ለማየት ስንታገል የተጨነረበረ ነው የሚሆነው፡፡ ሚልኩ ይታያል - ድምፁ ይሰሟል፡፡ ሁሉም ካለበት ይወጣልና፡፡

ደናግሎች - ክረምት ያለፈለት ትወልድ በሐሰት ያልረከሱ ናቸው፡፡ ወሸት እኮ እውነት አለመለጥ - የእውነት ሚዛወር ነው፡፡ በአፋቸው ወሸት አልተገኘም፡፡ ሐሰት ‹‹ሰውነት›› - ምድራዊነት ነው፡፡ ‹‹ሰውነት›› በእነርሱ የለም ሰማያዊነት - መላኮታዊነት - አሟልከትነት - ከሁሉም በላይ ልጅነት እንጂ ፈጽሞ ‹‹ሰውነት›› አልተገኘባቸውም፡፡ የእግዚአብሔር ዝናብ፣ የእግዚአብሔር ክረምት ይህንን ከእነርሱ አጥቧልና፡፡

ደናግሎች - ከሴቶች ጋር ያልረከሱ ናቸው፡፡ ሴቶች በትወልዱ የሃይማኖት ቤቶች ናቸው፡፡ ጌታቸው ሩቅ አገር ያለ - ባለቤታቸው ከእርሱ ጋር እንደሌለ የሚያስተምሩ አንድ ቀን ያወም ቀን ሲሞላለት የሚሞላስ እንደ ሆነ የሚያስተምሩና የሚዘክሩ እንዲሁም መታሰቢያ የሚከብሩለት ዛሬ በጣም ብዙ ናቸው፡፡ በቤታቸው የሚለመቱ ብዙ ናቸው፡፡ ጌታቸው አንድ ቀን እንደሚሞላስና አሁን እንደ ሌላ እወቀት ስለሆናቸው አሁንን ለእነርሱና ራሳቸው ለፈጠሩት አገልግሎት ሠውተዋል፡፡ እነዚህ የስርቆትን - ውኃ ሻጮች ናቸው፡፡ ባቢሎን - ጋለሞታዋ - ባለቀይና ሐምራዊ ልብስ፡፡ ደማቅ ተቋም - አሸብራቂ ሥርዓት፡፡ ነገር ግን የእባብ ሚዝ ከእርሱ ጋር ነው፡፡ ወዮ! በገጽታቸው ለተጠመደ፡፡

የደናግሎች መለጥ - ክረምት ያለፈለት ትወልድ መምጣት ለባቢሎን መቅሰፍት ነው፡፡ የመለጣቸው አገልግሎት ጅማሬ የባቢሎን መወደቅ አዋጅ ነውና፡፡ ‹‹ወደቀች! ወደቀች!›› ይሉ ዘንድ የነቢያት መናፍስት ጌታ አምላክ ከእነርሱ ጋር ነውና፡፡ ኤልሳዕ እንደ ኤልያስ ከባቢሎን ጋር ከኤልዛቤል ጋር አገለገልን? ኤልያስ ምንም እሳት ቢያወርድ፣ ምንም የበዓል ነቢያትን ቢገዳደር ይፈራታል፡፡ የኤልሳዕ መለጥ (እጥፍ መንፈስ) ግን መጀመሪያ ኤልዛቤልን ከግዛቱ ጠርጎ ማውጣትና ማጥፋት ነው፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን ዘመንንና ትዕይንት ነው፡፡ ነፍሱን የጣለ - ማንነቱን ታግሎ ያሸነፈ በቤተ ክርስቲያን ማን አለ? የእግዚአብሔር ችሎታ ታየ እንጂ የእኛን ለእግዚአብሔር ሕይወት ብቃት አላሳየም፡፡ ነፍሱን የሚይጥል - ራሱ የሚገለጥበትና የሕይወቱ ደለል የሚነሳበት በመንግሥቱ የታል? ወዶች ሆይ÷ የኤልዛቤል መታረድ በመንግሥቱ መንፈስ ነው፡፡ እውነትና ምሕረት በተገናኙበት በዚያ፡፡ ጽድቅና ሰላም በተስማሙበት በዚያ፡፡

ወዶች ሆይ፡- እናም መንፈሳዊ ጊዜን ተመልከቱና የራሳችሁን ሰዓት ተመልከቱ ማነው የዘገየው? የፈጠነ ወስ? ትጠይቁ ዘንድ ብትወዱ ጠይቁ፡፡ አሁን ምን ያህል ነው? አሁን የቤተ ክርስቲያን ዘመን አይደለም፤ የመንግሥቱ ዘመን እንጂ፡፡ ጌታ እግዚአብሔር በሁሉ ይህንን ያምጣ! ሴላህ!!

የማነት (የአሮጌው ቤት) ለወጥ ዋጋ

ልጅነት እስካሁን ይተረካል፡ ከተሸሸገበት ከመጋረጃም ይወጣል፡፡ *መጋረጃም የሥጋዊነት መላት ይሁን እንጂ እግዚአብሔር* ግን በልጅነት ሳይገለጥ አይተወም፡፡ ልጅነት ለፍጥረት የእግዚአብሔር ማንነት መሉ መልስ ይሆናል፡፡ በጅማሬ ፍጻሜን የሚከቀልል የአብ የዘላለም ሐሳቡ ነው ልጅነት፡፡ ታዲያ ዛሬ እንደ ልጅ የት ነን? በልጅነት ስም ብቻ ያለ መለጥ ባለንበት ቦታ የምንረግጥ ከሆነ ቃል - ታላቅ ቃል ብቻ አለን፡፡ በዚህ ሁኔታ መሞትም ግድ ነው፡ እንደ ገና በአዲስ ሕይወት... በትንሣኤ እንድንጀምር ይህ የእግዚአብሔር የሞዳን አሠራሩ በመሆኑ አይተንና አስተወለን እንድን ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን፡፡ ይህም መዳን ጅማሬና ፍጻሜ ያለው ነው፡፡ በተጀመረብን በእርሱ በመሬድና በመኖር እርሱንም በመለጥ እርሱ ራሱ ይጠቀልለናል፡፡ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ የሆነው ማጨረሻ አለወና፡፡ በትክክል በዚህ ከተያዝንና ከተመሠረትን በተያዝንበት

በዚያው ወደ ፍጻሜ ልንዘረጋ በነቃብን መንፈስ እንዘረጋለን እንጂ አንደክምም። ዕለት ዕለት እንታደሳልን እንጂ በጣስበስ አንገኝም። ይህም የመጥራቱ ተስፋ ምን ያህል በእኛ ሕያው እንደ ሆነ ልብ ብለን ልናየው ያስፈልገናል።

በከንቱ ትምክህት ሩቅ የደረስን ቢመስለንም የትም አልደረስንምና መለስ ብለን ጅማሬአችንን ብንመረምረው መልካም ነው እላለሁ። ጅማሬአችን ለፍጻሜአችን ያዘረጋናልና በወስጥ መላወጥ ብናከብረው - ብንኖረው - በእወቀት ብናደርገው በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አለው። ዋጋውም ኤሜጋን - አብን መውረስ ነው። የክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እኛ መውረድ ዓላማው ሕይወት ሊሆነንና ሊበዛብን በመሆኑ የእኛ የልጅነት ሥልጣን መውረስ በአባታችን ቤት መኖር በቤቱ ቤት ልንሆን እንጂ በእርሱ አመካኝተን ከንቱ መቅበዝበዝ እንድንቅበዘበዝ እርሱ ስለ እኛ ይህን አላየም።

<<የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው>>(ምሳ.1÷7) የሚለውን የመጽሐፍ ከፍል መቼም ሁላችንም ሳናነበው አልቀረንም። ግን ግን በስንቶቻችን እግዚአብሔርን መፍራት በሕይወታችን ነገሠ? ይህ ከቡር የሆነው ዓላማ በእኛ የእግዚአብሔር ሕይወት መበዛት ጅማሬ ነው። እግዚአብሔርን መፍራት የሕይወታችን መሠረት ነው። አዎን አስረግጬ እላለሁ። - የሕይወታችን ጅማሬ ነው.. እስቲ <<መፍራት>> የሚለውን ቃል በሳወል ሕይወት እንመልከት። - ሐዋ.9÷1-6 <<... ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ። በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ ሳወል ሳወል ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ። ጌታ ሆይ ማን ነህ? አለው። እርሱም። - አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ የመጪያወን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብስብሃል አለው። እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ። - ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም። - ተነሥተህ ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን ይነግሩሃል አለው።>> በዚህ ከፍል እንደምንመለከተው በሳወል ሕይወት የሆነው ነገር ካለበት ከጨለማ ሥራ - ከምድራዊ ነገር እንዲለይ - ለምድራዊ ነገር መሮጡን እንዲያቆም - ፊቱን ወደ በራለት ብርሃን ዞር እንዲያደርግ መደረጉ ለእርሱ የልብ ለወጥ ነው - የሥፍራ ለወጥ ነው - የልብ ፈወስ ነው። <<በመንቀጥቀጥና በመደነቅ>> መሆኑ ወደ ክርስቶስ ከተማ የመግባቱ ምሥጢር የሕይወት ጅማሬ በእርሱ መመሥረቱ አይመለጣችሁም? ይህም <<የጥበብ መጀመሪያ የተባለው እግዚአብሔርን መፍራት>> ካለንበት ምድራዊ አስተሳሰብ ወደ እግዚአብሔር የዘላለም ሐሳቡ ዘወር ሚድረጉ የእግዚአብሔርን አምባገንነት የሚልጥ ሳይሆን በፍቅሩ ጅማሬ - በማዳኑ ልክ ለሳወል በተገለጠበት መንገድ የሳወልን ምድራዊነት በምድር ላይ ጥሎና ሕይወትን ባየበት ነገር እንዲያነሣ እንዲከተለው ሚድረጉ ነው ያለ ጥርጥር።

የሕይወት ጅማሬ የድንጋይ ልብ መወገድ ከሆነ በትጉት ልብ - በሚቀጠቀጥ ልብ - የላይኛውን አይቶ በሚደነቅ ልብ ማን እግዚአብሔርን አይፈራ? የመንቀጥቀጥ ትርጓሜ ከዚህ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? የእግዚአብሔር መገኘት፣ የእግዚአብሔር መለጥ ሰማይና ምድርን ሞኝወጡ እርግጥ ነው። ከመኖወጥ በኋላ ስላለው መጽናት መኖወጥ ቀድሚል። ይህች የእግዚአብሔር ጥበብ - የእግዚአብሔር መንገድ ናት። የእግዚአብሔር ሥራ ዘላለማዊና ፍጻሚ ያላት ናት። የጅማሬና ፍጻሜም ስንል ስለ እኛ እንደ ሆነ ይግባን። ስለ ራሱ ፈጽሞ አይደለም። እርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ያው ነውና ስለዚህም የጥበበኞችን ጥበብ የሚፈርስበት - የአስተዋዮችን ማስተዋል የሚሸርበት በእጅ ያልተሠራች በእወነትና መንፈስ የተመሠረተች መንግሥት አለችን። መንግሥቱም ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሆነች ደስታ ናት። ይህንን መንግሥት ሰማየት በእያንዳንዳችን ጀምሮአል እያልኳችሁ ነው። <<ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈፀም ይህን ነግሬአችኋለሁ>>ዮሐ.15÷11 - የተነገረን - የተገለጠልን ነገር ለሞኖሩ እያንዳንዳችን ምስክር ነን። ከፍ ብለን ብንመለከት <<ደስታዬ>> የሚለው የትኛው እንደ ሆነ የተገለጠው ቃሉ ይነግረናል። <<በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ...>> ይላልና። ቃሉ እርሱ እርሱም ቃሉ አይደለምን? <<በደስታ የተገለጠው የእግዚአብሔር ሎሚስ ክርስቶስ አይደለምን? የክርስቶስስ ደስታ የአብን ፈቃድ ሙጸም እንደ ሆነስ አታውቁምን? ስለ እኛ ከዚህ ወጪ አይተናል ወይ? እንግዲያውስ ደስታችን ክርስቶስ በእኛ እንዲፈጸም በእኛ በኖረው ደስታ ድንዛዜአችንን እናስወግደው። በጅማሬአችን ፍጻሜአችንን ትኩር ብለን ልንመለከተው ግድ ሆኖአል።

የሰው መንገድ ከልቡ ወጪ ሌላ እግዚአብሔርን በከንፈሩ ብቻ የሚገለግልበት በመሆኑ ከእግዚአብሔር የራቀ መንገዱም ፍጻሜ የለውም። ፍጻሜ ያለ ጅማሬ እንዳልተሰየመ በዚሁ ሞት እንችላለን። በፊደል ገበያ ፊደል ፊደልን ይተርካል እንጂ መንፈስን ሊተርክ አይችልም። መንፈስ ግን በፊደል የተሰወረውን ወደ መለጥ ያመጣል። አካልም ይሰጠዋል። ይህም መንፈስ ከልጅነት ሌላ ፈጽሞ አይደለም። እግዚአብሔር በልጁ ልጅነትን ከጀመረብን እንደ ልጅ የልጅነትን መንፈስ ሊገኝብንና ሊበዛብን በእርግጥ ይጠበቃል። የጀመረብንም እራሱ ለፍጻሜ ከእኛ ጋር ይተጋል - በእኛ ይተጋል።

<<ስለ ምን፣ - ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ትሉኛላችሁ የምለውንም አታደርጉም? ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገውን ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ። ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል፤... ሰምቶ የሚያደርገው ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመሥላል፤...>> (ሉቃ.6÷46-49) የልጅነት ከብር የአብን ፈቃድ፣ አብ የሚለውን ሚድረግ ከሆነ በዚህ ጥቅስ የምናየው ግን ያለማንነቱ ከማንነቱ ወጪ በመሆን የሚያደክመትን ሲገልፅ እናያለን። - <<ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገውን ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ።>> አላቸው። ስለዚህ

አንድ ነገር ሊያዩ ግድ ነው፡ በልኩ ልካቸውን ሚስፈር አለባቸው፡ ከዚህ ከተገለጠው ልክ ወጪ መሆናቸውን ሲያወቁ ወደ አንድ ነገር ሊጠቀለሉ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ቤትን ለመሥራት በዓለት ወይም በአፈር መሥራት ከተቻለ የሚበልጠውንና የተሻለውን ፈትነው የሚዙበትን ማንነት ነበር የሚያሳያቸው፡ ይህም የሕይወት መዘገብ መጽሐፍ በፊታቸው - በልቦናቸው ማበቡ ነው፡

የልጆች ልክ ካዩትና ከሆኑት ከራሱ ወጪ ስለ አይደሉ በተገለጠላቸው መለጥ ከወዴት እንደ መጣ የትስ እንደሚሄድ ጠንቅቀው በማወቃቸው በሕይወት እርሱን ይተርኩታል፡፡ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እራሱን ሚለየቱ ከእርሱ ሌላ ሚልክ እንዳይሳልባቸው ነበር፡፡ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት የመለዳችን ወራት በመሆኑ ሚችንም ከሆነልን ከዚህ ወራት - ከክርስቶስ ፊት ወጪ ሌላ ቢሆንልን እንፍራ ክርስቶስ የልጅነት መላት ነው፡ አብን የተረከ - ያሳየ - የአብ መለጥ ነው፡ ከዚህ ወጪ ምን ጥበብ አለን? ልጅ አብ ሲያደርግ ያየውን ሲያደርግ ልጆች ደግሞ ልጅ ሲያደርግ ያዩትን እንዲያደርጉ እራሱን ገልጦላቸዋል፡፡ እንግዲህ መላስ ብለን ክርስቶስ በዘሙ የሠራቸውን ሥራ ሞት ብንችል ለእኛም ካየው ልክ ወጪ ልንኖርና ልንሆን አላየንምና ግድ አለብን፡፡

የጳውሎስ ከነበረበት ሥፍራ ለአንዴና ለሚጨርሻ ጊዜ መጠቅ እጅግ አስደናቂ ነገር ቢሆንም ለተገለጠለት ታላቅ ራዕይ በመታዘዝ ምላሽ ሚጠቱ ነገሩን መለጥ ወይም መታየት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ‹‹ንጉሥ አግሪጳ ሆይ ስለዚህ ከሰሚይ የታየኝን ራዕይ እምቢ አላለሁም›› (ሐዋ.26÷19)፡፡ ጳውሎስ ይህን መልስ ለንጉሥ አግሪጳ የመለሰው ለክስ ቀርቦ በነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ‹‹እምቢ አላልኩም›› እምቢ ሚለት አለ መቻል የተገለጠለት መለጥ ሰሚየዊ እንጂ ምድራዊ አለ መሆኑን የሚልጥ ነው፡ ማንም ለሰሚየዊ መለጥ እምቢ ሚለት አይችልም፡ ስለዚህ ከተገለጠለት ነገር የተነሣ ከትወልዱ ወጪ በመሆኑ ለእስር - ለሞት ተፈልጓል፡፡ ይህም በሕይወት እወነትን - ከርስቶስን በመለጡ ትወልዱ የሚደርገወን አያደርግም ነበር - ከትወልዱ እወቀት የተለየ እወቀት ነበረው፡ በመሆኑም ጥያቄን በሁሉ ላይ ፈጥሮ አልፏል፡፡ መንገዱ እንደ መንገዳቸው ሚለት ነው፡ ኢየሱስ በታየለትና በሚታይለት ነገር በሕይወት መንፈስ ሕግ መሆኑ ከትወልዱ ለይቶታል፡፡ ይህም ጅማሬወና ፍጻሜው ነው፡ የታየለት እንደሁም የሚታይለትም በሕይወት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ተጀምሮበታልና በክርስቶስ ጌትነቱን ይገልጥበታል፡፡ ለፍጥረት ይታይበታል፡፡ የሕይወት አለ ሞቋረጥ አንዳችም ጊዜ ለምንም ነገር ሥራ ፈትነትን በሕይወቱ አይፈጥርም፡ ሁል ጊዜ በጌታ ኃይል የበረታ ነገረ ጅማሬን መያዝ ለፍጻሜ ተስፋ አለው፡

ስለዚህ እያንዳንዳችን ክርስቶስ ሊበራልን ያስፈልጋል፡፡ በልባችን የበራውን - መንገዳችንን ያቀናውን ልንሄድበትና በሕይወት መለጥ ከእርሱ ጋር በቤቱ ልንኖርና ልንፈጽመው ያስፈልገናል፡፡ ወድዶና ፈቅዶ በታየን እይታ አይተን ልንጓዝ የመንገዳችን መጀመሪያ ሆኖአል፡፡ ኢየሱስ ለጳውሎስ ሚስፈሉ ለእኛም ሚስፈሉ አይደለምን? አሁን የትና እንዴት እንዳለን እያንዳንዳችን እናወቃለን፡፡ በእወቀት ነን እንላለን ነገር ግን አላዋቂ ሆነናል፡፡ በርቶልናል እያልን እወሮች፣ እንሰሚለን እያልን ደንቆሮዎች፣ ጠግበናል እያልን ረሀብተኞች ሆነናል፡፡ ያለ መንፈስ በፊደል ብቻ ሆዳችንን ሞልተን የጠብን ሲሚስለን በጠኔ አልቀናል፡፡ ማንም ሊያይልን የሚችል ስወር ጠኔ ይዞናል፡፡ ወገኖቼ ማንንም አናታልል! መንፈሳዊያን ሚስለን ሥጋዊ ሆነን መገኘታችን እግዚአብሔር ነውራችንን መለጡ ነውና ከዚህ ፈጥነን እንሽሽ!

መረዝ ወይም አለ መረዝ ለሥጋ ባይጠቅምም ስለ መንፈሳዊ መረዝ ካልሆነ ግን እያንዳንዳችን ሸለፈታሞች ነን፡፡ ስወር ሸለፈት! ይህ በእግዚአብሔር ፊት ፀያፍ ነው፡ ሚስወገድ ካለብን በወጪ የሚታየወን በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠወን ነወር ጥለን ካለንበት አዘቅት እንውጣ! እያዩ አለ ሞት መንፈሳዊ እወርነት ነው፡ እየሰሙ አለ ሚከተዋል መንፈሳዊ ድንቁርና ነውና እንሽሽ! ወደ መቅደሱ እንግባ! በመቅደሱ እወነትና መንፈስ ኃይላቸወን የሚልጠበት - አምልኮአቸወን የሚያሳርጉበት ሥፍራ ነው፡ እንግዲህ መቅደስ ሚስፈለጉ የተገለጠ እወነት ሆኖ ሳለ ወደ መቅደሱ የገባን እየሚከለን በወጪ ተገኝተናል፡፡ ለዚህም ሕይወታችን ምስክር ነው፡ ከተገለጠልን ከእግዚአብሔር እወነት ጋር ሕይወታችንን ስናስተያይ ኃይለኞችና ጽኑአን ሚሆን ሲገባን ከሃይማኖት ቤት እንዲሁም ከዓለም ባነሰ ሕይወት ላይ እንገኛለን፡፡ ይሄ ደግሞ ግልጽና መንፈስን ሊያታልል አይችልም፡ የእግዚአብሔር እወነት ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ከተገለጠልን ወደ በለጠው የሕይወት መለጥ ሊያዘረጋን የሚገባ ነገር ነበር፡፡ የሰሚይ መለጥ ምድር ልትቋቋመው የምትችለው ጉዳይ አይደለም፡ ደግሞም ቀጣይነቱ የሚያጠራጥር ነገርም አይደለም፡ መለጡ ቀጣይነቱን ይዞ ነው የሚለጠው፡ ስለዚህ ኢየሱስ ከተገለጠልን መዘርጋታችን የግድ ሊሆን ነው ሚለት ነው፡ እንግዲህ ከሕይወታችን መጉደል ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንዳልተገለጠልን ማን ሊከድ ይችላል? እግዚአብሔር ይዋሽ ዘንድ ሰው አይደለም! ይህ ከእርሱ ይራቅ! ለተገለጠልን ነገር ጉልበት ሚጣታችን - አቅም ሚጣታችን እንደ ብርታት ቆጥረን እየኖርን ከሆነ እንዲህ ዓይነት እግዚአብሔር እወነተኛው እግዚአብሔር አይደለምና መንገዳችንን እንመርምር! እወነተኛው እግዚአብሔር በልጁ የገለጠው በቃልም በሥራም ብርቱ ነቢይ ነበርና፡፡

እነዚያ ለዋርኞች ንግዳቸወን የሚጣጠፉት በቤተ መቅደስ ወስጥ ሆነው አልነበረምን? ከቤተ መቅደስ ወጪ እንዳይሚላችሁ - እያሉ የሌሉ እየሱስን ያስመረሩ ሃይማኖተኞች አይደሉምን? መቅደሱ ስሙ ነውና በስሙ ይገዙና ይሸጡ ነበር፡፡ ስም ብቻ! ስመኝ የሚጠራ - የሚያምንበት - አለን? መገዛት መሻጥ እኮ ይኸው ነው፡ ደግሞም ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም፡ እየኖርነው

- እየሆነው ስለ ሆነ የለዋጮች ማንነት ለእኛም በግልጽ ይገባናል፡፡ በእርሱ ሆነው - ከእርሱ ወጪ መኖር በእርሱ ዘንድ ከእርሱ ሕይወት ወጪ መግዛትና መሻጥ በሥጋ ገበያ መገኘት - ሥጋዊነትን ማኮረፍ - መሸቃቀጥ አይደለምን? ስለዚህ በእርሱ ለእርሱ መሆን - በእርሱ ለእርሱ መሥራት ትክክለኛ ሕይወትን መመላለስ - መራመድ በመሆኑ - ለሚይጠፋው መበል እንሠራለን፡፡

ሰምቶ የሚያስተወል ሕዝብ መገልበጡ - ከእግዚአብሔር ሕይወት ወጪ ለከንቱነት ታልፎ መሰጠቱ - የሰወነት ዘመኑን እስኪጨርስ ሣር እንዲበላ መተዉ ነው፡፡ እግዚአብሔር በከንፈሩ ከሚከብረው ሕዝብ ጋር ምን ኅብረት አለው? በሁለትነት ላይ ያለ ርኅራኄ ይፈርዳል፡፡ መንግሥቱም የምትወሰደው ከዚህ ሕዝብ ነው፡፡ ‹‹ኃይለኞች ይናጠቋታል›› ስለሚል፡፡ እነዚህ ኃይለኞች የተባሉት በመቅደሳቸው የሚኖሩ በእርሱ እርሱን የሚያወድሱ ሚለትም በሰማይ ያለችውን የአብን ፈቃድ ወደ ምድር ጥልቀት የሚመጡ - የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚገልጡ - ለፍጥረት ነፃነትን የሚያወጁ ከልጁ የተሞሩና የሚከብቁ ልጆች ናቸው፡፡ መንግሥቱ ለእነዚህ ትሰጣለች፡፡ እነሱም ይኖሩአታል - ይመላለሱአታል - ይተርኳታል - ይገልጧታል፡፡ ሕይወታቸው ናትና! ስሙ የተባረከ ይሁን!

እግዚአብሔር በየዘመኑ ዘመን ሲለውጥ የሚጀምረውንም ሆነ የሚጨርሰውን እኩል በቤተ መቅደሱ ያዘጋጃቸዋል፡፡ አንደኛውን ወደ ፍፃሜ ሲያንደረድረው አንደኛውን ለጅማሬ ያጣድፈዋል፡፡ እግዚአብሔር በዔሊ የሰፈረውን ዘመን ሲጨርስ በብላቴናው ሳሙኤል መሣሪያ ድንቅ ትንሣኤ ነው፡፡ ይሄ ነው የዘመናት ለወጥ፡፡ አንደኛው ቤት ሲያረጅ ሁለተኛው ገና ጉልበታም ነው፡፡ አንደኛው ቤት ማጥት ሲሳነው ሁለተኛው ቤት ብሩህ ነው፡፡ ሁለተኛው ቤት የሚመጣውን፣ ሊሆን ያለውን ያያል፡፡ ለሚረዘም ለአንደኛው ቤት ስለ ፍፃሜው - ስለ ሞቱ - ስፍራውን ስለ መልቀቁ ተሰወሮ የነበረውን ራዕይ የሚገልጥለት ሁለተኛው ቤት ነው፡፡ እግዚአብሔር በወሰጠኛው ቤተ መቅደሱ የተናገረውን የተገለጠለትን የእግዚአብሔርን ሥራ፣ ሲሆን ያለውን፣ ስለሚመጣው ዘመን ይገልጣል፡፡ ይሄ የሁለተኛው ቤት አገልግሎት ነው፡፡ ይህም ከራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር ምርጫ ጥሪው የተነሣ እንጂ፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለልጅ ልጃችን ልናወርስ አንችልም ወይም እኛ በተጠራነው መጠራት አሳልፈን ለመስጠት እግዚአብሔር ሊያመልከተን ይገባል፡፡ በዔሊ ቤት የዔሊ ልጆች አባታቸውን በሕይወት የጠበቁ ሳይሆኑ የአባታቸው ገዳዮች ነበሩና፡፡ የስንፍናቸው ብዛት - የልባቸው ጥንካሬ፣ የድፍረታቸው ልክ ለእነርሱም ሆነ ለአባታቸው የዘመናቸው ፍጻሜ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ለሞታቸው መቅደሱንና መሥዋዕቱን አርከሰዋል፡፡

በዚህ ጊዜ ሳሙኤል የት ነበር? ምንስ ያደርግ ነበር? እስቲ 1ሳሙ፡3÷1 እንመልከት፡፡ ‹‹ብላቴናውም ሳሙኤል በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፡፡›› ሳሙኤል ለዔሊ አገልጋዩ እንጂ ልጁ አይደለም አልወለደውምና፡፡ ሊወልደውም አይችልም፡፡ ከእርሱ የተወለዱት በነውራቸው መላት እግዚአብሔርን ሲያስቆጡ ከእነርሱ ወገን ያልሆነው ሳሙኤል ግን በብላቴናነቱ በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፡፡ የሳሙኤል ማንነት ከተፈጠረበት - ከተወለደበት ማንነት እንጂ ከዔሊ መኖራቸው በእርሱ ላይ የሚመጣው የባሕሪይ ለወጥ አለየንበትም፡፡ ምክንያቱም ሳሙኤል ይኖር የነበረው በቤት ወስጥ ሌላ ቤት ነበር፡፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔርን ለመኖር - ሥራውን ለመሥራት ቅባቱ ካላገዘን፣ ጥሪው ካልሳበን፣ ምርጫው ካልገነነብን አይሆንም ያልናችሁ፡፡ እግዚአብሔር ለፈቃዱ፣ ለዓለማው በሥራ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የአንደኛው ቤት መጥዘዝ የበለጠውን የእግዚአብሔርን መለጥ ያደምቀዋል እንጂ እግዚአብሔርን አይሰወረውም፡፡ በመቅደሱ ያበራውን መበራት ገና ሳይጠፋ ሌላ ብርሃን ያበራል፡፡ በብርሃን ላይ ሌላ ብርሃን፣ በመለጥ ላይ ሌላ መለጥ የሚያቋርጠው የእግዚአብሔር ከቡር መለጡ ማንነቱን፣ መኖቱን፣ ሕልውናውን የሚመስከር አይደለምን?

የምስክሩን ታቦት ግን የምናገኘው በቤተ መቅደስ ወስጥ ነው፡፡ በዚያ ቃል አለ፡፡ በዚያ ድምፅ አለ፡፡ በዚያ ትንሣኤ አለ፡፡ ምንም ወራቱ የብላቴናነት ቢሆንም ለሳሙኤል የእግዚአብሔር ቃል ባለበት ሚደሩ በራሱ የሕይወቱ ምስክርነት በመሆኑ እግዚአብሔርን ስቦታል - አወርዶታል፡፡ የተገለጠው ቃል የሕፃንነትን ወራት ይሽረዋል፡፡ ልጅ አባቱን ወደሚወርስበት የልጅነት ሥልጣን - ስፍራ ያመጣዋል፡፡ የሳሙኤል ብላቴንነት ምንድር ነው? ብትሉኝ በጊዜው የሚለጠወን የእግዚአብሔርን ቃል ወይም ሐሳቡን አለማወቁ፣ የእግዚአብሔር ቃል ለእርሱ አለ መለጡ እንጂ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ቃል ብርቅ በነበረበት ዘመን ላይ መሆናቸው በራሱ የአለማወቃቸውን ልክ የሚያጎላ ነበር፡፡ ካህኑ ዔሊም እጅግ አርጅቶ ስለ ነበር፣ ዓይኖቹ ሞዘዝ ጀምረው ስለ ነበር እንዴት የእግዚአብሔር ቃል ይገለጥ? በዚህን ጊዜ ነው ሳሙኤል የሚያስፈልገው፡፡ ሳሙኤል ካልተገለጠ እግዚአብሔርን ማን ይግለጥ? ‹‹ብርቅ ነበረ›› ሚለቱስ እግዚአብሔር የተሰወረበት ጊዜ አይመጣችሁምን? በጭቅና በጨለማት - በፅኑ ልቅሶና በወርደት የተገኘው ሳሙኤል ለእግዚአብሔር የታመነ ካህን ነው፡፡ እርሱ ጊዜውንና ሰዓቲቱን ይጠባበቃል፡፡ በቤተ መቅደስ ወስጥ፡፡

ሞትና ትንሣኤ አብረው መጓዛቸው በመጽሐፍ ብዙ ቦታዎችን ልንጠቅስ እንችላለን፡፡ ለትምህርታችን ተጽፏልና፡፡ ሞት ትንሣኤን ያገለግላል፡፡ ከተሰወረበት - ከተደበቀበት - ከመቃብር እንዲወጣ ያግዘዋል፡፡ ለብርሃን አሳልፎ ይሰጠዋል ይገልጠዋል፡፡ የቀደመው ሚለትም ፊተኛው ቤት መገለጡ ለተሰጠው ዘመን ሲሆን ሁለተኛው - ኋለኛው ግን መሰወሩ ለእግዚአብሔርና ለሚመጣው ዘመን ተስፋ ነው፡፡ የዔሊ ተቀባይ ሳሙኤል፣ የሳኦል ተቀባይ ዳዊት፣ የአስጠጊ ተቀባይ አስቴር፣ የሐማ ተቀባይ

ሞርዶክዮስ… እነዚህ የሚያሀሉ ምስክሮች በዙሪያችን አሉልን፡፡ እነዚህ በጥቂቱ የዘረዘርናቸው ሰዎች አንዱ ያለ አንዱ አልተደረጉም፡፡ አንዱ የአንዱ ሚድመቂያ ገላጯም ነወና አስፈላጊ ናቸው፡፡

አንድ ነገር ግን ልብ ልንል ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም እነዚህ አንደኛ የሚመስሉ ቀዳሚ የሆኑት የማንነታቸው ልክ ቢሚሞር አጩራረሳቸው ማንነታቸውን የሚልጥ ነው፡፡ አሮጌነታቸውን የሚኮርከም ጯምር ነው፡፡ የዔሊ ክህነት ልብ በተሰበረበት የሐናን የሚረ ለቆሶ፣ የልቧን ስብራት፣ የወስጧን ጩኸት አለ መመልከት በመነፈስ ሳይሆን እንደ ሥጋ ወጯጪ የአፏን እንቅስቃሴ ብቻ በሞት መፍረዱ እርሱንና ክህነቱን ወጯጪ ያደርገዋል፡፡ የክህነት አገልግሎት ከቤተ መቅደስ ወጪ ባለ መሆኑ ዔሊ በተገኘበት ፍጻሜው አንገቱ ሚስበሩ የልቡ ጥንካሬ አይደለምን? ‹‹አንገቱን ያደነደነ ድንገት ይሰበራል›› ይላልና፡፡ ማንነቱን በልጆቹ ቢያጯድ ትክክለኛ ቅን ፍርድ ነው፡፡ ብዙወን ጊዜ ወላጆች ማንነታቸውን በልጆቻቸው ያዩታል፡፡ ይህም የእግዚአብሔር አሠራር ነው፡፡ የዘራነወን፣ የሆንነወን ከእኛው ተገልጦ እናየዋለን - ያንኑ ደግሞ እናጯደዋለን፡፡ ካህን ሳይገባ ያስገባልን? ሳያይ ያሳያልን? ሳይታረቅ ያስታርቃልን? ካህን በሕይወት ሳለ የእግዚብሔርስ ቃል እንዴት ብርቅ ሊሆን ይችላል? እነዚህን ሁሉ ስሚከት ዔሊ ምንም እግዚአብሔር ቢሾመወም መላቱን ሳይሆን ጉድለትን በሰፊው እናይበታለን፡፡ ‹‹በዚያን ዘመን የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ነበረ፡፡ ራዕይም አይገለጥም ነበር›› (1ሳሙ3÷1)፡፡ ካህኑ ዔሊ በስፍራው እያለ የእግዚአብሔርን ቃል ብርቅ እንዲሆን ያደረገው - ራዕይ እንዳይገለጥ ያደረገው ነገር ምንድር ነው? የምንል የዔሊ ዓይኖች ስለ መፍዘዝ እንጂ ሌላ ምክንያት አናገኝለትም፡፡ የዓይን መበራት የሰወነት መበራት በመሆኑ ዓይን ካላየ እግዚአብሔርን ተራመድ ብንለው ወዴት ይራመዳል፡፡ ወደ የትስ ያራምዳል? ሕዝቡን ወዴትም ሊያደርስ አይችልም፡፡

በእግዚአብሔር ቤት ስንኖር እንዲሁ በድንግዝግዝ የሚኖር ሕዝብ አለ፡፡ ደግሞም በሚስተዋል የሚኖርም አለ፡፡ እነዚህ ሁለት ነገሮች ሲታዩ ቀላል ይመስላሉ፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልብ ዋጋ ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ የዔሊን ዘመን ከሳሙኤል ዘመን የእግዚአብሔር ምርጫ ከየትኛው ጋር እንደሚበረታ ሚስተዋል አንችላለን፡፡ እንዲሁም ለትምህርታችን እንደ መሆኑም መጠን አካሄዳችንን የሚያቀናወና ፈትነን የምንይዝበት መነፈስ ይፈጥርልናል፡፡

ሳሙኤል ከሐና የወስጥ ጩኸት ምላሽ ወይም መለጥ በመሆኑም ጅሚሬወና ፍጻሜው አንድ እንጂ ልዩ ልዩ ሊሆን አይችልም፡፡ በወስጥ ምጥ ተገኝቷል፣ በወስጥ አድጓል፣ በወስጥ አገልግሏል፣ በወስጥ አድሯል፣ መለጠም ከወስጥ ወደ ወጭ ነው፡፡ ይሄ ለእያንዳንዳችን የሕይወት ልኬት እንጂ ተረት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ሊሠራብን የወደደወን ከዕለታት አንድ ቀን ሲደርስ ከየትም ስቦ ሊሠራብን ሳይሆን አሁን የተሰወረብንን፣ የተጀሚረብንን፣ የተሰነቀብንን ተስፋ ለዓለም ይገልጠዋል እንጂ ድንገተኛ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ የለም፡፡

በሳሙኤል ሲጀምር ከማነፀን ነው፡፡ በዳዊት ሲጀምር በአባቱ ቤት በበግ እረኝነት በሕፃንነት ወራት ነበረ፡፡ በአስቴር ሲጀምር አባትና እናት ባልነበራት ወራት ነበረ… ገና ምንም ሳይኖር እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የገለጠበት መለጡ ለምጯው ለጥሪው ለይቷቸዋል፡፡ ምንም ባለ ማወቅ፣ ብላቴንነት ወራት ቢሆኑም ጥበቡን፣ ወቅቱን በእነርሱ በመለጥ ጅሚሬን ወደ ፍፃሜ ያራምድ ነበር፡፡ በየዘመናቱ እግዚአብሔር የሚጣቸው ምርጦቹ አስተዳደጋቸው በሰወም በእግዚአብሔርም ፊት ሞገስ ያገኙ ነበሩ፡፡ በሁሉ ያድጉ ነበር፡፡ ዕለት ዕለት የሚጨምር፣ የሚታይ የእግዚአብሔር ሥራ - የሚያድግ የእግዚአብሔር እርሻ - ትወልዱን የሚመገቡ የእግዚአብሔር ብስሎች ናቸውና ጅሚሬና ፍፃሜ አላቸው እያልናችሁ ነው፡፡ ንጉሡ ሳኦል ዳዊትን ቀድሞ መለጡ እግዚአብሔር ተሳስቷልን? አይደለም! እግዚአብሔር በሕዝቡ ልብ አንድ ነገር አይቷል፡፡ ይሄወም የልባቸው መሻት፣ የሰወነት ጩኸት፣ የነፍሳቸው ጩኸት ሞልቶ ስለ ነበር ሳኦል የዚህ የሕዝብ ጩኸት ምላሽ መሆኑን እናያለን፡፡ ሳኦል የሰው ምርጫ እንጂ የእግዚአብሔር ምርጫ አይደለም፡፡ እንዲህማ ባይሆን ኖሮ ‹‹ንጉሥ አንግሥልን›› ባሉት ጊዜ ሳሙኤልን ባላስከፋው ነበር፡፡ የሳሙኤል መከፋት የእግዚአብሔር በሕዝቡ ማዘን ነው፡፡ ሕዝቡ ሳሙኤልን ባይቀበል እግዚአብሔርን አልተቀበለምና በስንፍናቸው ልክ በመሻታቸው ልክ ተገልጦ ሊበቀላቸው - እግዚአብሔርም አብሮ ተባብሮአል፡፡ ሕዝቡ በፊቱ የሚፈርድን ሰው ፈለገ እግዚአብሔርም በሰወነት ብቻ የገዘፈወን የሰው ንጉሥ ሰጣቸው፡፡ የእግዚአብሔርን ንግሥና አልፈለጉም፣ በሳሙኤል የተገለጠወን እግዚአብሔር ንቀውታልና ለሰው መንግሥት ሕዝቡን አሳልፎ መከጡቱ የሰወነታቸውን መላት በሰው ግዛት ሊጨርስ ካልሆነ ሌላ ለምንድር ነው? ሳኦል የቀደመባት - ያስፈለገበት ምክንያቱ አምላኩን የናቀወን ሕዝብ እግዚአብሔር ሊንቅበት ፈልጎ እንጂ ጽድቁን ሊገልጥበት አይደለም፡፡ ለጽድቁ መለጯማ የኋለኛው ሰው ዳዊት ከሳኦል ጋር አብሮ በአንድ ዘመን ነገር ተጀምሮበታል፡፡ እግዚአብሔር ለቤቱ ቀናተኛ ነወና ክብሩን ለማንም አይሰጥም፡፡ እጅ በሥራውም አይገለገልም፡፡ በዘመናት ሁሉ እርሱ ብቻወን ጌታ ነው! ስሙ የተባረከ ይሁን!

በሰው የተሾመው ሰወነት በሰወነት መላት እስከ ወዲያኛው ሟሽለብ እንጂ ሌላ ተስፋ አይኖረወም፡፡ በሳኦልም ሕይወት - መንገድ የምንመላከተው ይህንኑ ነው፡፡ አጀማሙን ካስተዋልን አጨራረሱ ከዚያ ወጪ ይሆናል ብሎ መጦት አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ በመነፈስ የተጀመረው በሥጋዊነት ያልቅ እንደ ሆነ እንጂ በሰወነት ተጀምሮ በመነፈስ መጨረስ ፈጽሞወንም የሚታሰብ አይደለም፡፡ በመጽሐፍም በየትኛውም ከፍል ልናገኘው አንችልም፡፡ በእግዚአብሔር ጀምረን ግን ሥጋዊነት ጠንቅ ሆኖብን ጨለማ

የሆነብን በዘመናችንም ብዙዎች አለን፡፡ ስንቶቻችን በጀመርንበት እንዳልጨረስን ሕይወታችንን ምክክር እንጠራለን፡፡ ሌላ ምክክር አያስፈልገንም፡፡ ታዲያ ሰው የሆነው ሳአል - ሰው የሚጠው ሳአል - በዓመፅ - በሰውነት መላት ዘሙን ቢጨርስ ያስገርማል? አያስገርምም! የሆነወን ነው የሆነው! አስተወሉ፡፡

በሰው የሚይገለገለው እግዚአብሔር በየዘመኑ ለዘመኑ ለወጥ ማንም አያግዘውም፡፡ እርሱ ብቻወን በቂ ነው፡፡ ዳዊትን ለሞምና ሳአልን ለመሻር ማን አገዘው? ቅባቱ ግን በስወር ድብቅ ጦርን አስነሥታለችና አንዱን ለሞት አንዱን ለሕይወት ትሠራለች፡፡ እግዚአብሔር የተመሳገነ ይሁን! የሳአል መሞት የዳዊት በሕይወት መገለጥ ከእግዚአብሔር ቅባት የተነሣ እንጂ ከማንም አይደለም፡፡ አንዱ ቅባት ለበቀል አንዱ እንዲሁም ለምሕረት አገልግሏል፡፡

ከሚታረድ መሥዋዕት ይልቅ መታዘዝ ዋጋው እጅግ ታላቅ በሆነበት አስጠን ከንጉሥ ልብ የወደቀችበት - ንጉሠን ያስቆጣችበት - አለ መታዘዝን በመፈፀሚ አይደለምን? ለአስቴር አስጠን ቀዳሚ ናት፡፡ በአስቴር የበለጠው ወበት ከአስጠን ወጫጋ ወበት በእግዚአብሔር ልክ ይበልጣል፡፡ ስለሚበልጠው አለ መታዘዚ በንጉሥ ፊት ቢገለጥ እሰየው የሚያጸጽት አልሆነም፡፡ እግዚአብሔር ሲሠራ ቢሆን ኖሮ የሚበል ነገር የለም፡፡ ትክክል ነወና! በአስጠን ትክክል ነው፡፡ በአስቴር ትክክል ነው፡፡ በሰወን ዘመን ትክክል ነው፡፡ እራሱን በዘመናት መካከል ከተሰወረበት መገለጡ ትክክል ነው፡፡ ስሙ ይባረክ! እንግዲህ ታሪክን እንደ ታሪክነቱ እያየን ብቻ የምናልፈው ከሆነ ከተረትነት ያለፈ ሚልእክት ሊሆነን አይችልም፡፡ ነገር ግን በእያንዳንዳችን፣ በሕይወታችን፣ በቤታችን፣ በጎረቤቶቻችን፣ በሰፈራችን፣ በሀገራችን፣ በቤተ ክርስቲያናችን፣ በዓለማቸን እየተፈጸመ ያለወን እግዚአብሔር እየሠራ ያለወን ሚስተዋሉ የበለጠ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

እግዚአብሔር በሥራ ላይ ነው! እንላለን እንጂ ምን እየሠራ እንደ ሆነ ለስንቶቻችን ተገለጠ? መንፈስ የሚለወን መንፈስ ካልገለጠ በስተቀር ለማን ተገልጧል? በልጁ የተተረከው የአብ መንገድ ለሁሉ ቢዘጋጅም ኃይለኞች የሚጠቁት ናት፡፡ በየዘመናት ጨቋኞችን ጨቋኝ ያደረገች - ኃይለኞችን ኃያል ያደረገች - ብርቱዎችን ያበረታች የእግዚአብሔር ጣት ነው፡፡ ለሥራወና ለዓላማው እርሱ ራሱ ጨቋኝ ከሆነ ለዓላማው ከጨከነው የተገኙ ጨቋኞች ከዚህ ኃይል የተገኙ ኃያሎች እግዚአብሔርን ለመገለጥ ቢጨክኑ - በተሰጣቸው ዘመን ላይ ቢበረቱ በእነርሱ እግዚአብሔር ጨኖ እንጂ - በእነርሱ እግዚአብሔር በርትቶ እንጂ ሌላ ትምክህት አናይም፡፡ የእግዚአብሔር የዘመናት ዓላማው ገድሎ ማዳን ሲሆን ይህንንም በፊተኛው ሰው ሞት በኋለኛው ሰው ሕይወትን አኑሮአል፡፡ ፊተኛወን ቤት ሞት ብሎታል ለሞትም ምልክት አድርጎታል፡፡ ኋለኛወን ቤት ሕይወት ብሎታል፡፡ እንግዲያው እግዚአብሔር አስቀድሞ የጨሰወን ሥራ ጊዜ ቢገልጠው ምን አዲስ ነገር አለ? አዲስነቱ ለእኛ ለምንድንበት ነው እንጂ፡፡ ይህንን የእግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያለወን የዘመናት ሐሳቡን ከተጋረደብን የሰወነት ነወር ዘወር ብለን ለቤቱ ምልክት የተደረገወን ልጁን በወስጣቸን በመሞልከት መዳናችንን እንፈጽም፡፡ የአዲስ ዘመን ለወጥ እርግጠኛ ሁኖአልና - አሜን!

እግዚአብሔር ለሰው የሚነው ስንት ነው;

(እ”Å TÖnKÁ)

ስለ እግዚአብሔር መንግሥት - ስለ መንግሥተ ሰማያት መጻፍ ከጀመርን እነሆ፣ ብዙ ቆይተናል፡፡ የተቀባው ብዕራችን ግን አሁንም ለምለም ነው፡፡ የልጆች ብርታት በወራት አይለካም፡፡ ልጆች በሽምግልናም ያፈራሉ፡፡ በእኛም የተሠራወን የሚለካወና ዋጋ የሚሰጠው አብ ብቻ ይሆናል፡፡ እርግጥ ነው በሚልእክታችን የሰወን ራስ ቆጥረን ይህን ያህል ‹‹ፍሬ አፈራን›› ላንል እንችላለን፡፡ መንግሥቱ ሰወን የሚቆጥር ሳይሆን የሚቃንስ ነው፡፡ የሰወን ራስ በመቁጠር እንኳ ከሁሉ እናንሳለን፡፡ ለሰው ራስ ቆጠራ ብናገለግል በእርግጥም ከስረን ነበር፡፡ በወንጌላችን ግን አስቀድመው ለነበሩበት የጥፋት ዓለም ተበላሽተው ወደ እግዚአብሔር ዓለም የተነጠቁት ጥቂት እወነ ተኞችን ስናስብ እጅግ ደስ ይለናል፡፡ በወንጌል ስም ማንንም አናታልልም፡፡ በወንጌል ስም የሰወን ቁስል በሚከ የሚኝ ትርፍ የተረገመ ይሁን፡፡ በክርስቶስ በራሳቸው የቆሙትንና ከምንጫቸው(ከሆዳቸው) የሚጠጡትን መፍጠር በአብ ምክር መገኘት ነው፡፡ ሕዝብን ለሚያዝሉና ለሚያጠቡ ‹‹እረኞች›› ወዮላቸው፡፡ ... የቁጥር ጉዳይ አይደለም፣ አትሳቱ፡፡ መንጋ አንድ አወራ ይመራዋል፡፡ ትልቁ ጉዳይ ከአንድ ወንድ ጋር መጨጸም ነው - እርሱም ክርስቶስ ጌታ!

ከእንግዲህ በልባችሁ ወዳለው ኪዳን ታዩ ዘንድ እንመክራለን፡፡ ማንም በሌሎች የትምህርት ሚደንዘዣ አይደነዝዝም፡፡ የሕይወታችን መጽሐፍ ተከፍቷል፡፡ የታተመውም ማነተም ተፈትቷል፡፡ ይህንንም(በልባችን) ያደረገው በጉ ነው፡፡ አገልጋዮች ይህንን ካልነገሩን የሚሰበሰቡን ለሌላ ድብቅ ዓላማ ነው፡፡ በስንዴ እርሻ ላይ ስንዴና እንክርዳድ አብረው ይበቅሉና አንድ እንግዳ ነገር ይከሰታል፡፡ የሚዝመወና ቶሎ የሚያየው ግን እንክርዳዱ ይሆናል፡፡ በስንዴ - በእወነት እርሻ ላይ እንክርዳድ - ሐሰት ቢረዝም አያስገርምም፡፡ እወሸት ረዥም ነው፣ ግን ሥር የለወም፡፡ በተነቀለ ጊዜም ራሱንም ሆነ የተከተለወን

አያድንም፡ እንደዚህ በሆነ እርሻ ላይ የሚለይ - ለይቶም የሚቃጥል መኪአከ - መኪእከት ግን ይመጣል፡፡ በጉ ከከፈተው መጽሐፍ(ሕይወት) በፊት የሰው ነገር ከፍ ከፍ ብሎ ታይቷል፡፡ በመለጠም የሻረው ይህንን ከፍታ ነበር፡፡

ወገኖች ሆይ፣ መንግሥቱ ከዘር ሁሉ ቢያንስ በፍጻሜው ከዛፎች ሁሉ ሊበልጥ ነው፡፡ ይህም የበለጠው ዛፍ የሰሚይን - ከፍ ከፍ ያሉትን ወፎች(መንግሥታትንና አሕዛብን) ያሳርፋል፡፡ የመንግሥቱ ቅንጣት ዘር ‹‹ትልቁን›› መሬት አበሰበሰ፡፡... የቤተ ክርስቲያን ዝክር ሆዳችንን(መበል ለሆድ ነው፣ ሆድም ለመበል - ሁለቱም በአንድነት እስኪጠፉ) - ነፍሳችንን እንጂ መንፈሳችንን አልመገቡም፡ በሕያው ቃል ሳይሆን በሚጠፉ መበል የተቆዘርነው ለብዙ ጊዜ ነው፡ ሕይወት በሌለውና ዓለምን በሚደግን ሣር ‹‹ወስጣቸውን›› አደለብን፡፡ የሳኦል ሠደቃ የዳዊት መገደያ ነበረ፡፡ ግን አልተገኘም፡ ልጆች የትም አይወሱም፡ ሚደሪያቸውና መኖሪያቸው ከሰው ጋር አይደለም፡ ሄሮድስ ሕፃኑን የፈለገው በነፍስ ከበብ ሁኖ ነው፡ አግኝቶታልን? ሕፃኑ በመንፈስ ከበብ ከአባቱ ጋር ነበርና አላገኘውም፡ ወገኖች ሆይ፣ በሳኦል ሠደቃ ዳዊት ይገኝ ዘንድ አይችልም፡ የእርሱ ስፍራ ሌላ ነበር፡፡ ኪዳኑም ሰማያዊ ነው፡ የአብ የግዛት ናማ የነበረችው መንግሥቱ የሳኦል(የነፍስ ተምሳሊት - ሥጋና ደም) አልነበረችም፡ ዛሬ ልጆችን ለመገደል የተዘጋጁ የእምነት ቤት ሠደቃዎች ብዙ ናቸው፡ ይሁን እንጂ ልጆች በሠደቃው አይገኙም፡ መበላታቸው ከሰማይ የወረደ - የተገለጠ ነው፡ በሳኦል ሠደቃ ዮናታን እንጂ ዳዊት አልተገኘም፡ ዮናታን የሳኦል ልጅ ነው፡ ለባቢሎናዊቷ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ዮናታን ምሳሌ ነው፡ ዮናታን ምንም ዳዊትን እንደ ነፍሱ ቢወድደውም የወደቀው ከሳኦል ጋር ነው፡ ዮናታንን ከሳኦል ቤት ያላስወጣው የዳዊት ፍቅር ነበረው፡ በ‹‹እግዚአብሔር ቤት›› ፍቅር የተባሉ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቤት ያልሆኑ ስንቶች አሉ?... የሳኦል ሠደቃ ለሳኦል ልጆች ነው፡ ዛሬም እንዲሁ ነው፡ ከቤተ ክርስቲያን ሠደቃ የተለየነው የእኛ ስላልሆነ ወይም ለእኛ ስላልተዘጋጀ ነው፡ የልጆች ግብጥ እግዚአብሔር ነው፡ እርሱ በእኛ ራሱን ደግሷል፡፡ ወዶች ሆይ፣ ወንድምን ለመገደል ከተዘጋጀ ሠደቃ(አገልግሎት - ፕሮግራም - ትምህርት...) ታመልጡ ዘንድ ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንጮኽለን፡፡ ይሄ የእውነት መንፈስ የኢየሱስም ምስክር ነው፡፡

ስለ ዘመን - ስፍረ ዘመን የሚጠኑ ብዙ ወንድሞች ጊዜን ሲደምሩ፣ ሲቀንሱና ሲያካፍሉ እስካሁን አሉ፡፡ የእግዚአብሔርን ፕሮግራም በእነርሱ ቀመር አንዴ ሲያቀርቡት በሌላ ጊዜ ሲያርቁት በከንቱ ይደክማሉ፡፡ የሰማይን ዘመን በምድር ዘመን ሊተረጉሙት ሽተው አጓጉል ሳቱ፡፡ በመጽሐፍ የተጠቀሰው ቀን ቀን መሳላቸው፣ ሌሊትም ሌሊት፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ዓላማ በዕድሜአቸው ልክ መተሩት፡፡ የትወልድ ቅሬታዎች ግን በመንግሥት ዕይታ ሞት(ሚዳት) በሆነላቸው ጊዜ በመጀመሪያው ሜጨረሻወን አዩ፡፡ እንደ ልጆች የመጀመሪያ ዘመን አጥኒዎች አይደለንም፡ የሜጨረሻ ዘመን እንደ መንግሥቱ መረዳት ቀን ወይም ልዩ ክስተት ሳይሆን የሰው(የሥጋና የደም) ሜጨረሻና የእግዚአብሔር መለጥ ነው፡ በእኛ መለጥ የጀመረው አብ በሰው ይፈጸማል፡፡ በዚህ ሚለዳ የእግዚአብሔር ልጆች ብርሃን የፍጥረትን ጭጋግ ያስወግዳል፡፡ እነርሱም ዓለም(ዘመን - ዘላለም) ሳይፈጠር ታወቁ፡፡ እግዚአብሔር እነርሱን ባወቀበት ‹‹ጊዜ›› ሁሉ ነበሩ፡፡ እነርሱንም እግዚአብሔር ከዕለታት አንድ ቀን አላወቀምና ከዘመን በፊት ናቸው፡ ከእግዚአብሔር ውጭ የሚኖር እግዚአብሔር የሚያወቀው ነገር ይኖር ይሆን? ሚወቅ መተባበር - መጣበቅ ነውና አይኖርም፡ እንግዲያውስ ዓለም ሳይፈጠር ያወቀን እኛ ከእርሱ ውጭ አይደለንም፡ የእወቀቱ - የመንፈሱ ልጆች ነን፡፡ በእኛም ሆነ በሌላ የሚኖር ዓለም እኛን አያወቀንም፣ ከክርስቶስ ጋር ሕይወታችን በአብ ተሰወሯልና፡፡ ክርስቶስ ሲገለጥ አብረን እንገለጣለን፡፡ ‹‹አብረን›› ሚለት ሁለት ሰዋት ይዘን ሚለት ነው? ይሄ የሃይማኖት ቧልት ነው፡ ራስና አካል አንድ ናቸው፡ ክርስቶስ ራስም አካልም ነው፡ አንዱ በሁሉም ይገለጣል፣ ሁሉም በአንድ ይገለጣሉ፡፡ እርሱ ከሁሉ ጋር ተባዛና አንድ ሆነ፡፡ አንድና አንድ አንድ ነው፡ እርሱ ተካፍሎም ተባዝቶም አንድ ነው፡ አንድ ሲባዛ አንድ፣ አንድ ሲካፈል አንድ አንድ ነው፡ የአንድ ኃይል ትልቅ ነው፡ አንድ ሞተ ሁሉም ሞቱ፡፡ አንድ ኖረ ሁሉም ኖሩ፡፡ የቱንም ያህል ብትቆጥሩ አንድ ነው የምትጨምሩት፡፡ ሁሉን ያበዛው አንድ ነው፡ ሃሌ ሉያ! እግዚአብሔር አንድ ነው፡ ራሱን ግን በእያንዳንዳችን ደሚ - አካፈለ - አበዛና ያው አንድ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሁለት አይደለም፡ አንድ ነው፡ ያለ እኛም ከእኛም ጋር፡፡

የመንፈሱ ልጆች - የዘሩ ዘር - የባሕሪው ልጆች እንደ ሆንን በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ ይሄ ከብር ነው - የሜጨረሻ ሐሴት! ልጅነት የተሰወረ ነው፡ እስሜኤል ከይስሐቅ በፊት ነው እንደ ሰው፡ ነገር ግን አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ መልከ ጼዴቅ በተገናኘው ጊዜ ሌዊ አሥራትን አወጣ፡ እንግዲያውስ እስሜኤል ከይስሐቅ ቀርቶ ከሌዊም በኋላ ነው፡ ቀድሞ የተገለጠ እውነተኛ ወራሽ አይደለም፡ እውነተኛ ልጆች ከሐሰተኛ ልጆች(እስሜኤል ከአብርሃም እንደ ነበረ ሐሰተኛ ልጆችም በሥጋ ተወልደው በቤት ናቸው) በኋላ ቢመጡም አስቀድመው በአብ ወስጥ ናቸው፡ ልጆች ባደጉና በተገለጡ ጊዜ ‹‹ልጆች›› የተባሉ ግን ያልተወለዱ ከአብ ቤት ይወጣሉ፡፡ ከአብ መቅደስ (ከትክክለኛው ከማንነታቸው ያልሆነው) ይወጣል፡፡

ባሕሪው ወለደን፡፡ ከአብ ተወለድን፡፡ ይሄ ተራ ነገር አይደለም፡ ሥጋዊ ትርጉም ስለ ሰጠው ነገሩ ደክሞበን ወይም ቀልሎበን ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ወለደን ስንል ግን አንድ ጥያቄ ይነሣል፡፡ ማንን ለመሆን ተወለድን? አባትና ልጅ ሁለት

ናቸወን? ምናልባት ልጅ እስኪያድግ ይሆናል፡፡ የአንበሳ ልጅ ደቦል ነው፡ የላም ልጅ ጥጃ ነው፡ የበግ ልጅ ግልገል ነው፡ የወሻ ልጅ ቡችላ ነው፡ ወዘተርፈ፡፡ ግን ደቦልም፣ ጥጃም፣ ግልገልም፣ ቡችላም... እስኪያድጉ ነው፡ ካደጉ በኋላ አንበሳ፣ ላም፣ በግ፣ ወሻ... ናቸው፡ የወሻ ልጅ ወሻ ነው፡ የእባብ ልጅ እባብ ነው፡ የጉሜሬ ልጅ ጉሜሬ ነው፡ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ነው፡ ‹‹እግዚአብሔር ከራሱ ሌላ ይወልዳል›› ያለን ርጉም ሃይሜኖት ነው፡ እስልምና፡- ‹‹እግዚአብሔር አይወልድም አይዋለድም...›› ይላል፡፡ እስልምና ‹‹እግዚአብሔር ይወልዳል›› ብሎ ካመነ እግዚአብሔር ከራሱ ሌላ አይወልድም ብሎ ለመቀበል ይገደዳል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እግዚአብሔርን ይወልዳል(ወለደ) ከሚለት አይወልድምን መረጠ፡ ‹‹እግዚአብሔር ይወልዳል ልጅ አለው›› ካለ በኋላ ‹‹ልጆቹ እርሱ አይደሉም፡ ከሚለኝ እምነት ‹‹እግዚአብሔር አይወልድም›› የሚለው እምነት ይጸድቃል፡፡ እግዚአብሔር ከወለደ - ልጅ ካለው ራሱን ነው የወለደው፡ አንድ ሲካፈል አንድ አንድ ነው፣ አንድ ሲባዛ አንድ አንድ ነው ያልናቸሁ ይሄ ነው፡ ደግመን እንላለን፡- እግዚአብሔር ልጅ ካለው ራሱን ነው የወለደው ካለዚያ አልወለደም አይወልድምም፡

ከአብ ተወለድን ሥጋና ደም አልወለደንም፡ ሥጋና ደም የሰወን እንጂ የእግዚአብሔርን የሚያሰብ ነው፡ እርሱ ግለ ሰብ አይደለም፣ ባሕሪይ ነው - ማንነት!

የተወለድንበት ዘር የአብ ልጅ ሆኖ በእኛ አደረ፡፡ እርሱ ያድጋል፡፡ ልጅነትም ግዛት ነው - መንግሥት የሆንነው ነው፡ ዳሩ ግን አልተገለጠም፡ ቢገለጥ ግን ከእርሱ ከራሱ አንሆንም፡ እርሱም በእኛ ራሱን ሆነ፡፡ በሕይወታችን መንግሥቱ ሰላም የሚዛው ይህንን እውነት በተረዳን ቅጽበት ነው፡ ወስጣችን ስለ ምንም ስለ ማንም አይንጫጫም፡ ሰላማችንም ጦርነትን ሁሉ ያሸንፋል፡፡ ልብ በሉ፣ ክርስቶስ ስለ ተዋጋ አላሸነፈም፡ አፉን ባለ መክፈት - በጸጥታ - በአብ መታመን ድል ነሣ፡፡ የቤተ ክርስቲያን፣ የሚስትሪዎች፣ የፕሮግራሞች ... ወግያ፣ ረብሻ፣ ሁከት፣ እንደ ጨረባ መንጫጫት፣ የለቅሶ፣ የዋይታ፣ ያለ መደማመጥ ሰፈር፣ የወስጥ ባዶነት ሚሰረጃ ነው፡ ባዶ ዕቃ ድምፅ አለው፤ በዚህ ዓይነት ሁከት የሚፈታም የሚታሰርም የለም፡ ስሜት ብቻ ነው፡ እግዚአብሔር በወስጣቸን ቀልሎ ማንን መፍታት ማንንስ ማሰር እንችላለን?... እግዚአብሔር በወስጣቸን ቢገዝፍ፣ ከንዱ ቢከብደን፣ አብን በወስጣቸን ፈጽመን ብንቀድሰው፣ ቢነግሥና ቢንሰራፋ... ጠላት የሚበል ነገር ትዝ አይለንም፡ በእግዚአብሔር ዓለም እርሱ የለምና፡፡ ሰይጣን ያለው በሰው ዓለም ነው፡ ከዚህ ዓለም (ከሥጋና ከደም) ከወጣሁ ግን በእግዚአብሔር ዓለም(በሕያው ክርስቶስ) ናችሁና ሰይጣን የለም - ወግያ የለም፡ Peace rules the Kingdom - ሴላህ!

ይሄ የተወለድንበት - የሆንነው - የምንገለጥበት - የምንገዛበት ዓለም ነው፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ መጣ - ወረደ - ተገለጠ፡፡ ይሄ ግዛቱ ነው፡ አብ በሥጋ(በእኛ) አደረ፡፡ ይሄ ነው መንግሥቱ፡፡ መንግሥቱ የእግዚአብሔር ክርስቶስ ነው - ክርስቶስ ልጆች ነው፡ እርሱ የልጆች ልብና ራስ ነው፡ እኔ እነግራችኋለሁ፣ የሰወና የእግዚአብሔር ክርስቶስ እንዳለ፡፡ የሰው ክርስቶስ ማን ነው? የእግዚአብሔርስ ክርስቶስ ማን ነው?... የሰው ክርስቶስ ሰው በትምህርቱ፣ በልማዱ፣ በማንነቱ፣ በምናቡ፣ በእምነቱ... የፈጠረው ‹‹ቅርጽ›› ነው፡ ሰው የሰወን ክርስቶስ በአንድ ሰሚይ ጥግ ግለ ሰብ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ ይሄ የሰው ክርስቶስ የሌለና በሰው የተፈጠረ ተረት ነው፡ አያድንም፡ ሐሰት ነው፡ ትልቁም የቤተ ክርስቲያን ድርሰት ይሄ ነው፡ በዚህ ስንቱ ታወረ ስንቱ በመንፈስ ጀምሮ በሥጋ ጨረሰ?

የእግዚአብሔር ክርስቶስ ሕያው ነው፡ እርሱ ሕልወናችን ነው፡ ያለ እርሱ የለንም፡ ከእኛ በላይ ነው፡ ከእኛ በታች ነው፡ በእኛ ወስጥ ነው፡ በእኛ ዙሪያ ነው፡ እርሱ መንፈስ ነው፡ በእኛ ነው፡ ከእኛ ጋር ነው፡ ለእኛ ነው፡ ከእኛ ነው፡ እኛ ነው፡ የሚቤዥ ንጉሥ ነው፡ አብ ፍጥረትን ሁሉ በመንፈስ የሚዛበት ሜዕከል ክርስቶስ ጌታ ነው፡

በሥጋ የሚታወቅ፣ በሥጋ የሚሰበክ፣ በሥጋ ሥርዓት የሚለገል፣ ‹‹በሥጋ ይመጣል›› ተብሎ የሚጠበቅ፣ በሥጋ የሚመላክ የሰው ክርስቶስ ልጆች አያወቁትም፡ እርሱ በእግዚአብሔር ዓለም የሌለ ‹‹ፍጡር›› ብቻ ነው፡ ስለዚህኛው ክርስቶስ እንዲህ በሚለታችን የሚደድ ጎበዝ ይኖር ይሆናል፡፡ በእርግጥ ስለ ሌለውና ስለሚያድነው የሰው ክርስቶስ ብለው ክርስቶስ ልጆችን - ክርስቶስ ወንድሞችን የጠሉ ስንቶች ናቸው? የሚርመው ግን ሃይሜኖት የራሱን ክርስቶስ በእግዚአብሔር መቅደስ ማነገሡ ነው፡ ያም ሐሰተኛ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መቅደስ - ‹‹እኔ እግዚአብሔር ነኝ›› አለ፡፡

ወንድሞች ሆይ፣ እግዚአብሔር በገለጠው በዚህ የጌታ ቀን ክርስቶስን አስቀድመን እንዳወቅነው ላናወቀው ተቆርጧል፡፡ ከሰንበት ትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ድረስ ክርስቶስን የተማርንበትና ያወቅንበት መረዳት መላወጥ አለበት፡፡ በእግዚአብሔር ቀን ክርስቶስ በራልን፡፡ ታሪካዊውና ኢየሱስን ለማወቅ መድከማችን በቃን፡፡ አሁን በእኛ ሳይኖር ‹‹ይመጣል›› የሚለውም አናስበው፡ እርሱ - የእግዚአብሔር ክርስቶስ ተቃዋሚው ነውና በዚህ በእግዚአብሔር ቀን ልናስወጣው ያስፈልጋል፡፡ ይሄ የትምህርት አጋንንት ካልወጣልን ልጅነትንም ሆነ መንግሥቱን ልናወቅ አይቻለንም፡

ክርስቶስ የአካሉ ሕልወና፣ ሕይወትና ማንነት እንጂ አንድ ግለ ሰብ ከቶወንም አይደለም። ክርስቶስ የምንኖረው - የምንራመደው - ሕይወት ነው። ወገኖች ሆይ፣ ከዚያ ሐሰተኛው ክርስቶስ ትድኑ ዘንድ ይህ ሚልአክ ወደ እናንተ ተልኳል።

ዳሩ ግን ሚልአኩን የምታዩበትና የምትረዱበት ስፍራ የትኛውም ስፍራ እንዳልሆነ ልታወቁ ይገባችኋል። የት ሁናችሁ ነው ይህንን ሚልአክ የምትሰሙት? ‹‹ሰው ሊናገር የሚገባውንና የሚይናገረውን ቃል›› ለሚሰሙት ከሰው መውጣት ያስፈልጋል። የእግዚአብሔርን ነገር ሚሰሙት ያለብን ከሰው ተለይተን ነው። ወገኖች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር በማንታችሁ መቅዳት ከፈለጋችሁ አሁን ካላችሁበት ሰፈር ወጡ። በጌታ ቀን መንፈስ ያመጣውን ለሞት ከአሮጌው ትምህርት ልንለይ ተገብቶናል። መረዳታችሁ በማንታችሁ ከሚወስን ይልቅ መረዳታችሁ ማንታችሁን ይወስናል። እንደ እግዚአብሔር ልጆች የቅርቡን አይታችሁ በምትረዱት ነገር የተወሰናችሁ ወስኖች አይደላችሁም። በሰማዊ ስፍራ ስለ እናንተ የተወሰነ የአብ ምክርና ጠልቃችሁ የምታዩት ፈቃዱ ናችሁ።

ልጅ እንዴት ነው ራሱን በእግዚአብሔር የሚያው? በልጅነት መንፈሳዊ ብሽታ የለም። ስለ እርሱም የሚያወቀው ነገር የለም። ክርስቶስ በሌሊት ከኒቆዲሞስ ጋር ሲናገር በምድር እንዳለ ሳይሆን በሰሚይ እንደሚኖር ነበር(ዮሐ.3÷13)። እርሱ ከሰሚይ የመጣ ነበርና በሰሚይ ይኖር ነበር። ሰሚይም ስፍራ ሳይሆን የተገለጠበትና የሚኖርበት ማንነት እንደ ነበረ የታወቀ ነው። ልጅ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ሲነጋገር እርሷ እንዳወቀችው እንደ ነቢይ ሳይሆን ራሱን ያየው እንደ ሕይወት ውኃ ምንጭ ነው። በውጭ ለሚያየውና ለሚረዳው ግን ከሰው(ነት) የተለየ አይመስልም። ልጅ ግን ምን ጊዜም ወስጠኛ እንጂ ወጪ አይመላከትም አልመሰከረምም።

የእግዚአብሔር ምክር - ዓላማ - ፕሮግራም በመንፈስ ቅዱስ በዝርዝር ስንረዳው ‹‹ሕይወት ነው - ክርስትና ነው›› ብለን አሁን የተቀበልነው ምልልስ ፈጽሞ ያረጅና ወራጅ ይሆናል። የመንግሥቱ ሚሪሐ ግብር በሕይወት - በአካሄድ(በትምህርት ሳይሆን) መተርነም ስንጀምር አብ ስለ እኛ ያለው ፈቃድ አሁን የሆነነው ወይም በሥጋ የምንኖረው በፍጹም አይደለም። እግዚአብሔር ያለው - የመከረው - በልባችን የጻፈው - የከፈተውና የተመላከተው ፈቃዱ ነን። በአፄጁ በመንግሥቱ መገለጥ ስለ ልጆች የተባለው መሉ በመሉ እርሱ ነው።

አብ ሁሉን አዲስ ያደርጋል። የተወለድንበት ዘር የሚጠፉ ሳይሆን የሚያድግ እንደ ሆነ እወነት ነው። ዘር ራሱን በአንድ ጊዜ ይገልጣል? አስቀድሞ ቡቃያ ነው፣ ኋላም ዛላ። ትግሉ በመጀመሪያ ከአፈር ጋር ነው። ዘር በዚያ ይበሰብሳል። ራሱን (የበሰበሰወን) በልቶ ይበቅላል። የበሰበሰበት አፈርም መበሉ ነው። ይሄ ተአምር ነው። ሕይወት ከበሰበሰው ነገር ይነሣል። የበሰበሰው የእንቁላል ፕሮቲን ጫጩት ይሆናል። ተደነቁ!... ዘር ሚሬትን ሰንጥቆ ይወጣል። ሞት ወደ ወጭ ገፈተረው። የትንሣኤው ኃይል አስደናቂ ነው። ዘር ከበቀለም በኋላ ከወጭ ሁኔታዎች ጋር ትግል አለበት። ነፋስ፣ ብርድ፣ ፀሐይ፣ መቀት፣ ድርቅ፣ ዝናብ፣ ፍጥረት... ሁሉ ይታገለዋል። አካባቢው ይጨቁነዋል። ... ግን ተቋቁሞ ያድጋል። ይበረታል - ይገዝፋል - ያሳርፋል - ጥላና መበል ይሆናል። በእኛ የተዘራው ዘር (መላኮት ዘር) እንዲህ ነው።

ከዛፍ የተገኘው ዘር ተዘርቶ ባደገ ጊዜ ያ ዛፍ ነው። የማነ ወይም የሌላ ዘር ተመልሶ ማነ ወይም ያ ሌላ ዘር መሆኑ ተፈጥሮ እንኳ የሚሞከረው አይደለምን?... በእኛ የተዘራው - የተዘራብን ወይም የተወለድንበት መላኮታዊ የአብ አብራክ(ዘር) በእርሱ በራሱ ቀን የምንሆነው ነው። እርሱ (እንደ ራሱ አሠራር) በእኛ ተመልሶ አብ ይሆናል። እርሱ በእያንዳንዳችን አብን ይሞላል። በፍጻሜ አብ በእኛ አዳኝ፣ ሜሐሪ፣ ፍቅርና የሁሉ ሜከኪያ ነው። ‹‹ምርጥ ዘር›› ዘር የሚዳቀልና የብዙ ትዕግሥት ውጤት ለመሆኑ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። በምርጥ ዘር ወስጥ የቀደመት ‹‹ዘሮች›› ማንነት በብዙ አይገኝም። በሚገባን ሁኔታ የሁኔታዎች - የምት ጥራትና ብዛት - የማንነትም ለወጥ ይካሄዳል። ይሄ የሰው ጥበብ ነው - ለመኖር በሚያደርገው ተጋድሎ የፈጠረው።

የእግዚአብሔር ጥበብ ግን ምንኛ ታላቅ ነው? የዚህ ጥበብ ልጆች ብቻ ጥበብን አወቁ። ስንዴ መልሶ ዘር ሆኖ ከሞተ በኋላ ስንዴ ሊሆን የገበሬው ጥበብ፣ ፈቃድና ፍጻሜ ነው። በመጀመሪያ የነበረ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ - እግዚአብሔር የነበረ እርሱ(በሚሬት ወስጥ) ዘር ሆነ። የእግዚአብሔር ክርስቶስ በእኛ የተዘራ አብ ዘር እንደ ሆነ በጌታ ልብ ካልሆነ ሌላ የምናወቅበት ጥበብ የለም። እኛ የሕያው እግዚአብሔር ሕያው እርሻ አይደለንምን? በእርግጥ እግዚአብሔር በእኛ ራሱን ዘርቶ - ክርስቶስ በእኛ ተዘርቶና ከቀደመው ዘር ጋር ተዳቅሎ ‹‹ምርጥ ዘር›› አይደለም። እርሱ የበቀለው የቀደመው በሌለበት ነው። ያ በእርሱ ተገደለ - በሰበሰ። ‹‹ክርስቶስ በእኛ›› ስንል የቀደመው ዘር በሌለበት ነው - የተባረከ ይሁን!

የተዘራብን አብ - ልጅ ዘር በሰሚይ፣ በምድርና ከምድር በታች ሁሉ ያድጋል። በእርሱ የሚይሞላ ስፍራ የለም። በእርሱም የሚይድንና የሚጠቀለል ፍጥረት የለም። ይሄ የእግዚአብሔር ታላቁ ሚርሐ ግብር ጅማሬውና መለጡ በእኛ መደረጉ

አያስገርምምን? የአብ ምርጫ እንዴት የተባረከ ነው! ዓለም ሁሉ በጥቂቶች ላይ በወጣው ፀሐይ ለእግዚአብሔር ይግላል፡፡ ለስሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ የወሰደው ለአሕዛብ ክብር ነው፡ ‹‹ምሕረቱ በምህረት ዕቃዎች ሊገለጥ ስለ ተወሰነ ነው›› በሉ፡፡ ከዚህም የተለየ ስለ መመረጣቸሁ ‹‹መገለጥ›› አይሁንላችሁ፡፡ ያዕቆብ ስለ ራሱ ብቻ ሳይሆን ስለ ኤሳውም ተመርጧል፡፡ የእስማኤል በረከት በይስሐቅ መሥዋዕት ጸና፡፡ ምድር በአባት(በአብርሃም) እና በዘሩ ይባረካል፡፡ አብ ዘሩን - የገዛ ራሱን በሠዋ ጊዜ ዓለም ዳነች፡፡ የእስማኤል ልጆች ቤዛ የይስሐቅ ልጆች ናቸው፡ ሁሉም አዎን፣ ሁሉም ያለ መጽሐፍ፣ ያለ ሃይማኖ፣ ያለ ዘር፣ ያለ ቀለም፣ ያለ ነገድ... በአንድ ሕያው ድንኳን ለዘላለም እግዚአብሔር ይለወጣሉ፡፡ ያም ድንኳን ክርስቶስ ልጆች(ነው) ናቸው፡፡

ክርስቶስ - ፍጥረት ሚፈፅያ ዛፍ በእኛ አብ እስከ ወሰነው እስከ ራሱ ስፍራ ያድጋል፡፡ ትልቅ ዛፍ እስኪሆን ያድጋል፡፡ ግን ዛፍ በዛፍ ላይ ያድጋልን? የለም፡፡ እርሱ ብቻውን ዛፍ ነው፡፡ ክርስቶስ በእኛ ብቻውን ነው - ሃሌ ሉያ! ሌላ ራስ - ሌላ እኔ የለም፡፡ ሰው የተከለከለውን ዛፍ ከመበላቱ በፊት ሰው(ነቱ) የተሰወረ ነበረ፡፡ ያንን ፍሬ በላና ሰውነቱን አገኘ፡፡ ሰው በዚያ ዛፍ ሰው ሆነ፡፡ አሁን ግን ክርስቶስ በእኛ ያለ ሰው ዛፍ ይሆን ዘንድ ተወስኗል፡፡ ክርስቶስ ሰውነት የሌለበት የእግዚአብሔር ሥርዓት ነው፡፡

በልጅነት ሰሚይ የምናየው ሟለት የምንረዳው አስቀድመን ካወቅነው በፍጹም የተለየ ነው፡፡ የቀደመው ሰሚይ(ሚዳት) ሟልፍ አለበት ወደዚህኛው ለመድረስ፡፡ ከልጅነት ሰሚያት ውጭ እስካሁን ያወቅነው ብዙ ነገር አሮጌ ነው፡፡ የሚዳት - የጥቅሶች የእግዚአብሔር እወቀትና ጥበብ አይደለም፡፡ በልጅነት የደረስንበት መገለጥ ፈጽሞ ልዩ ነው፡፡ ልጅነት የካህናትና የነገሥታት መንግሥት ነው፡፡ መንግሥትም የአብ ግዛት ነው፡፡ የትርጉም ብዝኃ በማንም ላይ አይኑር፡፡ ካህናትና ነገሥታት ልጅነት ነው፡፡ ልጅነት መንግሥት ነው፡፡ ካህናትና ነገሥታት መንግሥት ነው፡፡ ልጅነት የተደረግነው ከዚህ ያነሰ አይደለም፡፡ ልጅ ባለበት እኛ ደግሞ ነን፡፡ ራሱንም ስለ እኛ አከበረ፡፡ መንግሥቱ ማንነት ነው - ሕልወና - አዲሱ ስብዕና ነው፡፡ ነገሥትና ካህናትም ሟለት የተወረሰ ማንነት ነው፡፡

ስላቀለልነው ብቻ የቀለለብን አንድ እውነት አለ፡፡ ምሥጠሩን ግን በመገፈስ ከሚመጣነው ዕድላችንን ሁሉ የወሰነ ነው፡፡ እስኪ እናንብበው - ‹‹ለተቀበሉት ሁሉ ግን፣ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፣ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም››(ዮሐ.1÷12-13)፡፡

ይሄ ለብዙ ወንድሞች የማንም አእምሮ ሊረዳው የሚቻል ሜዳ ላይ ያለ ወንጌል ነው፡፡ በመሠረቱ ይሄ የመጽሐፍ ከፍል ‹‹ገብቶኛል›› የሚል ከተገኘ እንደ ገባው የሚታወቀው ከትምህርቱና ከአካሄዱ ነው፡፡ መጽሐፍን በሥጋና በደም መገለጥ ያነበብንበት ዘመን የዚህም ሆነ የሌላው እውነት አካሉ ደብዛዛ ነው፡፡ የሚይለወጥ - የሚያድን ነው፡፡ እውነቱ እውነት ሁኖ ሳለ የሚይጨበጥ አድርጎታል የእስከ ዛሬው ትምህርት፡፡ መገለጡ እውነት ነው - ኮንክሪት ነው፡፡ እርግጠኛና ጽኑ ነው፡፡ እውነቱ - ‹‹ይሆኑ ዘንድ›› ይላልና፡፡

ቃል ሥጋ እንጂ ትምህርት፣ ደንብ፣ አንቀጽ፣ ጥቅስ፣ መጽሐፍ ... እንዳልሆነ ሁሉ በእኛም ከሥጋ - ከማንነት ውጭ ሌላ ሊሆን አልቻለም፡፡ እኛ በሃይማኖት ጨለማ አደረግነው እንጂ ቃል ከሥጋ ውጭ የሆነው የለም፡፡ የሆነ ቢመስል እንኳ ምሳሌ ነው - ጥላ ነው፡፡ መንግሥቱ መሆንን - መደረግን ይነግረናል ያንኑ ያደርገናል፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ›› የሰሚያት ብይን ነው፡፡ በእግዚአብሔር ከመሆን - ከመደረግ - ከሟጸም ሌላ እንዳለ ያወቅንበት እወቀት የሥጋና የደም ነው - ባዶ ሃይማኖት፡፡

‹‹ልጆች እንሆን ዘንድ›› ከእግዚአብሔር ተወለድን፡፡ መላኮታዊ ዘር - የሕይወቱ(የማንነቱ) ‹‹ኢሴንስ›› በሥጋ ተገለጠ፡፡ በመገፈስ ሥጋ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር የነበረው ቃል በሥጋ አደረ፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ሰው ሆነ›› ስንላችሁ እግዚአብሔር ሰው በእግዚአብሔር ተገለጠ - ወረደ - መጣ ሟለታችን ነው፡፡ ይሄ ነው ፍጹም የእግዚአብሔር መገለጥ፡፡ እግዚአብሔር በሥጋ መገለጡ ግን ከእነዚያ አንዱ ነው አይባልም፡፡ እነዚያ የተገለጠባቸው ዓይነቶችና ጎዳናዎች የዚህ የሟጩሻው (በሥጋ የመገለጡ) ምሳሌና ጥላ ናቸው፡፡ እርሱም እኛ የምንሆነውን ሆነ፡፡ በልጅነት የምንደርስበትን - የምንሆነውን ገለጠ፡፡ እርሱ ቀዳሚ(መንገድ ጠራጊ) ነው፡፡ በእርሱ የተወሰነልንን - የተለካልንን - በእግዚአብሔር የጸደቀልንን - የሟከበቀን ክብር፣ ስፍራ፣ ማንነት አየን፡፡ በክርስቶስ በመንግሥቱ መርሕ የበራልን እውነት የሆነው፣ እየሆንን ያለነውና የምንሆነው ነው፡፡ በእግዚአብሔር እግዚአብሔር ሰው - ክርስቶስ ልጆች ከምንሆንበት ያነሰ ሚዳት አይሠራም፡፡ እርሱም ነው ኃጢኣት ሟለት፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሰሚያት ልጆች ዘንድ እግዚአብሔርን የሚይለካ - እግዚአብሔርን የሚገልጥ - እግዚአብሔርን የሚይመጥን ... ነገር ሁሉ ነው ኃጢኣት ሟለት፡፡

የእግዚአብሔር ዓላማ የመለጥ ዓላማ ነው፡ መለጠም ያለ ሥጋ አይደለም፡ አምላክና አባት በሥጋ የተገለጠበት ምሥጢር ነው ያለ ጥርጥር ታላቅ የተባለው ምሥጢር፡፡ መለኮት - መለኮታዊው ባሕሪይ - መለኮታዊው ማንነት በሥጋ ተናገረ - በሥጋ አደረ - በሥጋ መጣ - ሥጋ ሆነ፡፡ የመጀመሪያው መጨረሻ መለኮት በሥጋ ሆኖ መለኮታዊነትን መግለጥ እንደ ሆነ በሁላችን ዘንድ የታወቀ ይሁን፡፡ ከዚህ ወድያም እግዚአብሔር የተሰወረ - የራቀ አይደለም፡ መለኮት - መንፈስ - አብ ሁሉ ነው፡ በሁሉ ይሆናል፡፡ መለኮት ራሱን ወደ ሥጋ የለወጠበት ምሥጢር የምሥጢሮች ሁሉ ምሥጢር አይደለምን?

የዚህም ምሥጢር አለ መበራት ለብዙዎች ራሳቸው በፈጠሩት ትምህርትና ሃይማኖት ጭቃ ወስጥ ሰጥመው የሚሰቡበትን ገመድ ከላይ ይጠባበቃሉ፡፡ ለዚህም የወሰጣቸው መቃተት ምስክር ነው፡ የእግዚአብሔርን ዓላማ በመንፈስ ሞት ከቻልን ምሥጢሩ የምንፈራው - ‹‹አዋቂ›› የምንጠይቅለት ምሥጢር አይሆንም፡ ምሥጢሩ የተገለጠ ምሥጢር ነው፡ መለኮት - አብ - ቃል - መንፈስ በሥጋ መጣ፡ በሰውነት ወረደ፡፡ ከርስቶስም እግዚአብሔር በሥጋ ነው፡ እግዚአብሔር አባትም ልጅም የሆነበት ምሥጢሩ ሩቅነቱ - ስወርነቱ ለሃይማኖት - ለሥጋና ለደም አእምሮ ብቻ ቢሆን ነው፡

እግዚአብሔር አባትና ልጅ የሆነበት ምሥጢር ግብ - ፍጻሜ አለው፡ እግዚአብሔር ልጅ(ሥጋ) ሆኖ የተገለጠበት ምሥጢር የዋነኛ ዓላማና ዕቅዱ ምሳሌ - ቀዳሚ ነው፡ ፍጻሜው በከርስቶስ ብዙ ልጆች ናቸው፡ በጌታ ቀን በመንፈስ ምክር በእግዚአብሔር ከእግዚአብሔር የተወለዱት የሚደርሱበትና የሚሆኑት ስፍራና ማንነት ትክክለኛ መገለጫና ምሳሌው እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠበት ልክ ነው፡ እርሱ ብዙ ልጆችን በመክራ ወደ ክብር አመጣ፡ መከራው ሲፈጸም ክብሩ ነጋ፡፡ የጣር ሌሊት የደኅንነትን ቀን አስከተለ፡፡ ስለዚህ ከርስቶስን እናየዋለን፡፡ በየት? በእኛ ሞልቶ፡፡ ለዘመናት የተሰወረውና አሁን የተገለጠው ምሥጢር የክብር ተስፋ ያለው ከርስቶስ በእኛ ዘመን መኖሩ ነው፡ ይሄም የእግዚአብሔር ከርስቶስ በእኛ ከርስቶስ ልጅ ነው፡ ምን ማለት ነው? በእኛ የተወለደው ልጅነት ከከርስቶስ ሌላ አይደለም፡ በራሱ አንድን አዲስ ሰው ፈጥሯልና፡፡ አንድ ከርስቶስ(ልጅ) በሁላችን እኛ ነው፡

‹‹እግዚአብሔርንም የመሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፡ በሥጋ የተገለጠ ... ለመላእክት የታየ….››(1ጢሞ.3÷16) መንፈስ በሥጋ የተገለጠበት አደራረጉ ለመላእክት ሳይቀር የተገለጠበት ድንቅ ነው፡ እግዚአብሔር ለመላእክት የታየው በሥጋ ነው፡ መላእክት ምንም መናፍስት ቢሆኑ በመታየት ከበብ ናቸው፡ የመላእክት ሥርዓት የሰው ሥርዓት ነው፡ የመላእክት ሥርዓት ብሉይ ነው፡ መላእክትን በልጅነት በመግሥቱም ሚዳት ካልተረዳነው ከምድር ነው - ታችኛው ስፍራ፡፡ የመላእክት ሥርዓት ከእግዚአብሔር ሥርዓት ለየቅል ነው፡ የእግዚአብሔር ሥርዓት ልጅ ነው፡ ልጅም እግዚአብሔር በሥጋ ነው፡ አብ ለዓለም ራሱን የገለጠው እንዲህ ነው፡

እግዚአብሔር - መንፈስ - መለኮት ስለ ፍጥረት እንደ ሆነው ለመሆን ነው የተወለድነው፡ ይሄ ማለት ታሪካዊውን ኢየሱስን ለመሆን ማለት አይደለም፡ እርሱን በሥጋ አናወቀውም፡ ኢየሱስ ግን ከርስቶስ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ሥጋ በሆነበት - በከርስቶስ ወደ አብ ሚደጋችን የእግዚአብሔር ፈቃድ የተገለጠም ዓላማው እንደ ሆነ ወዶች ሆይ ታወቁ ዘንድ ንቁ፡፡ በቤተ ክርስቲያንና በክርስትና ስም እየተጫወትነው ያለው መንፈሳዊ ቁማር ይበቃናል፡፡ እግዚአብሔር አባት የሠራውና የፈጠረው - ያደረገውም ከፍታ ስንረግጥ ያደረገንን ከማን - ራሱን ከመሰል የተለየ ማንነት አይኖረንም፡ እርሱ ብቻውን በሁሉ ይኖራል፡ በሰው(በፍጥረት) ሁሉ ያለ ሰው(ሰው በሌለበት) ይገኛል፡፡ ፈጣሪ እንጂ የተፈጠረው ይሰወራል፡፡ ፈጣሪ ግን በተፈጠረው መኖሩና መገለጡ ነው የድንቆች ድንቅ - ይህም የሚጨረሻው ክብር ነው!

ለዚህ ስፍራ ከአብ በቀር ምንም አልመረጠንም፡ እኛ ከርስቶስን የመረጥነው ወይም የተቀበልነው አይደለም፡ ሰዎች፡ - ‹‹ከርስቶስን ምርጫዬ አደረግሁት - እንደ ግል አዳኜም ተቀበልኩት›› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ይሄ ከባቢሎን ጠቅ የጋትነው መርዝ ነው፡ ፈቃዳችን እንዳዳነን አደንዝዘው ነገሩን፡፡ አብ ከገለጠለት በቀር ወልድን ያወቀ የለም፡ ወልድም ከገለጠለት በቀር አብን ያወቀ የለም፡ ከርስቶስ መረጠን(ዮሐ.15÷16) እንጂ እኛ አልመረጥነውም፡ ፈልጎ አገኘን እንጂ አላገኘነውም፡ ከመዶ በጎች አንዱ በጠፋ ጊዜ እረኛውን ፈልጎ ያገኘው በጉ አይደለም፡ እውነቱ የዚህ ተቃራኒ ነው፡ አንድ ድሪም በጠፋ ጊዜ መበራት አብርታ የፈለገችው የድሪሙ ባለ ቤት ናት፡፡ ሰው እግዚአብሔርን ያወቅ፣ ይፈልግና ይድን ዘንድ ምርጫ የለውም፡ እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ምርጫ ይጠናቀቃሉ፡፡

መለኮት በሥጋ የልጅነት አምላያ የክብርም ማንነት ከሆነ ሃይማኖት አልወለደንም፣ አንዳችም አላደረገልንም፡ የሃይማኖት ልጆች - የጨገፉ ልጆች አይደሉምን; ሥርዓት አልወለደንም፡ ትምህርት አልወለደንም፡ በአንድነት ፎክን ስንናገር÷ ወገኖች ሆይ፣ ሥጋና ደም ግለ ሰብ አይደለም፡ ጎረቤቶቻችን ወይም በአንድ ሃይማኖት ጥላ ሥር የተሰባሰቡ ወይም ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች አይደሉም፡ ሥጋና ደም በሁሉ የተገኘ ባሕሪይ - ማንነት ነው፡ በእግዚአብሔር በሁሉ በሞላ ጊዜ ከሁሉ የሚወገድ - የሚታረደውም የሰባ ፊሪዳ እርሱ ነው እንደ መንፈስ ምክር፡፡ የሚይጠፋው ዘር በእኛ ሥጋ በሆነ - ባደረ ጊዜ ከዚህ ከአሮጌው ማንነት ተዋጀን፡፡ የባሕሪው ልጆች ነንና የጉዲፈቻ ልጆች አይደለንም፡ አብ እያንዳንዳችንን ከሌላ ቦታ አንሥቶ ቤቱ ካሉት

ጋር አልቀላቀለንም። በእርግጥ እንደዚያ ኮብላይ ልጅ ጠፍተን ነበር። መጀመሪያችን ግን እርሱ ነው ምንም በገዛ መንገዳችን እንድንሄድ ቢተወንም። ከእርሱ ተገኝን፣ ከእርሱም ዘንድ በተገኘ <<ድርሻ>> ለጥቂት ጊዜ ኮበለልን። ነገር ግን ያ ድርሻ ሲያልቅ ወደ ቤታችን - ወደ አብ ስቦን ተመለስን። ወዳልነበርንበት አልመጣንም። የሚበለው ጥፋት - ሞት - ኃጢአት ሳይኖር ነበርን። ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ዘንድ ነን። አሁን ላለንበትና በጌታም ቀን ለምንሆነው የታወቅነውና የተወሰንነው ያኔ ነው - በእግዚአብሔር ልብ በነበረው ቀን - ሃሌ ሉያ!

ዘፍ.15÷2-4 - <<ቁ.2 አብራምም÷ አቤቱ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ምንን ትሰጠኛለህ? እኔም ያለ ልጅ እሄዳለሁ፣ የቤቴም መጋቢ የደማስቆ ሰው ይህ ኤሊዔዘር ነው አለ። ቁ.3÷ አብራምም - ለእኔ ዘር አልሰጠኸኝም፣ እነሆም በቤቴ የተወለደ ሰው ይወርሰኛል አለ። እነሆም፣ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል መጣለት - ይህ አይወርስህም፣ ነገር ግን ከጕልበትህ የሚወጣው ይወርስሃል።>>

ኤልዔዘር ከአብርሃም ሳይሆን በአብርሃም ቤት የተወለደ ነው። የአብርሃም ቤት የአብርሃም ዕድገት፣ የሚለወጥ ሕይወትና ልምምድ ሊሆን ይችላል። አብርሃምም ይሁን ማንም ከዕድገቱ፣ አሁን ካለበት ሕይወቱ፣ እምነቱና ልምምዱ እንደሚበልጥ ያወቁ ይሆን? አብርሃምና ቤቱ ሚለት እምነቱ፣ ሥርዓቱ፣ ባሕሉ፣ ኑሮው፣ አገልግሎቱ... ሁለት መሆናቸውን ሞት ትችላላችሁን?... በአብርሃም ቤት ሚለት በእምነቱ፣ በሥርዓቱ፣ በባሕሉ፣ በኑሮው፣ በአገልግሎቱ... የተወለደ የአብርሃም ግን የዘሩ(የአብራኩ) ልጅ ያልሆነ ይወርሳል ሚለት ሐሰት ነበረ። በአብርሃም(በእምነት) ቤት የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች ግን ያልሆኑ ኤልዔዘሮች ይኖሩ እንደሁ እንጂ አይወርሱም። ለመወረስ መወለድ ያስፈልጋል። አብራም - <<ይወርሰኛል>> ሲል እግዚአብሔር ግን - <<አይወርስህም>> አለው።

የእምነት ቤት ልጆች አይወርሱም - በልጅነት አይገለጠም - አባት አይሆኑም። ወራሾች እነማን ናቸው? የዘሩ - የባሕሪው - የማንነቱ - የእርሱነቱ ልጆች ናቸው የሚወርሱት። ይሄ የሰውኛ ሚዳት (አእምሮ) የሚፈነዳ ሊሆን ይችል ይሆናል። ሰው(ሥጋና ደም) እግዚአብሔርን ማሸብ አይችልም። አያወቅምም። እግዚአብሔር ከበራልን ብቻ እናወቀዋለን። ሰው እስከ ዛሬ ዋሸ። ከእንግዲህ በቃ። በክርስቶስ መገለጥ ለማንም መዋሸት አይሆንለትም። እውሸትም ዘመን ነበረው። አሁን ግን ተፈጸመ። በዚያ ዘመን የማናውቀውን አገለገልን። ከዘሙ ጋርም አብረን ዋሸን። ከእንግዲህ ግን ሌሎች ስለ ክርስቶስ የተናገሩንን የምንናገርበት - የምስተጋባበት ጊዜ ላይ አይደለንም። በእኛ እርሱ ሚሉና ፍጹም መገለጥ ነው። ሃይማኖት ክርስቶስ በአየር - ከእኛ ውጭ እንደ ተገለጠና እንደሚገለጥ የነገረን ትወፊቱ ይበቃናል። ስለዚህ ከእንግዲህ ከማንነታችን - ከመዘገባችን - ከአዲስ ኪዳን - ከልባችን እንናገራለን። ይህ መዘገብ በዚህ ሸክላ ወስጥ አለና! እግዚአብሔር አባታችን መካከለኛውን አስወገደው። ከመጋረጃው ወዲያ ያለው እርግጠኛና ጽኑ ነው። መጋረጃውም እግዚአብሔርን የሸፈነውና የጋረደው ሥጋ ነው - ሉሲፈር። አሁን ግን መልክ ጴጴቅ ሰንጥቆ ገብቷል። ፊት ለፊት እናየዋለን - እናወቀዋለን - እንተባበረዋለን።

ለብዙዎቻችን በልጅነት የተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ሐሳብና ምሥክር ገና አልገባንም። ለእርሱም ሥጋዊ ትርጉም ሰጠው። የሩቅ ተስፋና የሚይጨበጥ ነገር አደረግነው። ጽኑና እርግጠኛው ነገር በትምህርት መዳራት አደበዘዝነው። ምናልባት ስለ ልጅነት፡ - <<አወቀናል፣ አወቀንም እያስተማርን ነው።>> ግን አልተገለጠልንም። ልጅነት በገዛ ዘሙ ሲገለጥ እግዚአብሔር በሥጋ መሆኑ እርግጠኛ ነው። ምን እንደምንሆን ገና አይገለጥ እንጂ አልታወቀም አይባልም። ግን ይሄ እርግጠኝነት(reality) ሲገለጥ እግዚአብሔርን ከመምሰል - እግዚአብሔርን በሥጋ ከመሆን ሌላ አይደለም። በሚቀጥሉ ዘመናት ከዚህ ያነሰ ነገር አይሠራም። በተዘጋጀው ቀን ግን የጸጋው ባለ ጠግነት በሁሉ ላይ ይበራል። የቀኑም ፀሐይ ሁሉን ለደኅንነት ያደምቃል። እግዚአብሔር አንድ መቅመር አስምሯል። የመቅሙ አንድ ጫፍ አልፋ ሲሆን ሌላኛው አሜጋ ነው። ሁሉም ፍጥረት በዚህ መቅመር ይገባ ዘንድ ይሄ ሕያው መቅመር በሥጋ መጣና ሁሉንም አዳነ። ስለ ሁሉ ስለ ሞቱም ሁሉም ሞቱ። የተነሣውም ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ሁሉ ነው። ይህም ታላቅ ጅማሬ ስለ ሁሉ በእያንዳንዱ ተራ ይፈጸማል።

እንግዲህ ገልጠን በምናገረው በዚህ ታላቅ እውነት ራሳችንን ወደምንለካበት መረዳት ወይም ስፍራ ሚመጣት አለብን። እግዚአብሔር ለአብርሃም ዋጋህ ታላቅ ነው። በአብርሃም ለሁሉም መገሩ ነበር። እግዚአብሔር የሰው ዋጋ ነው። ሰው ነው ሰውን ያረከሰው። በእግዚአብሔር ልብ ያለው ወድ ዋጋ ሰው ይሁን እንጂ ሰው ራሱን ከራሱ ጋር ሲያስተያይ ራሱን በእንስሳ መሰለ። ሰው የእግዚአብሔር ምሳሌና መልክ ነው። ይህም መልክ ከአፈር ጋር ተቀላቀለና ደበሰ። የእግዚአብሔር እሳት - ገሀነም እሳት - የእሳት ባሕር ያ የሚያጠራው ድኝ ያንን አፈር አቃጥሎ መልኩን ለማውጣት መሆኑን ታውቁ ይሆን? ለእያንዳንዳችን እንደ ብልት ልክ አለን - በእግዚአብሔር በራሱ የተለካ ልክ! ለሰው የሞተው - የኃጢአትን ዋጋ የከፈለው ሰው ቢሆን የሰው ልኩ ሰው ነበርና ሰው ከሰው ሌላ አልነበረም። ሰው ከተከፈለለት ዋጋ ተነሥቶን ሰው ከሰው ሌላ የከበረ እንደ ሆነ እንረዳለን። ለሰው መልአክ ቢሞት - ቢከፈል ሰው መልአክ ነበረ። ለሰው የተከፈለው እግዚአብሔር ነው። ሰው

በእግዚአብሔር ተተማ - ተለካ፡፡ ሰው የእግዚአብሔር መለጥ እስኪሆን ብቻ ጨልማት፡፡ በእግዚአብሔር ቀን እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ልቡን ለሰው ሲገልጥ መረማቸን ድንበር አይኖረውም፡፡

ሰው በማእከት፣ በሰወ፣ ወይም በልዩ ፍጥረት አልተገዛም፡፡ አልተዋጀምም፡፡ ሰው በክርስቶስ ተገዝቷል፡፡ ሰው ስንት ያወጣል? ክርስቶስን ያህል፡፡ ድንቅ? የድንቆች ድንቅ እንጂ - ክብር ሃሌ ሉያ!